# እግዚአብሔርን እንወቅ

ከሰሎሞን ጥላሁን

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228

ራዕይ አሳታሚ
1990 ዓ.ም. አዲስ አበባ

# እግዚአብሔርን እንወቅ

ራዕይ አሳታሚ

የመ. ሳ. ቁጥር 101539

አዲስ አበባ

RP O3 2M



## አበርክቶ

እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ለብዙ በረከት ምክንያት ላደረገው ለጋሼ ሰለሞን ከበደ፡፡

በዚህች መጽሐፍ ርእስ ዙሪያ ያሉትን ወሳኝ ሐሳቦችን በሚመለከት ብርሃን ለፈነጠቀልኝና አስተማሪም ጓደኛም የመሆን ችሎታ ላለው ለዶክተር ስቲቭ ብራያን፡፡

ዋጋ የሚያስከፍል ድጋፏ በሕይወቴ ስኬት ላይ በግልጽ ለሚታየው ለእህቴ ገነት ጥላሁን (እታለም)፡፡

ለትጻር ጓደኛዬና የፍቅር አስተማሪዬ ሙሊ!

## ምሥጋና

የመነሻ አብርሆት ሳያገኙ ጽሑፍ አይታሰብም፤ ወንድሜ ፍሬው ታምራት በቤተክርስቲያናችን የዚህን ጽሑፍ ጥንስስ ጥሎ ባይሄድ ይህች መጽሐፍ አትገኝም ነበር፡፡

# መክስተ አርእስት

## ክፍል አንድ
## የእግዚአብሔር መገለጥ

1. ጠቅላላ/ጥቅል መገለጥ .................... 12

1.1. ተፈጥሮ የመለኮት መገለጫ ሲሆን
1.2. የሰው ኅሊና የመለኮት መገለጫ ሲሆን
1.3. ታሪክ የመለኮት መገለጫ ሲሆን
1.4. የጥቅል መገለጥ ብቃት እስከ ምን ድረስ ነው?

2. ልዩ መገለጥ ......................... 22

2.1. በድምጸ-መለኮት
2.2. በህልምና በራእይ
2.3. በመላእክትና በአስተርእዮተ-መለኮት
2.4. በተአምራት
2.5. በክርስቶስ
2.6. በመጽሐፍ ቅዱስ

## ክፍል ሁለት
## የእግዚአብሔር መታወቅ

1. እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው?.......57

1.1. በእግዚአብሔር መታወቅን ማወቅ ማለት ነው::
1.2. እግዚአብሔርን በግል መለማመድና መቀራረብ ማለት ነው::
1.3. እግዚአብሔርን ማወቅ÷ መለማመድና ማየት እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም ጥንቃቄ ያሻዋል::

2. እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?.. 66





2.1. ሁልጊዜ ወቅታዊና አንገብጋቢ ስለሆነ ነው::
2.2. ገለል ሊያደርጉት/ቸል ሊባል/ የማይቻል እውነታ ስለሆነ ነው::
2.3. የማንነታችን መታወቂያ ስለሆነ ነው::
2.4. የሚያመጣው ውጤት ጠቃሚ ስለሆነ ነው::
2.5. ፈቃዱን ለማወቅ ጠቃሚ ስለሆነ ነው::

3. እግዚአብሔር የሚታወቀው እንዴት ነው?.......... 81

3.1. በቃል ኪዳኑ ነው::
3.2. በሕይወታችን ላይ ጌታ ሲሆን ነው::
3.3. በኑሯችን ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ስንፈቅድለት ነው::
3.4. ሁልጊዜ በፊቱ ስንገኝ ነው::

## ክፍል ሦስት
## የእግዚአብሔር ማንነት

1. የእግዚአብሔር ኅልውና/መኖር.................. 89
2. የእግዚአብሔር ባሕርይ.......................... 90
3. የእግዚአብሔር ጠባይ.............................. 91

3.1 የማይወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት........ 93

ሀ. ነፃ ነው (በራሱ ኅልው ነው)
ለ. የማይለወጥ ነው
ሐ. ዘላለማዊ ነው

3.2 የሚወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት........... 104

ሀ. የእግዚአብሔርን ነባሪነት የሚያስረዱ ጠባያት
ለ. የእግዚአብሔርን የኅሊና ጠባይ የሚያስረዱ
ሐ. ግብረገባዊ ጠባዩ

## ክፍል አራት
## ሰው

1. አስተምህሮተ-ሰው ለምን አስፈለገ?................. 127

1.1 አስተምህሮተ-ሰው ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምሮዎች ጋር በመዛመዱ::
1.2 አስተምህሮተ-ሰው የሰው አንገብጋቢ ፍላጎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጠት መገናኛ ነጥብ በመሆኑ::
1.3 የዘመኑ ተምህሮአውያን ከፍተኛ ትኩረት ሰው በመሆኑ::

2. ሰው ለምን ተፈጠረ?................................ 131

2.1 እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ሰውን ፈጠረው
2.2 ሰው የሕይወቱ ዓላማ ምንድን ነው?

3. ሰው "በእግዚአብሔር አምሳል"................. 136

3.1 "የእግዚአብሔር አምሳል" በአዲስ ኪዳንና በቤተክርስቲያን ታሪክ
3.2 "በእግዚአብሔር አምሳል" ማለት ምን ማለት ነው?

3.3 "በእግዚአብሔር አምሳል" መፈጠር ያለው ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ...................................... 147

ማጣቀሻ ............................................. 151





## መግቢያ

ለምን ይህ መጽሐፍ አስፈለገ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሳልቃጣ አንብቡልኝ ብዬ ባስቸግር አግባብነት ያለው አልመስልህ ስላለኝ፥ አስቀድሞ ይህ መጽሐፍ ለምን አስፈለገ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መርጫለሁ:: መጽሐፉ ከመጻፉ በፊት በአእምሮዬ የሚከተሉት ጥያቄዎችና መሰሎቻቸው ይመላለሱ ነበረ::

⇒ የክርስትና እምነት ለሰው ልጆች ጊዜ የማይሽረው መልእክት ያለው ነው ብለን እናምናለን፤ ይህንን ደግሞ ማረጋገጥ የምንችለው በየትውልዱ የጊዜው መልእክት ሲኖረን ነው:: ታዲያ ይህ ትውልድ የሚያስፈልገው መልእክት ምንድን ነው?

⇒ ክርስትና በዘመናት መካከል ቀጣይ እንዲሆንና የምግባር ልቀት እንዲኖረው ያደረገው ምንድን ነው?

⇒ በመጪው ዓለም አምላካዊ ተስፋ ላይ የተመሠረተችው ቤተክርስቲያን "በክፉው በተያዘው" የአሁኑ ዓለም ውስጥ በመጻተኛነት ስታልፍ እያደር እንዳትጥለው የሚያሳስበው ዕንቁ ምንድን ነው?

⇒ ዓለም በሕዝብ ብዛት፥ በቴክኒዎሎጂ እድገት ፥ በከተሞች ስፋት፥ በማሕበራዊ ለውጦችና በፖለቲካ ነውጦች እየታመሰች ነው፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ከሁሉም አቅጣጫ ለሰው ልጅ ጥያቄ መልስ ያልሆኑ መልስ መሰል ሐሳቦች እየተሰነዘሩ ነው፥ ታዲያ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን ለዓለምና ለራሳችን የምንናገረው ምንድን ነው?

በአጭሩ ለእነዚህና ለመሰል ጥያቄዎች መልሱ የዚህች መጽሐፍ ርዕስ የሆነው "እግዚአብሔርን እንወቅ" የሚለው ሐሳብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: እግዚአብሔር በፈጣሪነቱና' እኩልታ በሌለው ንጉሠ ነገሥትነቱ በሕዝቡ መካከል እንዳይዘነጋ፥ የአምልኮአችንም ባሕል መንፈስን ማርካት ብቻ ሳይሆን ምግባርን መለወጥ እንዲሆን፥ ቤተክርስቲያን በአብዛኛው አትርፌበታለሁ በማለት

የምታስባቸው ጉዳዮች ውጪአዊ በመሆናቸው የውስጥ ውበቷ አምላኳን በደንብ መገንዘቧ እንደሆነ እንዲታወስ ይህችን መጽሐፍ ለመጻፍ ቃጣሁ::

አንድን መጽሐፍ ከጅምር ሐሳቡ እስከ ሕትመት ድረስ የሚያደርሱ የብዕር ወዳጆች፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ወላድ እናቶችን ይመስላሉ:: መቼም ወላዶች ሁሉ በዘጠኝ ወር አይወልዱም:: ግማሹ ቀደም ሲል ግማሹ ይተላለፋል ሁለቱም ግን የየራሱ የጎን ጠንቅ አያጣም፥ ይሁን እንጂ በወቅቱ መውለድን የሚያህል መልካም ነገር የለም፥ ለቀናው ለሆነለት ማለቴ ነው:: ቢሆንም ካለመውለድ ግን ዘግይቶም ይሁን ቀድሞ መውለድ ይሻላል:: ከዚህ አኳያ ይህችን መጽሐፍ አንባቢ አይቶ የትኛው ቦታ እንደሚፈርጃት አላውቅም:: ግን ምጡ በዝቶብኝ ወልጃታለሁና ያነበበ ሁሉ ያሳድጋት፤ ሕጻን ሊኖረው የሚችለውም ነገር ሊኖራት ይችላል:: ከዚህም የተነሳ ለአንባቢ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አትሰጥ ይሆናል፤ ነገር ግን "እግዚአብሔርን እንወቅ" በሚል ርእስ ዙሪያ ሊነሱ ይገባቸዋል ብዬ የገመትኳቸውን ሀሳቦች ለማንሳሳት ሞክሬአለሁ:: ይህም ሆኖ ግን ለአንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ሳልሰጥ ባልፍ፥ ቀጣይ ጸሐፊዎች በዚህች መጽሐፍ መንደርደሪያነት መልስ እንዲያዘጋጁ እጋብዛለሁ::

በመጽሐፉ ውስጥ አንዳንድ የአማርኛ ስያሜዎች ለብዙዎች እንግዳ ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ:: የሥነ-መለኮት ትምህርትን በአማርኛ ማስፋፋት ከታሰበ አንዳንዴ እንዲህ ዓይነቱ ግድ ይፈጠራል:: መጽሐፉ ግን ሲጻፍ በዓላማው ቃላትን ለማስተዋወቅ አይደለም፤ ይልቁንም ከቃላቱ በስተጀርባ ያሉትን ሐሳቦች ማስተላለፍ እንጂ:: ደግሞም ከዚህች መጽሐፍ ተደራሲያን ውስጥ በቋንቋና በሥነ-ጽሑፍ ዕውቀት የደረጁና ታላላቅ የሚባሉ በርካታ እንዳሉ ስለማምን በመጽሐፉ ውስጥ የስያሜ ቃላትን ስጠቀም ለመታረም በተዘጋጀ ልብ ነው:: በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሐሳቦች በአራት አበይት ክፍሎች ተከፍለዋል፤ እያንዳንዱም ክፍል በስሩ ዋና ዋና ርእሶችንና ንኡሳን ርእሶችን ይዟል:: በእነዚህም ውስጥ ያሉትን ሥነ-መለኮታዊ ሐሳቦች በተቻለ መጠን ከአማኙ የእለታዊ ኑሮ ጋር ለማዛመድ ሙከራ ተደርጓል:: ስለዚህ መጽሐፉ በጠባዩ በእምነታቸው ጀማሪዎች ከሆኑት አንስቶ ለአገልግሎት እስከደረሱ የበሰሉ





አማኞች ድረስ ሊነበብ የሚችል እንደሆነ ይገመታል:: ከዚህች መጽሐፍ የሚገኘው በረከት ለእግዚአብሔር ምርጦች፥ ክብሩና ምስጋናው ደግሞ ለልዑል እግዚአብሔር ይሁን::

*"እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤ እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል"*
(ትንቢተ ሆሴዕ 6÷3)::

# ክፍል አንድ
# የእግዚአብሔር መገለጥ

በምድር ላይ መፈጠር የተቀረጠ የህልውና ግዴታ መሆኑን የተረዳው የሰው ልጅ፥ አዕምሮው የጠየቀውን ጥያቄ ሁሉ በመሰለው መንገድ እየመለሰ ይኸው እዚህ ደርሷል:: በአብዛኛው የጥያቄዎቹ መልሶች የምድር ኑሮን ለማቅለል ጠቅመውታል:: ከዚህ የተነሳ ሳይንስ "በነፍስ አድንነት" እየተገመተ የዘመነኞች ሃይማኖት ሆኗል:: በመሆኑም ሰው የመንፈስ የነፍስና የሥጋ ጥያቄውን ሁሉ ጠቅልሎ ለሳይንስ አደራ ሰጥቷል::

*የቦታ ርቀት ጥያቄዎች* :- ጥያቄዎች መሆን ካከተሙ ቆይተዋል፤ በልዩ ልዩና ዘመናዊ በሆኑ የመገናኛ መንገዶች መልስ አግኝተዋል:: ከዘመናት በፊት የዓመታት መንገድ የነበረውና አይደፈሬው የአትላንቲክ ውቅያኖስን በፈጣን ጄት አውሮፕላን በጥቂት ሰዓታት ማቋረጥ ተችሏል:: በዘመናዊ የኤሌክትሪክ ባቡር ወይም ጥይቱ ባቡር (Bullet Train) በመባል በሚታወቀው በግማሽ ሰዓት ውስጥ ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ የሚከለውን ርቀት መግባት ተችሏል:: እነዚህ ሁሉ ከሆኑ ደግሞ ዓመታት ተቆጥረዋል::

*የበሽታ ጥያቄዎች* :- ከጥቂት በሽታዎች በቀር አብዛኛዎቹ የበሽታ ጥያቄዎች መልስ ተገኝቶላቸዋል:: ከዓመታት በፊት አንድን ሕዝብ በቀላሉ ያጠፉ የነበሩ ወረርሺኝ በሽታዎችን፥ በዚህ ዘመን በአንዲት ክትባት ከምድረ ገጽ ማስወገድ ተችሏል:: ኮሌራ፥ ፈንጣጣና ልምሻ በታዳጊ አገሮች ካልሆነ በስተቀር በዚህ ዘመን የአደጉ አገሮች ችግር አይደሉም:: ቀደም ሲል ይደረግ የነበረው የቀዶ ጥገና ሕክምና በሳይንስ በተራቀቁ አገሮች ዘዴው ተቀይሯል፤ ትርፍ አንጀትና አንዳንድ የካንሰር በሽታዎች ታማሚው ስለት ሳይነካው በጨረር ሕክምና መፍትሄ ማግኘት ተችሏል::

*የመረጃ ጥያቄዎች* :- መረጃ ፍለጋ አገር ማቋረጥና የሰው ኃይል ማብዛት የኋላ ቀሮች ፈሊጥ እንደሆነ እየተቆጠረ ነው:: በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው የሚፈልገውን ማንኛውንም የኤኮኖሚ፤





የፖለቲካ፤ የሳይንስና የማህበረሰብ መረጃዎች ኢንተርኔት በተባለ ዘመናዊ የኮምፒውተር መገናኛ መስመር ማግኘት ይቻላል:: ጥቂት የኮምፒውተር ቁልፎችን በመነካካት ዓለምን ማሰስ ተችሏል፡

*በጽሑፍ ያልተቀመጡ የዓለም ታሪክ ጥያቄዎች* :- ሰው በከርሰ ምድር ምርምር መሬትን በቁፋሮ እያስጨነቀ ያለፉ ታሪኮችን እያናዘዛት ነው:: በዚህም ብዙ በጽሑፍ ያልሰፈሩ የዓለም ታሪኮች ምስጢርነታቸው ቀርቷል::

ይሁን እንጂ ሳይንስ ሊመልሰው ያልቻለው አንድ አቢይ ጥያቄ አለ፤ ይህም ጥያቄ "እግዚአብሔርን የማወቅ ጥያቄ" ነው:: ሳይንስ "ፈጣሪ እንዴት ሊታወቅ ይችላል?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ ስላልቻለ "ፈጣሪ የለም፤ እኛም እንዲያው ዱብ እጣዎች ነን" የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰ:: ሳይንስ በዚህ ገጽታው ሲታይ እኔ የማላውቀው ነገር ሁሉ ህልውና የለውም በማለቱ፥ ራሱ ሳይንስ ኢ-ሳይንስ ነው:: አንዲት ፍሬ-በል እንስሳ ከአንድ ዛፍ ላይ አንድ የበሰለ ፍሬ ለመብላት ብዙ ከደከመችና ከዘለለች በኋላ ልትደርስበት ባለመቻሏ ስለተናደደች "ድሮውንስ ቢሆን ከዚህ ከበሰበሰ ፍሬ ጋር ምን አታገለኝ" ብላ ጥላው ሄደች ይባላል::

በእርግጥ በዚህ የመግቢያ ሀሳብ ላይ ስለ ሳይንስ እግዚአብሔርን አለማወቅ የተገለጸው በደምዳሚያዊነት (Generalization) አይደለም:: ምክንያቱም አማኒያን ክርስቲያን ሳይንቲስቶች እንዳሉና ሳይንሳዊ እውቀታቸውንም ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚጠቀሙበት ይታወቃልና ነው:: ሆኖም ግን በአብዛኛው ሳይንስ ኢ-ተዳሳሽ ስለሆነው ዓለም ያለው ዝንባሌና አቅጣጫ አምላክ የለሽነት ነው:: ከሚታይና በሳይንሳዊ ግኝት ሊደረስበት ከሚችል ነገር ውጪ ህልውና ያለው ነገር የለም ባይ ነው::

እኛ ያልደረስንበትና በህዋሶቻችን ያልተረዳናቸው ነገሮች ሁሉ ኅልውና የላቸውም ማለት ደግሞ ሳይንስ አሁን በግኝቶቹ የደረሰባቸው ነገሮች ከመገኘታቸው በፊት ኅልውና አልነበራቸውም ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ልክ ነው ከተባለ፥

ሳይንስ የተፈጠረን ነገር የሚያገኝ ሳይሆን ፈጣሪ ነው ማለት ነው:: እግዚአብሔርም በዓለም ጥበብና ፍልስፍና የሚገኝ ባለመሆኑ "አላማኝ" ጠቢባንና ፈላስፎች የለህም አሉት "እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል" (ዕን.2÷20):: እግዚአብሔርን የማወቅ ጥያቄ ሳይንስ ያልመለሰው ሊመልሰውም የማይችል ጥያቄ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ ፈጽሞ የተለየና የላቀ ስለሆነ ነው:: "እነሆ እግዚአብሔር _ትልቅ_ ነው እኛም አናውቀውም" ተብሎ እንደተጻፈ ነው::

ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር መታወቅ ምን ይላሉ? "ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም" አለው እግዚአብሔር ለሙሴ (ዘጸ.33÷20):: "የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን ሁሉን የሚችል አምላክንስ ልትመረምር ትችላለህን?" (ኢዮ.11÷7-12) አሉት ለኢዮብ ጓደኞቹ:: "የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው÷ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም" (ሮሜ.11÷33)::

"ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምሥጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን" (1ጢሞ.1÷17):: "እርሱ ብቻ የማይሞት ነው ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን አሜን" (1ጢሞ.6÷16)::

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር አምላክ ይህንን ያህል ምጥቀት ያለው አምላክ ከሆነ የቀደሙት የእምነት አባቶች እንዴት ተረድተው ተከተሉት? እኛስ ከምን ተነስተን ነው አምላካችን ብለን የምናመልከው? ቅዱሳት መጻሕፍትስ ይህን ያህል ስለ እግዚአብሔር አርቅቀውና አምጥቀው ሲናገሩ ምን ማለታቸው ነው? እግዚአብሔር በባሕሪው እንዲህ ከሆነ÷ በቃ በፍጹም ሊታወቅ አይችልም ማለት ነው? የሚል ጥያቄ ይመጣ ይሆናል ተገቢም ነው::





በእርግጥ እግዚአብሔር በማንኛውም ዓይነት መልኩ ወሰን የሌለውና አይበየኔ (undefinable) አምላክ ነው:: የሰው ልጅም ሆነ ተፈጥሮ በቁጥጥሩ ሥር ሊያደርገው አይችልም:: ሰው የተደበቀንና የተሰወረን ነገር ፈልፍሎና ፈልጎ እንደሚያወጣ እግዚአብሔርን ፈልፍሎና መርምሮ አያገኘውም :: ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት ይታወቃል? ለሚለው ጥያቄ መልሱ እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል! የሚል ነው::

*መግለጥ ማለት:- መግፈፍ÷ ማሳየት÷ መንገር ÷ መተርጎም÷ ማስረዳት÷ ግልጥ ሆኖ መታየት ማለት ነው::*[1]

ምንም እንኳ ከባሕሪው አርቅቆት ተነስተን እግዚአብሔር አምላክ ምጡቅ ነው÷ አይወሰኔ ነው÷ አይበየኔ ነው ብንልም እግዚአብሔር የማንነቱን ደብዛ ያጠፋብን ከፉ ወይም በራሱ የማይተማመን ዓይን አፋር አምላክ አይደለም::[2] እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች በበቂ ሁኔታና መንገድ ገልጧል፤ ከዚህም የተነሳ "የአላውቀውምና ላውቀውም የምችልበት መንገድ የለም" ምክንያትን ዘግቷል:: ሰው ስለ እግዚአብሔር አምላክ ማወቅ አልችልም ባለማወቄም ተጠያቂ አልሆንም ማለት አይችልም:: *<u>ክርስትና ይህንን ዓይነቱን የሰው ያለማወቅ አቅምና የመለኮትን የርኅራኄ ግልጠትን አስታርቆ የያዘ እምነት ነው::</u>*[3]

ሰው አምላክን እንዴት ማወቅ ይችላል? የሚለውም ጥያቄ መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው:: *በተፈጥሮው ፍጹም ያልሆነው የሰው ልጅ÷ ከመለካት በላይ ፍጹም የሆነውን አምላክን ማወቅ የሚችለው÷ አምላክ ራሱን ሲገልጥለት ብቻ ነው::*[4] ይህም ማለት የሰው ልጅ ከአምላክ ጋር የፈጣሪና የተፈጣሪ ግንኙነትና ኅብረት ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ሆን ብሎ ለሰው ልጅ ራሱን ይገልጣል ማለት ነው::

ነገር ግን ይህ መልስ ደግሞ በራሱ ሌላ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፤ ጥያቄውም:-"ይህ ራስን የመግለጥ የመለኮት ጠባይ እንዴትና በምን ዓይነት መልኩ ታይቷል?" የሚል ነው:: ይህንን ዋና ጥያቄ ደግሞ በሁለት መሠረታዊ ክፍሎች በመክፈል መመለስ ይቻላል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸውን መንገዶች በሁለት በመክፈል ጠቅላላ

መግለጥ (General Revelation) እና ልዩ መገለጥ (Special Revelation) በማለት ይሰይሙአቸዋል። እነዚህን የመገለጥ ዓይነቶች ዝርዝራቸውን ከማየታችን በፊት አጭር ትርጉማቸውን መመልከቱ ጠቃሚ ነው

እግዚአብሔር አምላክ *በሁሉም ቦታ፤ ሁል ጊዜ፤ ለሁሉም ሰው* ራሱን በመግለጥ የሚገናኝበት መንገድ ጠቅላላ መገለጥ በመባል ሲታወቅ፥ ይህም በዓለም ዙሪያ በየትኛውም ዘመን ለኖሩና ወደፊትም ለሚኖሩ የሰው ልጆች በሙሉ ራሱን በተፈጥሮ አማካኝነት የገለጠበት መንገድ ነው። ዓላማውም ሰው በተፈጥሮ አማካኝነት ከተረዳው መገለጥ የተነሳ አምላካዊ ባሕሪውንና ምግባራዊ ሕጉን በማስተዋል ምላሽ እንዲሰጥ ነው። አማኝም ሆነ የማያምን "ይህንን ዓይነቱን መገለጥ አላገኘሁም" ማለት አይችልም። በተለያየ ዘመንና በተለያየ የዓለም ክፍል የኖሩ የሰው ልጆች ሁሉ ይህ ዓይነቱ መገለጥ ደርሷቸዋልና።[5]

ሁለተኛው ዓይነት የመለኮት መገለጥ ደግሞ ልዩ መገለጥ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ እግዚአብሔር አምላክ ራሱን *ለተወሰኑ ሰዎች፤ በተወሰነ ጊዜ፤ በተወሰነ ቦታ* የገለጠበትን መንገድ የሚያሳይ ነው። ታሪካዊ ማረጋገጫውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ ዓይነቱ መገለጥ አምላክ ከሰዎች ጋር ያደረገውን ቀጥተኛ ግንኙነትና ልዩ ልዩ ተአምራትን የሚያጠቃልል ሲሆን የመጨረሻ ደረጃውንም ያገኘው በክርስቶስ የሥጋ መገለጥ ነው (ዕብ.1፥1-3)። ይህ መገለጥ በቀጥታ የማዳን ዓላማ ያለው መገለጥ ነው።

1. <u>ጠቅላላ መገለጥ/ጥቅል መገለጥ</u>

አንድ ሰው በልዩ ልዩ ድርጊቶች ማንነቱን እንደሚገልጥ ሁሉ እግዚአብሔርም እንዲሁ በልዩ ልዩ አምላካዊ ድርጊቶች ራሱን ገልጧል። ሰዎች አንዳንድ ጭብጦችን (Facts) በመናገርና በመጻፍ ከሚገልጡት ሌላ፥ በፊታቸው ገጽታና በአካላቸው ንቅናቄም ራሳቸውን ይገልጣሉ። ሰዎች ለጋስ ወይም ንፉግ፥ ሥልጡን ወይም ያልሠለጠኑ መሆናቸው የሚታወቅበት ብዙ የባሕሪያት መገለጫዎች አሏቸው። ምንም እንኳ ሰዋዊ የሆነን ተፈጥሮ ከመለኮት ጠባይ ጋር ማዛመድ እንዲሁም ማመሳሰል





ቢያስቸግርም፥ እግዚአብሔርም እንዲሁ በልዩ ልዩ ዓይነት ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ራሱንና ባሕሪውን ገልጧል። ይህንንም በጸጋው ላይ የተመሠረተ ግልጠት ያደረገው ከሰው ልጆች ጋር ሕብረትንና ተግባቦትን ለመፍጠር ነው።

*እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በቁሳዊው ዓለም ክንዋኔዎች ራሱን ባይገልጥ ኖሮ፥ ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ አስመልክቶ ምንም ተስፋና ዕድል አይኖረውም ነበር*። ስለዚህም ብሉይ ኪዳናዊው ማስረጃ እንዲህ በማለት ያስተጋባል፦ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል.."(መዝ.19፥1)። በዚህ ሥፍራ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ክብር አስተውሎ የሚናገረው ከጠቅላላ መገለጥ በመነሳት ነው።[6] በአዲስ ኪዳን ጽሑፎችም ቢሆን ይኼው ሀሳብ ተደግሞ እንመለከተዋለን፤ "...እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና..." (ሮሜ.1፥19)።

እነዚህ ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች የሚጠቁሙን በማንኛውም ቦታና ጊዜ የኖረ ሰው ከኅሊናው፥ ከተፈጥሮ ልዩ ልዩ መልእክቶች እንዲሁም በታሪክ ውስጥ ከሚከሰቱ ድርጊቶች በአንድነት የእግዚአብሔርን ኃይል፥ ጥበቡንና በጎነቱን እንዲሁም መለኮታዊ ህልውናውን ምንጊዜም በግልጽ ሊያውቅ እንደሚችል ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ላለማወቅ ከንቱ ምክንያት የሚሰጡ ሰዎች በጠቅላላ መገለጥ የበራላቸው ብርሃን በመጨረሻው ፍርድ ይኮንናቸዋል (ሮሜ2፥12-15)።[7] ባጭሩ ጠቅላላ መገለጥ የሚባለው በተፈጥሮ/በፍጥረት/ በኩል የተገለጠውና በሰው ኅሊናና በታሪክ በኩል የተገለጠው የአምላክ መገለጥ ነው። ከዚህ በመቀጠልም የዚህን ዓይነቱን የአምላክ መገለጥ አንድ በአንድ እንመለከታለን።

## 1.1. <u>ተፈጥሮ የመለኮት መገለጫ ሲሆን</u>

በመዝ.19÷3 ላይ "ነገር የለም መናገርም የለም ድምጻቸውም አይሰማም ድምጻቸውም ወደ ምድር ሁሉ÷ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ" ብሎ ሲናገር በቁ.1እና2 ላይ "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" በማለት የሰማይ ፍጥረታት የመለኮትን መገለጥ እንዴት ባለ ስልት እንደሚያሳዩ የተናገረውን ሲያብራራ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ በሰማይ ጠፈር ላይ ፦ ቀን በፀሐይ ብርሃን÷ ሌሊት በከዋክብትና በጨረቃ ድምቀት÷ በማይካድ ሁኔታ ይናገራል። ፈጣሪ በሰማይ ሠራዊትና በምድር ፍጥረታት ራሱን በቀን ሃያ አራቱንም ሰዓት ገልጧል። ይህንን የአምላክን ህልውና ከተፈጥሮ በዓይኔ አይቼ መረዳት አልችልም የሚል ዓይነ ሥውር እንኳ ፀሐይ በትኩሳቷ የአምላክን ህልውና ትነግረዋለች (መዝ.19÷6)።[8] እግዚአብሔር አምላክ ህልውናውን ግዑዝ በሆነውና በአስደናቂው የተፈጥሮ, ውበት ውስጥ ገልጧል። በሰማያት ግርማ÷ በጥልቁ ባሕር÷ በፀሐይ ሙቀት÷ በተራራው ግዝፈት÷ በጨረቃና በከዋክብት ድምቀት÷ በሜዳ ሣርና በመስክ አበቦች እንዲሁም በዱርና በደኑ ተገልጦ ይኖራል።

እነኝህ ሁሉ ከበስተኋላቸው እጅ እንዳለ ይናገራሉ። በአጠቃላይ ከቅንጣቲት(Atome) አንስቶ እስከ ግዙፉ የከዋክብት ሠራዊት (Galaxy) ድረስ፤ እንዲሁም ረቂቅና ደቂቅ ከሆኑት እስከ ውስብስብ የሆኑ ሕይወት ያላቸው አካላት ድረስ እግዚአብሔር አምላክ ህልውናውን በእጆቹ ሥራዎች ሁሉ ገልጧል። የበጎነቱም ባህሪይ ያለ አድልዎ ለሁሉም ስለ መገለጡ መጽሐፍት ይመሰክራሉ። "እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና÷ በጻድቃንና በኃጢያተኞችም ላይ ዝናቡን የዘንባልና" (ማቴ.5÷45)። ደግሞም በሐዋ.14÷15-17 ጳውሎስና በርናባስ እግዚአብሔር አምላክን ላላወቁ የልስጥራ ሰዎች እንዲህ አሉ "ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሰራ÷ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት÷ ሲሰጠን÷ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው እራሱን ያለምስክር አልተወም።" ደግሞም





በሮሜ.1÷18-23 እግዚአብሔር ራሱን ስለ መግለጡ ተጠቅሶአል። በአጠቃላይ ተፈጥሮ ለሰው ልጆች የሚያደርገው የማያቋርጥ ጥንቃቄና ሰፊ ልግስና በስተጀርባው ያለውን የፈጣሪ ህልውና ሲያረጋግጥ ነው። የአጥናፈ ዓለሙም ዋነኛና ተቀዳሚ ዓላማ ለአምላክ ክብር እየኖሩ ለህልውናውም የምስክርነት አገልግሎት መስጠት ነው።[9] ይህ ደግሞ የቀንና የሌሊት የማያቋርጥ አገልግሎታቸው ነው። ይህ እስከ አሁን የተመለከትነው የጠቅላላ መገለጥ ትንታኔ ከእኛ ሕይወት ጋር ምን ግንኙነት አለው? የሚል ጥያቄ ያስነሳ ይሆናል፤ ለዚህም መልሳችን እንደሚከተለው ይሆናል።

አምላካችን ታላቅ የሆነና ማንም ሊሰራው የማይችለውን የሰራ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህ ብቻ ሳይሆን እኛ ደግሞ የዚህ የአጥናፈ ዓለሙ ጌታ ልጆች ነን። ዛሬ በምድራችን ላይ ጉድ የሚባለውን የአውሮፕላን ቴክኖሎጂ ለዓለም ያስተዋወቁ "ዘራይት ብራዘርስ" የሚባሉ ወንድማማቾች ቤተሰብና ልጆች ብንሆን ምን ይሰማናል? ወይም በአገራችን ታዋቂ አትሌት የተባለው የጀግናው ኃይሌ ገ/ሥላሴ እህት÷ ወንድም÷ እናት÷ አባት ወይ የቅርብ ጓደኛ ብንሆን ይሰማን የነበረው ኩራት የላቀ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ሰው በዕውቀት ተራቆ መኪና÷ አውሮፕላን÷ መርከብ÷ ሮኬት÷ ኮምፒውተር÷ ወዘተ. ሠራ፤ እግዚአብሔር ግን ይህንን ሁሉ የሰራውን የሰው ልጅ በእጁ ሠራው በአስትንፋሱም ነፍስ ዘራበት። በዘመናዊው ዓለም እንደተለመደው ታዋቂ ሰዎች በአንድ ካርድ ላይ ሥማቸውን ጽፈው እንዲፈርሙልን ብዙ ማጎብደድ ይፈልጋሉ እግዚአብሔር ግን ቸርነቱን በነጻ ለፍጥረት ሁሉ ይለግሳል።

የተፈጥሮ ተጠቃሚዎች ስንሆን በስተጀርባው ያለውን ለጋስ አምላክ ቸል እንዳንል ልንጠነቀቅ ይገባናል። በጸሎታችን ውስጥ እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ነገሮች ምን ያህል አመስጋኞች ነን? መዝሙሮቻችን የተፈጥሮን ልግስና ምን ያህል ይዳስሳሉ? ሰው ከተፈጠረው ነገር ያገኘውን አንዱን ካንዱ አጋጭቶ ለፈለሰፈው ነገር በጭንቅ ዋጋ ያስከፍለናል፤ ለመብራት ለውሀ ሳንከፍል ተጠቃሚዎች መሆን አንችልም፡፡ እግዚአብሔር ግን ለቀን ብርሃን÷ ለሌሊት ጨረቃና ለጅረቱ ውሀ ዋጋ/ቤሳ አልጠየቀንም፤

አመስጋኞች ልንሆን ይገባናል። ተፈጥሮ ራሱ የጸጋ ስጦታ መሆኑን አንዘንጋ።

ደግሞም እግዚአብሔር ራሱን በተፈጥሮ ውስጥ ገልጧል ካልን ተፈጥሮን የመንከባከብ ሃላፊነት አለብን። ለተፈጥሮ እንክብካቤ በሚደረገውም ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥም መሳተፍ አለብን ሌሎች ስለ ተፈጥሮ ሲገዳቸው ፈጣሪያቸውን የሚያውቁ ሰዎች ቸል ሊሉ አይገባም። በዚህ በጥቅል መገለጥ ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ የምንመለከተው ደግሞ የሰው ኅሊና የመለኮት መገለጫ መሆኑን ነው።

## 1.2. <u>የሰው ኅሊና የመለኮት መገለጫ ሲሆን</u>

ከምድር ፍጥረታት ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘው የሰው ልጅ፥ የኅሊና ክሂሉና ምግባራዊ ጠባዩ የእግዚአብሔር ጠቅላላ መገለጥ መታያ ነው። ሰው እንደ እንስሳ በደመነፍስ ሳይሆን በኅሊና ፍርድ የሚኖር ፍጡር ነው። ከዚህም የተነሳ ምግባራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የኅሊና ዳኝነት ይሰጣል። በዓለም ላይ ያለ የሰው ልጅ ምንም እንኳ በቋንቋ በባሕልና በአኗኗር የተለያየ ቢሆንም በምግባራዊ ፍርድ ሰጪነቱ ግን ተመሳሳይ ነው። በሁሉም አገር ያሉ ሰዎች መግደል ልክ እንዳልሆነ ያምናሉ። ውሸት፣ አመንዝራነትና የመሳሰሉት እኩይ ባሕሪያት ልክ እንዳልሆኑ በተለያየ መንገድ ያምናሉ። ስለዚህ ለኑሮ ሕግና ሥርዓት እንደየባሕላቸው ያወጣሉ። ይህም ከሰዎች ምግባራዊ ዝንባሌ ጀርባ ምግባራዊ አምላክ መኖሩን ያመለክታል።[10]

ከዚህ ሌላ በዋነኛነት ደረጃ በየትኛውም አገርና ዘመን የነበረና ያለ ሰው ሁሉ የማምለክ ዝንባሌ አለው። ሁሉም አንድ የፈጠረው አምላክ እንዳለና እርሱም የዚህ ፈጣሪ የእጅ ሥራና ተፈጣሪ መሆኑን ያውቃል። ይህ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ባሉ ሰዎች ዘንድ ያለው ሃይማኖታዊ የልብ አዝማሚያ፥ በሰው ውስጥ ካለ የአምላክ እውቀት የመነጨ ነው። አንድ ፖሉታርክ የተባለ የጥንታዊቷ ግሪክ ፈላስፋ፥ የሰው ልጅ አምላክን የሚፈልግ ፍጡር እንደሆነ ሲጽፍ እንዲህ አለ፦ "በዓለም ዙሪያ ቅጥር የሌላቸውን ከተሞች ታገኙ ይሆናል፥ የነገሥታት ቤተመንግሥት የሌላቸውን ከተሞች ታገኙ ይሆናል፥ የሥነ-ጽሑፍ ቅርስ የሌላቸውን ከተሞች





ታገኙ ይሆናል ወይ ደግሞ ቤተ ተውኔት የሌላቸውን ከተሞች ታገኙ ይሆናል ነገር ግን ቤተ መቅደስ ወይም ቤተ ጣዖታት የሌሉአቸውን ከተሞች እስከዛሬ ያገኘ አንድም ሠው የለም" ብሏል።[11] ምንም ቢሆን ምን በሰው ልጆች ኅሊና ውስጥ ይህንን ግዙፍ ዓለም በጥበቡ የዘረጋ አንድ ኃይል መኖሩን የሚያረጋግጥ አንድ አሻራ አለ። ከዚህም የተነሳ ሰውና ሃይማኖት በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በዓለም ላይ ላለ ለማንኛውም ሰው ውስጡ ተቀበለውም አልተቀበለውም ኅሊናው የዓለማት ፈጣሪ እንዳለ በከፍተኛ ድምጽ ይመሰክራል።

ችግሩ እውነተኛውን አምላክ የሚያመልከው የትኛው ነው? የሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ሰው በማይካድ የኅሊና ምስክር እግዚአብሔርን እያወቀ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አላከበረውም አላመሰገነውምም፣ ከዚህም የተነሳ በኃጢአት ውድቀት የደበዘዘው እግዚአብሔርን የማወቅ አቅም የበለጠ ጨለመበት። ስለዚህ በልዩ ልዩ የአምልኮ ምግባርና የሃይማኖት ሽፋን ውስጥ በመሆን የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ለወጠ፣ በፈጣሪም ፋንታ የተፈጠረውን አመለከ አገለገለም። (ሮሜ.1፥21-27)።[12]

በሐዋ.17፥22-23 ጳውሎስ አቴናውያንን "ለማይታወቅ አምላክ" በማለት ሲያመልኩ አገኛቸው። ለእነዚህ ሰዎች ስለ አምላክ መኖር ማስረጃ መስጠት አላስፈለገውም ነበር። ይልቁንም ጳውሎስ ትክክለኛው አምላክ የትኛው እነደሆነ ስለ አምላክ ከሚያውቁት ግንዛቤ በመነሳት አብራራላቸው። እኛም በወንጌል ስርጭት አገልግሎታችን ሰው ሁሉ የጋራ የሆነ የአምላክ ዕውቀት እንዳለው መረዳት አለብን። ይህም ማለት ለሰዎች ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ዕውቀት በምንናገርበት ጊዜ ከምንስማማበት የጋራ ባሕሪይ ተነስተን ወደ ትክክለኛው አምላክ የሚመጡበትን መንገድ መምራት ይኖርብናል ማለት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ምስክርነታችን ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ካለን ልዩነት ሲጀምር ሰዎች መንፈሳቸው እንዲቆጣ ልባቸውም እንዲዘጋ እናደርጋለን። ይህ ማለት ግን ሰዎች ወንጌልን እንዲሰሙን ስንል እውነትን እንሸቅጥ ወይም እናመቻምች (Compromise) ማለታችን ፈጽሞ

አይደለም:: የዚህ ሐሳብ ትኩረት ስልት ላይ እንጂ ይዘት ላይ አይደለም::

እግዚአብሔር በሰው ኅሊና ውስጥ አምላክን የማወቅ ኃይል ካስቀመጠ በኋላ ሰው በማንኛውም ዓይነት ደረጃ እግዚአብሔርን የማወቅ ዕድሉን ቢዘጋና የዘላለም ሞት ፍርድ ቢቀበል እግዚአብሔርን ፍርደ ገምድል አያሰኘውም:: (ሮሜ.2÷12-16):: ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ ፈቃዱ የሆነ አምላክ ማንንም ሰው ስለማንነቱ መረጃ ሳይሰጥ ለፍርድ አይጠይቅም:: ስለዚህ ሁሉም በበራለት ብርሃን መጠን ፍርድን ይቀበላል::

እግዚአብሔር በጥቅል መገለጥ በኩል ራሱን ከገለጠባቸው መንገዶች በሦስተኛና በመጨረሻ ደረጃ የምንመለከተው የታሪክ ክስተት የመለኮት መገለጫ የሚሆንበትን መንገድ ነው::

### 1.3. <u>ታሪክ የመለኮት መገለጫ ሲሆን</u>

እግዚአብሔር አምላክ በዓለም ላይ ለአንድ ዓላማ የሚሰራ በእኔነቱ የነበረ÷ ያለና የሚኖር አካላዊ (Personal) አምላክ ነው:: ይህ ዓይነቱ የኀልውና እንቅስቃሴውም በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ባለው የመብት ጣልቃ ገብነት ሊታይ ይችላል:: ከዚህም የተነሳ ታሪክ ስለእግዚአብሔር መኖርና ስለ ባሕሪውም ይጠቁመናል:: ጠባብና ውስን ከሆነው የአገራችን ሁኔታ ተነስተን የሰፊውን ዓለም ታሪክ ብንቃኝ÷ ከታሪክ ጀርባ በዕቅድ የሚሰራ አምላክ እንዳለ እንገነዘባለን:: የዚህችን አገር ታሪክ ወደ ኋላ ሦስት አሥር ዓመቶች ቆጥረን ብንመለከት ሰባት ጊዜአዊና 'ቋሚ' መንግሥታት ሲነቀሉና ሲተከሉ እንመለከታለን::

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የረጅም ዓመታት የዘውድ አገዛዝ በኋላ÷ ፋታ የሚል መፈክር ይዞ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን የስድስት ወር መንግሥት ብቅ አለ:: ይሁን እንጂ ወታደራዊው ደርግ ከሌሎች 59 የንጉሡ ሹማምንት ጋር ጭጭ አደረገው:: በምትኩ ጀነራል አማን አምዶም ሥልጣን ላይ ወጡ፤ ነገር ግን በኩዴታ ሥልጣናቸውንም ሕይወታቸውንም አጡ:: ከዚያም ተፈሪ ባንቲ የሚባሉ ሌላ ጀነራል የአገሪቱ መሪ ተባሉ::





እሳቸውም በወታደራዊ ሸፍጥ ተገደሉ ተባለ:: ከዚያም በተመሳሳይ ሁኔታ ከመስመር እስኪወጡ ድረስ ኮሎኔል አጥናፉ አባተ የአገር መሪ ተባሉ:: ከዚያ በኋላ አሁን ባለው መንግሥት እስኪገለበጥ ድረስ "ለማንም ለምንም የማይበገር የመከላከያ ሠራዊት አለን" ብሎ የነበረው የኮሎኔል መንግሥቱ አገዛዝ ነበር:: ቀጥሎ የሚሆነው ደግሞ ምን እንደሚሆን እኛ አናውቅም:: የታሪክ ባለቤት ግን ሰፊው ሕዝብ ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሆነ ይታወቃል:: እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው ታሪክ እየሰራና እየወሰነ የአንዲትን አገር ብሎም የዓለምን ታሪክ ይሠራል÷ ይወስናል ሁሉን መስመር ውስጥ እያገባ ወደ ፍጻሜ ያመጣል::

ዛሬ ኃያላን አገሮች ተብለው የሚቆጠሩ እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች ከ 300 እና ከ 400 ዓመታት በፊት ከነመኖራቸውም የሚታወቁ አገሮች አልነበሩም:: ታዲያ እኚህ መንግሥታት ከየት መጡ? ዛሬ የቦቲ ጫማ ቅርጽ ባለው አነስተኛ የቆዳ ስፋት የምትገኘው ጣሊያን በአዲስ ኪዳን ዘመን ከቅኝ ገዢነቷና ከአስገባሪነቷ የተነሳ "መንገድ ሁሉ ወደ ሮም ያደርሳል" የተባለላት ኃያል አገር ነበረች:: ታላቋ ብሪታኒያም "ፀሐይ በእንግሊዝ ግዛት ውስጥ አይጠልቅም" (“The Sun never set in the British Empire” ተብሎላት ነበር:: ታዲያ ያ ማንነታቸው የት ገባ? ዛሬ በአንድ የባሕር ጠርዝ ተወስና የምትገኘውና ስሟን እንኳ በዓመት አንድ ጊዜ የማንሰማው ቱርክ የተባለች አገር በጊዜዋ "የኦቶማውያን ግዛተ አፄ" (The Ottoman Empire) በሚል ስም ሰሜን አፍሪካንና የአካባቢው አገሮችን ታስገብር ነበር:: ባጭሩ ጠረኞቹ የጥንቱ ፊንቂያውያን የት ገቡ? የታለች የነናቡከደናፆር ታላቂቱ ባቢሎን? ካርቴጅያኖችስ ወዴት ገቡ? ፈላስፋይቱን ግሪክንስ ምን ዋጣት? ሁሉም አልፈው የነበረ ታሪክ ሆነዋል:: የዚህ ሁሉ ምክንያት ግን የፖለቲካና የባሕል ለውጥ ሳይሆን የታሪክ ሁሉ ደራሲ የሆነው እግዚአብሔር ምዕራፉን ሲገልጥ ነው::

እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ የሰው ልጆች በየትኛው መልክአ ምድራዊ ክልልና በምን ያለ ጊዜም መኖር እንዳለባቸው የሚቆጣጠር÷ የሚመድብና የሚወስን የበላይ ገዢ ነው:: *"ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን*

*ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ሥፍራ ዳርቻ መደበላቸው"* (የሐዋ.17፥26-27)።

ታዲያ በዘመናት መካከል ያሉ አማኞች ሁሉ ታሪክ ሲለዋወጥ ፈተና ይገጥማቸዋል። አንዳንዶቹ የተለወጠው መንግሥት ሁሉ ይዞት የመጣው የውሸት ተስፋ ሲማርካቸው፥ አንዳንዶቹን ደግሞ አዲስ መንግሥት ይዞት የሚመጣው ዛቻና ማስፈራራት ልባቸውን ያርደዋል። በሁለቱም መንገድ ከእምነታቸው የሚያፈገፍጉ ብዙዎች ናቸው። እግዚአብሔር የታሪክ ባለቤት መሆኑን ያልተገነዘቡ ከአማኝነት/አገልጋይነት/ ወደ ፖለቲካ ካድሬነት ተለውጠው የነበሩ ብዙ ናቸው። መንግሥት በተለወጠ ጊዜ እምነታቸው የተናጋ ጥቂቶች አይደሉም። ይህ ደግሞ የቆመ የሚመስለው በወደቀው ላይ የሚጠቋቆምበት ሳይሆን በየጊዜው እያንዳንዱን አማኝ ሊገጥመው የሚችል ፈተና ነው።

በትንቢተ ዳንኤል ምዕ.11፥1-12፥3 ላይ እግዚአብሔር ወደ ፊት ባሉት ዘመናት ውስጥ የሚከሰት የአራት መንግሥታትን መነሳትና መውደቅ ለባሪያው ለነብዩ ዳንኤል አስቀድሞ ይነግረዋል። እነዚህ ነገሥታት ከየት እንደሚነሱና መቼም እንደሚነሱ አወዳደቃቸውም እንዴት እንደሆነ የታሪክ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ከወዲሁ ይነግረዋል። ከዚህም ጋር አብሮ በእነዚህ መንግሥታት መውደቅና መነሳት ሳቢያም ብዙ አይሁዳውያን ከአምልኮተ ያህዌህ እንደሚያፈገፍጉና እንደ ሚሰናከሉ ይነግረዋል። ደግሞም በተቃራኒው በእነዚያ ቀውጢ ቀናት የሳለ ሰይፍንና የሸንገላ ተስፋን ተቋቁመው በታማኝነት የሚጸኑ አማኞችም እንደሚኖሩ ይነግረዋል። "ቃል ኪዳኑን የሚበድሉትንም በማታለል ያስታል ነገር ግን *አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም"* (ዳን.11፥32)። እግዚአብሔር የእምነታችንን ጽናት ከሚፈትንበት መንገድ አንዱ ታሪክ ሲለዋወጥ ያለንን ታማኝነት በመለካት ነው። ስለ ጠቅላላ መገለጥ እስከ አሁን ድረስ የተመለከትነውን "የጠቅላላ መገለጥ ብቃት እስከ ምን ድረስ ነው?" የሚለውን ጥያቄ በመመለስ እናጠቃልለዋለን።





## 1.4. <u>የጥቅል መገለጥ ብቃት እስከ ምን ድረስ ነው?</u>

ሰዎች በተፈጥሮ አማካኝነት የእግዚአብሔርን ኃያልነትና አምላክነት ያያሉ፤ ሮሜ.1፥19 ይህንን ይናገራል፦ *"እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና"* ከዚህም ሌላ ሰዎች በተፈጥሮአቸው የሕግን ሥራ መሥራትና ምግባራዊ ፍርድን መፍረድ ይችላሉ። ሮሜ.2፥14 ይህንን ይናገራል፤ *"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕሪአቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና እነርሱም ኅሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ"* እንዲህም በመሆኑ ጥቅል መገለጥ የእግዚአብሔርን ኅልውና ያሳያል። ለአማኞች ደግሞ ይህ ጥቅል መገለጥ የዳኑበትን ልዩ መገለጥ የበለጠ ይተረጉምላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ መገለጥ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ከሰጠው ጥቅል መገለጥ ጋር ሲታይ የበለጠ መንፈሳዊ መረዳት ይሰጣል።

ይሁን እንጂ ይህ ጥቅል መገለጥ ስለ እግዚአብሔር መገለጥ ሙሉ የሆነ ዕውቀትና መንፈሳዊ እውነትን አያስተላልፍም። አስተማማኝ የሆነ የዘላለም ሕይወት ተስፋም ለመመሥረት በቂ አይደለም።

ጥቅል መገለጥ የፍጥረትን ግዝፈትና ውበት የፈጣሪንም ታላቅነትና ርቅቀት፥ እንዲሁም ሰው ሁሉ ከሚያየው ነገር በስተጀርባ ታላቅ የሆነ ሠሪና አድራጊ መኖሩን ለኅሊና የሚያረጋግጥ ቢሆንም፥ ያ አድራጊና ፈጣሪ ምን እንደሚወድና እንደሚጠላ፥ ምን እንዳለና እንዳላለ ሙሉ መረጃ አይሰጥም።

ከጠቅላላ መገለጥም ተነሥተን እውነተኛ ሃይማኖት ለመመሥረት አንችልም። እንዲህ ዓይነቱ መገለጥም በኋለኛው ዘመን እግዚአብሔር አብ ወደ እኛ የላከውን ክርስቶስን ወደ ማወቅ አያደርስም። ይህ ዓይነቱ መገለጥ የሚያድነውን ጸጋ ስለማያመጣ ኃጢያተኞችን ከኃጢያት ባርነት አላቆ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን ወደሚገኝ ነጻነት አያደርስም። ለእንዲህ ዓይነቱ አምላካዊ ግንኙነት እስከ አሁን ከተመለ

ከትናቸው ከተፈጥሮ፥ ከሰው ኅሊናና ከታሪክ አስረጅነት የላቀ ልዩ መገለጥ የግድ አስፈላጊ ነው:: ይህንንም እንደሚከተለው እንመለከታለን::[13]

## 2. <u>ልዩ መገለጥ</u>

ሁለት የተራራቁ ግለሰቦች ሊገናኙ የሚችሉባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች ይኖራሉ፤ አንድ ሰው ሩቅ ላለ ዘመዱ ደኅንነቱን ለመግለጽ፥ በሰው በኩል የቃል መልዕክት መላክ ይችላል:: ከዚህ ይልቅ ደግሞ ዘርዘር ያለ ደብዳቤ ቢጽፍ ይሻላል:: ነገር ግን ከሌጣ ደብዳቤ ይልቅ ደግሞ ፎቶ ቢጨመርበት ይመረጣል:: መቼም ዘመኑ የተሻሻለና ቴክኒዎሎጂ ያደገፈው ስለሆነ ከቃል መልዕክት፥ ከደብዳቤና ከፎቶም ይልቅ በቪዲዮ የተቀረጸ መልዕክት አስተማማኝ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ሁሉ የበለጠ ጥሩ የሚሆነው ያው ሰውየው መጥቶ ሲገናኝ ነው:: የእግዚአብሔርን መገለጥ አስመልክቶም ያለው የጠቅላላና የልዩ መገለጥ ጉዳይም ይህንኑ የሚመስል ነው:: እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው መንገዶች ከጠቅላላ ወደ ልዩ እየገሰገሰን ስናያቸው ከመረጃዊነት ይልቅ ቀጥተኛና ግንኙነታዊ ሆነው እናገኛቸዋለን::

ልዩ መገለጥ ማለት:- እግዚአብሔር አምላክ ለማዳንና ሕብረትን ለመፍጠር ሲል <u>ለተወሰነ ሰው/ሰዎች/</u> <u>በተወሰነ ጊዜና በተወሰነ ቦታ</u> <u>*በራሱ አነሳሽነት ራሱን ይገልጣል*</u> ማለት ነው:: እግዚአብሔር ራሱን መግለጥ ያስፈለገበት ምክንያት፥ ሰው በውድቀቱ የተነሳ እግዚአብሔርን የማወቅና የመፈለግ አቅሙ ስለተበላሸ ነው:: የሰው ልጅ እግዚአብሔር ታላቅ፥ ኃያልና ሊያስፈራ የሚገባ መሆኑን እያወቀ አሁንም በገዛ መንገዱ በመሰለውና በስሜቱ እየተነዳ ከውድቀቱ ሊማር አልቻለም:: ውድቀቱም ከእግዚአብሔር ሐሳብ የራሱን ሐሳብ ስለሚያስቀድም ነው:: ሁሉን የሠራውን አምላክ ሳይሆን እኔ ባወቅሁትና በተረዳሁት ብቻ ልሂድ እያለ ነው:: ሰው በኃጢያቱ የተነሳ ከ150ኛ ፎቅ ላይ እንደተወረወረ ቲማቲም ሆኖአል:: ራሱን ሊረዳ እስከማይችል ድረስ ኃጢያት የሰውን ሁለንተና አበላሽቶአልና፥ እግዚአብሔር በራሱ አነሳሽነት ራሱን በልዩ ሁኔታ ለሰው ልጆች ይገልጥ ዘንድ ግድ ሆኖአል <u>*ሮሜ.3፥11-20::*</u>





በዚህ ዓይነቱ ልዩ መገለጥ ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር አካላዊ አምላክ መሆኑ ይረጋገጣል:: አንዳንዶች እንደሚሉት ሐሳብ ወይም አንድ ኃይል ሳይሆን፥ ከሰው ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚችል "እኔነት" ያለው አካላዊ ባሕሪይ ያለው አምላክ ነው (He is a personal God) ይህም ማለት ያዝናል፥ ይደሰታል፤ ከማንነቱም አንጻር ይወዳል፥ ይጠላልም::

እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው እግዚአብሔር ለተለየ ሕዝብ ራሱን ሲገልጥ፥ የተገለጠላቸው ሰዎች የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት ሳይሆን፥ እርሱን ለሌሎች ይገልጡ ዘንድ የበረከት መተላለፊያ አድርጎ ሊጠቀምባቸው ነው:: ለምሳሌ በዘፍ.12፥2-3 ላይ እግዚአብሔር አብራምን ሲጠራው፥ ለራሱ ብቻ በረከት እንዲሆን ሳይሆን "...የምድር ነገዶች ሁሉ <u>*ባንተ ይባረካሉ*</u>" በሚል ጥሪ ነው የጠራው:: ደግሞም ዘጸ.19፥6/ 1ጴጥ.2፥9 "...የእርሱን በጎነት <u>*እንድትነግሩ*</u> የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" ይላል:: ስለዚህ የእሥራኤል መመረጥ ለአሕዛብ በረከት ማስተላለፊያ ትሆን ዘንድ እንደነበረ ሁሉ፥ እንዲሁ የቤተ ክርስቲያንም መመረጥ ላልዳኑ የደኅንነት በረከት መተላለፊያ ትሆን ዘንድ ነው::

ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ በአንዴ የተዘረገፈ አይደለም:: በዘመናት መካከል ርምደታዊ (Progressive) በሆነ መልኩ የሚገሰግስ ነው:: ይህ የእግዚአብሔር መገለጥ እየጨመረና እያደገ የሄደ ጉዳይ እንደሆነ ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ባለው ርምደትና ግስጋሴ እንመለከታለን:: በብሉይ ኪዳን የተጠቀሱት የእግዚአ ብሔር የማንነቱ ማስረጃዎች በአዲስ ኪዳን በበቂ ብርሃንና በመጨረሻ ሥልጣናዊነት ተገልጠው እንመለከታለን (ዕብ.1፥1-3):: ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በውስጡ በጣም ባለጠጋ የሆነ መረጃ ያለው ክፍል ነው:: ከብሉይ እስከ አዲስ ያለውን የአምላክ መገለጥ በአጭር ዐረፍተ ነገር ይገልጣል:: በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ሀሳቦችን እናያለን:: (1) እግዚአብሔር ለሰዎች እንደተናገረ፥ ምክንያቱም "ለአባቶቻችን በነቢያት <u>*ተናግሮ*</u>..." ይላልና ነው:: (2) ባለፈው ዘመን የተፈጸመው ከአሁን ጋር ግንኙነት እንዳለው፥ ምክንያቱም "ከጥንት ጀምሮ...በዚህ

ዘመን" ስለሚል:: በቁጥር 1 መጨረሻ ላይ፥ "በነቢያት ተናግሮ" ይላል፤ ይህም የመጽሐፍ ቅዱሱን ትንቢት መሠረታዊ ባሕሪይ እንድናይ ያደርገናል:: *የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት:- (1) የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ስለዚህም እውነት ነው:: (2) ተጨባጭ ትርጉም አለው፤ ስለዚህም መዘላበድ አይደለም:: (3) ተፈጻሚነት አለው፤ ስለዚህ ነቢያት "አለ" ካሉ ሙሉ በሙሉ ይሆናል፤ ነገር ግን የትንቢት ተፈጻሚነት በሁለት የጊዜ ገደብ ይታያል፡ ወዲያው የሚፈጸምና ጊዜውን ጠብቆ የሚፈጸም:: በኃይል፡ በንጽሕናና በሥልጣን የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት የሚወዳደር የለም::*

"በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና" የሚለው ሐሳብ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥ ፥ አንድን ነገር በመደጋገም ሳይሆን ከአንድ ጊዜ በላይ፥ በተለያየ ዓይነት መንገድ፥ መናገሩን የሚገልጥ ሐሳብ ነው:: ለአስረጅነት የሚከተለውን ምሳሌ ብቻ እንውሰድ::

'ያህዌ' እሥራኤልን ከባርነት ነጻ ሲያወጣ፥ ራሱን በአሥር መቅሰፍቶች በኩል ገልጧል:: እያንዳንዱ በግብጽ ላይ የወረደው መቅሰፍት፥ የግብጽ አማልክቶችን የሚገዳደር ቀጥተኛ መልዕክት አለው:: እዚህ ላይ አሥሩንም መቅሰፍቶችና ትርጓሜአቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ባይሆንም፥ ለአንባቢ ግንዛቤ ያህል፥ ሁለቱን ብቻ እንጠቅሳለን::

በዘጸ.7፥20 ላይ "በትሩን አነሣ፥...የወንዙን ውኃ መታ የወንዙም ውኃ ተለውጦ ደም ሆነ" ይላል:: የእስራኤል አምላክ ከግብጽ ዓባይ ጋር ምን ጉዳይ ቢኖረው ነው? የሚል ጥያቄ መጠየቅ አስፈላጊ ነው:: በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው፥ ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የግብጽ የልብ ምት ከዓባይ ወንዝ ጋር ክፉኛ የተቆራኘ ነው:: ከላይኛው ግብጽ ወደ ታችኛው ግብጽ ለመምጣት ከፍተኛ የትራንስፖርት ጥቅም የሚሰጥ ዓባይ ነው:: ከዚህም ሌላ ዓባይ ለግብጽ ግብርና ከፍተኛ ስትራተጂካዊ አስተዋጽዖ ያለው ወንዝ ነው:: ባጭሩ ግብጽን የሰሀራ በርሃ አንደኛው ክፍል እንዳትሆን ያደረጋት ዓባይ ነው::

ከዚህም የተነሳ የግብጽ ዓባይ ይዘፈንለታል፥ ይዘመርለታል፥ ይመለካልም:: የሕያዋን ወላድነት፥ የምድሪቱ ባርኮትና ደስታ በዓባይ ታማኝነት ላይ በጽኑ የተመሠረተ እንደሆነ





ይታሰባል:: ስለ ዓባይ ብዙ ማለት ቢቻልም፥ በአጭሩ ዓባይ ከአማልክቶቻቸው መካከል አንዱና ዋነኛ ነበረ:: ነገር ግን የእሥራኤል አምላክ በዓባይና በግብጽ አማልክቶች ላይ የበላይ መሆኑን ያሳይ ዘንድ፥ ዓባይን እንደማይጠጣ፥ ዓባይን እንደማይዘፈንለትና እንደማይመለክ አደረገው:: ዓባይን ከመታው ከሰባት ቀን በኋላ ደግሞ ሌላ መቅሰፍት ሆነ::

'ያህዌ' በምድረ ግብጽ ጓጉንቸሮችን አፈላ፤ የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች እንደሚናገሩት በአካባቢው በርካታ የጓጉንቸር ሥዕላ ሥዕሎች አግኝተዋል:: ጓጉንቸር የምርት ዋስትና ሰጪ ናት ተብሎ ስለሚገመትም ጥንታዊ ግብጻውያን በምልክት አስቀርጸው በአንገታቸው ያስሩ ነበር:: የእሥራኤል አምላክ 'ያህዌ' ግብጽን ሲቆጣ ፥ እንደብርቅ የሚታዩትንና ውኃ ባለበት ቦታ ብቻ የሚገኙትን ጓጉንቸሮች፥ በግብጻውያን ጉያ ከነእርጥበታቸው አፈላቸው:: "የእንቁራሪት አምላክ በአፍንጫችን ይውጣ" እስከሚሉ አደረሳቸው:: በጠቅላላው በአሥር ዓይነት መልኩ ግብጻውያንንና አማልክቶቻቸውን አስጨነቀ::

በዚሁ በእብራውያን መልእክት ላይ፥ በቁ.2 "በዚህ ዘመን መጨረሻ" ይላል፤ ለጸሐፊው ማነጻጸሪያው የብሉይ ኪዳን ዘመን ነው:: ይህ ሐሳብ ሙሉነት የጎደለውና የቀደመው የመሥዋዕት ሥርዓት የሚያበቃበትና መሢሑ የተገለጠበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው:: "በልጁ ተናገረን" ሲል ደግሞ እግዚአብሔር በልጁ የመገለጡ ጉዳይ፥ የግልጠቱ መጨረሻ ወይም ጫፍ እንደሆነ ሲነግረን ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሔር አምላክ ልዩ መገለጥ ከአሪት ዘፍጥረት አንስቶ በተጠቀሰው የሰው ልጆች የደኅንነት ታሪክ ውስጥ እየተተረተረና እየተገለጠ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ የአካል መገለጥና የደኅንነት ሥራ ድምዳሜውን አገኘ (ዮሐ.1፥1-18)::

ነገር ግን በማንኛውም ዓይነት መልኩ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ራሱን ሲገልጥ ሰዎች ስለ ማንነቱ ያላቸውን መረጃና ንደፈ ሐሳባዊ (Theoretical) ዕውቀት እንዲጨምሩና እንዲያሰፉ አይደለም:: ይልቁንም እርሱን ለማወቅና ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ እንዲችሉ ነው እንጂ:: ባጭሩ የልዩ መገለጡ ዋነኛ ዓላማ ግንኙነት/ኅብረት/ለመፍጠር ነው:: "Knowing God is not informational it is relational"[14] ስለዚህ እግዚአብሔርን

አውቀናል እያልን ከመረጃ ያለፈ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት የሌለን ከሆነ ራሳችንን እንፈትሽ! በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ዕውቀት ማደግ አለበት:: ይህ ዕውቀት ባለበት የሚቆም ሳይሆን ማደግ የሚገባው ነው:: ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች በትርጉም ደረጃ የተመለከትነው ልዩ መገለጥ በምን ዓይነት ሁኔታ ተገልጧል? የሚለውን ጥያቄ እንደሚከተለው እንመልሳለን::

## 2.1. <u>የልዩ መገለጥ መንገዶች</u>

"በዕውቀትና በኃይሉ ታላቅና ኢ-አላቂ (Infinite) የሆነው ይህ አምላክ በምን ዓይነት ልዩ መልኩ ለውስኑ የሰው ልጅ ራሱን ገለጠ?" የሚለው ጥያቄ አይቀሬ ነው:: መቼም ፍጡር የሆነው ሰው እግዚአብሔርን መርምሮ አይረዳውም፥ ስለዚህ አምላክ በሰው ደረጃና አቅም ሰውኛም በሆነ መልኩ መገለጡ የግድ ነው:: ለሰው ቅርቡ ሰው ነው፤ ለሰው ቅርቡ የሰው ጠባይ ነው፤ ሰው የሚገባው የሰው ነገር ነውና::[15] ስለዚህ እግዚአብሔር የተገለጠበት ቋንቋና ልማድ ከሰው ልጆች ተሞክሮ (Experie - nce) ጋር በሚስማማ ሁኔታ ነው:: ከእነዚህም የመገለጥ መንገ ዶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል::

### 2.1.1.<u>በድምጸ መለኮት</u>

በተለይ በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች በቀጥታ በድምጽ በመነጋገር መግለጹ የተለመደ ነበር:: ለምሳሌ፡- “ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርሚያስ የመጣ ቃል እንዲህም አለው...” ኤር.18÷1:: “የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ...” (ሕዝ.12÷1፤8፤17፤26፤ ሆሴ.1÷1፤ አሞ.3÷1):: እያለ ለነብያት በድምጽ ራሱን ገልጧል:: ስለ ራሱ፥ ስለ ዕቅዱና ስለ ፈቃዱ በሰዎች በኩልና ለሰዎች በድምጽና በቀጥታ በንግግር ይገልጣል::

ይህ ድምጸ መለኮት፥ ልዩ ልዩ ዓይነት መልክ ሊኖረው ይችላል:: በቀጥታ ከውጪ በጆሮ የሚደመጥና የሚሰማ ሊሆን ይችላል፥ ወይም ደግሞ በፀጥታ የእግዚሔርን ድምጽና መልዕክት





በአዕምሮ/በልቡና/ መስማት ሊሆን ይችላል:: ልክ አንድ ሰው በጸጥታና በእርጋታ መጽሐፍ ሲያነብ የመጽሐፉ ድምጽ በጆሮው እንደማይሰማው፥ ሆኖም በልቡናው የመጽሐፉን ንግግር እንደ ሚያደምጥ ሁሉ የእግዚአብሔርም ድምጽ እንዲሁ ይደመጣል:: ብዙ ጊዜ የተለመደውም ይኼኛው መንገድ ሳይሆን አይቀርም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቀጥታም በሚደመጥ ድምጽ ለብዙ ቅዱሳን እንደተገለጠም የሚከተሉት ሦስት ማስረጃዎች ይበቃሉ::

ሙሴን እግዚአብሔር አፍ ለአፍ ማናገሩ፡- *"ባሪያዩ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው:: እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ አናግረዋለሁ"* በማለት እግዚአብሔር ስለ ሙሴ ይመሰክራል (ዘኁ.12÷8):: የእግዚአብሔር ጥሪ ለሳሙኤል፡- *"እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው ይላል"* (1ሳሙ.3÷1-14):: ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ ማናገሩ፡-*"ሳውል ሳውል ስለ ምን ታሳድደኛለህ የሚል ድምጽ ሰማ ጌታ ሆይ ማነህ አለው:: አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ አለው"* (ሐዋ.9÷4)::

### 2.1.2 <u>በሕልምና በራእይ</u>

ሕልም የኅሊናን ንቁነትን የማይጠይቅ በእንቅልፍ ዓለም ካለ ትርዒት ጋር የተያያዘ ግንኙነት ነው:: ውስብስብ የሆነ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕሪይ ነው:: በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ዕውቀት የሕልምን ትርጉም አስመልክቶ ሳይንሳዊ ማብራሪያ መስጠት ባይቻልም፥ እግዚአብሔር አምላክ የመንፈሳዊውን ዓለም ሚስጢር በሕልም በኩል ለሰዎች እንደሚገልጥ ግን ለብዙዎቻችን እሙን ነው:: ቅዱስ ቃሉም ስለዚህ ምስጢር በኢዮብ 33÷14-18 ላይ እንዲህ ብሎ ይናገራል፡- *“እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውልም:: በሕልም፥ በሌሊት ራእይ፥ አፍላ እቅልፍ በሰዎች ላይ ሲወድቅ: በአልጋ ላይ ተኝተው ሳሉ፥ በዚያን ጊዜ የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል: በተግሳጽም ያስደነ ግጣቸዋል፥ ሰውን ከክፉ ሥራው ይመልሰው ዘንድ፥ ከሰውም ትዕቢትን ይሰውር ዘንድ ነፍሱን ከጉድጓድ፥ በሰይፍም እንዳይጠፉ ሕይወቱን ይጠብቃል::”*

ከዚህም ሌላ በዘፍ.28÷10-15 እንደተጠቀሰው ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን በሄደ ጊዜ በመንገድ መሽቶበት ድንጋይ ተንተርሶ ተኝቶ እግዚአብሔር ከመጀመሪያ አንስቶ ያዘጋጀለትን የበረከት ተስፋ በሕልም ሲያጸናለት እንመለከታለን ። ደግሞም በትንቢተ ዳንኤል 2÷1 እንደተጠቀሰው ንጉሥ ናቡከደናፆር ያለፍቺ ሚስጢሩ የማይታወቅ ሕልም እንዳለመ ይህንንም ዳንኤል እንደፈታለት እንመለከታለን::[16] ስለዚህ እግዚአብሔር በሕልም ነገሥታትን ያስጨንቃል፥ ቅዱሳኑን ያበረታታል ያጽናናልም፡

እግዚአብሔር የመንፈሳዊውን ዓለም ሚስጢር የሚገልጥበት ሌላው ተመሳሳይ መንገድ ደግሞ ራእይ ነው:: ራእይ በሚታይበት ጊዜ ራእዩን የሚያየው ሰው በንቁው አዕምሮው እያለ ኀሊናው ከባሻገር የሚወሰድበት ሁኔታ ነው:: እንደ ሕልም በእንቅልፍ ዓለም ካለ ትርኢት ጋር የተያያዘ ግንኙነት የለውም:: ሆኖም በቀንም በሌሊትም ሊመጣ ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ ሕልም፥ ተመስጦ (Trans) እና ራእይን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው ይባላል:: ቢሆንም ከሕልምና ከተመስጦ ይልቅ ራእይ ጠለቅ ያለን የእግዚአብሔር መገኘት የሚያመለክት ይመስላል:: ለማገናዘብም ያህል (ዘፍ.46÷2፤ ኤር.1÷11፤ ዳን.10÷3) ማየት ይበጃል::

### 2.1.3.በመላእክትና በአስተርእዮተ መለኮት

መላእክት ስማቸው ከአገልግሎታቸው ትርጉም የተገኘ ነው:: በፍጥረታቸውም መናፍስት የሆኑ ናቸው:: አገልግሎታቸ ውም መልእክትን ከእግዚአብሔር መንበር ወደ ሰው ልጆች ማምጣት ነው:: ሰው መልሶ ወደ እግዚአብሔር ሲልካቸው አንመለከትም፤ ነገር ግን ሰዎች በግልጠተ መላእክት ጊዜ ለሚጠይቁት ጥያቄ መላእክት እዚያው መልስ ሲሰጡ እንመለ ከታለን:: (ሉቃ.1÷26-38፤ መሳ.13÷3-21):: ብሉይ ኪዳናዊው ሕግጋትና ሥርዓትም ለእሥራኤል ሕዝብ በመላእክት በኩል ተሰጥቶአል (ገላ.3÷19፥ ዕብ.2÷2)::

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማጽናናት፥ ለመታደግ፥ በጠላቶች ላይ ለመበቀል እንዲሁም በአመጸኞች ላይ ለመፍረድ መላእክቱን እንደሚልክ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አሉ::





በአጠቃላይ እግዚአብሔር ራሱን በመላእክት በኩል ስለ መግለጹ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ርምደታዊ በሆነ መልኩ እየፋፋ የተገለጠ ሁኔታ ነው:: (ዳን.9÷20-22፤ ሉቃ.1÷26፤ ገላ.3÷19፤ ሕዝ.12÷27 ፤ ዮሐ.9÷7፤ የሐዋ.12÷6-11)::

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ዓይነት መልክ ራሱን ይገልጥ ነበር:: እንደ ሰው፥ እንደ ደመና፥ እንደ እሳትና እንደ መልአክ በመሆን በብሉይ ኪዳን ራሱ በተለያዩ መንገዶች ገልጧል:: ይህም ዓይነት አገላለጡ ከግሪክ ቃል በተወሰደ የእንግሊዘኛ ስያሜ (Theo-phany) የሚባል ሲሆን የአማርኛው ስያሜ አስተርእዮተ መለኮት በመባል ይታወቃል[17] (ዘጸ.3÷2)::

### 2.1.4. በተአምራት

አንድ ክስተት ተአምራዊ ነው ለማለት ባልተጠበቀና ቅጽበታዊ በሆነ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ሁኔታዎችን ከመደበኛው የተፈጥሮ ሕግጋት ውጪ አድርጎ መገኘት መቻል አለበት::[18] ለምሳሌ:- የቀይ ባሕር መከፈል (ዘጸ.14÷15-31) ፥ በውኃ ውስጥ የሰጠመን የብረት መጥረቢያ ማንሳፈፍ (2ነገ.6÷1-7) ፥ 38 ዓመት ተሽብቦ የነበረን ሰው "ተነሳና አልጋህን ተሸክ መህ ሂድ" ማለት (ዮሐ.5÷1-9) ፥ የሰበትን ሕግ ተቋቁሞ በተንጣ ለለ ባሕር ላይ በእግር መራመድ (ዮሐ.6÷19)፥ ከአራት ቀን የሞት የእንቅልፍ ዓለም "አልዓዛር ና!" ብሎ ጠርቶ ማስነሳት (ዮሐ.11÷38-44) ፥ ንጹሕ ውኃ ብቻ የተሞሉ ስድስት ጋኖች ደርድሮ እኔ ነኝ ያለ የወይን ጠጅ መቅዳትና (ዮሐ.2÷1-11) የመሳሰሉት ሲሆኑ፥ *ክብርን ለእግዚአብሔር የነፍስ መዳንን ለሰው ልጅ የሚሰጡ* እንዲህ ዓይነት ክስተቶች የመለኮት መገለጫ ናቸው::

### 2.1.5. በክርስቶስ

አንድ ሰው ከአካባቢው በተለየ መልኩ አንድን ነገር ሲያደርግ ወይም ደግሞ በውጪ ከሚታየው ማንነቱ ጋር የሚቃረን ድርጊት ሲያደርግ “ለመሆኑ ማን ነው እሱ?” የሚል ጥያቄ እንጠይቃለን:: አንዳንድ ሰው ከውጪ ሲያዩት የሚመስለው ነገርና በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ እውነተኛ ማንነቱ ሲገለጥ

የሚታየው ነገር "ይኼ ሰው ለመሆኑ ማን ነው?" "ይኼ ሰው ማን ቢሆን ነው ይህንን ነገር ያደረገው?" "ይኼ ሰው ምን ዓይነት ቢሆን ነው ሰው ሁሉ እንደዚህ የሚወደው /የሚፈራው/ የሚያከብረው?" ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል:: "ለመሆኑ ማነው እሱ?" የሚለው ጥያቄ በየዕለት ኑሮአችን የምንጠይቀው ጥያቄ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ከውልደቱ እስከ ሥጋ ሞቱ ድረስ የነበረው እያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴ "ለመሆኑ ማን ነው እሱ?" የሚያሰኝ ማንነት ያለው ነው::

*በሃይማኖት መሪነቱ ስናየው፡-* እነ ነብዩ ሙሴ፥ እነ ሐዋሪያው ጳውሎስና ሌሎቹም የእምነት አባቶች እኛ አምላክ ነን አላሉም:: ክርስቶስ ግን አምላክነት የእኔ ነው ብሏል:: ሁሉም መንገዱ ይኸውና አሉ:: እርሱ ግን መንገዱ እኔ ነኝ አለ:: ሁሉ ሕይወት ወይ በዚህ ወይ በዚያ ይገኛል አሉ:: እርሱ ግን ሕይወት እኔ ነኝ አለ:: ሁሉም እውነተኛው በዚህ ወይ በዚያ አለ አሉ:: እርሱ ግን እውነት እኔ ነኝ አለ::[19]

*በአስተማሪነቱ ስናየው፡-* ትምህርቱ ከሌሎች የሃይማኖት አስተማሪዎች በዓይነቱ ብቸኛ በጥራቱ ፍጹም ነው:: ከለሳና ማደሻ የሌለው አንዱ በቃኝ ዓይነት ነው:: በግምትና በይሆናል ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ነው ያስተማረው:: በጊዜው የነበሩ የሕግ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሏል በሚል ክስ መጻሕፍትን፣ ነብያትንና ሙሴን በእርሱ ላይ ለማስመስከር ተነሱበት፣ ቢሆንም ምስክሮቹ በእርሱ ላይ ሳይሆን ስለ እርሱ መሰከሩ::[20]

ለመሆኑ ይኼ ኢየሱስ ማን ነው? አንድ ጊዜ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ደቀ መዛሙርቱን "*ለመሆኑ ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል?" ሲል ጠየቃቸው:: ደቀ መዛሙርቱም "አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ ነው ሲሉህ አንዳንዶቹ ኤልያስ ነው ይሉሃል ሌሎቹ ደግሞ ኤርምያስ ነው ሲሉህ የቀሩት ደግሞ ከነብያት አንዱ ነው ይላሉ" ሲሉ መለሱለት ኢየሱስም "እነርሱስ እንዲህ አሉ እናንተስ ማን ነው ትላላችሁ? ሲል ጠየቃቸው:: (ማቴ.16፥14-16 ሕያው ቃል ትርጉም)::*





ዛሬ ይህንን ጥያቄ እያንዳንዳችን ልንመልሰው የሚገባ ጥያቄ ነው:: ለመሆኑ ይህ ኢየሱስ ማን ነው? እግዚአብሔርስ በእርሱ በኩል ተገልጧል ስንል ምን ማለታችን ነው? ከብዙ ማስረጃዎች ውስጥ ጠንካራ ከምንላቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ንባባት ውስጥ አንዱ የሆነውን የዮሐንስ ወንጌል ምዕ.1፥1 እና ቁ.14ን ሰፋ ባለ መልኩ እንመለከታለን::

### 2.1.5.1 ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ..." (ዮሐ.1፥1)

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው በጣም ጥቂት ቦታ ነው:: በዋነኛነት የተጠቀሰውም በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል የመጀመሪያው ምእራፍ ላይ ነው (ዮሐ.1፥1-18):: ምንም እንኳ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ የሚገኝ ባይሆንም በቤተክርስቲያን ውልደትና እድገት የመጀመሪያዎቹ ሦስትና አራት ምዕተ ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስን ማንነት አስመልክቶ ባለው ትምህርት ዋነኛና ቁልፍ ሐሳብ ሆኖ አልፏል::[21]

ከሐዋርያት ቀጥሎ የነበሩት ሐዋርያዊ አባቶች (Apostolic Fathers) ይህንን የክርስቶስ መጠሪያ በጥልቀትና በስፋት ለማጥናት ሙከራ አድርገው ነበር:: እነዚህ አባቶች ለዚህ "ቃል" ለተሰኘው ለክርስቶስ መጠሪያ ለምን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡት አስፈለገ? "ቃል" የሚለውስ የጌታ መጠሪያ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ ከነበረው ዓለም ጋር ምን ዓይነት የፍልስፍና ተዛምዶ ነበረው? ዮሐንስ *በመጀመሪያ ኢየሱስ ነበረ፥ ኢየሱስም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ኢየሱስም እግዚአብሔር ነበረ...* በማለት ለምን አልጻፈም? በዚህ በዮሐንስ ወንጌል ላይ *"ቃል"* የሚለው ቃል የአንድ ነገር መጠሪያ፥ ስያሜ ወይም በፊደል የሚገለጽ ሃሳብ፥ ከሚለው የተለምዶ ትርጉም ሌላ ምን ፍቺ ሊኖረው ይችላል? እኛስ ዛሬ ለዚህ ስያሜ የምንሰጠው ትርጉም በታሪክ ውስጥ ለዘመናት ሲሰጥ የነበረው ትርጉም ውጤት መሆኑን አውቀናል ወይ? ጌታ ኢየሱስ ቃል መሆኑን ብዙ

ብናወሳም ታሪካዊ ዳራው ገብቶናል ወይ? እነዚህና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ ዮሐንስ ወንጌሉን በጻፈበት ጊዜ የነበረው የግሪክ ዓለም ይህንን *"ቃል"* የተባለውን ቃል እንዴት ይረዳው እንደነበረ ማወቅ ግድ ይሆናል።

ከታሪክ ምስክርነት እንደሚታወቀው ክርስትና ተወልዶ ያደገው የግሪኮች ባሕል፥ ፍልስፍናና ቋንቋ የወቅቱን ዓለም አመለካከትና አኗኗር ከፉኛ ቀርጾት በነበረበት ወቅት ነው። በተለይ ደግሞ በቋንቋው በኩል የነበረው ተጽእኖ ከፍተኛ ስለነበረ፥ የመካከለኛውና የቅርብ ምሥራቅ አካባቢ አገሮች፥ የአስገባሪዎቻቸው ቋንቋ የሆነውን ግሪክ መናገር ግድ ሆኖባቸው ነበር። ክርስትናም የተወለደው በዚያን ወቅት ስለነበረ አራቱን ወንጌላት ጨምሮ ሃያ ሰባቱም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ብሉይ መጻሕፍት በዕብራይስጥ ሳይሆን በግሪክ ቋንቋ ነው የተጻፉት። የአራተኛው ወንጌል ጸሐፊ የሆነው ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ግሪካዊ አስተሳሰብ ለዋጠው ሕብረተሰብ ነበር። የዚህ ወንጌል የመጀመሪያው አንባቢዎች አማርኛና እንግሊዘኛ ሳይሆን የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪዎችና ጥንታዊ ግሪካዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ነበሩ።[22] ባጭሩ እግዚአብሔር ያንን ጊዜ፥ ያንን ባሕልና ያንን ቋንቋ መርጦ ለዘመናት የሚበቃ መልእክቱን ማስተላለፊያ አድርጎታል።

ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት ወንጌሉን ሲጽፍ የተጠቀመባቸው ቃላት ሕይወት ያላቸውና ወቅታዊ ነበሩ። *"ቃል"* ተብሎ ወደ አማርኛ የተመለሰው መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪኩ *"ሎጎስ"* የሚል ስያሜ አለው። ስለዚህ ዮሐንስ በምዕ.1፥1 ላይ *"ኢን አርኬ ኤን ኸ ሎጎስ ካይ ኸ ሎጎስ ኤን ፕሮስ ቶን ቴዎን ካይ ቴዎስ ኤን ኸ ሎጎስ" (በመጀመሪያ ሎጎስ ነበረ ሎጎስም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሎጎስም እግዚአብሔር ነበረ)* ብሎ ጻፈ። ይህ አባባል በጊዜው የነበረውን ግሪካዊ አስተሳሰብ እና ፍልስፍና ክፉኛ የሚገዳደር ነበር። በተለይ በቁ.14 ላይ *ሎጎስም ሥጋ ሆነ* የሚለው የዮሐንስ አስተሳሰብ የጊዜው ዓለም ስለፍጥረትና ስለፈጣሪ የነበረውን አመለካከት እንዲለውጥ የሚያስገድድ ፍጹም አዲስ (Radical) ሐሳብ ነው። ለመሆኑ ይህ "ቃል" ወይም "ሎጎስ" የሚለው ስያሜ ለወቅቱ የግሪክ አስተሳሰብ





ምን ትርጉም ነበረው? የሚለውን ጥያቄ ከዚህ ቀጥሎ ለመመለስ እንሞክራለን።

## ሀ. <u>ቃል በግሪካውያኑ አስተሳሰብ</u>

ይህ "ቃል/ሎጎስ/" የሚለው ስያሜ በዮሐንስ አጠቃቀም ሲታይ በውስጡ በጊዜው የነበረውን የግሪክ ፍልስፍና የሚቃረን ሥነ-መለኮታዊ ሐሳብ የያዘ ስያሜ ነው። የብዙ ዘመናዊ ፍልስፍና መነሻ በሆነችውና ሶቅራጥስን፥ አሪስቶትልንና ፕሌቶን ባፈራችው ጥንታዊ ግሪክ፥ የአጥናፈ ዓለሙ (Universe) ጅማሬና የነባራዊው ዓለም የእንቅስቃሴ ምስጢር ምን እንደሆነ መፈለግና መፈላሰፍ ዓይነተኛ ጠባይዋ ነበር። ይኼ ሁሉ ፍጥረት ከምን ተሠራ? የፍጥረትስ ሕግ አንዱ ካንደኛው ሳይጋጭ እንዴት በሥርዓት ይጓዛል? ዘመናትስ ሳይዛቡ ወቅታቸውን ጠብቀው የሚፈራረቁት እንዴት ነው? የውልደትና የሞት ምስጢሩ ምን ጋ ነው? ማነው ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ ያለው? የሚሉት የጊዜው ፍልሱፋን ጥያቄዎች መልሳቸውን ሙሉ በሙሉ ያሳረፉት ሎጎስ ወይም ቃል በሚለው ሐሳብ ላይ ነው።

ይህ *"ቃል"* የሚለው ስያሜ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ በነበረው ዓለም አካልነት የሌለው በአንጎል ውስጥ ያለ ሐሳብ፥ አመክንዮ (Logic) ፥ የዓለማት ህልውና ሥርዓተ ሕግ፥ የነገሮችና የክስተቶች ተቆጣጣሪ፥ የዓለማት ነፍስ የሚሉ በርካታ አጠቃቀሞችና ፍቺዎች ነበረው።[23]

በዚያን ጊዜ በግሪካውያኑ ዘንድ 'ዓለምን በሥርዓትና በግብቡነት እንድትኖር ያደረገ ጠቢብና ሉዓላዊ የሆነ አንድ እኔነት ያለው አካላዊ አምላክ አለ' የሚል እምነት ፈጽሞ አልነበረም። ለእነርሱ ዓለም የተፈጠረችውም ሆነ የምትመራው አንድ ረቂቅ (Abstract) በሆነ አካላዊነት በሌለው መርህ ነው። ይህ አካልነት የሌለው መርህም *ሎጎስ /ቃል/* ነው ይላሉ። ዓለምም ሆነ ዓለማት ከመመሳቀል (Chaos) ተጠብቀው በሥርዓት የሚሄዱት በዚሁ ሎጎስ በተባለው ረቂቅ መርህ (Abstract principle) ነው ይላሉ። እንዲያውም ከዚህ አስተሳሰባቸው በመነሳት ሁሉም ነገር በውስጡ ተቀጣጣይ /ተለኳሽ/ የሆነ ሎጎሳዊ ዘር (Logos spermaticos) አለው ይላሉ።[24] ከዚህም ጋር

በተያያዘ መልኩ 'እያንዳንዱ ሰው ሊጫር የሚችል የመለኮትነት ኃይል አለው ስለዚህ አምላክን ፍለጋ ወደ ውጪ አትሂዱ ወደ ውስጥ ተመልከቱ' የሚለውም የዘመኑ ኑፋቄአዊ አስተሳሰብ ከጥንታዊ የግሪክ ኢስጦይኮች የመጣ ነው። ሎጎስ የሚለው ቃል ፍቺ በግሪካውያኑ ዘንድ እስከ አሁን እንደተመለከትነው ከሆነ÷ ቀጥሎ ደግሞ ዮሐንስ ሎጎስ የሚለውን ስያሜ እንዴት እንደተጠቀመበት እንመለከታለን።

### ለ. "ቃል/ሎጎስ/" በዮሐንስ አጠቃቀም

ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ በጊዜው "ሎጎስ/ቃል/" የሚለው ስያሜ የያዘው ፍልስፍናዊና አእምሮአዊ አስተሳሰብ ላይ መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ የሆነ ትርጉም ያዘለ ቦንብ ነው የጣለበት። *ለዮሐንስ ሎጎስ የሚለው ስያሜ እንደ ግሪኮቹ ረቂቅ የሆነ አካላዊነት የሌለው ኀሊና ወይም እሳቤ (Concept) ሳይሆን÷ ዓላማ ያለው አካላዊ አምላክ ነው*፡ ዮሐንስ ሎጎስ የሚለውን ስያሜ ከግሪካውያኑ አስተሳሰብ መንጥቆ በማውጣት ከይሁዲነትና ከክርስትና እምነት ጋር አስማምቶና አጥምቆ ነው የተጠቀመበት።[25] ይህንንም ሐሳቡን ሎጎስ ከሥነ-ፍጥረት አኳያ ያለውን ድርሻ በማሳየት ይገልጠዋል።

### ሐ. ቃል በሥነ-ፍጥረት ላይ ያለው ድርሻ

ለዮሐንስ ቃል ከማይለካ የሃላፊ ጊዜ (Eternity past) አንስቶ የነበረ በዘፍ.1÷1 ላይ "*በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ*" ከመባሉ በፊት የነበረ ነው። እርሱም በምድርም፣ በባሕርም ሆነ በሕዋ/ጠፈር/ የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት ሁሉ የፈጠረ ነው ይላል። "*ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሁሉ በእርሱ ሆነ÷ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም*" ይላል። ይህ·ማለት ነገሮች ሁሉ ሲፈጠሩ÷ ቃል ከእግዚአብሔር ጋር በእኩል ደረጃና በእግዚአብሔርነት የመፍጠር ድርሻ ነበረው ማለት ነው። "*ሁሉ በእርሱ ሆነ*" ሲል በአጥናፈ ዓለሙ ያለውን ተፈጥሮና የተፈጥሮ ሕግጋት ሁሉ ማለቱ ነው። ስለዚህ እርሱ ማለትም÷ "ቃል" ሁሉን ነገር ፈጥሮ ወደ ህላዌነት ያመጣ እንጂ÷ የይሖዋ ምስክሮች ነን በሚሉት ዘንድ እንደሚባለው ራሱ የተፈጠረ አይደለም። ይህ





ሎጎስ የማያቋርጥና ጊዜ የማይገዛው ህልውና ያለው ነው። ጸንቶ የተመሠረተ የሚመስለን ነገር ሁሉ አላፊ ጠፊ ሲሆን ይህ "ቃል" ግን ለዘላለም ይኖራል። *የተፈጠረውና ቁሳዊ የሆነው ነገር ሁሉ የሎጎስ ውጤት ነው። "ከሆነውም አንዳች ያለ እርሱ አልሆነም"* ይላልና።

ደግሞም በቆላ.1÷16 ላይ፦ "*እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፣ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት÷ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው። ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።*" ይላል። ነገር ግን በዚህ *ሥፍራ "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው"* ሲል÷ ከተፈጠሩት ነገሮች አንደኛ ማለት ሳይሆን÷ "ፍጥረት ከመፈጠሩ በፊት የነበረና የበላይ አለቃ ነው" ማለቱ ነው። ይህ ጥቅስ ካለበት ዐውድ (Context) እንደምንረዳው በኩር የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ከመሰል ዘሮቹ መጀመሪያ የተወለደ፣ ቀዳማዊ፣ አንጋፋ፣ ወይም ቅድምና ያለው ማለት አይደለም። ይልቁንም ፍጥረት *ከመፈጠሩ በፊት የነበረና ያለ÷ ያለርሱ ዕውቀትና ያለርሱ ሥራ አንዳች አልተፈጠረም* ለማለት ነው። ብኩርና የሚለው ስያሜ ቅድምናን ሳይሆን እልቅናን የሚያሳይ ነው።

ከዮሐንስ ሐሳብ ወጣ ብለን ሌሎች ክፍሎችን ስንመለከት ይህንኑ የክስቶስን የመፍጠር ድርሻ እናያለን። ለዚህም ማብራሪያ የዕብራውያን መልእክት 1÷2-4 ያለውን አጭር ትንታኔ እንደ ሚከተለው እንመልከት።

በዕብ.1÷2 "ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን"። "ዓለማትን" ሲል÷ ሰማይና ምድርን ብቻ ሳይሆን የሚታይ የማይታየውን÷ ዘመናትንና የተፈጥሮ ሕግጋትን ማለቱ ነው። በቁ.3 ላይ ደግሞ "እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕሪው ምሳሌ ሆኖ÷ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢያታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ..." ይላል። "የክብሩ ነጸብራቅ" የሚለው ሐረግ ከቃሉ በላይ ትርጉም ያለው ሐሳብ ነው። ለምሳሌ ሙሴ÷ የእግዚአብሔርን ክብር አንጸባረቀ፣ ነገር ግን ሙሉነት አልነበረውም፣ ጊዜውን ጠብቆ ፈዟል። ነጸብራቅ የሚለው የአምላክን ብርሃናዊ ባሕርይ ተካፋይነቱን የሚያሳይ

ነው:: (ዮሐ.1÷9):: "ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ" ሲል÷ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ነገሮችን በመፍጠር ብቻ አላቆመም፤ ይደግፋል÷ ይቆጣጠራል÷ የወደፊቱን ይይዛል÷ ይጠቀልላል÷ ይወስናል (ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ.1÷10 ላይ "በዘመን ፍጻሜም ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው::" ያለው):: በተለይ በማዳን ሥራው÷ እግዚአብሔር ራሱን እንዴት በክርስቶስ በኩል እንደገለጠ እንመለከታለን:: "ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ..."[25] ይህ ያለቀ የተፈጸመ ክንዋኔን ያሳያል፤ በመስቀል ሞቱ የተፈጸመውን ማዳኑን ያሳያል:: "በራሱ" የሚለው ሐሳብ ደግሞ ክርስቶስ እኛን ከኃጢአት ሲያነጻ የውጪ ኃይል እርዳታ አላስፈለገውም፤ ምንም ዓይነት ወኪል በዚህ የማንጻት ሥራ ውስጥ እንዲገባ አላስፈለገውም ማለት ነው:: በእንዲህ ዓይነት መልኩ እግዚአብሔር አብ በልጁ "በቃል" በኩል አምላክነቱንና ፈጣሪነቱን በሙላት ገልጧል::

## መ. ቃል ሥጋ ሆነ

ጥንታዊ ግሪካውያን ዓለምን ቁሳዊና መንፈሳዊ በሚል በሁለት ገጽታ ይመለከቱ ነበር:: ለእነርሱ ይህ ቁሳዊው ዓለም እጅግ የረከሰና ፍጹምነት የሌለው በመሆኑ አማልክት ጣልቃ የማይገቡበት ነው:: ወንጌላዊው ዮሐንስ ግን ይህንን ሐሳብ ውድቅ ሲያደረገው እንመለከታለን:: በዚህ በዮሐ.1÷4-13 ያሉትን ሐሳቦች አልፈን ቁ.14 ላይ ስንመለከት ዮሐንስ አስቀድሞ ቃል ረቂቅ ሐሳብ ሳይሆን አካላዊ ነው ብሎ ከተሟገተው የበለጠ የግሪካውያኑን አስተሳሰብ የሚያስደነግጥና የሚያፈርስ ሀሳብ እናገኛለን::

ሐዋርያው ዮሐንስ÷ "አማልክት በመንፈሳዊው ዓለም ብቻ ተወስነው በሰው ልጆች ዓለም ውስጥ ጣልቃ ሳይገቡ ይኖራሉ" ብለው የሚያስቡትን ግሪካውያን÷ "አምላክ የሆነው ቃል በመካከላችን መጣ" "እንዲያውም እኛ የለበስነውን ሥጋ ለበሰ" በማለት የጊዜው ዓለም በሚሰማው ቋንቋ "ካይ ኾ ሎጎስ ሳርክስ ኤጌኔቶ" "ቃልም ሥጋ ሆነ"÷ "ምጡቅና ሩቅ የሆነው አምላክ ቅርብ ሆኖ ራሱን ገለጠ" ብሎ ቁርጡን ይናገራል:: ይህንን ቁ.14 ቀድሞ በቁ.1 ከተነገረው ሐሳብ ጋር ስናገናዝበው÷ በምጥቀቱና





በፈጣሪነቱ አምላክ የሆነው ቃል÷ የኹነታ /የመሆን/ (State) ለውጥ ሲያካሂድ እንመለከታለን፤ ምክንያቱም *በቁ.1 "ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" ይልና÷ በቁ.14 ደግሞ "ቃልም ሥጋ ሆነ" ይላል:: እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚያስፈልገው ጉዳይ÷ በቃል ዘንድ የተደረገው የመሆን ለውጥ አምላክ መሆንን ትቶ ሰው ሆነ በሚል ግንዛቤ ሳይሆን÷ ቃል /ሎጎስ/ እግዚአብሔር ነው÷ ቢሆንም ይህ ቃል ግን ሥጋ ሆነ ማለት ነው::* ቃል ሥጋ ሆነ ስንል÷ አስቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ቃልነት /በእርሱ ተናጋሪነትም/ ዓለም በእርሱ የተፈጠረ አካላዊ ቃል፤ መለኮትነት ያለው የአብ ቃል÷ ሰውን ለማዳን "ደማም ደመነፍሳም፤ የሕያዋን ገላ ያለው፤ በአጥንትና በዥማት የጸና" የሰውን ሥጋ የለበሰ፤ ሥጋን የሆነ፤ እንደ ሰው በመኖር የሰው ልጅ የተባለ ማለታችን ነው::[26]

የቃል ሥጋ መሆንን ስንመለከት አምላክ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል የወረደበትን የመጨረሻ ዝቅታ እንመለከታለን:: ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ አገልጋይ መሆንን በመምረጥ በሰው ምሳሌ ተገለጠ:: ፈጣሪ ራሱ በሰው መልክና ለሰው ዓይን በሚታይ በሚዳሰስና በሚጨበጥ ሁኔታ ተገለጠ÷ ተወሰነ÷ ተሰበሰበ፤ ሊራብ÷ ሊጠማ÷ ሊጎሳቆል በሚችልም ሥጋ ራሱን ገለጠ::

ስለዚህ ይህ የአምላክ የውድ ግልጠት "ወይ ውረድ ወይ ፍረድ" የሚለውን ተረት ፉርሽ ያደርገዋል:: አንድ ጊዜ ወርዶ ራሱን ገልጧል:: አሁንም በአብ ዘንድ ባለው ክብር ይገኛል:: በኋላም አንዴ ለፍርድ ይመለሳል እንጂ አይመላለስም::

ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በመካከላችን አለ:: ይህም ዋስትናችንና የእርሱ የመሆናችን ማሕተም ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ስለሃይማኖታችን መሠረት እንዲህ ብሎ ይናገራል::

"እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤
በሥጋ የተገለጠ÷
በመንፈስ የጸደቀ÷
ለመላእክት የታየ÷
በአሕዛብ የተሰበከ÷

በዓለም የታመነ፥
በክብር ያረገ።" (1ጢሞ.3፥16)። በማለት ቅዱሳት መጽሐፍት "የቃልን ሥጋ መሆን" እንዲህ ባለ አነጋገር ዘግተውታል።

### ሠ. አማኞች ከቃል ሥጋ መሆን ምን እንማራለን?

የምናመልከው አምላክ እዚያ ማዶ ያለ ሳይሆን ታሪካችንን የእርሱ ታሪክ አድርጎ የተካፈለ ትሁት ጌታ ነው። መከራችንንና ጭንቀታችንን ሊካፈል የወደደ አምላክ ነው። ይህ ዓይነቱ እምነት በየትኛውም ሃይማኖት የሌለ የክርስትና ብቸኛ እውነት ነው። ምጡቅ ሆኖ፥ ሩቅ ሆኖ፥ የማይደረስበትና የማይገኝ ሆኖ ሳለ፥ ወዶና ፈቅዶ ከምሕረቱና ከፍቅሩ የተነሳ ሰው ሆነ፤ አምላክነቱን ሳያጎድልና ሳያሳንስ በእኛ ደረጃ ተገኘ፤ በመካከላችንም አደረ። ስለዚህ የአምላክ ሥጋ መሆን የክርስትናችን ልዩ ውበትና ግርማ ነው። ስለሆነም አማኝ የሆንን ሁሉ በደስታ በተሞላ ልብ ሆነን ይህንን እለት እለት ማድነቅና ስለ እርሱም ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ይገባናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ስለ ትሕትናና ዝቅ ስለ ማለት ሲያስተምራቸው ዋነኛ ምሳሌ አድርጎ የተጠቀመው ሌሎች ነብያትንና ሐዋርያትን ሳይሆን የክርስቶስን ትሥጉትነት (Incarnation) ወይም የቃልን ሥጋ መሆን ነው። ፊል.2፥5-11:- *"በክርስቶስ የነበረ ይህ ሀሳብ በእናንተ ዘንድ ይኑር"* ሲል እውነተኛ አማኞች ሁሉ ይህ የክርስቶስ ትሥግውታዊ የትሕትና ጠባይ ሊታይባቸው ይገባል ማለቱ ነው። ያለንበት ዘመን ሰዎች በሰዎች ጭንቅላት ላይ እየተውጣጡ ሽቅብ የሚተኮሱበት ጊዜ ነው። "አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ" የሚለው የቅኖች አባባል 'የኋላ ቀሮችና' 'የፈዛዞች' ምልክት የሆነበት ዘመን ነው። ስለዚህ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት ነን ካልን በክርስቶስ ትሕትና የመመላለስ ግዴታ አለብን።

የቃል ሥጋ መሆን ጥርት ያለና ብቸኛ እግዚአብሔርን የማወቂያ መንገድ ነው። እግዚአብሔር ራሱን በሙላት በክርስቶስ በኩል ገልጧል (ዮሐ.14፥8-11)። ነብያትና መላእክት ከእግዚአብሔር መልእክትን ይዘው መጡ፤ ክርስቶስ ግን ላኪውም





መልእክቱም ሆኖ መጣ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ቅድስናውና ኃይሉ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ክርስቶስን ብቻ ማወቅ ይበቃል[27] (ዮሐ.14፥8-11)።

ደግሞም በክርስቶስ የሥጋ መገለጥ የተነሳ ደኅንነታችን የተረጋገጠ ነው። የክርስቶስ ሞት የአንድ ነቢይ፥ መልአክ ወይም የታላቅ ሰው ሞት አይደለም። ይልቁንም አምላክ በሞት ሸለቆ ያለፈበት፥ በትንሣኤውም ሞትን የወጋበት በመሆኑ ለደኅንነታችን ዋስትና ነው። የውሉም ቦታ መስቀሉ ነው። በክርስቶስ የሥጋ መገለጥ የተነሳ፥ ኃጢያተኛው የሰው ልጅና ቅዱሱ እግዚአብሔር ዳግም ኅብረት ሊያደርጉ ቻሉ። ኃጢአት የፈጠረውም ግርዶሽ የተጣሰው በክርስቶስ ትሥግውት ነው። ባጭሩ የቃል ሥጋ መሆን ሳይታሰብ፥ መስቀል የደኅንነት ማዕከል መሆኑን ማሰብ አይቻልም። ስለዚህ አምልኮተ እግዚአብሔር ለክርስቶስ የተገባ ነው። እርሱ ከፍጡራን የበላይና የላቀ ብቻ ሳይሆን ከአብ እኩል አምላክነት ያለው ነው። ስለዚህ እርሱ ከአብ እኩል ከመንፈስ ቅዱስም እኩል ከእኛ አምልኮአችንን፥ ምስጋናችንንና ውዳሴአችንን ይቀበላል።[28] አንድ ቀን ፍጥረት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ ይገነዘባል (የሐዋ.1፥11)።

### 2.1.6. በመጽሐፍ ቅዱስ

አንድ መጽሐፍ አንባቢው እንዲመርጠው የሚያደርገውና የአነባበቡንም ዲሲፕሊን ወይም ሥርዓት የሚወስነው የደራሲው ዓላማ ነው። ከአንድ መጽሐፍ ጋር የሚገናኝ ሰው አስቀድሞ አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቃል:- ይህ መጽሐፍ ለሳይንስ መማሪያ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው? የታሪክ መረጃዎችን ያጠናቀረ መጽሐፍ ነው? ወይስ አዕምሮን ለማዝናናት የተጻፈ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው? ወይ ደግሞ የሕይወት ልዩ ልዩ ገጽታዎችን በማንጸባረቅ አንባቢው ስለ ሕይወት ጠልቆና ተመራምሮ እንዲያስብ የተጻፈ ነው? ከዚህ ሁሉ አልፎ፥ የሆነስ ሆነና ደራሲው በመጽሐፉ ርዕስ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ የተገባ /የበቃ/ ሰው ነው ወይ? በማለት ይጠይቃል።

እነዚህና መሰል ጥያቄች የአንድን መጽሐፍ ተነባቢነት በእጅጉ ይወስናሉ:: አንዳንድ መጽሐፎች ለአንባቢዎች በመጽሐፉ ሽፋን ላይ በማን እንደተጻፉና ለምንስ ዓላማ እንደተጻፉ ይገልጻሉ:: ስለዚህ ብዙ አስተዋይ አንባቢዎች አንድን መጽሐፍ ከመግዛታቸውና ከመዋሳቸው ወይም ከማንበባቸው በፊት፥ ጊዜ ወስደው እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ይጠይቃሉ:: የሚያሳዝነው ግን አብዛኛዎቻችን የመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቃሚዎች አስቀድመን እነዚህን ወሳኝ ጥያቄዎች አንጠይቅም:: አንዳንዶቻችን መጽሐፍ ቅዱስን አንስተን በነሲብ በመግለጥ እናነባለን፤ ሌሎቻችን ደግሞ ከዘፍጥርት አንስተን በመደዳ ለማንበብ እንጀምርና ኦሪት ዘሌዋውያን ላይ ያለው የክህነት፥ የመሥዋዕትና የአምልኮ ሥርዓት ሲተረክ ይሰለቸንና እናቆማለን::

መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈበት ዓላማና ከደራሲው ማንነት የተነሳ ከመጽሐፉ ተጠቃሚ ልንሆን የምንፈልግ ሁሉ አስቀድመን የመጽሐፉን ተፈጥሮ ልናውቅ ይገባናል ::

### 2.1.6.1. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ገጽታዎች</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ቀደም ብለን ያየናቸውን ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር የመገለጫ መንገዶች በመረጃ መልክ ሰብስቦ የያዘ ሰነዳዊ መጽሐፍ ነው:: የእምነት መሠረቶች ሁሉ የሚወጡት ከዚሁ መጽሐፍ ብቻ ነው:: በአንድ በኩል በሰዎች እጅ የተጻፈ ሰነድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ምንጩ እግዚአብሔር የሆነ ሰነድ ነው:: ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች እጅና በሰዎች ቋንቋ የተጻፈ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?

#### ሀ. <u>መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች እጅና በሰዎች ቋንቋ የተጻፈ ነው::</u>

ይህ በጥንቃቄ ልናየው የሚገባ ግንዛቤ ነው:: መጽሐፉ በሰዎች እጅ የተጻፈ ነው ስንል ፥ ከሰማይ እያንዳንዱ ፊደል ተጽፎና ተጠርዞ ቁልቁል የተወረወረ ምትሀታዊ መጽሐፍ አይደለም፥ ይልቁንም ሰብአውያን ደራሲያን አንድ ርዕስ ጉዳይ ይዘው በተወሰነ አገር ለኖሩ የተወሰኑ ሰዎች በቋንቋቸውና





በባሕላቸው ውስጥ ሆነው የጻፏቸው የመጽሐፍት ስብስብ ነው ማለታችን ነው ::

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ረገድ ሲታይ የጥንታዊነት ባሕሪ ያለው መጽሐፍ ነው:: በ1600 ዓመታት መካከል ውስጥ በኖሩ ከ40 በማያንሱ የተለያዩ ሰዎች የተጻፈ መጽሐፍ ነው:: ይህም ማለት የቋንቋው ፈሊጥና የባሕሉ ነጸብራቅ ካለፈ ዘመን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው ማለት ነው::[29] ከዚህም ሌላ መጽሐፉን የጻፉት ሰዎች የየራሳቸው የሆነ የአጻጻፍ ዘይቤ ተጠቅመዋል:: እንዲህም በመሆኑ ፁመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ሥነ-ጽሑፋዊ ቅርጾችን በቀላሉ ማየት ይቻላል::

ትራኬአዊ ሥነ-ጽሑፍ --- ነገሥት፥ መጽሐፈ ሳሙኤል፥
መጽሐፈ ዜና መዋዕል፥ አስቴር፥ አራቱ
ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ
ሕግጋታዊ ሥነ-ጽሑፍ--- ዘሌዋውያንና ከፊል ዘጸአት
ቅኔአዊ ሥነ-ጽሑፍ --- መኀልየ መኀልይ
ጥበባዊ ሥነ-ጽሑፍ --- መጽሐፈ ምሳሌና መክብብ
ግጥማዊ ሥነ-ጽሑፍ --- መጽሐፈ መዝሙር
ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ --- የትንቢታት መጽሐፎች በሙሉ
መልእክታዊ/ደብዳቤያዊ ሥነ-ጽሑፍ --- የጳውሎስ፥ የጴጥሮስ፥
የዮሐንስ፥የያዕቆብ
ራእያዊ ሥነ-ጽሑፍ -- ሕዝቅኤል፥ ከፊል ዳንኤል፥ዮሐንስ ራእይ

ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ አዕምሮአውያን የታሪክ ዘጋቢያን የጻፉት የይሁንታ ትርክት፥ የፈላስፎች ቅኔ፥ የዚህ ዓለም መንግሥት ሕግጋት ወይም የሚርተኞች ንግርት የተጻፈበት መጽሐፍ አይደለም:: ጸሐፊዎቹ ሙሉ በሙሉ በአምልኮተ እግዚአብሔር የተወረሰ ንጸረተ ዓለም (world view) ያላቸው ናቸው:: መጻሕፍቱን የጻፉት ሰዎች በጊዜ የተገደቡ ናቸው፤ ነገር ግን ጽሑፋቸው ጊዜን ጥሶ መሄድ የቻለ ነው:: ጸሐፊዎቹ በነበሩበት ዘመን ቋንቋና ባሕል የተወሰኑ ናቸው፤ ቢሆንም ጽሑፋቸው ቋንቋንና ባሕልን ሁሉ አልፎ ሰዎችን የመገዳደር ጠባይ አለው:: ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ከመጽሐፉ ሁለተኛ ጠባይ የተነሳ ነው::

## ለ. መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ መለኮት ነው::

ምንም እንኳ መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ብዕርና ብራናቸውን አንስተው በራሳቸው ቋንቋና ባሕል ውስጥ ሆነው ቢጽፉትም፥ የሐሳባቸውና የመልእክታቸው አካሔድ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ሥር ነበር:: ገለጻውና ቋንቋው የሰውና ሰውኛ ቢሆንም፥ ሐሳቡና ግልጠቱ ሙሉ በሙሉ የመለኮት ነው:: የጽሑፋቸው ቀዳማይ መገኛና ምንጭ እግዚአብሔር ነው፤ አንዳቸውም ቢሆኑ ከራሳቸው ልብ አመንጭተው አልጻፉም:: መጽሐፉም ስለ ራሱ እንዲህ ብሎ ይመሰክራል:-*"ይህንን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ጴጥ.1፥20-21 ፡ 1ጢሞ. 3፥16) ::*

ስለዚህ አሁን እንድናነበውና ለሥልጣናዊነቱም እንድንገዛ የሚያደርገን ይህ መለኮታዊ ጠባዩ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ መለኮት የመሆኑ ቅደመ ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ይህንን የመለኮት ቃል ከማንኛውም ጥንታዊ መጽሐፍ ተርታ ይመድቡታል:: ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥንት ሰዎች ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት የሚያትት መጽሐፍ እንጂ ከዚያ ያለፈ ነገር እንዳለው አይቆጥሩትም:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከምንነት ጥያቄ አንጻር ሲታይ ከሌሎች መጻሕፍት ተርታ የሚፈረጅ ተራ መጽሐፍ አይደለም:: ሥረ መሠረቱና መገኛው እግዚአብሔር ነው:: በውስጡም ያለው ቃል የእግዚአብሔር መገለጥ ነው:: ይህም መገለጥ የተሰጠው ለዚህ ሥራ አስቀድሞ በተመረጡ "አፈ መለኮታውያን" (በእግዚአብሔር ስም ስለ እግዚአብሔር በሚናገሩ ሰዎች) ነው::[30]

ምንም እንኳ በውስጡ ያሉትን 66 መጻሕፍት ከ40 በላይ ሰዎች በ1600 ዓመታት መካከል ቢጽፏቸውም' ከአጻጻፍ ዘዬና ከሥነ-ጽሑፋዊ ቅርጽ ልዩነት በስተቀር፥ የሐሳብ ግጭት ሳይኖረው በአንድ ሰው እጅ የተጻፈ ይመስል፥ የመሠረታዊ ሐሳብ ስምሙነት አለው:: ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ መለኮት ከመሆኑ የተነሳ ነው:: አሁን



ETHIOPIAN EVA...
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228



ስናነበው በውስጡ ያለው የመጀመሪያ ታሪክ በጊዜ በማይለካ ሁኔታ ወደ ኋላ ሲወስደን፥ የመጽሐፉ መጨረሻ ደግሞ በትንቢታዊ ስልቱ ወደ ፊት ወዳለው ተናፋቂ ዘላለም ይወስደናል::

ስለዚህ አስቀድመን በተመለከትናቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች፥ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ድርጊቶቹና እንዲሁም በቃል ሥጋ መሆን፥ ራሱን እንደገለጠ እንዳየነው ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስንም ስንመለከት እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ የገለጠበት ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን::

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ/መገለጫ ነው ከምንልበት ምክንያት አንዱ በውስጡ ካለው ነቢያታዊ ቀመር በመነሳት ነው:: "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚለው ነቢያታዊ ቀመር (Messenger Formula) በብሉይ ኪዳን ብቻ ከ2300 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል:: ይህ የሆነው ነቢያት የተለመደ የአነጋገር ወግ መምረጣቸው ወይም ደግሞ ነገራቸውን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ገጽታ ለማላበስ ፈልገው ሳይሆን የሚናገሩት ሁሉ ከእግዚአብሔር የመጣ ቃል መሆኑን ለማስረገጥ ነው (ዘዳ.18፥18፤ ኤር.1፥9፤ ሕዝ.13፥1-16)::

እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉት ነቢያት የትንቢታቸው መሠረት ከራሱ ከእግዚአብሔር የተገኘ ስለሆነ፥ በእግዚአብሔር ስም ተናገሩ ማለት እግዚአብሔር ተናገረ ማለት ነው:: ስለዚህ የእነዚህን ነቢያት ቃል አለመቀበል ማለት እግዚአብሔርን አለመቀበል ማለት ነው:: የነብያትን ቃል አለመታዘዝ ማለትም እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ማለት ነው (ዘዳ.18፥19፤ 1ሳሙ.13፥13-13፤ 1ነገ.20፥35-36):: እነዚህ ጥቅሶች ነቢያትን ያልሰሙ ሰዎች የሚደርስባቸውን ቅጣት ያሳያሉ:: ምክንያቱም ነቢያት የእግዚአብሔር አፍ ሆነው ተናገሩ እንጂ እነርሱ ስለ እግዚአብሔር የሚመስላቸውንና የገመቱትን ነገር አልተናገሩምና ነው::[31]

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ብሉይ ኪዳንን እየጠቀሱ ሲጽፉ ብሉያት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን እንደሚያምኑ ይገልጻል (ማቴ.19፥5 / ዘፍ.2፥24) ፤ (የሐዋ.4፥24

/ መዝ.2÷1-2)÷ (ሮሜ.9÷17 / ዘጸ.9÷16) ምንም እንኳ በብሉይና በአዲስ መካከል የኪዳን ልዩነት ቢኖርም አዲስ ኪዳናዊውን መልእክት ለመገንዘብ የብሉይን መሠረታዊ ሐሳብ መረዳት ግድ ነው:: ምክንያቱም በሁለቱ ኪዳናት በኩል የሚተላለፈው ሥነ-መለኮታዊና ሃይማኖታዊ መልዕክት ወጥና ተከታታይ ነው:: ከዚህም የተነሳ በአዲስ ኪዳን ጽሑፎችና በብሉይ ኪዳን ጽሑፎች መካከል ቁርኝትና "የድርና ማግ" ጠባይ ይታያል:: ስለዚህ ብሉያዊውን ሃይማኖታዊ ግንዛቤ ዘሎ አዲስ ኪዳናዊውን ሐሳብ ብቻ ለመጨበጥ መሞከር÷ "እኔ የምኖረው ሁለተኛ ፎቅ ላይ ስለሆነ አንደኛ ፎቅን አፍርሱት" እንደማለት ነው::

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የብሉይን መጻሕፍት በሥልጣናዊነት ተቀብሎ መጥቀስ ብቻ ሳይሆን ÷ እርስ በርሳቸው የመደጋገፍ÷ ሥልጣናቸውንም የመቀባበልና የመጣጣም ጠባይ እጅጉን ይታይባቸዋል:: ለምሳሌ ሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክቱን በሚጽፍበት ጊዜ "የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ..." በማለት የጳውሎስን ጽሑፎች ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ተርታ ሲፈርጃቸው እንመለከታለን:: (2ጴጥ.3÷16) ሐዋርያው ጳውሎስም መልእክቶቹን በሚጽፍበት ጊዜ ብሉይ ኪዳናዊውንና አዲስ ኪዳናዊውን መጻሕፍት እንደ አንድ እየቆጠራቸው ሲጠቅስ እንመለከታለን:: ለምሳሌ ያህል 1ጢሞ.5÷18ን ሲጽፍ "መጽሐፍ የሚያበራየውን በሬ አፉን አትስር ይላል" ብሎ ከዘዳ.25÷4 ላይ ይጠቅስና ደግሞ "ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል" በማለት ሉቃ.10÷7ን ይጠቅሳል:: ይህም የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች አድራጎት÷ ብሉይና ሐዲስ ያላቸውን ስምሙነትና የሥልጣን እኩልታ ያሳያል:: እንግዲህ ከላይ እንደጠቀስነው መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ከመሆኑ የተነሳ ሥልጣናዊም ነው::

### 2.1.6.2. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊነት</u>

"ሥልጣን" የሚለውን ቃል ስንተረጉም በኅብረተሰቡ ውስጥ በሰዎች መካከል ያለውን "የአለቃና ምንዝር" ልዩነት እናስባለን:: ማን ለማን ተጠሪ ነው? ማን በማን ላይ ሹም ነው? ለዳኝነት





ወሳኙና ባለመብቱ ማን ነው? እንላለን:: ይሁን እንጂ በኅብረተሰቡ ውስጥ በገንዘብ አቅም÷ በኃይልና በመሳሰሉት የበላይ የሆነው አካል ባለሥልጣን ይባላል:: በዚህ በተፈጠረው ዓለም ከሰው ልጆችም ሆነ ከመንግሥታት÷ በሁሉም ነገር የበላይ የሆነ አለ÷ የሚለው ሐሳብ ላይ ከተስማማን÷ እንግዲያው የሰዎችን እምነትና የኑሮ ሥርዓት መወሰን ያለበት ይኸው የበላይ ነው::

ለክርስቲያኖች በእምነትና በኑሮ ጉዳዮች ላይ የበላይ ባለሥልጣን እግዚአብሔር ነው:: ምክንያቱም እርሱ የመጨረሻ ከፍተኛ ኀልውና ያለውና እኛም ከመኖራችን በፊት የኖረ÷ እንዲሁም በራሱ ኀልው የመሆን ማንነት ያለው እርሱ ብቻ በመሆኑ ነው:: ይህ የእግዚአብሔር ሥልጣን በሕዝቡ ላይ የሚካሔደው ደግሞ በልዩ ልዩ ወኪሎች ሳይሆን÷ የተገለጠው ማንነቱን በያዘው በሕያው ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ነው::

በአገራችን በየወቅቱ ከሚታተሙት በአንዱ ክርስቲያናዊ መጽሔት ላይ ለሁለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንዳንድ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ቃለ ምልልስ ተደረገላቸው:: አቶ እገሌ ለተደረገላቸው/ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ሃሳባቸውን ለማንተራስ "የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ ይላል" የሚል ሐረግ ይጠቀማሉ:: ሌላኛው አቶ እገሌ ግን ሐሳባቸውን የሚያቀርቡት÷ "እኔ እንደሚመስለኝ"÷ "እነደተለ ማመድኩት ከሆነ"÷ "በቤተ ክርስቲያናችን ደንብና ሥርዓት መሠረት" በማለት ነው:: ስለዚህ ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የግንዛቤአቸው ሥልጣን ያረፈው የተለያየ ቦታ እንደሆነ እነገነዘባለን:: አንዱ በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣናዊነት ላይ ሲደገፍ አንደኛው ደግሞ በልምምድ÷ በመሰለኝ÷ በሥርዓትና በደንብ ላይ ነው:: ይህ ማለት ግን ልምድ÷ ሥርዓትና ደንብ አያስፈልገንም ማለት አይደለም:: የእምነት÷ የአስተምህሮና የምግባር መመዘኛ ሥልጣን መነሻችን ሊሆኑ አይችሉም ለማለት እንጂ::

የመጽሐፍ ቅዱስ መገኛ እግዚአብሔር ከሆነ መጽሐፉ ሥልጣናዊ መጽሐፍ ነው ማለት ነው:: የዚህን መጽሐፍ ሥልጣን ለማረጋገጥ ደግሞ ወደሌላ ከፍተኛ ባለሥልጣን መሄድ አያስፈልግም:: ማንም ሆነ ምንም÷ ምንጊዜም በሚበልጠው ላይ ነው የሚሠለጥነው:: ስለዚህ በእውነተኛነቱና በትክክለኛ ምክር

ሰጪነቱ የመጨረሻው በላጭ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ከእርሱ በላይ ሥልጣን የለም:: ከዚህ አኳያ እኛ ማን እንደሆንንና እንዴትስ መኖር እንዳለብን የመጨረሻውን መመሪያ የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው::

ሥልጣን ምን እንደሆነና የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወታችንና ለምግባራችን አማራጭ የሌለው ሥልጣናዊ ቃል መሆኑን ለመረዳት፥ የዘመናችንን አስተሳሰብ እንመልከት:: በአሁኑ ጊዜ "እውነተኛው/ትክክለኛው/ የቱ ነው?" የሚለው የምግባር ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ የተለያየ መልስ እየተሰጠው ነው:: ሌላው ቀርቶ በክርስቲያኑም ማኅበረሰብ እንኳ የምግባር ልክታ ቅጡን እያጣ ነው:: አንድ መካከለኛ ሥልጣን ያለ አይመስልም::

ከታሪክ እንደምንረዳው ብዙዎች ትክክለኛው ኃይለኛ የሆነው ክፍል ነው ብለው ነበረ:: ነገር ግን ኃይለኞች ሁሉ ጥሩነት ስለሌላቸው "ኃይለኛ ልክ ነው" የሚለው ሐሳብ ኅብረተሰብን ክፉኛ ጎድቶ አልፏል አሁንም በሚኖርበት አካባቢ ጎጂ ነው:: ኔሮ የተባለው የሮማው ቄሳር፥ የጀርመኑ ሂትለር፥ እንዲሁም የራሺያው እስታሊን ኃይለኞች ነበሩ፤ ነገር ግን የሠሩትን በደል ዓለም በጸጸት ታስበዋለች::

ሰዎች ልክነትን ከጎሳቸውም አንጻር የሚያዩበት ጊዜ አለ:: "የእኔ ጎሳ/ብሔረሰብ ልክ ነው ያለው ሁሉ ልክ ነው" ይላሉ:: እንዲህ እያለ ጎሳና ኅብረተሰብ ሁሉ የየራሱን ልክታ ይፈጥራል:: ይሁን እንጂ የልክነት መለኪያ የእኔ ጎሳ ከሆነ የእኔ ጎሳ ነፍስ ሲያጠፋ እኔም ነፍስ ላጠፋ ነው፤ የእኔ ጎሳ ጣዖት ሲያመልክ እኔም ላመልክ ነው...:: ይህንን ዓይነት መለኪያ የያዙ ሩዋንዳውያን የልክነት መለኪያቸውን ሞከሩት:: "ሲያል ያለው አፍሪካ ውስጥ ነው" እስኪባል ድረስ አእላፋት ቱትሲና ሁቱ በእርስ በርስ ጦርነት ለእልፈት በቁ:: ለዚያውም አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ናቸው:: የጠቡም መነሻ ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደሆነም ይነገራል::

ሌሎች ደግሞ አንድ ነገር ልክ መሆኑን የምንለካው ብዙሃኑ ሲደግፈው ብቻ ነው ይላሉ:: ማኅበረሰቡ ተስማምቶ





የሚወስነው እንጂ ጥቂቶች ለብዙሃኑ አይወስኑም ይላሉ:: ነገር ግን እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ ብዙ ተከታዮችን አፍርቶ የነበረው ጂም ጆንስ የተባለው ሰው 900 ሰዎችን ራሳቸውን እንዲገድሉ አድርጓል::[32] እንግዲህ ብዙሃኑ የሰው ዘር በሙሉ ለዓለም ችግር መሠረታዊ መፍትሄ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ሲገድሉ ነው ቢልስ? ጤናማው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አልስማማ ብሎአቸው ብዙዎች ቤተ ክርስቲያንን ቢተው ብዙዎች ስለሆኑ ብቻ ልክ ሊሆኑ ነው ማለት ነው? እንዲህ ከሆነ ደግሞ እውነት አንጻራዊ ትሆናለች:: እውነት ግን አብረዋት ካሉ ሰዎች ብዛት አንፃር ሳይሆን ብቻዋን ከፍጹምነቷ አንፃር ፍጹም በሆነው እግዚአብሔር ትለካለች:: እውነት ፍጹም እንጂ አንጻራዊ አይደለችምና::

አንዳንዶች ልክ የሆነው ነገር የሚለካው ከሚሰጠው ደስታ አንጻር ነው ይላሉ:: ሥቃይና ኀዘን የሚያመጣ ሁሉ ልክ ያልሆነ ነገር ነው ይላሉ:: ነገር ግን ብዙ ደስታዎች ከሥቃይና ከኀዘን ጀርባ ይገኛሉ:: አንድ ነገር ልክ ነው ልክ አይደለም የሚባለው ወዲያው ከሚሰጠው ደስታ አንጻር የሚለካ ከሆነ ብዙ ልክ የሆኑ ነገሮች ልክ ላይሆኑ ነው:: ደግሞም ሁሉም ደስ የሚያሰኘው አንድ ዓይነት ነገር ስላልሆነ፥ ሁሉም በየፊናው ደስ የሚያሰኘውን ሲያደርግ ዘመነ መሳፍንት ይደገማል ማለት ነው::

አንዳንዶች ደግሞ ጨርሶ ልክ የሆነው ነገር አይታወቅም ብለው ይደመድማሉ:: ያም ያም ልክ ነኝ የሚልበት መንገድ ሁሉ ችግር ስላለበት ልክ የሆነው ነገር አይታወቅም ይላሉ:: ይሄ ደግሞ ኅብረተሰብን /የሰውንም ምግባር/ ያለመለኪያ የሚያስቀር አደገኛ አመለካከት ነው:: ስለዚህ የመጨረሻ ምርጫችን ወደ አንድ የበላይ መሄድ ነው::[33]

እንደ አማኝነታችን ከኅብረተሰቡ የልክታ መለኪያ ወጥተን ስንመለከት አንድ መልስ እናገኛለን:: “ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እወነተኛ ይሁን” (ሮሜ.3፥4):: አንድ ምግባር ትክክል ነው የሚባለው እግዚአብሔር ትክክል ነው ሲል ብቻ ነው:: ይህ አመለካከት የክርስቲያን ብቸኛ አመለካከት ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ለሁሉም የቀረበ እውነት ነው:: ትክክለኛ የሆነው፥ ኃይለኛው፥ የእኔ ጎሳ፥ ብዙሃኑ ወይም ደስታ የሚሰጠኝ

ሳይሆን፥ ምንጊዜም ልክ የሆነው ምግባር፥ እግዚአብሔር በቃሉ ሥልጣን የገለጸው ብቻ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ፈቃድ ደግሞ በደካማው፥ በጥቂቶች፥ በሌላ ጎሳና ለሰውም ደስ በማያሰኝ መልኩ ሊገለጥ ይችላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቃሉ መልካም ነው ካለው መልካም ነው!! ክፉ ነው ካለው ክፉ ነው!!ይህ ዓይነቱ የምግባር ልክታ ከሁሉም የበላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር ትእዛዛዊ ቃል ስለሆነ ማንኛውም ምግባራዊ ጥያቄ መልሱ የሚወጣው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።[34]

አንዳንዶች ይህ አንባገነናዊነትና ጨቋኝነት ነው ይላሉ። ነገር ግን  አንባገነናዊ የሚባለው ይህ የበላይነት መብት ይገባኛል ባዩ ሟቹና ጊዜአዊው ፍጡር ቢሆን ነበር። ነገር ግን ፍጹም የበላይ ባለሥልጣን የሆነውን 'የበላይ ባለሥልጣን' ነው ማለት ምንም ስህተት የለውም። በምግባራዊ ፍጹምነትና በሙሉነት ህልው የሆነ አምላክ ካለ፥ ከዚህ ማንነቱ የተነሳ የምግባር ሁሉ የመጨረሻ ባለሥልጣን እርሱ ብቻ ነው። እግዚአብሔርም ሥልጣኑን የሚገልጠው በቃሉ አማካይነት ነው።

ቤተ ክርስቲያን የምዕመናንን ምግባር መለካት ያለባት በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ነው። አመራሯም ሆነ አስተዳደሯ በምድራዊ ሕግና ሰው ሰራሽ ባሕል ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት። የትምህርቷም ሆነ የተግባሯ ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት። በውስጧ በማንኛውም ዓይነት ብልት የሚገለጡት መንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ ለቃሉ ሥልጣን መገዛት መቻል አለባቸው። ለቃሉ ሥልጣን ለማይገዙ በሯን መክፈትና አሹልኮ ማስገባትም የለባትም። እያንዳንዱ አማኝ ለዚህ ቃል የመገዛት ኃላፊነት ስላለበት፥ ቃሉን የማንበብና የማጥናት የፍቅር ግዴታ አለበት።

### 2.1.6.3. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት</u>

የዘመኑ የዜና ምንጮች ሮይተር፥ ኢ.ዜ.አ፥ ዋልታ፥ አጃንስ ፍራንሴ...የሚያወሩት የታመነ የዜና ምንጭ በሚል ቅጽል ሲጠራ እንሰማለን። ከእነዚህ የወሬ ባለሟሎች መረጃ በመነሳት ታላላቅ ሰዎችና መንግሥታት ከፍተኛ ውሳኔዎችን ይወስናሉ።





እነዚህ የዜና ምንጮች የዓለምን ወቅታዊ ታሪክ በማቅረብ የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። እንግዲህ በተፈጥሮአቸው ፍጹም ያልሆኑት የሰው ልጆች የሚሰጡት መረጃ "ከታመነ የዜና ምንጭ" በሚል ቅጽል ከተጠራ፥ ይልቁንም በማንነቱ ፍጹም የሆነው እግዚአብሔር ምንኛ የታመነ ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱስ መገኛ እግዚአብሔር ነው የሚለው ሀሳብ ላይ ከተስማማን ከዚህ የተነሳ መጽሐፉ የታመነ ነው ማለት እንችላለን ።

ተአማኒ ማለት፦ ለአደራ የሚታመን፥ ለቃል ኪዳን ታማኝ፥ ላለውና ለተናገረው ቃል የታመነ እሙን፥ ይክዳል ይበድላል ተብሎ የማይጠረጠር ማለት ነው።[35] መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ዓይነት ጠባይ አለው። ይህም ሊሆን የቻለው  እስትንፋስ መለኮት በመሆኑ ነው። ለዚህም የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ ይላል፦"*የእግዚአብሔር ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ የተላከ ስለዚህም ሕይወት <u>የማይዋሽ</u> እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ ፥... (ቲቶ 1፥2)።*

ስለዚህ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ሁሉ ተአማኒ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይዋሽ አምላክ ነው። እግዚአብሔር በሚገባው ተስፋና በመሐላው አይዋሽም። "እግዚአብሔር፥ የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለፈቀደ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር፥ በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ..." (ዕብ.6፥17-18)።

ይህንን ሐሳብ በድርድር/ተጠይቃዊ  በሆነ መልክ ብናቀርበው እንዲህ ማለት ይሆናል፦

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር ከቶ አይዋሽም
ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ከቶ አይዋሽም

ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በጸለየው ጸሎት ለእኛም የጸለየልን እንዲህ ብሎ ነው "በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው" አለ (ዮሐ.17÷17)።

በእግዚአብሔር ዘንድ ጨለማ እንደሌለ ሁሉ በእርሱ ዘንድ ዋሸንትም የለም። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ በመሆኑ ቃሉም ምንጊዜም ተአማኒ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የትምህርታችንም ሆነ የልምምዳችን መለኪያ ነው። እውነትን ከሐሰት÷ ሀቅንም ከውሸት የምንለይበት የመጨረሻው ከፍተኛ መለኪያ የተጻፈው ቃለ እግዚአብሔር ነው። ማንኛውም ሃይማኖታዊ ጉዳዮቻችን የሚፈተሹት በእግዚአብሔር ቃል ነው። ማንኛውም መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ልምምድ ተቀባይነት የሚያገኘው በዚህ የታመነ ቃል ተፈትሾ ሲያልፍ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል አዎ ያለው ብቻ አዎ ነው!!

## 2.1.6.4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊነት</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ሕይወት የመለወጥ ከፍተኛ ኃይል አለው÷ ይኸም የሆነበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ የመነጨው ሕይወትን ከሚሰጥና ሕያው ከሆነ አምላክ ስለሆነ ነው። ዕብ.4÷12. *"የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና÷ የሚሰራም÷ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው÷ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል÷ የልብንም ስሜትና ሃሳብ ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።"*

የእግዚአብሔር ቃል በሰው ሁለንተና ውስጥ የመለኮትን ሥራ ይሠራል። በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ጠባይ ያለው አንዳችም መጽሐፍ የለም፤ ሌሎች መጽሐፎች መረጃ ከመስጠት አልፈው ሕይወትን አይለውጡም። ይህንን ታላቅ መጽሐፍ በማስተዋልና በእርጋታ ያነበቡ ሰዎች ታላቅ በረከትን አግኝተውበታል በቅንነት እግዚአብሔርን የፈለጉ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን አግኝተውበታል፤ ሕይወታቸውም ተለው ጧል።[36]





ደግሞም በዮሐ.6÷63 ላይ እንዲህ ይላል:-"*...ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።"* ሰው ከቃሉ ሲገናኝ መንፈስና ሕይወት ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ነው የሚገና ኘው። በእርግጥ ይህ ግንኙነት ሲፈጠር የሕይወት ለውጥ ይከሰታል (ኢሳ.40÷ 27-31)። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በቃሉ ሲገናኝ የሚከሰተውን ያሳያል። እግዚአብሔር ደካሞችን በቃሉ አማካኝነት ሲያገኛቸው ኃይለኞችና ብርቱዎች ይሆናሉ። ተስፋ በቆረጠና ጨለማ በሆነ ሕይወት ውስጥ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር በቃሉ ሲገናኛቸው ሕይወታቸው በብርሃን ይሞላል፤ ተስፋቸውም ይለመልማል።

## 2.1.6.5. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ግቡነት/ግልጽነት</u>

ሕሙማን ከዶክተሮች ለበሽታቸው ፈውስ የሚሰጣቸው የፋርማሲ መድኃኒት ማዘዣ÷ ባለሞያዎች ብቻ እንዲያነቡት ሆኖ የተጻፈ ነው። የመድኃኒቱን ዓይነት ለሌላው መናገር የሚችሉት ያንን ጽሑፍ ማንበብ የሚችሉ ባለ ሞያዎች ብቻ ናቸው። መድኃኒቱ ምን እንደሆነ÷ በቀን ስንት ጊዜ እንደሚወሰድና የሚያመጣውም የጎን ጠንቅ (Side Effect) ምን እንደሆነ ማወቅ የምንችለው÷ ባለሞያው አንብቦ ሲነግረን ብቻ ነው። ይህ ለኃጢአት በሽታ መድኃኒት የሚሆን መልእክት ያለበት መጽሐፍ ቅዱስ ግን÷ በኃጢአት የተነሳ ሕመምተኛ የሆነው የሰው ልጅ ሁሉ አንብቦ ይረዳዋል፤ ከኃጢአት የሚያድን መልእክት ያለው መሆኑንም ሰምቶ ይገነዘበዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ባይሆን ኖሮ÷ እግዚአብሔር በቃሉ የሚያናግረው በትምህርት የዘለቁትን ብቻ በሆነ ነበረ። ስለዚህ ለሁሉም ሰው የቀረበ ጥሪ በመሆኑ ሁሉም ሰው አንብቦ መልስ ምስጠት አለበት፤ አማራጭ የለውም ያስጠይቀዋልና። በጎ ምላሽ ስጥተው የተቀበሉት ደግሞ የመንፈሳዊውን ነገር ምስጢር በሚመለከት ሊዘልቁበት ይችላሉ። እንዲያ ካልሆነ ግን ሥነ-ጽሑፋዊ መልኩን ብቻ ይዘው ይቀራሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ምስጢሩ 'ከተራው ሕዝብ' ተሸሽጎና ተሰውሮ ለተወሰኑና ለምርጦች ብቻ የተገለጠ ኅቡእ መጽሐፍ አይደለም። ቃሉ የመለኮት ቃል ቢሆንም ለሰው ልጆች

መዳንም ሆነ ለሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በግልጽ የሚናገር መጽሐፍ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ግቡዕ/ግልጽ ነው ማለት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ ትምህርቶቹ የእግዚአብሔርን እርዳታ በመፈለግ ታዛዥና ፈቃደኛ በሆነ ልብ ከተነበቡ፥ ለሰው ልጆች ሁሉ ግልጽ ነው ማለት ነው።

መጽሐፉ የባለሞያዎች መጽሐፍ (Proffesional Text Book) አይደለም፤ ማንኛውም አንባቢ መልእክቱን ሊረዳውና ሊያስተውለው ይችላል። እንዲህ ማለት ግን፥ በመጽሐፉ ውስጥ የተባለውን ነገር ሁሉ ማንም በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ተራ መጽሐፍ ነው ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር አሻራ ያረፈበት የመለኮት እስትንፋስ በመሆኑ ጥልቅና ረቂቅ ትምህርቶችን የያዘ መጽሐፍ ነው። ይሁን እንጂ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናቸው የተነሳ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የመረዳት ከፍተኛ ችሎታ አላቸው፡- *"ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ። እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት __ቅባት__ በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ"* (1ዮሐ. 2፥27) የሚለውን ምክር እናስታውሳለን። ደግሞም *"ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አስችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም"* (1ቆሮ.2፥14-15)።

በዚህ ዘመን *"ቅባት"* የሚለውን ቃል ከአግባብ በወጣ መንገድ እየተጠቀምንበት ስለሆነ፥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል። በአንዳንዶች ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግማሹ ባለ ቅባት ሌላው ያለ ቅባት እንደሆነ እየተገመተ ነው። ነገር ግን ዮሐንስ መልእክቱን የጻፈው በተለየ ሁኔታ ለተቀቡ አገልጋዮች ሳይሆን በአንድ ማኅበረ ምዕመናን ላሉ ቅዱሳን ሁሉ ነው። ለእርሱ ሁሉም የተቀቡ ናቸው። እርግጥ ነው በሁላችንም ዘንድ ያለው ጸጋ በአንድ ዓይነት መጠንና መንገድ አይገለጥ ይሆናል፤ ነገር ግን ሁላችንም ዘንድ ያለው ጸጋ ግን አንድ መንፈስና አንድ ጸጋ ነው።





ይሁን እንጂ እያንዳንዳችን ይህንን ቅባት የተቀበልን መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልገናል። ቅባቱ ከእኛ ጋር ከሆነ እርሱ ያስተምረናልና። ይህ የተቀበልነው ቅባት ደግሞ ሌላ ነገር ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው እርሱ ፥ የርሱ ወገን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለማወቅ፥ ለማደግና ለመታዘዝም የማይችል ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸውም በእውነት መንገድ የሚሄዱ አማኞች ሁሉ ይህንን ቅባት እንደተቀበሉ ከሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት መረዳት እንችላለን። "እናንተስ" የሚላቸው በመካከላቸው የተወሰኑትን ሳይሆን ሁሉንም (ጉባኤውን) ነው። እንደ ዮሐንስ እምነት ሁሉም በመካከላቸው የሚነሳውን የሀሰት ትምህርት በቅባቱ መዝነው ሊያውቁ ይችላሉ። ስለዚህ በዘመናችን ስለ ቅባት የሚሰጠውን ትምህርትና ትርጓሜ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚነግረን እውነት ጋር አስተያይተን የእግዚአብሔር መንፈስ (ቅባቱ) በረዳን መጠን ለይተን እንገንዘ።

ወደ ዋናው ሐሳባችን በመመለስ፥ ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነው ብንልም፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በቀላሉ ለመረዳት አስቸጋሪ መሆናቸው አይካድም። ይህንንም ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ጳውሎስ ጽሑፎች በተናገረበት ሥፍራ እንመለከታለን፤ *"ጌታችን መታገሡም እናንተ እንድትድኑ ብሎ መሆኑን አትዘንጉ የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስም በተሰጠው ጥበብ መጠን የጻፈላችሁ ይህንኑ ነው። እርሱ ስለዚህ ጉዳይ በመልእክቶቹ ሁሉ በዚሁ ዓይነት ጽፎአል በመልእክቶቹ ውስጥ አንዳንድ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ነገሮች አሉ ዕውቀት የጎደላቸውና ወላዋዮች ሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህንም ነገሮች ያጣምማሉ ይህንንም በማድረጋቸው ይጠፋሉ"*(2ጴጥ.3፥15-16)።

ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም። ለዚህም ደግሞ ራሱ መጽሐፉ ስለ ግልጽነቱ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ለአዋቂዎች ለሕፃናትም ፍጹም ግቡ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ከዚህም የተነሳ ለሕፃናት ግልጽ እንዳልሆነ በመታሰብ፥ ሕፃናት የማያገኙበት ከፍ ያለ ቦታ የተሰቀለና የተደበቀ ዕቃ አይደለም። "ሕፃናት በማይደርሱበት

ቦታ አስቀምጡት" (Keep Away From The Reach Of Children) የሚል ማስጠንቀቂያ የለውም:: ይልቁንም "ሕፃፃትን ተዉአቸው ወደ እኔ ይመጡ" ዘንድ ብሎ በተናገረ ጌታ የተሰጠ ቃል ነው::

እግዚአብሔርም ከሕዝቡ ጋር በኪዳን ሲገናኝ ጎልማሶችም ሆኑ ሕፃናት ቃሉን የማንበብና የመረዳት ኃላፊነት እንዳላቸው ተናግሯል:: *"እኔ ዛሬ አንተን የማዘውን ይህንን ቃል በልብህ ያዝ:: ለልጆችህም አስተምረው በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሳም ተጫወተው:: በእጅህ ምልክት አድርገህ እሰረው በዓየኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ:: በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው"* (ዘዳ.6፥6-7)::

የእሥራኤል ሕዝብ በሙሉ ሕጉን አውቆ ልጆቹንም የማሳወቅ ግዴታ ነበረበት:: ዛሬ የእኛ ልጆች የእግዚአብሔርን ሕግ የሚማሩት በሳምንት አንድ ቀን እሑድ ጠዋት ብቻ መሆን የለበትም:: ይህንን ኃላፊነታችሁን የምትወጡ ወላጆች በርቱ:: የዘነጋን ደግሞ ልብ እንበል:: የኪዳኑ ሕዝብ በመንገድ፥ በሥራ ቦታ፥ በመኝታ ሁሉ ቃሉን የማውራት የማሰብና የማሰላሰል ኃላፊነት ነበረበት:: በመዝ.1 ላይም ቃሉን በቀንና በሌሊት የሚያስበውን ሰው የተባረከ ይለዋል:: ሰው ራሱን ያስለምድ እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ልዩ መጠራት አያስፈልገውም:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ለወለዳቸው ልጆቹ የማይስማማቸውን ወተት አልሰጣቸውም:: *የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፥ ነፍስን ይመልሳል፥ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል* (መዝ.19፥7):: ደግሞም በመዝ.118፥130 *"የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትን አስተዋዮች ያደርጋል* ይላል:: ይሄ አማኞችን ሁሉ ሊያጽናና የሚገባ ቃል ነው:: ማንም አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል አንብቤ አስተዋይ መሆን የምችል አይደለሁም ማለት የለበትም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ማንም ሰው ሊረዳው በሚችል መልኩ ራሱን የገለጠበት ዓይነተኛ መንገድ ነው::





ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ከተራው ሕዝብ በሚቀርብለት ጥያቄ ሁሉ "አ!ይሄንን ጥያቄ የምትጠይቁት መጻሕፍት ግልጽ ስላልሆኑላችሁ ነው" ሲል አንዴም አንመለከትም:: ይልቁንም በተደጋጋሚ ይመልስ የነበረው መልስ፥ "በሕጉ አላነበባችሁምን" "በመጻሕፍ አላነበባችሁምን" እያለ ነበር (ማቴ.12፥3፤ 22፥31):: እዚህ ላይ የጌታ መልስ ያተኮረው የመጽሐፍቱ አስቸጋሪነት ላይ ሳይሆን የሰዎቹ አለማስተዋል ላይ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል:: በዚህም የሕጉ ቃልና መጻሕፍት እያንዳንዱ ሰው ሊያውቀው በሚችል መልኩ እንደተጻፉ ገልጿል:: ከዚህም ሌላ አብዛኞዎቹ የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን የተቀባይ አድራሻን ስንመለከት የተጻፉት ለቤተክርስቲያን መሪዎች ሳይሆን ወይም ደግሞ የሐዋርያት የእርስ በርስ ደብዳቤዎች ሳይሆኑ በየቦታው ለነበሩ ምዕመናን የተጻፉ ናቸው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲጽፍ "በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ..." ይላል (ፊሊጵ.1፥1.):: "ወደ ገላቲያ አብያተ ክርስቲያና ት ..." ይላል (ገላ.1፥2):: "... በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን..." ይላል (1ቆሮ.1፥2)::

ከዚህም አልፎ ደብዳቤዎቹ በተለያየ ማኅበረ ምዕመናን ዘንድ እየዞሩ እንዲነበቡ ማሳሰቢያ ሲሰጥም እንመለከታለን:: የቆላስይስ አማኞችን ደብዳቤ ሲደመድም "ይህቺም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ ከሎዶቂያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ" (ቆላ.4፥16):: እንግዲህ ከዚህ, እንደምንረዳው የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክቶች የተቀበሉ ሰዎች በትምህርት የተራቀቁና የተለዩ መንፈሳውያን ሳይሆኑ በክርስቶስ ቤዛነት የዳኑ እንደኛ ዓይነት ተራ ሊባሉ የሚችሉ ሰዎች ናቸው ::

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት በዋነኛነት ደረጃ የሚያስፈልገው መንፈሳዊነትና ቃሉን ለመታዘዝና ለመጠበቅ ያለ የልብ ፈቃደኛነት እንጂ የተለየ የአዕምሮ ዕውቀትን የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም (1ቆሮ.2:14):: እንደ እውነቱ ከሆነ ለብዙዎቻችን ለመልስ የሚስቸግረን ጥያቄ ቃሉን ምን ያህል አውቀናል

የሚለው ሳይሆን፥ ለማውቀው ቃል ምን ያህል ታዛዥ ሆኛለሁ የሚለው ጥያቄ ነው። ባጭሩ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ /ግቡ/ ነው ስንል የእግዚአብሔርን እርዳታ ከልብ በመፈለግ፥ ለመታዘዝም በመዘጋጀት የሚያነቡት ሁሉ፥ በሚረዱት መልክ የተጻፈ ነው ማለታችን ነው።

*ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥*
*ሕዝቡም የሚያነበውን ያስተውሉ ነበር።*
(መጽሐፈ ነህምያ 8፥8)





# ክፍል ሁለት

## የእግዚአብሔር መታወቅ

*"...የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ" ኤፌ.1፥15-17።*

1. እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው?

ሰው የተፈጠረው ለምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ አንድ መልስ አለው:- *እግዚአብሔርን ለማወቅ ነው* (ሮሜ. 1፥21)። ሰው በሕይወቱ ዓላማ ሊያደርገው የሚገባው ቁርጥ ሐሳብ ምንድን ነው? *እግዚአብሔርን ማወቅ ነው።* በምድር ላይ ከምንም ነገር በልጦ የመጨረሻው መልካም ነገር የሆነና ለሰው ደስታ፥ ሐሴትና የነፍስ ጥጋብ የሚሰጠው ምንድን ነው? *እግዚአብሔርን ማወቅ ነው።* ከሁሉም ነገር ይልቅ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ሲመለከት ደስታ የሚሰጠው ምንድን ነው? *እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። "ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና"* (ሆሴዕ 6፥6)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው? *እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት"* (ዮሐ.17፥3)።[37]

እምነቱን ከምር ካልያዘ ሰው በቀር እነዚህ ወሳኝ ሐሳቦች በልቡ ውስጥ እሳት የማይጭሩበት ክርስቲያን ይኖራል ብዬ አልገምትም። ይህ ዕውቀት የሰዎች እሴተ ሥርአት (Value System) የሚለካበት ነው። ሰዎች በሕይወት ጎዳናቸው ለነገሮች ቅድሚያ የሚሰጡት ካላቸው የእግዚአብሔር ዕውቀት አንጻር ነው። በሕይወታችን በሚገጥሙን መከራ ጣጣ (Crisis) የምንወስዳቸው ውሳኔዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ምን ያህልና እንዴት እንደምናውቀው ይጠቁማሉ።

የአንድ ሰው አስተሳሰብ፥ ወደዚህ ምድር የመጣሁትና የመፈጠሬ ምክንያት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው የሚለው መረዳት ላይ ካረፈ፥ ይህ ሰው ለሕይወት ውጣ ውረድ የሚሰጠው ምላሽ በአካባቢው ከተለመደው የተለየ ይሆናል። ለዚህ ዓይነት ሰው በየታክሲው ላይ የሚታየው "ሕይወት እሾህ የሞላባት መራራ ተክል ናት" የሚለው መፈክር አይዋጥለትም። "ዘላለም ለመኖር ዕድል ለሌላት ነፍስ ሰላም አትንፈጋት" የሚል የራስ አድን የምሬት መፈክር አይስማማውም።

ሕይወትን ይኖሯት ዘንድ የሚያስመኘው የአኗኗራችን ቅርጽና ልዩ ልዩ ስኬቶች ሳይሆኑ ሕይወትን በዓላማ መኖራችን ነው። ከእኛ ምናብ ጋር የተቆራኘው የዚህ ዓለም ንግድ ነው ወይስ የዘላለም ግብ ነው? አንድ ጊዜ እጅግ ሰፊ እርሻ ያለው አንድ ባለጠጋ ገበሬ፥ ጆን ዌስሊ የተባለውን ስመ ጥር እንግሊዛዊ ሰባኪ ወደ ቤቱ ጋበዘው። ገበሬው ያለውን ብልጽግና ለማሳየት፥ ሰፊ እርሻውን ሊያስጎበኘው ሞከረ፤ ይሁን እንጂ ቀኑን ሙሉ ጎብኝተው ግማሹንም እንኳ መጨረስ አልቻሉም። ታዲያ በቀኑ አመሻሽ ላይ በሀብቱ ብዛት ልቡ የኮራው ገበሬ መለስ ብሎ፥ "እህሳ ዌስሊ ምን ታስባለህ?" በማለት የማሞካሻ ቃል ፍለጋ ጠየቀው። ዌስሊም ከጥቂት የዝምታ ጊዜ በኋላ፤ "ይህንን ሁሉ ሀብት በማስተዳደር ልብህ በክፉ እንደሚጠመድ እገምታለሁ" አለው። የዚህ ሰፊ እርሻ ባለቤት ልብ አሁን እየኖረበት ካለ ዓለም ጋር የተቆራኘ ነው። ዌስሊ ደግሞ ልቡ የተቆራኘው ገና ሊገባበት ከሚናፍቀውና እየሄደበት ካለው ዓለም ጋር ነው። እንግዲህ ለዘላለምና ለአሁን፥ ለመጪውና ላለው ነገር ሁሉ የምንሰጠው ዋጋ ባለን የእግዚአብሔር እውቀት ላይ የተመሠረተ ነው።[38]

ለመሆኑ እግዚአብሔርን ማወቅ ስንልስ ምን ማለታችን ነው? እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ንድፈ ሐሳባዊ (Theoretical) ዕውቀትን ማካበት ማለት ነው? ወይስ የሆነ ዓይነት ጀርባን ሁሉ ውርር የሚያደርግ ስሜት ነው? ወይስ የሆነ የመለኮት ድምጽ መስማት ነው? ወይስ ራእይ ማየት ነው? የቱ ጋ ነው ይህ "እግዚአብሔርን ማወቅ" እያልን የምናወራው ጉዳይ ዋና ሐሳቡ የሚያርፈው? እነዚህ ጥያቄዎች በጣም ወሳኝ ናቸው። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ የምንታለልባቸው ሐሳቦች ናቸው።





ከተሳሳተ ግንዛቤ በመነሳት እግዚአብሔርን የምናውቅ እየመሰለን በሚገባ ሳናውቅ የቀረንባቸው ጊዜያቶች ብዙ ናቸው።

አንድ ሰው የጎረቤቱን ቤት /ሕንፃውን ክፍሎቹንና የቤቱን ዕቃ/ የሚያውቀውን ያህል የቤቱን ባለቤት አያውቀውም። አንድን መጽሐፍ አንብበን የምናውቀውን ያህል ደራሲውን አናውቀውም። ከዚያው አንጻር ደግሞ የአንድን አገር ቋንቋ ማወቅና ባለ ቋንቋውን ሕዝብ ማወቅ አንድ ዓይነት አይደለም።

እንደ ቤትና ሕንፃ ዓይነት ግዑዝ ነገር በማየትና በመጎብኘት ይታወቃል። የአንድ መጽሐፍን ሐሳብና መልእክትም በማንበብና በመሸምደድ ማወቅ ይቻላል። የአንድን አገር ቋንቋም በማጥናትና በመማር ማወቅ ይቻላል። ነገር ግን ሕይወት ያለውን ፍጡር ማወቅ ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች የማወቅን ያህል ቀላል አይደለም። ሕያዋንን አስመልክቶ፥ ምንም እንኳ ያለፈ ታሪካቸውን ብናውቅ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ቀረብ ባለ መልኩ የጠባይ ልወውጥ ካላደረግን በስተቀር ዕውቀታችን ከመረጃ ዕውቀት አልፎ እውነተኛ ዕውቀት አይሆንም።[39]

አንድ ሰው "ይህንን ውሻ ወይም ፈረስ አውቀዋለሁ" ሲል ከዚህ በፊት አይቼው አውቃለሁ ከማለት በላይ ትርጉም ያለው ነገር ነው። ይህ ዓይነቱ ዕውቀት ሰውየው ከዚህ እንስሳ ጋር የገጠመው ቀደም ያለ ልምምድ መኖሩን ያሳያል። የውሻውን ተናካሽነት ወይ የፈረሱን ገርነት አውቆታል ማለት ሊሆን ይችላል።

ሰዎችን አስመልክቶ ያለው ዕውቀት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ውስብስብ ነው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ሰዎች የግዑዛንንና የእንስሳትን ያህል የተገለጡ ባለመሆናቸው ነው። አንድን ፈረስ ወይም አንድን ውሻ ለመለማመድ ብሎም ለማወቅ ጥቂት ቀናት በቂ ናቸው። ነገር ግን አንድን ሰው ለብዙ ወራት ወይም ዓመታት አብረው ቆይተው በእርግጥ "የታውቀዋለህ ወይ?" ጥያቄ ቢመጣ መልሳችንን በቀላሉና በፍጥነት ለመስጠት ያዳግተናል። ምክንያቱም ሰዎችን የማወቃችን መጠን የሚወሰነው እኛ ዘንድ ባለ የዕውቀት አቅም አይደለም። እኛ ዘንድ ያለው ሰዎችን የማወቃችን መጠን የሚለካው የሚታወቁት ሰዎች ስለ

ራሳቸው መታወቅ በለቀቁልን ልቅቀት መጠን ነው። የእኛ ድርሻ ሰዎቹን ስናገኛቸው እነርሱን ለማወቅ ፍላጎታችንንና ክፍተታችንን (ሐሳባችንን፥ ዓላማችንን፥ ፍላጎታችንን፥ ድካማችንንና ብርታታችንን) ማሳየት ነው። እንግዲህ ከዚያ በኋላ እነርሱን ማወቃችን የሚወሰነው በእነርሱ ነው።[40] ሌሎች ሰዎችም እኛን የሚያውቁን እኛ በከፈትንላቸው መጠን ነው ማለት ነው። ታዲያ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው? ለዚህ የምንሰጠው የመጀመሪያ ብያኔ የሚከተለው ነው።

### 1.1. እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ በእግዚአብሔር እንደምንታወቅ ማወቅ ማለት ነው።

*"ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደገና ወደ ደካማ ወደሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ?"* (ገላ.4፥8-9)።

ወደ ጌታ በመምጣታችን ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር የታወቅን መሆናችንን ነው። በዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ውስጥ የሚቀድመው "እግዚአብሔርን አወቅሁት" የሚለው ሳይሆን "እግዚአብሔር እኔን ያውቀኝ ነበር ለካ" የሚለው ነው። የእኛ እግዚአብሔርን ማወቅ እግዚአብሔር እኛን ሳያውቅ ሊከሰት የሚችል ጉዳይ አይደለም። አስቀድመን እኛ አውቀነው ከዚያም እንደምናውቀው ልናስረዳው አንችልም። የእኛ እርሱን ማወቅ በእርሱ ቁጥጥር ስር ያለ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔርን እንደምናውቀው ስንነግረው "ኧረ ባክህ እኔ እኮ አላወቅሁህም ነበር" ብሎ የሚገረም አምላክ አይደለም *(መዝ.139፥1-16) (ዮሐ.1፥44-52)።* እግዚአብሔርን የማወቅ የመጀመሪያ ደረጃ በእግዚአብሔር እንደምንታወቅ ማወቅ ነው። ለሰው ትልቁ ዕውቀቱ በእግዚአብሔር እንደሚታወቅ ማወቁ ነው። ይህ ዕውቀት በራሱ እግዚአብሔርን የማወቅ እርምጃ ነው።[41]

እኛ እያንዳንዳችን በመሥሪያ ቤታችን አለቆች፥ በአካባቢያችን ሹማምንቶች፥ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና





አገልጋዮች በስም ስንታወቅ የሚሰማን ስሜት እንዴት ያለ ነው? በምንሠራበት ቦታ፥ በመኖሪያ ቤታችን ወይ በቤተ ክርስቲያን የአገራችን ፕሬዘዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስቴር መጥተው "እገሌ እንደምን ከረምክ? ምነው ሰሞኑን አይቼህ አላውቅም?" ብለው ቢጠይቁን የአገር መሪዎች በስም ስለአወቁን የሚሰማን ስሜት ምን ዓይነት ነው? ከዚያ እኛም ከዚህ ኩራት በመነሳት "ጠቅላይ ሚኒስትሩን አውቃቸዋለሁ እኮ እሳቸውም በደንብ ያውቁኛል!" ማለት እንጀምራለን።

ይሁን እንጂ እነዚህ ውሱን የሰው ልጆች ምንም በሥልጣን ከፍ ያሉ ቢሆኑም በምክር ቤት አባልነት የሚያውቋቸውን ሰዎች በሙሉ በስም አያውቋቸውም። በዓይን ያዩአቸውን ሰዎች እንኳ ላያስታውሱ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን እያንዳንዳችንን ገና ሳናውቀው ያውቀናል *(ዮሐ.10፥3) (ኢሳ.45፥3)።*

እግዚአብሔር ሙሴን በምድያም በርሃ የአማቱን የዮቶርን በጎች ሲጠብቅ አገኘው። አስቀድሞ ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ በጉልበት ነጻ የሚያወጣ መስሎት የራሱን ሙከራ አድርጎ ነበር። ነገር ግን ስላልተሳካለት ኮብልሎ በምድያም ምድር በከብት አርቢነት የራሱን ኑሮ ጀመረ። ሙሴ እግዚአብሔርን ከማወቁ በፊት እግዚአብሔር ሙሴን አውቆት ነበርና ሰዓቱ ሲደርስ ለሙሴ ተገለጠ (ዘጸ.3)።[42]

ነቢዩ ኤርምያስ ለእንቢተኛይቱ እስራኤል ነቢይ ለመሆን ገና ሲመረጥ ወደ እርሱ የመጣው የመለኮት ድምጽ፥ *"በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ"* የሚል ነው (ኤር.1፥5)።

እግዚአብሔር ለሐዋርያው ጳውሎስ የተገለጠው እግዚአብሔርን እየፈለገ በነበረበት ወቅት ሳይሆን ይልቁንም መንገዱንና ፍለጋውን ሲቃወም እግዚአብሔርንም የሚያውቁትን ሲያሳድድ ነው የተገለጠለት። እንዲህ ከመሆኑም የተነሳ ከሃይማኖታዊ ኩራት ተላቆ፥ እኔ የማልጠቅም ባሪያ ነኝ በሚል መንፈስ፥ አምላኩን የሚያገለግል ሐዋርያ ለመሆን በቃ። በእግዚአብሔር መታወቃችንን ማወቅ ኩራታችንን ያስወግድልናል (ኤፌ.3፥9)።[43]

## 1.2.<u>እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እግዚአብሔርን በግል መለማመድና ከእርሱም ጋር መቀራረብ ማለት ነው።</u>

አንድ ሰው እግዚአብሔርን በሚገባ ሳያውቅ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ዕውቀት ሊኖረው ይችላል። በርካታ ስብከቶችን እንሰማለን፥ ጥቅሶችንም እናጠናለን፥ መንፈሳዊ ካሴቶችንም እናዳምጣለን፥ የቻልነውን ያህልና ያገኘነውን ያህልም መጻሕፍት እናነባለን፤ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የተገኙትን የቪዲዮ ካሴቶችን እንመለከታለን። ከዚያም ካገኘነው መረጃ በመነሳት ስለ እግዚአብሔር ብዙ እንናገራለን። ከዚህ የተነሳም አንዳንዶቻችን ከሌሎች የተሻለ የእግዚአብሔር ዕውቀት እንዳለን ራሳችንን እንቆጥራለን። እርግጥ ነው እነዚህ የተጠቀሱት ነገሮች በጥንቃቄና በሚለይ መንፈስ ከተጠቀምንባቸው ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚጠቅሙ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በራሳቸው እግዚአብሔርን የማወቃችን ምልክቶች አይደሉም።

የሰዎችን የሕይወት ምስክርነት ማንበብና መስማት፥ ስለ ጸሎት የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ማንበብ፥ ነፍሳትን ወደ ጌታ የማምጣትን ዘዴ ማጥናትና መማር፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀምን መማር፤ ሰዎችንም ማስተማር ይቻላል። በተለይ በዚህ መረጃዎች እንደ ልብ በሚገኙበት ዘመን ብዙ መንፈሳዊ ዕውቀት ማካበት ይቻላል። ይህንንም ሁሉ ሲያደርጉ በመታየትም የቤተክርስቲያን መሪ ወይም አገልጋይ (ሽማግሌ፥ መጋቢ፥ ወንጌላዊ ሌላም ሌላም) ተብሎ የሚያሾም ማንነት ልናገኝ እንችል ይሆናል። "እንዴት ያለ እውቀት አለው!" ልንባልም እንችላለን። በእርግጥ ሰፊ እውቀትም ሆነ እነዚህ የተዘረዘሩ ሹመቶች መልካምና ጠቃሚ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች በራሳቸው እግዚአብሔርን የማወቃችን ዋንኛ ምልክቶች አይደሉም።

ትልቁ ጥያቄ ግን በሕይወት የእውነታ ገጠመኞችና ምቹ ባልሆኑ ጎዳናዎች ውስጥ እግዚአብሔርን አስመልክቶ ያለን የመረጃ ዕውቀታችን ሲፈተን፥ "እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ" እንላለን ወይ? ስለ እግዚአብሔር ማወቅና እግዚአብሔርን ማወቅ ቁርጡ የሚለየው ዕውቀታችን ተግባራዊ በሆነ የሕይወት መስከ





ተፈትኖ ሲያልፍ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ሲል መከራ በሚቀበልበት ጊዜ ለጢሞቴዎስ እንደዚህ ብሎ ጻፈለት፡- *"ስለዚህ ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብዬአለሁ፥ ነገር ግን አላፍርበትም <u>የመንኩትን አውቃለሁና</u> ፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቻለሁ"* (2ጢሞ.1፥12)። ሐዋርያው ይህንን ደብዳቤ የጻፈው በተንደላቀቀ ቪላ ሆኖ ሳይሆን፥ በሮም እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ነው። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ *"<u>የመንኩትን አውቀዋለሁ</u>"* ማለት ከመረጃ ያለፈ ዕውቀት እንዳለ ይጠቁማል። አደራዬን ሊጠብቅ ይችላል ብቻ ሳይሆን ፥ እንደሚችል እኔም አብሬው ተጉዤ ተረድቻለሁ እመሰክርማለሁ የሚል ነው። እግዚአብሔርን ለማወቅ እግዚአብሔርን በግል ሕይወት መለማመድና መቀራረብ ያስፈልጋል። ሰዎች እንኳ እርስ በርስ በደንብ የሚተዋወቁት በዕለታዊ ኑሯቸው ውስጥ የማያቋርጥ ግንኙነት ሲፈጥሩ ነው።

በቀደሙት ዘመናት በአገራችን በአብዛኛው ኅብረተሰብ የተለመደው የጋብቻ መንገድ በቤተሰብ በኩል የሚፈጸም ነው። አሁንም በአንዳንድ ቦታ ይኖራል። ሴትዋም ሆነች ወንዱ የሚያገቡትን ሰው የሚወስንላቸው ቤተሰብ ነው። ሴትዋ የምታገባው ወንድ የማን ልጅነቱን፥ መንደሩንና ትውልዱን ከማወቅ አልፋ ጠባዩ ምን እንደሆነ፥ የሚወደውና የሚጠላው ምን እንደሆነ አታውቅም። ልታውቅም ብትሞክር ዕውቀቷ ሰውየውን የሚያወቁትን ሰዎች በመጠየቅ መረጃዊ የሆነ ዕውቀት ነው። ባሏን በደንብ አወቀችው የሚባለው ግን አብረው ኑሮ ሲጀምሩና በመቀራረብም ሲላመዱ ነው። ይሄ በሁላችንም የሕይወት ገጠመኝ ውስጥ የሚኖር ጉዳይ ነው። ሁኔታዎች አብረናቸው የምንኖራቸውን ሰዎች ጠባይ ሲገልጡ "ለካ አላውቀውም/አላውቃትም/ ኖሯል፥" ያልንባቸውም ሆነ የተባልንባቸው ጊዜአቶችና አጋጣሚዎች ጥቂቶች አይደሉም። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለትም ስለ እግዚአብሔር መረጃ መሰብሰብ ማለት ብቻ አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔርን በግል መለማመድና መቀራረብ ማለት እንጂ።[44]

## 1.3. በእግዚአብሔር እንደምንታወቅ ማወቅ፥ እርሱንም መለማመድና ማየት እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም ጥንቃቄ ያሻዋል።

*ዘጸ.33፥8-23*

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኛው ድንኳን እየተነጋገረ ሳለ በመሪነት አገልግሎቱ ውስጥ፥ ወሳኝ የሆኑ ሦስት ጥያቄዎችን ጠየቀ። አስቀድሞ የአቅጣጫና የዕቅድ ጥያቄ ጠየቀ። *መንገድህን እባክህ አሳየኝ* (እቅድህን አሳየኝ) *ይህም ሕዝብ ሕዝብህ እንደሆነ ተመልከት አለው* ቁ.13። *እግዚአብሔርም እኔ ካንተ ጋር እሄዳለሁ አሳርፍሃለሁ* ቁ.14 የሚል መልስ ሰጠው። ቀጥሎም የእግዚአብሔርን መገኘት የማረጋገጫ ጥያቄ ጠየቀ። እግዚአብሔርም *"ይህ ያልከውን ነገር አደርጋለሁ"* ቁ.17 አለው።

ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘና ከአምላኩ ጋር እጅግ የተቀራረበ ሰው በመሆኑ እግዚአብሔርን በሚፈራና በሚያከብር ልብ እነዚህን ጥያቄዎች ጠየቀ። እግዚአብሔር ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ያነጋግረው ነበር (ቁ.11)። እግዚአብሔር ሙሴን በስሙ ያውቀው ነበር (ቁ.12)። እነዚህ የጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች በቀጥታ ሕዝቡን የሚመለከቱ ናቸው። ነገር ግን በሦስተኛ ደረጃ የጠየቀው ጥያቄ እጅግ የተለየና ከራሱ ሕይወት ጋር የተገናኘ ጥያቄ ነው። እግዚአብሔርን የማየት ጥያቄ ጠየቀ። *"እባክህ ክብርህን አሳየኝ"* አለ ቁ.19 ። ሙሴ እስከ ዛሬ የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል፤ አሁን ግን "ሙሉ በሙሉ ብርሀንህንና ፊትህን ልመልከተው" የሚል ይመስላል። እግዚአብሔር ግን ሦስተኛውን ጥያቄ ከታላቅ ማስጠንቀቂያ ጋር መለሰለት። *"እኔ ምልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ... ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፥ በዓለቱም ላይ ትቆማለህ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው አለት አኖርሃለሁ፥ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ ፊቴ ግን አይታይም"* (ቁ.19-20)።[45]





እግዚአብሔር ራሱን በሙላት ሲገልጥ ሁልጊዜ አብሮት ማስጠንቀቂያ አለ። በደማስቆ መንገድ ክርስቶስ ዓይን በሚያጠፋ ብርሃን ለጳውሎስ ራሱን ሲገልጥ፥ "የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ላንተ ይብስብሃል" የሚል ማስጠንቀቂያ በእብራይስጥ ቋንቋ አስደመጠው (ሐዋ.26፥12)። እግዚአብሔር ራሱን በሙላት ሲገልጥ የተገለጠላቸው ሰዎች ተዝናንተው ሃሌሉያ! እያሉ የሚቀበሉት ጉዳይ አይደለም። አብሮት ወዮታና ድንጋጤ አለ። ከዚያ በኋላ ግን ታላቅ የሕይወት ለውጥ ይከተላል። *የእግዚአብሔር ክብር በሙላት የተገለጠላቸው ሰዎች በፍጹም እንደቀድሞው መሆን አይችሉም። አስቀድሞ ሕይወታቸው ይናወጣል ከዚያም ለዘላለም ይለወጣል።*

ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በሚያስፈራ ቅድስናውና በአስደንጋጭ ክብሩ ባየው ጊዜ እራሱን ቀድሞ እንደሚያይ ማየት አልቻለም። *"ከንፈሮቼ በረከሱበት ሕዝብ መካከል የምኖር ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ የሠራዊት ጌታ የሆነን ንጉሡን እግዚአብሔርን በዐይኖቼ አይቻለሁና መጥፋቴ ስለሆነ ወዮልኝ አልሁ"* ይላል፥ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ተራክቦ ያደረገው ኢሳይያስ (ኢሳ.6፥5)። እግዚአብሔርን ማወቃችን የሚለካው እግዚአብሔርን በሕይወታችን ባየነው ልክ እንጂ ተሰብስበን በምናደርገው ሞቅታ አይደለም። እግዚአብሔርን ማወቃችን በእረፍት ቀኖቻችን በጉባኤ አዳራሽ በሚታየው ማንነታችን አይለካም። በአዳራሹ የሆኑ መልካም ነገሮችና መንፈሳዊ ተራክቦዎች (communion) ሁሉ የቀን ተቀን ሕይወታችንን ካልቀረጹት በነፋስ የተወሰደ የጊዜው ሞቅታ ብቻ ሆኖ ይቀራል።

ብዙ ጊዜ የራሳችንን ማንነት ከሰዎች ጋር እያስተያየን የምንኖር ስለሆነ፥ ብዙ የምንቆጥረው ቅድስናና ጽድቅ ይኖረናል። እግዚአብሔርን ሙሴ እንዳየው ብናይ፥ እግዚአብሔርን ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳየው ብናይ "እግዚአብሔርን በአይኖቼ አይቻለሁና መጥፋቴ ስለሆነ ወዮልኝ" እንል ነበር። ሕይወታችንንና የእግዚአብሔር እውቀታችንን እርስ በርሳችን እየለካን ስለሆነ ምንም ወዮ የሚያሰኝ ነገር የለንም። እገሌን አይቼዋለሁና፥ እገሊትን አይቻለሁና ወዮልኝ ማለት አይቻልም። እግዚአብሔርን

በሕይወቱ ያየና የተለማመደ ሰው ግን ራሱን ትሁት ያደርጋል የራሱ የሆነ ትምክህት ያጣል።

ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በክብሩና በቅድስናው ካየው በኋላ ራሱን/ማንነቱን/ እንደቀደመው ማየት አልቻለም። እኔ የተበላሸሁ ነኝ የማልጠቅም ነኝ አለ። ከእግዚአብሔርም መልአክ አንዱ እየበረረ መጥቶ ከመሰዊያው በወሰደው የእሳት ፍም ከንፈሮቹን አስነክቶ *"በደልህ ተወግዶልሃል ኃጢያትህም ተሰርዮልሃል"* አለው። እግዚአብሔር ለሙሴ ጀርባውን /ጥላውን/ እንኳ ባሳየው ጊዜ ምሕረቱን ቸርነቱን አስቀድሞ ነው። ለኢሳይያስም ሲገለጥለት የበደል ይቅርታን ሰጥቶት ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ፣ ማየትና መለማመድ እጅግ ጠቃሚ ነው፤ ቢሆንም ጥንቃቄ ያሻዋል።

2. እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድር ነው?

ሰው በምድር ላይ ባለ ዘመኑ ሁሉ ኑሮው በጥያቄ የተሞላ ነው። በምርምርና በማወቅ ፍላጎት የተሞላ ነው። ጠይቆ ባገኘው መልስ ሳይረካ ሌላ ጥያቄ የመፍጠር ፍጥነት ያለው ፍጡር ነው። ከዕለተ ውልደቱ አንስቶ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ጥያቄ እንደጠየቀ ሕይወቱ ያልፋል። ለምን ይሄ ነገር ሆነ? የሆነውስ ከመቼ ግዜ ጀምሮ ነው? ያደረገውስ ማን ነው? ምክንያቱስ ምንድን ነው? የሚሉት ጥያቄዎች ሰው ወደዚህ ምድር ከመጣ ጊዜ አንስቶ፥ ከዚህች ምድር እስከሚሄድ ድረስ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ናቸው።

ሕፃናት አፋቸውን መፍታት ሲጀምሩ አንደበታቸውን የሚያለማምዱት በጥያቄ ነው። እቤት ከእናቱ ጋር የሚውል ሕፃን እናቱን "እማማ አባዬ ጠዋት ጠዋት ወዴት ይሄዳል?" ብሎ ይጠይቃል። *"ሥራ ለመሥራት"* ቢባልም "ለምን እቤት አይሠራም?" ይላል። "ደመወዝ አያገኝም" ቢባልም "ለምን አንቺ አትከፍይውም?" ይላል እናቱን። ጥያቄው አያቋርጥም፣ እንደውም አንዳንድ ጊዜ ሕጻናት የሚጠይቁት ጥያቄ ለመልስ ያስቸግራል። ዕድሜና የአዕምሮ ብስለት እየጨመረ ሲመጣም የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች ይዘታቸውና ዓይነታቸው እየተወሳሰበ ይመጣል። ረቀቅ





ያሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንጀምራለን። እንደውም ጥያቄ የለመደ አዕምሮ መልስ እስካላገኘ ድረስ ዕረፍት የለውም።[46]

የዓለም አፈጣጠርንና የተፈጥሮ አሰራር ለማወቅ እንጠይቃለን፥ ወደፊት ኑሮአችንን እንዴት እንደምንመራ እንጠይቃለን፥ ምን ዓይነት ባል ወይም ሚስት ነው የማገባው? የምኖረውስ ኑሮ ምን ዓይነት ሊሆን ይችላል? እንላለን። አንዳንዴ የኑሮ አጣብቂኝ ውስጥ ስንገባ ደግሞ ለምን ተፈጠርኩኝ እንላለን። ይህንኑ ተከትሎ የሚመጣው ሌላ ጥያቄ ደግሞ ለመሆኑ ማነው የፈጠረኝ? የሚለው ጥያቄ ነው። ለመሆኑ ፈጣሪ ማነው የሚለው ጥያቄ የዓለም ትልቁ ጥያቄ ነው። ይሁን እንጂ ባለፉት ተከታታይ ርዕሶች ይህ አምላክ ራሱን ያልሸሸገ የመገለጥ አምላክ እንደሆነ ተመልክተናል።

ነገር ግን የብዙ ሰዎች ሕይወት እርካታ ያጣው እግዚአብሔርን ማወቅ የሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ ስላልተመለሰላቸው መሆኑን እንመለከታለን። ይሄ መሠረታዊ ጥያቄ ካልተመለሰ ደግሞ ሕይወት ከእርካታ ትገለላለች። ምክንያቱም ለሰው ክብሩ ሳይንሳዊ ግኝቱ አይደለም፣ ለሰው ሞገሱ የተሻለ የምድር ኑሮ አይደለም፣ የሰው እፎይታው በሚታየው ዓለም ያለው ዕንቆቅልሽ መፈታቱ አይደለም። ለሰው ክብሩ ሞገሱና እፎይታው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የፈጠረውን አምላኩን ማወቅና ለእርሱም ክብር በመስጠት መኖሩ ነው።

የጥያቄ እፎይታና የእንቆቅልሽ ፍቺ የሚገኘው ሰው እግዚአብሔርን ሲያውቅ ብቻ ነው። ይህ ዋና ጥያቄ የተመለሰላቸው ሰዎች ዕረፍት የሚነሱትን ሌሎች ጥያቄዎችን ይጥላሉ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ጥቂቶቹ መልሶቻችን የሚከተሉት ይሆናሉ :-

2.1. <u>እግዚአብሔርን ማወቅ ሁልጊዜ ወቅታዊና አንገብጋቢ ስለሆነ ነው።</u>

ድሮም፥ አሁንም ሆነ ወደፊትም፥ ዘመናዊ ዕውቀት እግዚአብሔር አምላክን ማወቅ ነው። ይህ ዕውቀት በየዘመኑ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ዕውቀት ነው። በዚህ ዕውቀት የኖሩ ሁሉ

ዘመናትን ዋጅተው አልፈዋል፡፡ እኛም በዚህ ዕውቀት የኖሩ ሰዎች የዘሩት ዘር ፍሬዎች ነን፡፡ በየዘመኑ ቅሬት በመሆን እውነተኛው እምነት እንዲቀጥል ያደረጉ እግዚአብሔርን ያወቁ ሰዎች ናቸው፡፡ ከ2000 ዓመታት በፊት ፍልስፍናና የሰው ልጅ ጥያቄ መርቀቅና መግነን በጀመረበት የሮማና የግሪክ ዓለም የኖረው ሐዋርያው ጳውሎስ ሊያውቅ ይመኝ የነበረው ምንድን ነበር? ከምኞቶቹ መካከል አንዱ በፊል.3÷9-11 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ገና ንግግሩን ሲጀምር በመሃላና በእርግጠኛነት ነው የሚጀምረው፡፡ *"አዎን÷ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ ዕውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ፡፡"* ካለ በኋላ *"እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ* (እንደ ሕያው ቃል ትርጉም፡- *ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኃይል በይበልጥ ለማወቅ) በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታን ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ፡፡"* በማለት ይናገራል፤ እግዚአብሔርንና ሚስጥሩን ለማወቅ በተጠማች ነፍስ ሆኖ፡፡ በምድር ያለኝ ክብሬና ማንነቴ እግዚአብሔርን ከማወቄ ጋር ሲነጻጸር ለእኔ እንደጉድፍ ነው፡፡ ይልቁንም እርሱንና ከሞት የተነሳበትን የትንሳኤውን ኃይል ሚስጥር ማወቅ የእውቀትና የክብር ቁንጮ ነው፡፡ ይላል ታላቁ ሐዋርያ፡፡

ጳውሎስ የትንሣኤውን ጌታና የትንሣኤውን ኃይል ነጣጥሎ አይደለም የተመኘው፡፡ እንደውም ጳውሎስ አስቀድሞ የተመኘው *"እርሱን"* ክርስቶስን የትንሣኤውን ጌታ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ኃይሉን እንዳውቅ ያለው፡፡ ዛሬ የብዙ አማኞች የልብ ናፍቆት የትንሣኤውን ጌታ ማወቅ ሳይሆን ኃይሉን ብቻ ማወቅ ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ከማወቅ ትክክለኛ መንገድ የራቀ ነው፡፡

በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሲሞን የሚባል ጠንቋይ በወንጌላዊ ፊሊጶስ አገልግሎት ወንጌል ሰምቶ በጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነ በኋላ የእግዚአብሔርን ኃይል በገንዘብ ለመግዛት ሲሞክር እንመለከተዋለን (ሐዋ.8÷ 9-25)፡፡ እግዚአብሔርን ከማወቁ በፊት ኃይል ተጠማ፡፡ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን በሲሞን አስተሳሰብ የምንመላለስ እንኖር ይሆንን? ከዚህም የተነሳ የብዙዎቻችን ጥያቄ እግዚአብሔርን ከማወቅ ይልቅ ኃይሉን መግለጥና መለማመድ ነው፡፡ በምድር ኑሯቸው





ኃይሉን አውቀናል ተለማምደናል ያሉትን ሰዎች በዘመን ምጨረሻ ጌታ *"ከቶ አላወቅኋችሁም"* ሲላቸው በውስጡ ያለው መልዕክት እናንተ አታውቁኝም ነበርና ማለቱ ነው (ማቴ.7÷22-23)፡፡ በዚህ ጥቅስ መሠረት በሕይወተ ሥጋቸው ትንቢት የተናገሩና አጋንንትን በጌታ ሥም ያወጡ ሁሉ በዘመን ፍጻሜ ጌታ ከእኔ ራቁ ይላቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የእግዚአብሔር መንግሥት መግቢያ ዋስትና÷ በክርስቶስ አምኖ የአብን ፈቃድ ማድረግ እንጂ÷ ዋስትናው የኃይል አገልግሎት አይደለም ማለቱ ነው፡፡

የክርስቶስን ኃይል ከክርስቶስ ነጥሎ ለማወቅ የሚደረግ ሙከራ ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይገባዋል፡፡ እግዚአብሔርን ሳያውቁ ኃይሉን ለማወቅ የሚደረግ ሙከራ ክርስቲያናዊ አይደለምና አስቀድሞ እግዚአብሔርን እንወቅ፤ እርሱን በማወቃችን ደግሞ እግዚአብሔር ኃይሉን ይጨምርልን! ከእርሱ ከሚገኘው ነገር ይልቅ እርሱን ማወቅ ይቅደም፡፡[47]

ለእውነት እንነጋገር ቢባል እግዚአብሔርን ለማወቅ ከጸለይነውና ከደከምነው ይልቅ÷ ከእርሱ ለመቀበልና ኃይሉንም ለመለማመድ የደከምነው ድካም ይበልጣል፡፡ አንድ ጊዜ አንድ የቤክርስቲያን አገልጋይ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር "አብዛኛውን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ፊቱን ከመፈለግ ይልቅ እጁን እንፈልጋለን" በማለት ተናገረ፡፡ በዚህ ረገድ መንፈሳዊ ጥረታችን የቅደም ተከተል ለውጥ ያስፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም ምንጊዜም ማንም ቢሆን ከሚሰጠው ስጦታ ይልቅ ራሱ ሰጪው ይበልጣልና ነው፡፡ በሌላ አባባል በኃይል ጥያቄ ጸሎታችን ላይ እግዚአብሔርን የማወቅ ጸሎት እንጨምርበት እናስቀድምም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ ለማወቅ ያልተጠማች ነፍስ በሌላ ነገር አትረካምና ነው፡፡

በመዝ.42÷1-4 እውነተኛውን የጻድቅ ሰው የነፍስ ጥማት እንመለከታለን፡፡ *"ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ÷ አቤቱ÷ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች፡፡ ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ? ዘወትር፡- አምላክህ ወዴት ነው ሲሉኝ እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ ይኼንን ሳስብ ነፍሴ በእኔ ውስጥ*

*ፈሰሰች..."* እያለ ጻደቁ አስደናቂ የሙጥኝታ ድምጽ ያስማል:: በእሥራኤል ምደረ በዳ በውሃ ጥም እያለከለከች እንደምትሮጥ ዋላ/ሰስ ተመስሎ:: የመዝሙረኛው ዋና ትኩረት ዋላዋ ሳትሆን የጥሟ ማረፊያ የሆነው ውሃው ነው:: በምሳሌው የምንጩ ውሃ የሚወክለው ሕያው አምላክን ነው:: ብዙ ጊዜ ወካዩን ወስደን ተወካዩን እንዘነጋለን:: በዚህ ሥፍራ ላይ ዳዊት ውሃ እንደምትጠማ ዋልያ ሁሉ እኔም በመቅደስህ መጥቼ እስካመልክህ ድረስ ቸኮልኩኝ ይላል::[48]

ዛሬ ነፍሳችን ግብግብ ብላ የምትጠማው ዕውቅት ምንድን ነው? ዛሬ ነፍሳችን የምትገሰግሰውስ ወዴት ነው? የዕውቀት ራባችንስ ምንድን ነው? የዕውቀት ትምክህታችንስ ምንድን ነው? ሰው ሊመካበት የሚገባ አንድ የተፈቀደ ትምክህት አለ:: ይህም በነቢዩ ኤር.9÷23-24 ላይ ይገኛል:-*"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ጠቢብ በጥበቡ አይመካ ÷ ባለጠጋም በብልጥግናው አይመካ ነገር ግን የሚመካው÷ ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማስተዋሉ በዚህ ይመካ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና÷ ይላል እግዚአብሔር"::*

በዚህ ሥፍራ ላይ የምድር ትምክህት ሦስት መሠረታዊ መገኛዎች ተጠቅሰዋል:: የሰዎች ትምክህት በአንድም በሌላም መንገድ ከእነዚህ ሦስት ጉዳዮች አይወጣም:: እነሱም÷ ጥበብ÷ ኃይልና ባለጠግነት ናቸው፤ በዚሁ ጥቅስ ላይ ደግሞ በተቃራኒ ሦስት የሰማይ ጠባያት ተጠቅሰዋል:: ምሕረት፤ ፍርድና ጽድቅ:: እግዚአብሔር ከጥበብ÷ ከኃይልና ከባለጠግነት ይልቅ መሃሪ÷ ጻድቅና ቅን ፈራጅ የሆነው ማንነቱ ሲታወቅ ደስ ይለዋል:: ከዚህም ሌላ ከመንፈሳዊ ሥነ-ስርዓት ይልቅ /በፊት/ እግዚአብ ሔርን ማወቅ መቅደም እንዳለበት ይህም ደስ እንደሚያሰኘው በሆሴዕ 6÷3-6 ተነግሯል:: *"እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል እንደወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን እንደዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደመጨረሻ ዝናብ ይመጣል...ከመስዋዕት ይልቅ ምሕረትን ከሚቃጠልም መስዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና"* ይላል በነቢዩ አፍ:: እግዚአብሔርን ሳያውቁ ኃይሉን ብቻ የፈለጉ አገልጋዮችና መሪዎች አገርን ለውርደት ሕዝብን ለግራ መጋባትና ለእልቂት





እንዴት እንዳበቁ ከብሉይ ኪዳን ታሪክ አንድ ምሳሌ ወስደን እንመልከት::

በግምት ከ3105 ዓመታት በፊት በአንድ አገር የማምለኪያ ማዕከል በሆነች ከተማ ውሰጥ አንድ ታሪክ ተከሰተ (1ሳሙ.1-4):: በዚያች ከተማ ውስጥ የነበረው የደብሩ አለቃ ሦስት ልጆች የነበሩት አንድ ካህን ነበረ::

ሁለቱ ልጆቹ የራሱ ሲሆኑ አንደኛው ግን ማደጎ ነው:: የሁለቱ ልጆች የሥራ ሞያም ያው እንደ አባታቸው ክህነት ስለሆነ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ናቸው:: ቅጽል ሥማቸው÷ *"ምናምንቴዎች"* (2÷12)፤ የሚወዱት ምግብ÷ *"ለአምላካቸው ከሚቀርበው መሥዋዕት ከአምላካቸው በፊት ጥብስ መብላት ነው"* (2÷13-17)፤ ምግቡን የሚያገኙበት መንገድ÷ *"በግድ/ በንጥቂያ/"* ነው (2÷16)፤ ፀባያቸው÷ *"ቁርባን መናቅ"* (2÷29)፤ ዕውቀታቸው÷ *"አምላካቸውን የማያውቁ ነበሩ"* (2÷12)፤ ሥነ ምግባራቸው÷ *"በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉትን የሚያባልጉ"* በስርዓት ያላደጉ ናቸው (2÷22)፤ የሚጠብቃቸው ዕድል÷ አምላካ ቸውን ስለናቁ በአምላካቸው የተናቁና ሊገደሉም የታሰቡ ናቸው (2÷25)::

ሦስተኛው ልጅ የስለት ልጅ ነው:: ቅጽል ሥሙ÷ *"የታመነ"* የሚል ነው:: እግዚአብሔር ከዋናው ካህን ይልቅ ለዚህ ብላቴና ሚስጢር ነግሮታል (3÷11)፤ ሥራው÷ *"በካህኑ ፊት አምላኩን ማገልገል ነው"* (3÷1)፤ አስተዳደጉ÷ *"በእግዚአብሔር ፊት የሚያድግ ነው"* ጥሪው÷ *"በልጅነቱ በእግዚአብሔር የተጠራ ነው"* የአገሪቱን የመጀመሪያ ሁለት ነገሥታት ቅብአ ነገሥት የቀባ እርሱ ነው::

እንግዲህ በአንድ ቤት ውስጥ ባሉ አገልጋዮች መካከል እንዲህ ዓይነት የሰፋ ልዩነት ነበረ:: እናም አንድ ቀን በዚያች አገር ላይ ሌሎች አማልክትን የሚያመልኩ ሰዎች ትልቅ የጦርነት ወረራ አካሄዱ:: የአገሬው ሕዝብ/ወታደር/ እንደቀድሞው ልማዱ መንፈሳዊ መሪዎቹን ሳያማክርና ወደ አምላኩም ሳይጸልይ በቀጥታ ወደ ጦርነት ሄደ:: ከዚያም ቀስት ሳይገትሩ ፍላጻም ሳይወረውሩ÷ በአንድ ጊዜ 4000 ሰዎች አለቁ:: የተሸነፉበት ቦታ

መጠሪያ ስሙ "አቤንኤዜር" ወይም የእርዳታ አለት የሚባል ቦታ ነው፤ ቢሆንም ቦታው እንደስሙ ሳይሆን ቀረ።

ከዚያም ከግድያ የተረፈ ወሬ ነጋሪ ለከተማይቱ ሽማግሌዎች ታሪኩን ሁሉ ነገረ። መቼም ከሽማግሌዎች ብልሃት አይጠፋምና እንዲህ አሉ፦ "*በሉ አምላካችን ለእኛ ቃል የገባበትን የኪዳኑን ታቦትና መንፈሳዊ መሪዎቻችንን ይዘን ወደ ጦርነት እንውጣ*" አሉ፤ በዕድሜ የገፉ ታሪክን የሚያውቁ ሰዎች። ስለዚህ ታቦቱ በብዙ ሺህ ወታደሮች ታጅቦ አፍኒንና ፊንሃስ በሚባሉ ሁለት ካህናት እየተመራ በድል እርግጠኛነትና በታላቅ የእልልታ ጩኸት ጦር ሜዳ ደረሱ። ጠላቶቻቸው የዚህን ታቦት ታሪክ ስለሚያውቁ በታላቅ ድንጋጤ ተዋጡ። ከዚህ በፊት ከዚህ ታቦት የተነሳ የወንዝ ፍሳሾች እንደቆሙ፥ አንድ ታላቅና ኃያል የሆነች ከተማ ቅጥሯ እንደተናደ ከታሪክ ሰምተዋል። ከዚህም የተነሳ ልባቸው ቀለጠ። ቢሆንም አንዴ መጥተናል አንመለስም በሚል ገጠሟቸው። በሚገርም ሁኔታም ለሁለተኛ ጊዜ አሸነፏቸው። የኪዳኑን ሕዝብ ከበፊቱ ስምንት እጥፍ አድርገው መቱአቸው።

እግዚአብሔርን በሚገባ የማያውቁ ካህናት፥ አውቀውትም በድፍረት በፊቱ የሚመላለሱ የካህኑ የኤሊ ልጆች፥ ለሰላሳ አራት ሺህ ሕዝብ ማለቅ ምክንያት ሆኑ! በእነርሱም ምክንያት ብዙ ሕዝብ ያለአባት ቀረ! የእስራኤል ክብር የሆነው ታቦቱ ተማረከ! ካህኑ ኤሊ ሞተ! በጠቅላላው ክብር ከእስራኤል ተወሰደ!! (1ሳሙ.4፥21-22)።

እግዚአብሔርን በሚገባ ሳያውቁት አብሮ መሄድ የሚቻል አይደለም። እግዚአብሔርን ማወቅ ልዩ ልዩ ሥርዓቶችንና ሕጎችን ከማወቅ በላይ ነው። በተለይ "*ወደ እኔ በሚቀርቡት አብዝቼ እቀደሳለሁ*" ይላል። እግዚአብሔርን በመካከላችን እንዲገኝ የሚያደርገው የሞቀ ዝማሬና የተሟላ የምንለው የአምልኮ ፕሮግራማችን ሳይሆን ከፕሮግራሞቻችን አስቀድሞ ከእግዚአ ብሔር ጋር ያለን አካሄድ ነው። ጌታ ዳሰሰኝ ተባረክሁኝ የምንለው ፕሮግራም ላይ ብቻ ከሆነ የሚቀረን አለ። በእርግጥ ሐሳባችንን የእርሱ ዓላማ ለውጦትና እኛንም አስተምሮን ከሆነ መልካም ብለናል፥ ያላስተዋልነውን ክፋት እንድንተው መክሮን እኛም ሰምተን ከሆነ መልካም ብለናል። እርግጥ ነው የሞቀ





ዝማሬና የተሟላ ፕሮግራም ያስፈልገናል። ይህ ኖሮ እግዚአብሔር የማይገኝበት ከሆነ በመገኘቱም ራሳችንን ለለውጥ ያላዘጋጀን ከሆነ ኪሳራ ነው። በክፉ ቀን ጸንተን እንድንኖር የሚያደርገን ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥርዓትና ልምምዳችን ሳይሆን እግዚአብሔርን በቅርብ ማወቃችን ነው።

"*ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥ ከሚቃጠልም መሥዋዕትም ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና*" ይላል ቃሉ፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ማወቅ በየዘመኑ አንገብጋቢ የሆነ ጉዳይ ነው።

### 2.2.<u>እግዚአብሔርን ማወቅ ገለል ሊያደርጉት/ቸል ሊባል/ የማይቻል እውነታ ስለሆነ ነው።</u>

ስለ እግዚአብሔር ስናስብ በመጀመሪያ ወደ አዕምሮአችን የሚመጣው ሐሳብ ምንድር ነው? ቶሎ የሚታየን ሐሳብ የትኛው ነው? እርቀቱ፥ ፈራጅነቱ፥ ኃያልነቱ፥...? ለአንዳንዶቻችን ደግሞ ቅርበቱ፥ ፍቅሩ፥ ርኅራሄው፥ መሐሪነቱ...? በሁለቱም አቅጣጫ ያሉት የእግዚአብሔር ባሕሪያት ናቸው። ይሁን እንጂ ለየብቻ ከታሰቡ ስለ እግዚአብሔር ያለን ግምት የተሳሳተ ይሆናል።

እግዚአብሔር እንደ አዲስ ኪዳኑ ያህል ቅርብ ሆኖ በማይገመትበት በብሉይ ዘመን እንኳን፤ ርቀቱና ቅርበቱ እንደማይጣሉ በቃሉ ተናግሯል። "*እኔ ለዘላለም የምኖር ከፍ ያልኩ ቅዱስ አምላክ ነኝ። እኔ ከፍ ባለና በተቀደሰ ሥፍራ እኖራለሁ ይሁን እንጂ መንፈሳቸውንና ልባቸውን ለማደስ ተጸጽተው ንስሐ ከሚገቡና ከትሁታን ሰዎች ጋር እገኛለሁ*" ይላል (ኢሳ.57፥15)። እግዚአብሔር በሁለቱም ባሕሪው ሊታሰብ ይገባል፤ በቅርበቱም በርቀቱም። ይህ ለሃይማኖታዊ ሁለንተናችን ወሳኝ ነው። ማንነታችንም የሚለካው ከዚሁ ቅደመ- ግንዛቤ አንጻር ነው። ጌታም ባስተማረን ፀሎት ላይ ርቀትና ቅርበት ሲታረቁ እንመለከታለን። "በሰማያት የምትኖር አምላካችን ሆይ" ከማለት ፋንታ "በሰማያት የምትኖር *አባታችን* ሆይ" ይላል። በሰማይ ሆኖ በምድር ላሉት አባት መሆኑ ታላቅ መንፈሳዊ ሚስጢር ነው። ከዚህም ሌላ "*ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን*" ይላል። የእግዚአብሔር ርቀትና ቅርበት በዕርቅ ካልታዩ ሰማይና ምድር ተራርቀው ይቀራሉ።

በዓለም ላይ ያሉ የማንኛውም ሃይማኖት አቅምና መንፈሳዊ ጥልቀት የሚወሰነው ስለአምላክ ካለው ስስና ጥልቅ ዕውቀት አኳያ ነው። ይህ ችል የማይባል እውነታ ነው። ስለዚህ በዚህ ዘመን በቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ቆሞ ያለ ታላቁ ጥያቄ የእግዚአ ብሔር ዕውቀት ጥያቄ ነው። ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን እግዚአብሔርን እንዴት ነው የሚያውቁት? ቤተ ክርስቲያንና አገለልጋዮቿ እግዚአብሔርን እንዴት ነው የሚያውቁት? ይህ በቸልታ የማይታለፍ ወሳኝ ጥያቄ ነው።[49]

የአንድ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጥንካሬ የሚለካው ባሏት የምእመናን ብዛትና የሞቀ የአምልኮ ፕሮግራም ወይም በሌሎች ውጫዊ በሆኑ ነገሮች ሳይሆን አባሎቿና መሪዎቿ ባላቸው የእግዚአብሔር ዕውቀት መጠን ነው። ለሰው ሁሉ ወሳኙ ጥያቄ አንድ ሰው ምን አወራ? ወይም ምን አደረገ? የሚለው ሳይሆን ሰው ሁሉ በልቦናውና በኑሮው እግዚአብሔርን እንዴት ነው የሚያስበው? እንዴትስ ነው የሚገልጠው የሚለው ጥያቄ ነው። ምክንያቱም የምንላቸውም ሆኑ የምናደርጋቸው ነገሮች እግዚአብሔርን እንዴትና እስከምን ድረስ እንደምናውቅ ይጠቁማሉ። ነፍሳችን የምታዘነብለው ልቦናችን ወደቀረጸው የእግዚአብሔር/የአምላክ/ ዓይነት ነው። አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር በምታስብበት ጊዜ ወደ አዕምሮህ የሚመጣው ምንድን ነው? ተብሎ ለሚጠየቀው ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ፣ እግዚአብሔርን የማወቁ ሁኔታ ሊለካ ይችላል። ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ደግሞ የሰዎችን የእግዚአብሔር ዕውቀት የምንፈትሽበት ሳይሆን እያንዳንዳችን ለራሳችን በቸልታ የማናልፈው ጥያቄ ነው።

ነገ ቤተ ክርስቲያን የት እንደምትደርስ መገመት የሚቻለው ዛሬ አባሎቿና መሪዎቿ ስለ እግዚአብሔር ባላቸው የዕውቀት መጠን ላይ ነው። ሃይማኖታችንም ትክክል ነው ማለት የምንችለው እግዚአብሔርን በትክክል ስናውቅ ብቻ ነው። የአንድ ቤተ ክርስቲያንም ትክክለኛነት የሚወሰነው ካላት ትክክለኛ የአምላክ ግንዛቤ አንጻር ነው። በእኛም የሚታየው ምግባር እግዚአብሔርን ምን ያህል እንዳወቅነው ይገልጻል። እነዚህ ጉዳዮች ክርስትናን አምርሮ ሊከተል ለሚወድ ሁሉ በቸልታ የሚታዩ አይደሉም። ለአንድ ሕንፃ መሠረቱ አስፈላጊ የሆነውን ያህል ለአምልኮአችንም ሆነ ለሃይማኖታችን፥ ትክክለኛው





የእግዚአብሔር ዕውቀት እንደዚያው አስፈላጊ ነው። መሠረቱ ያልሰመረ ሕንፃ እንደሚፈራርስ ሁሉ የሰመረ የእግዚአብሔር ዕውቀትም ከሌለን፥ የተፍረከረከ መንፈሳዊ ሕይወት ይኖረናል። ስለዚህ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ዕውቀት ለሰው ሁሉ ግድ ነው። በቸልታ የሚታለፍም ጉዳይ አይደለም።

በሕንድ አገር ጥንታዊ የሆነ "ሀሪ ክሪሽና" የሚባል ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች አሉ። ይህ ሃይማኖት ሳይንሳዊ ተፈጥሮ እየተሰጠውና ዘመናዊ የሆነ ካባ እየለበሰ በአሁኑ ጊዜ በአውሮፓና በአሜሪካ ተቀባይነት አግኝቷል። በዚህ እምነት መሰረት አሁን ያለው የተፈጥሮ እውነታና ነባራዊው ዓለም ቅዠት ወይም ህልም ነው ይላሉ። በዓለም ላይ የሚታዩት ለውጦችና ነውጦች ሁሉ አምላክ ተኝቶ የሚያልመው ህልም ነው ይላሉ። ስለዚህ አንድ ቀን ይህ አምላክ ሲባንን፥ የሚታየው ዓለም ሁሉ እንደጉም በንኖ ይጠፋል ይላሉ። እንደዚህ ሃይማኖት ከሆነ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል/መልክ/ የተፈጠረና የአምላክም የእጁ ሥራ ሳይሆን፥ ሁላችንም ብንሆን ቅዠቱ ነን ማለት ነው። አምላክን እንዲህ ስለሚያውቁት ሃይማኖታቸውም እንዲህ ነው ማለት ነው። ዛሬ እግዚአብሔር አምላክን እንዴት ነው የማውቀው? የሚለው ጥያቄ እያንዳንዳችን ልንመልሰው የሚገባን ጥያቄ ነው ።

## 2.3.<u>እግዚአብሔርን ማወቅ የማንነታችን መታወቂያ ስለሆነ ነው።</u>

የአንድ ሰው ትክክለኛ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የሚለካው ይህንን ችል የማይባል የእግዚአብሔር ዕውቀት በትክክል ሲረዳ ብቻ ነው። ለእግዚአብሔር ያለን ግንዛቤ ትክክለኛ ሲሆን ትክክለኛ ሥነ-መለኮት ይኖረናል። ከትክክለኛ ሥነ-መለኮት ደግሞ ትክክለኛ ሃይማኖት ይወጣል። በምድር ላይ የምናያቸው አብዛኛዎቹ የስህተት ሃይማኖቶች፥ እንዲሁም እያንዳንዱ በሰዎች የሚፈጸም ኃጢያት ምክንያቱ ቢመረመር ሰዎች እውነተኛውን አምላክ ባለማወቅ ወይም ስለ እውነተኛው አምላክ የተሳሳተ አመለካከት በመያዛቸው እንደሆነ እንገነዘባለን። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለ እግዚአብሔር ዕውቀት እንዳላቸውና ይህንንም ዕውቀት ያገኙበት የራሳቸው የሆነ የአምላክ የመገለጥ ምንጭ እንዳላቸው ይናገራሉ።[50]

ለምሳሌ እስላሞች:- የአምላክ ዕውቀት እንዳላቸው ይህንንም ዕውቀት ያገኙት ከቁርአን እንደሆነ ይናገራሉ ሃይማኖቱ የተሳሳተ ነው የምንለው በዋነኛነት የመገለጡ ምንጭ የተሳሳተ ስለሆነ ነው:: አይሁዶች:- የእግዚአብሔር መገለጥ በሙሴ መጽሐፍ ብቻ ነው ይላሉ:: ስለዚህ ይሁዲነት ግማሽ ዕውቀት ያለው ሃይማኖት ነው:: ባሕላዊ እምነቶች:- ብዙ አማልክት አሏቸው፤ ይህም ለእግዚአብሔር የላቸውን የተሳሳተ ዕውቀት ያሳያል:: የይሖዋ ምስክሮች ነን የሚሉት:- የእግዚአብሔርን በሥጋ መገለጥ አይቀበሉም ያከረረ ጸረ ሥላሴ አቋም አላቸው:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት:- የእግዚአብሔር መገለጥ የሚገኘው በሰማንያ አንድ መጻሕፍት እንዲሁም በሌሎች ተጨማሪ የገድል መጻሕፍት ነው ያላሉ:: ስለዚህ የሥልጣን ምንጫችን አንድ ዓይንት ስላልሆነ እምነታችንም አንድ ዓይነት አይደለም አንስማማም:: ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በስድሣ ስድስቱ መጻሕፍት በብሉይና በሐዲስ እንደሆነ እናምናለን:: እንግዲህ ከዚህ አኳያ እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የአንድ ሰው ሃይማኖታዊ መለያ ስለሆነ ነው::

አንድ ሰው "አምላክን የምታውቀው እንዴት ነው?" ተብሎ ለሚጠየቀው ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ በመነሳት ሃይማኖታዊ መለያው ይታወቃል:: "አል ዋሂደክ ወላ ሸሪክ ለክ" ሲል ቃሉ አረብኛ ስለሆነ ሳይሆን የአባባሉ ትርጉም ከሥላሴ ትምህርት ጋር ስለሚጋጭ እስልምና እግዚአብሔር አምላክን እኛ እንደ ምናውቀው አያውቀውም እንላለን:: "ማሪያምን ያመነ እግዚአ ብሔርን የለመነ ይድናል" የሚል ጽሑፍ መኪና ውስጥ ወይም ቤት ውስጥ ተለጥፎ ብናይ÷ ቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው እንላለን፤ ምክንያቱም በዚህ እምነት መሰረት ሃይማኖትና ማሪያምን ነጥሎ ማየት ስለማይቻል:: ደግሞም አንድ ሰው አብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ የተገለጠው አንዱ ክርስቶስ ነው አንጂ አንድ አምላክ በሦስት አካላት የለም፤ ብሎ ሲያስተምር ብናገኘው÷ ይህ ሰው የሐዋርያት ቤተክርስቲያን /OnlyJesus/ አባል እንደሆነ እናው ቃለን::





ነገር ግን ብዙ ጊዜ በእኛ በወንጌል አማኞች ዘንድ፥ ይህንን ዕውቀት አስመልክቶ በግልጽ የሚታይ ስህተት አለ:: ራሳችንን ከሌሎች የምንለይበት መንገድ እኛ እግዚአብሔርን የምናውቅበት መንገድ የተለየ በመሆኑ ሳይሆን "በምናደርጋቸውና በማናደርጋቸው" ("The dos and The donts") ነገሮች ነው:: "እኛ ሌሎች የሚያደርጉትን ክፉ ነገሮች አናደርግም፤ ሌሎች ደግሞ እኛ የምናደርገውን መልካም ነገር አያደርጉም::" በማለት ከሌሎች የምንለየው በማድረግና ባለማድረግ እንደሆነ እንገምታለን:: ነገር ግን እነዚህ የሚደረጉና የማይደረጉ ነገሮች የክርስትናችን መለያ ካደረግናቸው በጣም አደገኛ ነው:: ምክንያቱም እንደሚከተለው ይሆናል::

አንዳንድ እኛ የምናደርጋቸውን መልካም ሥራዎች፤ በሌሎች የሃይማኖት ክፍል ውስጥም ያሉ ሰዎችም ያደርጓቸዋል:: በተቃራኒውም እኛ የማናደርጋቸውን ክፉ ነገሮች የማያደርጉም የሌላ ሃይማኖት ሰዎች አሉ:: ለምሳሌ እኛ አስካሪ መጠጥ አንጠጣም ስለዚህ ክርስቲያኖች ነን እንላለን:: በጣም አክራሪ የሆኑ ሙስሊሞችም አይጠጡም፤ ስለዚህ እኛ ሙስሊሞች ወይም እነርሱ ክርስቲያኖች ሊሆኑ ነው ማለት ነው:: እኛ አጭር ቀሚስ ስለማንለብስ /ፓንክ ስለማንቆረጥ/ ክርስቲያኖች ነን እንላለን:: ስለዚህ ሌሎች ረጅም ቀሚስ የሚያደርጉ ፓንክ የማይቆረጡ ሁሉ ክርስቲያኖች ሊሆኑ ነው:: ነገር ግን የእኛ መለያዎች እነዚህና መሰል ውጪያዊ መለኪያዎች አይደሉም:: ዋነኛ የማንነታችን መታወቂያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን እግዚአብሔርን እንዴት እንረዳዋለን? የሚለው ጥያቄ ላይ ማረፍ አለበት:: ሁሉም ሰው በየቋንቋው እንደምን አደርክ? ተብሎ ቢጠየቅ (ሌሊት በአካባቢያችን ድቤ ሲቀጠቅጥ የሚያድረውን ጭምር) "እግዚአብሔር ይመስገን" ማለቱ አይቀርም:: ይህንን ማለቱ ግን አንድ ዓይነት ነን ማለት አይደለም:: ትልቁ ጥያቄ "የትኛው እግዚአብሔር ይመስገን?" የሚለው ነው::

## 2.4. እግዚአብሔርን ማወቅ የሚያመጣው ውጤት ጠቃሚ ስለሆነ ነው።

- ኃይለኛና ብርቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን የሚቻለው በሕይወታችን ዘመን ሁሉ እርሱን በጽኑ ስናውቅ ነው።

አምላካቸውን በትክክለኛው የልብ ሐሳብ የሚያውቁ ሰዎች እጅግ ብርቱዎች ናቸው። ስለዚህም የዓለምን ክፋት በጽኑ ይቃወማሉ። ኃይለኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን የምንችለው በትክክለኛው ሐሳብና ስሜት በትክክለኛም ዝንባሌ እርሱን ስንፈልግ ብቻ ነው። ብዙዎች በመከራ መጽናት አቅቶአቸው እምነታቸውን ሲክዱ እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች ግን ይበረታሉ። *"ንጉሡ ቀደም ብሎ ሃይማኖታቸውን የካዱትን ሁሉ በማታለል የእነርሱን ድጋፍ ያገኛል፤ እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች ግን ይበረታሉ፤ ይህንንም ንጉሥ አጥብቀው ይቃወማሉ"*/(ዳን.11÷32)።[51] በኮሚኒስት ቻይና ቤተክርስቲያን እንዳትሞት ታላቅ ተጋድሎ ካደረጉት ሰዎች መካከል አስተማሪነት ባላቸው መጻሕፍቱ የሚታወቀው ዋች ማን ኒ የተባለ ሰው፥ በምስክርነት ሕይወቱ ስላስቸገራቸው ኮሚኒስቶች ምላሱን ቆረጡት እግዚአብሔር ግን አስደናቂ የጽሑፍ ጸጋ ሰጠው። ከዚህም የተነሳ በስብከቱ ከደረሳቸው ሰዎች ይልቅ በጽሑፍ የደረሳቸው ሰዎች በለጡ። በመከራ የሚጸኑ እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው። እግዚአብሔርን የማወቅ ሌላ ጠቃሚ ውጤት ደግሞ የሚከተለው ነው።

- ደፋር የእምነት አርበኛ መሆን የሚቻለው እግዚአብሔርን በማወቅ ብቻ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ቀላልና ሊጎዱ የሚችሉ የማይመስሉ ነገሮች እምነታችንን ይፈትናሉ። አንዳንዴ ደግሞ በሕይወት መኖራችንንና አለመኖራችንን የሚወስኑ ነገሮች ይገጥሙናል። የላላውም ሆነ የጠበቀው ፈተና ዋና ዓላማው እኛን ከእምነታችን ለመፈንቀል ነው። ስለዚህ የላላውም ሆነ የጠበቀው ፈተና ከእምነታችን እንዳይፈነቅለን እግዚአብሔርን በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል።





**ከክ.ል.500 ዓመት በፊት በባዕድ አገር በምርኮ የተጋዙትን ሦስት ወጣቶች** የገጠማቸው ይኸው ነው። ***"ንጉሡ ናቡ ከደናፆር ላቆመው የወርቅ ምስል እንድትሰግዱ ታዛችኋል በምድር ላይ ተደፍቶ የማይሰግድ*** *ቢኖር በሚነደው የእሳት ነበልባል ውስጥ* ***ወዲያኑ ይጣላል"*** የሚል የንጉሥ ትዕዛዝ ደረሳቸው (ዳን.3÷5)። **ቢሰግዱ በሕይወት** ሊኖሩ÷ ባይሰግዱ እንደ እንጨት ሊማገዱ **ምርጫ ቀረበላቸው**። እነዚህ ወጣቶች እግዚአብሔርን ከመከራቸው **ቀን በፊት የሚያውቁ** በመሆናቸው ደፋር ነበሩ። *"ባትሰግዱ* ***ከእጄ የሚያድናችሁ*** *የለም"* የሚለውን የንጉሥ ዛቻ ሳይፈሩ ***"ንጉሥ ሆይ*** *በዚህ ጉዳይ ላይ ራሳችንን የምንከላከልበት መልስ* ***ልንሰጥህ*** *አንፈልግም፤ እኛ የምናገለግለው አምላክ ከዚህ* ***ከሚነደው*** *ከእሳት ነበልባልም ሆነ ከአንተ እጅ ሊያድነን* ***ይችላል***። *ንጉሥ ሆይ እርሱ ሊያድነን ፈቃዱ ባይሆን እንኳ* ***አማልክትህን*** *እንደማናመልክና ላቆምከውም የወርቅ ምስል* ***እንደማንሰግድ እወቅ"*** አሉት (ዳን.3÷18)።

ሰዎች እግዚአብሔርን ባወቁት መጠንና ደረጃ ስለስሙ ዋጋ ይከፍላሉ። እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ስለስሙ ምንም ዋጋ አይከፍሉም። እግዚአብሔርን በጥቂቱ የሚያውቁ ሰዎች ስለ ስሙ በጥቂቱ ዋጋ ይከፍላሉ። እግዚአብሔርን በደንብ የሚያውቁ ሰዎች ስለ ስሙ ሕይወታቸውን÷ ስማቸውንና ክብራቸውን ይከፍላሉ። ዛሬ ግን የሚያሳዝነው ማንም በአዋጅ ሳያስፈራራን የምንሰግድላቸው ነገሮች እጅግ ብዙ ናቸው። ይህም እግዚአብሔርን በሚገባ ካለማወቃችን የተነሳ የሚታይብን ባሕርይ ነው። እግዚአብሔር ራሱን በሚገባ የገለጠላቸውና በእርሱም ተማምነው የሚሄዱ ሕዝብ ይስጠን!!

## 2.5. እግዚአብሔርን ማወቅ ፈቃዱን ለማወቅ ጠቃሚ ስለሆነ ነው።

ሕይወት በሁሉም ሰው ዘንድ እኩል አቅጣጫዋን ጠብቃ የምትሄድ ባለመሆንዋ÷ ሰዎች ነገ ምን እንደሚሆን ለማወቅ የሚነግራቸውን ፍለጋ ይቅበዘበዛሉ። ከዚህም የተነሳ ነገ ስለሚሆነው ነገርና በሕይወታችሁ ወደፊት ስለሚከናወነው ነገር እንንገራችሁ ባዮች በጣም ብዙ ናቸው። በየጋዜጣው ጀርባ ያለው የኮከብ ቆጠራ÷ እኛ የነገን ሕይወታችሁን እንንገራችሁ÷ ስለ ኑሮአችሁ÷ ስለ ሥራችሁ÷ ስለ መውጣት መግባታችሁ÷ እኛ

እንወስንላችሁ የሚሉ ዘመናዊ ጋዜጦች ብዙ ናቸው:: "ይሄን ያመጡት ዘመኑንና ዲሞክራሲውን ተጠቅመው የሚነግዱ ናቸው" ማለት እንዳንችል፥ ጥንትም ቢሆን አሁን በአገራችን የነገን ጉዳይ እንነግራችሁአለን የሚሉ ሟርተኞች፥ ሞራ ገላጮችና የቡና አተላ ጠንፋፊዎች ሞልተዋል::

ይሁን እንጂ የማንም ሰው ነገና የወደፊት የሕይወት አቅጣጫ በሟርተኞች ንግርት፥ በሰማይ ከዋክብት ላይና በቡና አተላ ጥንፋፊ ውስጥ አይደለም:: የሰው ልጅ ሕይወት *"ትንፋሽንና መንገድን"* ሁሉ በእጁ በያዘ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ነው::

ዛሬ የብዙዎቻችንን ሕይወት የአቅጣጫ ጥያቄ ወጥሮ የያዘበት ወቅት ላይ የምንገኝ ሰዎች ነን:: በሕይወት መስቀልኛ መንገድ ላይ ቆመን በውሳኔ አጣብቂኝ ውስጥ የገባንባቸው ቀናት ጥቂት አይደሉም:: ሌሎች ሰዎች እንደሚመስላቸውና እንደወደዱ እንደሚወስኑት፥ ውሳኔ ለአማኝ ቀላል አይደለም:: ምክንያቱም አማኝ በሚወስነው ውሳኔ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳይተላለፍ ስለሚጠነቀቅ ነው:: እንግዲህ አማኝ በሕይወቱ የሚገጥሙትን ልዩ ልዩ የውሳኔ ጥያቄዎች መመለስ የሚችለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲያውቅ ነው:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ራሱን እግዚአብሔርን ከማወቅ ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው::

መቼም ለአማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ የበለጠ ምንም ነገር የለም:: ብዙ አማኞች እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ከመፈለጋቸው የተነሳ "ጌታ ሆይ ፈቃድህን አሳውቀኝ?" ይላሉ:: "ጌታ ሆይ ደስ አሰኝህ ዘንድ እንዳደርግ የምትወደው ምንድር ነው?" ይላሉ:: ነገር ግን እግዚአብሔርን ከትናንቱ ዛሬ እያወቅነው ስንመጣ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ መልስ ያገኝልናል:: አምላካችንን ማወቃችን እየጨመረና እያደገ ሲመጣ የእርሱ ፈቃድና ሐሳብ ምን እንደሆነ ማወቅ እንጀምራለን:: ነገሮችን ሁሉ እርሱ እንደሚያይ እያየን ፈቃዱን የምናውቀው እግዚአብሔርን ስናውቅ ነው:: "ፈቃደህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን" የሚለው ጸሎት ሕይወት የሚኖረው እግዚአብሔርን በሚያውቁ ሰዎች ውስጥ ነው:: እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ደግሞ





በየደቂቃው በእርሱ መገኘት ውስጥ መሆን ማለት ስለሆነ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ያሉ ሰዎች ደግሞ ሁልጊዜ ፈቃዱን ይፈጽማሉ::

## 3.እግዚአብሔር የሚታወቀው እንዴት ነው?

### 3.1.<u>እግዚአብሔር የሚታወቀው በቃል ኪዳኑ ነው::</u>

ከሠላሳ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ንጉሣዊ አገዛዝ፥ በመሬት ሥሪቱና በአስተዳደሩ በኩል የነበረው የሥልጣን ተዋረድ፥ በአንድ ተራ ገበሬና በንጉሡ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደ ሰማይና ምድር አድርጎታል :: ይህ ማለት ግን ከዚያ በኋላ ያሉት መሪዎች ከተራው ሕዝብ ጋር እጅግ የተቀራረቡ ናቸው ለማለት አይደለም::

ከጤናውና ከአንጡራ ጉልበቱ በቀር የኔ ነው የሚለው ንብረት የሌለው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ጭሰኛ በመባል ይታወቅ የነበረው ክፍል ሲሆን የሚኖረው ለሰው ተቀጥሮ አለያም የሰው መሬት ተከራይቶ በ"ግረስ፥ ከምርቱ ሲሶ/አሥራት እየከፈለ ነው:: ይህ ሰው "ገባር" ተብሎም ሊጠራ ይችላል:: ሌላው ክፍል ደግሞ "ባለርስት" ወይም "መልከኛ" በመባል የሚታወቅ በመሬቱ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ነው:: በእርሱ ላይ ደግሞ ለተወሰነ ክልል እንደ ንጉሥ የሆነ "ባላባት" የሚባል አለ:: እንግዲህ ይህኛው ቅደም ተከተል በአብዛኛው የመሬት ሥሪቱን የሚመለከት ነው::

ከዚህ ሌላ በንጉሡ ሥልጣንና ሹመት ውስጥ ከታች "ምክትል ገዢ" ወይም "ምስለኔ" የሚባል ሲኖር፥ ቀጥሎ "ወረዳ ገዢ"፥ ከዚያም "አውራጃ ገዢ"፥ ከዚያም "ጠቅላይ ገዢ"፥ ቀጥሎም "አገር ግዛት"፥ ከዚያም "ጠቅላይ ሚኒስትር" ብሎ በመጨረሻ "ንጉሠ ነገሥት" ይላል:: እንግዲህ በየመሀሉ እንደ "ሊጋባና ራስጌ ቤት" ያሉትን ቅርንጫፍ ሹመቶችን ትተን፥ ለጭሰኛውና ለገባሩ የንጉሡ ርቀት ምን ያህል እንደሆነ መመልከት እንችላለን::

ከዚህም የተነሳ የመሬት ክርክሮችንና የመብት ጉዳዮችን ለማስፈጸም ይህንን ረጅም ሰንሰለት ለመበጠስ የማይቻል ነው:: ስለዚህ በየማህሉ ያለው የአማላጅ ሥርዓት ለብዙዎች ግድ ነበር:: አንደኛውን አማላጅ ሳይዙ ወደ አንደኛው መሄድ ከቶውንም የማይቻል ጉዳይ ነው::[52] ይህ የአስተሳሰብ ተጽዕኖ በአገሪቱም ሃይማኖት ላይ በእጅጉ ሲንጸባረቅ ይስተዋላል:: ንጉሡ ይህንን ያህል ከራቀ እግዚአብሔርንም ከእርሳቸው አቅርቦ ለማየት ሕዝቡ አይሆንለትም:: ስለዚህ "*መዳን የሚገኘው በእምነትና በጸጋ ብቻ ነው*" የሚለውን የወንጌል መካከለኛ መልዕክት ለማመን ለብዙዎች ቀላል አልሆነም:: አንዳንዶቹ እንኳንስ የሰማዩን፥ የምድሩን ጌታ ልንደርስበት ቸግሮናል፣ በሚል ምሳሌአቸውን ይደረድራሉ::

እንግዲህ በእንዲህ ዓይነት እግዚአብሔርን እሩቅ አድርጎ በሚያስብ ኅብረተሰብ ውስጥ ስንኖር፥ "እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው እንዴት ነው?" ለሚለው ጥያቄ ምን መልስ አለን? ይህንን ለመመለስ አስቀድመን ከዘፍ. ምዕ.1-11 ድረስ ያለውን ታሪክ መቃኘት ይኖርብናል::

በእነዚህ ምዕራፎች ላይ በእግዚአብሔርና ለክብሩ እንደ ምሳሌው በሰራው የሰው ልጅ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ጥቁር የኃጢያት ቀለም ሲደፋ እንመለከታለን:: በምዕራፍ ሦስት ላይ በተፈጸመው የሰው አለመታዘዝ አዳምና ሄዋን ከበረከት ሲባረሩ፥ በምዕራፍ አራት ደግሞ በምድር ላይ የመጀመሪያው የሰው ልጅ የማኅፀን ፍሬ የሆነው ቃየል፥ በምድር ላይ ከሰው ልጅ የመጀመሪያው ነፍስ ገዳይ ሲሆን እንመለከታለን:: በምዕራፍ ስድስት ላይ ደግሞ "*እግዚአብሔር ዓለምን ተመለከተ የተበላሸች እንደሆነችና በውስጧም ያሉት ሰዎች ሁሉ በክፋት እንደሚኖሩ አየ*" (ቁ12):: ስለዚህ በምዕራፍ ሰባት ላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር በዘመኑ በጽድቅ ያገኘውን ኖኅንና ቤተሰቡን አስቀርቶ "*በምድር ላይ የሚኖር እስትንፋስ ያለውን ነገር ሁሉ*" በውኃ ደመሰሰው (ቁ.12):: ከሞት ከተረፈው የኖኅ ቤተሰብ የተገኘው ትውልድ ደግሞ በምዕራፍ 11 ወደ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ለማለት የባቢሎንን ግንብ ሰራ :: ይህም እግዚአብሔርን አስቆጣው ቋንቋቸውንም ከፋፈለው በምድርም በተናቸው::





በጠቅላላው በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ሰው ለራሱ በተተወ ቁጥር ከእግዚአብሔር ሲሸሽና እግዚአብሔርን ሲያሳዝን እነመለ ከታለን:: ስለዚህ ያለማንም አነሳሽነት እግዚአብሔር ራሱ ሁኔታው በሰው ልጅ ማንነት ላይ የማይወሰን ቃል ኪዳኑን በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም አመጣ:: ይህ ኪዳን "በሰው ልጅ ማንነት ላይ የማይወሰን ነው" ስንል ኪዳኑ ከመገባቱ በፊት ያለውን የሰው ማንነት አይጠይቅም ማለታችን ነው::

ለመሆኑ ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ቃል የመዝገበ ቃላቱ ትርጉም "*የመተማመኛ ቃል ፥ የእርቅ ምልክት ሀሰት የሌለበት ጸንቶ የሚኖር ቃል*" ማለት ነው::[53] ኪዳኑን በሚገቡት በሁለት ቡድኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ሲሆን፥ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ አንደኛው ወገን ለአንደኛው የሚወጣው ግዴታ አለ::

ስለዚህ "*በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት ኃጢያት ባለማቋረጥ በማበላሸቱ ሰው የእግዚአብሔርን በረከት እንዴት ማግኘት ይችላል?*" የሚለው ጥያቄ በዘፍ.12፥1-3 ባለው ቦታ ላይ መልስ ያገኛል:: መልሱም "እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሚገባው ኪዳን መሠረት ነው" የሚል ይሆናል:: "*እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው:- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ :: ታላቅም ሕዝብ አደርግሃለሁ ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረ ዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን ፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፤ የሚረግሙ ህንም እረግማለሁ ፤ የምድርም ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ:: አብራምም እግዚአብሔር እንደተናገረው ሄደ...*"

በጥንት ቅርብ ምሥራቅና በአካባቢው ባሉት አገሮች ሁለት ዋነኛ የኪዳን ዓይነቶች ነበሩ:: አንደኛው፥ በሁለት እኩያሞች መካከል የሚደረግ "*እኩላዊ ኪዳን*" (***Parity Covenant***) የሚባል ሲሆን ይህም በ1ሳሙ. 18፥3፤ 1ነገ. 5፥12 የተገለጸው ዓይነት ነው:: በእንዲህ ዓይነቱ ኪዳን ውስጥ ሁለቱም ቡድኖች በጋራና በእኩል ደረጃ አንድ ዓይነት ግዴታዎችን ለመወጣት ይስማማሉ:: ሁለተኛው የኪዳን ዓይነት ደግሞ "*ሱዘራዊ*" ***(Suzerain)*** በመባል የሚታወቀው ነው:: ይህ ዓይነቱ ኪዳን የእኩያሞች ኪዳን

አይደለም። ይህ በጥንት ቅርብ ምሥራቅ አገሮች በጌታና በባሪያ መካከል የሚደረግ ሥምምነት ነው። በዚህ በሱዘራዊ ኪዳን ውስጥ ቃል ለሚገባለት ሰው የሚሆኑትን ነገሮች የሚወስነው ራሱ ኪዳኑን መስራች የሆነው ጌታው ነው። ኪዳኑን የቀረበለት ሰው ቢፈልግ ሊቀበል ባይፈልግ ላይቀበል ይችላል።[54]

በዚህ ኪዳን መሠረት ሁለቱ የኪዳን አባላት ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው በመካከላቸው የአማላጅ ሥርዓትን የሚጋብዝ ነገር የለም። ንጉሡ ከባሪያው ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ይህ ኪዳን የመነጨው ከራሱ ከንጉሡ ከእግዚአብሔር በመሆኑ ኪዳኑ የተገባለት ሰው የማንነቱ ሁኔታ ለመባረኩ አይወስነውም። ይሁን እንጂ ኪዳን ተቀባዩ ኪዳን ሰጪው ንጉሡ እግዚአብሔር የገባለትን ተስፋ ለመቀበል በእግዚአብሔር መታመን ግዴታው ነው። እንግዲህ በኪዳን ተጋቢዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ቀጣይነቱ የሚወሰነው አንዳቸው ላንዳቸው ባላቸው መተሳሰብና መስጣጣት ላይ ነው። እንግዲህ በዚህ መሠረት ራሱን ዝቅ አድርጎ ከሰው ልጆች ጋር ቃል ኪዳን በመግባት ራሱን የገለጠውን እግዚአብሔር በሚገባ ለማወቅ ሌላ ሦስት ወሳኝ ነገሮች ያስፈልጉናል።

## 3.2. <u>እግዚአብሔር የሚታወቀው በሕይወታችን ላይ ጌታ ሲሆን ነው።</u>

*መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቋንቋዎች ያሉት የእግዚአብሔር የሁለቱ ኪዳናት ስሞች ማለትም፡- "ያህዌ" የሚለው* የእብራይስጥ *መጠሪያና "ኩሪዮስ" የሚለው* የግሪክ *መጠሪያ ሁለቱም የሚያመላክቱት "ጌትነት"* የሚለውን ሐሳብ ነው። ለዚህም በዘዳ.6፥4-5 እንዲህ ተብሎ ተጠቅሶአል *"እሥራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።"* ይህንንም ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.22፥37 ላይ እንዲህ በማለት ተናግሮታል። *"<u>ጌታ አምላክህን</u> በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ"* ከዚህም ሌላ በሮሜ 10፥9 ላይ *"<u>ኢየሱስ ጌታ</u> እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ"* ይላል። ደግሞም በፊሊ. 2፥11 ላይ ስለ ክርስቶስ





ሲናገር እንዲህ ይላል። *"... መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር <u>ኢየሱስ</u> <u>ክርስቶስ ጌታ</u> እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።* ይላል።[55]

በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱሳዊው የኪዳን ግንዛቤ የሚያሳየን የጌታና የባሪያ ግንኙነት ነው። ይህንን በሰፋ መልኩ ስንመለከተው የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ የዚህ ዓይነቱ ኪዳን ተገዢ ነው። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ጌታ ነው።[56]

ስለዚህ በዚህ ትምህርታችን ውስጥ የምንጠይቀው ወሳኝ ጥያቄ ፡- ዛሬ የቃል ኪዳኑ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ጌትነቱ እንዴት ነው? ከእርሱ ጋር ኪዳን ከተጋባን በኋላስ ለእርሱ ያልተሰጠና የተሰወረ ወይም በከፊል የተደበቀ ሕይወት አለን ወይ? እንዲህ ከሆነ የኪዳኑን ጌታ ለማወቅ የምናደርገው ሙከራ ሁሉ ከንቱ ይሆናል። ከዚህ ጌታ ጋር በኪዳን መገናኘት ማለት ከሕይወት ክልል አንዲት ቅንጣት ሳያስተርፉ ለጌትነቱ መስጠት ማለት ነው።

እኛ ወንጌል አማኞች ነን፤ በዚህም ከሌሎች የተለየን ነን፤ በምንልበት ጊዜ እግዚአብሔር በኪዳን ባለቤትነቱ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ በሁለንተናችን ላይ ጌታ ነው ማለታችን ነው። ግን አርገነዋል ወይ? ነው ዋናው ጥያቄ። እግዚአብሔር በነብዩ ሚልኪያስ ምዕ. 1፥6 ላይ ከጠየቀው ጥያቄ ነፃ የምንሆን ስንቶች ነን? *"እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ ፥ ልጅ አባቱን ፥ ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንኩ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንኩ መፈራቴ ወዴት አለ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"* መልሱ በየግላችን የሚመለስ ነው።

እግዚአብሔርን ለማወቅ የምንፈልግ ከሆነ በሁሉ ነገራችን ላይ እንዲሰለጥን ልንፈቅድለት ይገባል። እንደ አንድ ጌታ የነገሮቻችን ሁሉ ጌታ እርሱ ሊሆን ይገባል። በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን ስንከተለው እንደሚገባ ልናውቀው ያልቻልነው ለምንድር ነው? የሚለው ጥያቄአችን መልሱን ያሳረፈው *"እግዚአብሔርን በሕይወታችን ሁለንተና ላይ ጌታ ስላላደረግነው ነው።"* የሚለው እቅጭ ሐሳብ ላይ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ

ከፈለግን የጌታ ጌትነት እያንዳንዱ የሕይወት ክፍላችንን ሊነካው ይገባል።

የጌታ ጌትነት በተቀጠርንበት ሥራ ላይ ይታያል ወይ? በሰዎች ግምት ዝቀተኛ ከምንለው ከቤት ሠራተኛ እስከ መንግሥት ሹም ማለቴ ነው። ብዙ ጊዜ በሥራ ቦታችን ላይ ስብዓዊ ጌቶቻችንን ብቻ ስለምናስብ እነርሱ ሲኖሩ እንሰራለን እነርሱ ሳይኖሩ አንሰራም። የምንሰራው ሥራ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ እንደሆነ አስበን ብንሰራ የጌታን ጌትነት እናከብራለን።

አንድ ጊዜ በምሽት ብዙ ጥቅስ በተለጣጠፈበትና መንፈሳዊ መዝሙር በሚደመጥበት ሚኒ ባስ ታክሲ ውስጥ ተሳፍረን እሰኪሞላ እንጠብቃለን። ከሞላ በኋላም ረዳቱ ጥሪውን ቀጠለ። "ሞልቷል እንሂድ" ብሎ ከተሳፋሪዎች አንድ ሰው ጠየቀው "አይ ይህቺን አጭር መንገድ አሥራ አምስት ሰው ሳልጭን አልሄድም" መባለት ሾፌሩ መለሰ። "እንደሱ ማድረግ ከፈለግህ 'ኢየሱስ ጌታ ነው' የሚለውንና ሌሎቹን ጥቅሶች ገንጥለህ የምንሰማውንም መዝሙር በዘፈን ቀይረህ መሆን አለበት" በማለት ሰውየው መለሰለት። ለዚህ የሰጠውን መልስ ባልናገረው እመርጣለሁ። እንግዲህ ለእነዚህ ዓይነት አማኝ ባለታክሲዎች ክርስቶስ በንግዳቸው ላይ ጌታ አይደለም ማለት ነው።

አንድ አስተማሪ የሆነ ሰው ደግሞ እንዲህ ብሎ አጫወተኝ፡- "በአንድ ቤተ ክርስቲያን በዘማሪነት የሚያገለግሉ ሁለት ወጣቶች ፈተና ተቀጻድተው ከሰሩ በኋላ÷ ለምን እንዲህ አደረጋችሁ ብዬ ስጠይቃቸው÷ እንዴ ይሄ እኮ ፈተና ነው" አሉኝ ብሎ ተናገረ። እንግዲህ ለእነዚህ ወጣቶች ጌታ ጌታ የሚሆነው መዝሙር ሲዘምሩ እንጂ ጌታ ፈተና ሲሰርቁ ጌታቸው አይደለም። ነጋዴው እንዴ ይሄ እኮ ንግድ ነው ካለ÷ በጉምሩክ የሚሰራ ክርስቲያን ጉቦኛ ሆኖ እንዴ ይሄ እኮ ኑሮ ነው ካለ÷ ተማሪው እንዴ ይሄ እኮ ፈተና ነው ካለ÷ እግዚአብሔር በሕይወት ላይ ጌታ አልሆነምና እግዚአብሔርን ማወቅ አይቻልም።





የዛሬ 250 ዓመት ገደማ በእንግሊዝ አገር የነበረው ክርስትና ለክርስቶስ ጌትነት ሥፍራ መስጠቱን ትቷል ብለው ያመኑ ክርስቲያኖች÷ በጊዜው ገና በመቆርቆር ላይ ወዳለችው አሜሪካን ግዛት በመግባት÷ "The Puritan Movement" በመባል የሚታወቅ እንቅስቃሴ ጀመሩ። በእነሱ እምነት መሠረት እያንዳንዱ ሥራ ከእግዚአብሔር ለአማኙ የተሰጠ ጥሪ ነው። ገበሬው በግብርናው ላይ በአግባቡ ባይሰራ÷ የፋብሪካው ሰራተኛ በተቀጠረበት ሥራ በአግባቡ ባይሰራ÷ የመንግሥት ሹም ዋልጌ ቢሆን÷ በቦታው ባስቀመጣቸው እግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ይሰራሉ፤ ጌትነቱንም አላከበሩም፤ ብለው ያምናሉ። ስለዚህ Puritans በነበሩበት ዘመን የአሜሪካን ኤኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ መጥቆ ነበር ይባላል። ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ጌትነት ሥፍራ በሰጠ መጠን በአካባቢያችን ላይ እንኳ÷ አዎንታዊ ለውጥ የምናመጣ ሰዎች እንሆናለን። እግዚአብሔርን ለማወቅ ሌላው ወሳኝ ነገር ደግሞ የሚከተለው ነው።

## 3.3. <u>እግዚአብሔር የሚታወቀው በሕይወታችን ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ስንፈቅድለት ነው።</u>

ቀደም ብሎ በተመለከትነው ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ጌትነት÷ በእኛ ላይ ያለውን ባለቤትነት የሚያመለክት ሀሳብ ሲሆን÷ ሥልጣን ደግሞ በበላይነት ማዘዝንና አለቅነትን የሚያሳይ ሐሳብ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ጌታዬ ነው ብለን የምንጠራው ከሆነ÷ እንደ ባለሥልጣን ልንቆጥረውና ልንታዘዘው ይገባናል። በቃሉ ለተገለጠልን እግዚአብሔር የማንታዘዝ ከሆነ ቃሉ በእኛ ላይ ሥልጣን እንዲኖረው አልፈቀድንም ማለት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን ስለፈጠረን በፈቃዱም ኪዳን ስለገባልን÷ በእኛ ላይ ባለሥልጣን የመሆንና የማዘዝ መብት አለው። ይህንን መብቱን በእኛ ላይ እንዲጠቀም በፈቀድንለት መጠን÷ ራሱን ለእኛ ይለቅልናል። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን በማወቅ ጉዳይ ባይታወር አንሆንም። ለእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ትእዛዝ እንቢተኛ መሆን እግዚአብሔርን ከማወቅ ርቆ ሕይወትን ተቅበዝባዥ ማድረግ ነው።[57] እግዚአብሔርን ለማወቅ ወሳኝ የሆነው ሌላው ሀሳብ ደግሞ:-

### 3.4. <u>እግዚአብሔን ለማወቅ የሚቻለው ሁልጊዜ በፊቱ ስንገኝ ነው።</u>

ከእግዚአብሔር ኅልውና ውጪ ሆነንና ከእግዚአብሔር ርቀን እግዚአብሔርን ልናወቅ አንችልም። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለች ነፍስ የእግዚአብሔር ዕውቀት ራቧን መጥገብ አትችልም። መጽሐፍ ቅዱስ በያቆብ 4፥8 ላይ *"...ወደ እግዚአ ብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል"* ይላል። በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን የማወቅ ጉዳይ የራቀብን አንደኛው ምክንያት፥ እግዚአብሔር እገኝበታለሁ ባላለው ሥፍራ ስለምንፈልገው ነው። እግዚአብሔርን በተገለጠበት ዘላለማዊ ቃሉ ውስጥ ስንፈልገው እናገኘዋለን፤ እርሱም ይናገረናል። እግዚአብሔርን በጸሎት የቆይታ ሥፍራ ስንፈልገው እናገኘዋለን፤ እርሱም ለመንፈሳችን ይናገረናል። እግዚአብሔር ከቅዱሳን ጋር በምናደርገው ኅብረት ስንፈልገው እናገኘዋለን፤ በሌሎች ጸጋ ውስጥ ሆኖ ይናገረናል። ዛሬ ለብዙዎቻችን እግዚአብሔርን በቃሉ ሥር ቁጭ ብለን መፈለግ አይሆንልንም። ለአንዳንዶቻችን ደግሞ እግዚአብሔርን በጸሎት ሥፍራ መፈለግ አይሆንልንም። ለሌሎቻችን ደግሞ እግዚአብሔር በበርኸኝነትና በግለኝነት ይገኝ ይመስል ከቅዱሳን ኅብረት ተገልለን ለብቻችን እንፈልገዋለን።

እንግዲህ እግዚአብሔር የሚታወቀው እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄ፡- እግዚአብሔር የሚታወቀው በቃል ኪዳኑ ብቻ ነው የሚል መልስ ሲኖረን፥ ከእርሱ ጋር ኪዳን የገቡ ሰዎች ደግሞ፡- እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ላይ ጌታ ሊያደርጉ፥ በሕይወታቸው ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ሊፈቅዱለትና ሁልጊዜም በፊቱ ሊገኙ ይገባል።





# ክፍል ሦስት
# ፦ስለ እግዚአብሔር ማንነት

## 1.የእግዚአብሔር ኅልውና/መኖር

በመጽሐፍ ቅዱስ ገና የመጀመሪያ ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥር ላይ የምናነበው "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" የሚለውን ሐረግ ነው (ዘፍ.1፥1)። ከዚህ ቁጥር እንደምንረዳው ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት እግዚአ ብሔር መኖሩን ነው። ከዚህም የተነሳ ሁሉም ነገር፥ አንድም ሳይቀር ከእርሱ ኅልውና የመነጨ እንጂ በራሱ ህላዌነትን ያገኘ ነገር እንደሌለ እንረዳለን።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በጊዜው ለነበሩት ሰዎች የተጻፉት እግዚአብሔርን ያምኑ ዘንድ ሳይሆን እግዚአብሔርን ስላመኑ ነበር። ላላመኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖር ለማስረዳት የተጻፈ አይደለም፤ ይህ ችግራቸው አልነበረምና። የእግዚአ ብሔርን መኖር አምኖ በጠማማው መልኩ ለመቅረብና ለማምለክ ከመሞከር አልፎ የአምላክን ኅልውና ጨርሶ መካድ የዚያን ዘመን ትውልድ ባሕሪይ አልነበረም፤ ይህ አለ ብለን የምንለው አምላክ፥ ያልነበረበት ጊዜ አልነበረም፤ ወደ ፊትም የማይኖርበት ጊዜ አይኖርም ለእንዲህ አይነቱ አምላክ መኖር አጥናፈ ዓለሙ ምስክር ነው። "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" መዝ (19፥1)። ስለ እግዚአብሔር ኅልውና ስናወራ በራሱ ሕልው የሆነ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም እንዲህም ዓይነት ኅልውና ያለው በመሆኑ ፍጥረት ሁሉ የእርሱ ተደጋፊ ነው፤ እርሱ ሕያው ብቻ ሳይሆን ለአጥናፈ ዓለሙ ሁለንተናዊ ሕይወት፥ ምንጭና መሠረት ነው። እግዚአብሔር በማንኛውም ዓይነት መልኩና መንገድ ቢገለጥም ለዚያ ለተገለጠበት ነገር ጥገኛና ተደጋፊ አይሆንም አይደለምም። እግዚአብሔር ለሰው ሁለንተና የሚያስፈልገውን ረቂቅና ግዙፍ ነገር ሁሉ ሰጪ እንጂ ለኅልውናው ከሰው ወይም ከሌሎች ፍጥረቱ ድጋፍ ጠያቂ አይደለም፤ እርሱ ግን ድጋፍ ሰጪና ፍጥረትን አጽኚ ነው። "እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው አይደክምም አይታክትም ማስተዋሉም

አይመረመርም።" (ኢሳ40፥28)። እርሱ ሰጪ ሲሆን ፍጥረት ሁሉ፥ ሰውንም ጨምሮ ተቀባይ ነው።[58]

## 2. የእግዚአብሔር ባሕርይ

እግዚአብሔር በባሕሪው ህጸጽ የሌለበት ንጹህ መንፈስ ነው። ነገና ከመጀመሪያው የፍጥረት ባለቤትነቱን ሲያረጋግጥ ከጨለማ ብርሃን የሚያወጣ መንፈስ ሆኖ ነው። "ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ" (ዘፍ.1፡2፥3)። ይህንን ዓይነቱን የእግዚአብሔር የባሕሪ መገለጥ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአምልኮ ማረፊያ ማን መሆን እንዳለበት ለሳምራዊቷ ሴት ሲናገር እንዲህ ብሏል፥ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐ. 4፥24)። በዕብ. 12፥9 ላይ ደግሞ "የመናፍስት አባት" ይለዋል። እንዲህ ማለት ግን እግዚአብሔርና ሥነ-ፍጥረቱ አንድ ናቸው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ሲባል፥ በግማሹ መንፈስ ሆኖ በግማሹ ደግሞ የሰው ዓይነት አካል ያለው ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በቅርጽና በክፍል ሳይመዳደብ ያለቁሳዊ ኀልውና የሚገኝ መንፈስ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር *"ሰውኛ"* (Anthropomorphic) በሆነ መልኩ የሚገልጣቸው ማለትም፦ እግዚአብሔርን እንደባለ ዓይን፥ ባለጆሮ፥ ባለ እግርና እጅ ያለው አድርጎ የሚገልጠው፥ ለሰው ልጆች ባሕሪውንና አድራጎቱን ተመልካችነቱንና ሰሚነቱን ለማስተማር እንጂ በውኑ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ዓይነት ገላ (አካል) ኖሮት አይደለም። በእንዲህ ዓይነት መልኩ ስለ እግዚአብሔር ባይገለጽ ኖሮ ስለ እግዚአብሔር ጨርሶ ምንም መናገር አይቻልም ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ ያለ ቁሳዊ አካል መኖሩ በማንነቱ ላይ ያለውን ብቃት አይቀንስም።

እግዚአብሔር የማይመረመርና የማይወሰን መንፈስ ነው ስንል ይህ ግንዛቤ ከእኛ የዕውቀትና የልምምድ አድማስ ፈጽሞ የራቀ መሆኑን መዘጋንት የለብንም፤ እኛ በጊዜና በቦታ በዕውቀትና በኃይል የተወሰንንና ገደብ ያለብን ነን። እግዚአብሔር በመሠረቱ የማይወሰን ነው፤ እያንዳንዱ ባሕሪውም እንዲሁ





አይወሰንም። እንግዲህ እግዚአብሔር ከጊዜ አንፃር ሲታይ ዘላለማዊ ነው፤ ከቦታም አንጻር ሲታይም በስፍራዎች ሁሉ የሚገኝ ነው፤ በዕውቀትም ቢሆን እርሱ ብቻ ሁሉን አዋቂ ነው፤ በኃይሉ ችሎት ደግሞ እርሱ ብቻ ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር ውሱን አለመሆኑ ደግሞ በፈጠረው አጥናፈ ዓለም ላይ ምጡቅ (Transcendent) ሆኖ መገኘቱን ያስገነዝበናል። ይህም ደግሞ ከፍጥረቱ ሁሉ ተለይቶ በራሱ ኀልውና የነበረ፥ ያለና የሚኖር መንፈስ መሆኑን ያስገነዝበናል። እርሱ እኛ ተፈጥሮ ብለን በምንጠራው ነገር ተዘግቶ ያለ አምላክ ሳይሆን፥ አንድም ሳይቀር በፍጥረታት ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ የሰለጠነ ነው። "አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም" (የሐዋ.17፥25) በአጥናፈ ዓለሙ የሚያልፈው እያንዳንዱ ታሪክ እግዚአብሔር በዕቅዱ ያዘጋጀው ነው። ነገር ግን የዚህኑ ያህል በጣምራ አብሮ ሊጤን የሚገባው እግዚአብሔር ምጡቅና ከፍጥረታት የራቀ ብቻ ሳይሆን በምጥቀቱ ያለው ማንነት ሳይጎድልና ሳያንስ በቅርብ በፍጥረቱ የኀልውና ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ እየገባ፥ ሕይወት ያላቸውንና ግዑዛን የእጆቹን ሥራዎች ይቆጣጠራል ያጸናልም። ስለዚህ ምጥቀቱና ቅርበቱ (Transcendent & Immanent) በእኩልታ ካልታዩ በቀር ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ግንዛቤ ማግኘት አይቻልም (ኢሳ፡57፥15)።

## 3.የእግዚአብሔር ጠባይ

የእግዚአብሔር ጠባይ ስንል በግብር/በተግባር የተገለጠው ግብረገባዊ ማንነቱን ማለታችን ነው። ይህም ደግሞ አካላዊነቱን ("እኔነት" ያለው) መሆኑን የሚያረጋግጥልን ነው። በራሱ ኀሊና ያለውና በራሱ የሚወስን ግብረገባዊ ኀላዌ ያለው መሆኑን አብረን እናስባለን። የእግዚአብሔር ጠባይ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ከመግባቱ አኳያ ሲታይ ደግሞ፥ ፍጹምና ሙሉ በሆነ መልኩ የተገለጠው በክርስቶስ መገለጥ በኩል መሆኑን እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር ከፍተኛውን የኀሊና አቅም የያዘ እርሱ ብቻ በመሆኑ፥ ለሰው ልጆች ምክኑያዊነት (Rationality) ሁሉ ምንጩ

ያው እርሱ ብቻ ነው:: እንደ አካላዊ አምላክነቱ ራሱን በመግለጡም አኳያ ሆነ ከሰው ልጆች ጋር ያደረገው ግንኙነት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአል:: እንግዲህ ከሰው ልጆች የኑሮ ሁኔታ አንፃር የሚገለጠው እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ባሕሪይ እርሱ ለሰው ልጆች ራሱን የገለጠበት የማንነቱ ማስረጃ ነው:: በመከራ ጊዜ ርኅራሔኄ፥ ለበደለኛነት ጸጋ፥ ለንስሐ ይቅርታ መስጠቱ፤ ለፈለጉት ሁሉ የመገለጡን ጠባይ ያስረዳል:: እግዚአብሔር በሁሉም ዓይነት ጠባዩ እራሱን ለሰው ልጆች እንደ አስፈላጊነቱ ይገልጣል፤ ይህ ሲሆን አንደኛው ጠባዩ ከሌላኛው ጠባዩ ሳይበላለጥ ነው:: ከእያንዳንዱ ጠባዩ ጋር በቀዳማይነት ሊጠቀስ የሚገባው ልዩ ጠባዩ ግን ቅድስናው ነው:: ከዚህም የተነሳ ፍቅሩን ስናስብ፤ ቅዱስ ፍቅር፥ ፍርዱን ስናስብ፤ ቅዱስ ፍርድ፥ ርኅራሔኄውን ስናስብ፤ ቅዱስ ርኅራኄ በማለት የዚህን አካላዊ አምላክ ጠባይ እንረዳለን እንገልጻለንም::

የእግዚአብሔርን ጠባይ በዝርዝር ከመግለጻችን አስቀድሞ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር፥ የእግዚአብሔር ጠባይ በሁለት ሊከፈል መቻሉን ነው:: ይህም የማይወረስ ጠባይና የሚወረስ ጠባይ ነው:: እነዚህ ሁለት የጠባይ ክፍሎች እግዚአብሔር ከእኛ በምን ይለያል? እና እግዚአብሔር ከእኛ በምን ይመሳሰላል? ወይም እኛ እግዚአብሔርን በምን እንመስላለን? የሚሉትን ሁለት ዓይነተኛ ጥያቄዎች የሚመልሱ ናቸው:: እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች በሚገባ መመለስ እግዚአብሔርን ያለማወቅ ምክንያት ከሚሆን ትልቅ ስህተት ይጠብቀናል:: እርግጥ ነው የእግዚ አብሔርን የማይወረስ ጠባይ (Incommunicable Attributes) ከሚወረስ ጠባዩ (Communicable Attributes) ለይቶ ለማቅረብ በምናደርገው ሙከራ ውስጥ፥ የማይወረስ መስሎ የሚታየው የሚወረስ፥ በተቃራኒው ደግሞ የሚወርስ መስሎ የሚታየው የማይወረስ፥ መስሎ የሚታይበት አጋጣሚ ብዙ እንደሆነ እንገነዘባለን:: ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት የሚወረሰውም ሆነ የማይወረስው ጠባይ መቶ በመቶ የሚወረስ ወይም የማይወረስ ባለመሆኑ ነው:: ይህንን በዚህ የጥናት ሂደት ውስጥ ተብራርቶ እናገኘዋለን::[59]





3:1 የማይወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት

ሀ.ነፃ ነው (በራሱ ኀልው ነው)

እግዚአብሔር ነፃ ነው ስንል ለምንም ነገር መቻውንም ቢሆን ጥገኛ አለመሆኑን መግለፃችን ነው:: ለእርሱ ኀልውና እኛም ሆንን ሌሎች ፍጥረታት አናስፈልገውም፤ ሆኖም ግን እኛም ሆንን ሌሎች ፍጥረታት እግዚአብሔርን ልናከብረውና ደስ ልናሰኘው እንችላለን:: ይህ ጠባዩ የፍጹምነቱ ምልክት ነው:: የኀልውናው መሠረት ያረፈው ሌላ አካል ላይ ሳይሆን በራሱ ነው:: ለእርሱ መኖር ሌላ ሰበብ አይፈልግም፤ ለሌሎች መኖር ግን እርሱ ሰበብ ነው (He is the uncaused cause):: በምግባሩ፥ በሕጉና በሥራው ሁሉ ነፃ ነው፤ በራሱ ለራሱ የበቃ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለአቴናውያን ፍልሱፋን ይህንኑ ነው የነገራቸው:- "ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም" (የሐዋ. 17:24-25):: እንግዲህ በአጥናፈ ዓለሙ ውስጥ ከሕግ በላይ ያለና ሕግን የሚሠራ የሕግ ጌታ እግዚአብሔር ለሰው ሕግን ይሠራል እንጂ በሕግ አይገዛም እርሱ በሉዓላዊነቱ የመንቀሳቀሻና የመኖሪያ ሕግ ያወጣል ለእርሱ ግን ሕጉ ራሱ ነው:: "ከሰማይ በታች ያለው ነገር ሁሉ የእኔ ነው ታዲያ እንድመልስለት ለእኔ ያበደረ ማነው?" (ኢዮ.41÷11 አዲስ ትርጉም):: እንዲሁም ኢዮብ 38-42÷6 ድረስ ያለውን ይመለከቷል::

አንዳንድ እግዚአብሔርን እንደ ኢዮብ ያላዩና ያልቀመሱ ሰዎች፥ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበትን ዓላማ ሲናገሩ እግዚአብሔር ብቸኝነት ስላጠቃው ከሰዎች ጋር ኅብረት ለማድረግ ሲል ፈጠራቸው ይላሉ:: ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔር የፍጥረቱ ጥገኛ የሆነ የኀልውናው ሙሉነት በሌሎች የሚወሰን ሊሆን ነው:: ሆኖም ግን በሦስትነትና በአንድነት ኀልውናው የተረጋገጠ እግዚአብሔር፤ የብቸኝነት ችግር ያለበት አይደለም:: (ዮሐ.17÷5)::[60]

## ለ. የማይለወጥ ነው

"እግዚአብሔር የማይለወጥ ነው" ስንል *በማንነቱ፥ በፍጹምነቱ፥ በዓላማው እና በሚገባው ተስፋ የማይለወጥ ነው ማለታችን ነው*:: ሆኖም ግን እግዚአብሔር ለተለያዩ ሁኔታዎች የተለያዩ የድርጊትና የስሜት ምላሾች ይሰጣል::

1.ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ምን ይላሉ ?

በመዝ 102 ላይ ከቶ የማይመሳሰሉ ነገሮች ሲነጻጸሩ እንመለከታለን፤ በአንድ በኩል እጅግ ጽኑ መስለው የሚታዩት ሰማይና ምድር፥ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር:: መዝሙረኛው እንዲህ ይላል:-

> አቤቱ፥አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥
> ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው::
> እነርሱ _ይጠፋሉ_፥ አንተ ግን _ትኖራለህ፥_
> ሁላቸው እንደልብስ ያረጃሉ፥
> እንደ መጎናጸፊያም _ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል_
> _አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥_
> ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም (መዝ 102፥25-27)::

ይህ በብሉይ ኪዳን ለያህዌ የተሰጠው የአይለወጤነት ባሕርይ በአዲስ ኪዳን ደግሞ በቀጥታ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥቶ እንመለከታለን "ስለ ልጁ ግን:-... ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ ሁሉም እንደልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም" (ዕብ. 1፥8-11 እንዲሁም ዕብ. 13፥8 ላይ የተጠቀሰውን ይመለከቷል):: ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድ የአለመለወጥ መለኮታዊ ባሕሪን ሙሉ በሙሉ እንደሚካፈል ማስተዋል እንችላለን::

እግዚአብሔር ከሰማይና ከምድር በፊት ኀልው ነው:: ሰማይና ምድርም ከጠፉ በኋላ ኀላዌው ይቀጥላል:: እግዚአብሔር





አጥናፈ ዓለሙን ለልዩ ልዩ ለውጥ ይዳርገዋል፤ እርሱ ግን ለምንም ለውጥ አይዳረግም::

ስለ ጽኑነቱ፥ ስለ ምሕረቱና ስለ ትዕግሥቱም ራሱ እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገር እንዲህ አለ:- "እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ስለዚህ የጠፋችሁ አይደላችሁም" (ሚል.3፥6):: ደግሞም በአዲስ ኪዳን ያዕቆብ የመልካም ስጦታ ሁሉ ምንጭ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ሲናገር እንዲህ ይላል:- "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው _መለወጥም_ _በእርሱ ዘንድ ከሌለ_ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ1፥17):: የማይለወጥ የሰማይ አምላክ የማይለወጥ የበጎ ስጦታ ምንጭ ነው::

እስከ አሁን በተሰጠው የእግዚአብሔር አለመለወጥ የትርጉም ማብራሪያ፥ እኛ ይለወጣል ወይም አይለወጥም ብለን ባሰብንበት የትርጉም አቅጣጫ ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍት በገለጹት መሠረት ብቻ ነው:: በዚህም መሠረት እግዚአብሔር አይለወጥም ስንል ጠባዩና ኀልውናው ከፍጹምነቱ አንፃር ሲታይ አይለወጥም ማለታችን ነው:: ይህንን እውነታ ጠንቅቆ መረዳት ደግሞ በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት አውቆ ራስን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ለማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን::

የእግዚአብሔር አለመለወጥ ከፍጹምነቱ አንጻር ብቻ ሳይሆን ከዓላማውም አንጻር ሊስተዋል ይገባል:: "የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው" (መዝ:33፥11):: ይህ ስለ እግዚአብሔር ምክር ጠቅለል ያለ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፥ እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ ስላሰባቸው እቅዶችና ስለ ዓላማው የሚያብራሩ በርካታ ጥቅሶች አሉ (ማቴ. 13፥35፤ 25፥34፤ ኤፌ. 1፥4፤11፤ 3፥9፤11 2ጢሞ. 2፥19 1ጴጥ.1፥20 ራእ. 13፥15):: እግዚአብሔር አንዴ አንድን ነገር ለመፈጸም ከወሰነ፥ ዓላማው አይለወጥም ግቡን ይመታል:: በእርግጥ በዚህ ዓይነት ባሕሪው እርሱን የሚመስል ማንም እንደሌለ በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል እንዲህ ብሎ ተናግሮአል:-

"እኔ አምላክ ነኝና ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። በመጀመሪያ መጨረሻውን ከጥንትም ያልተደረገ ውን እነግራለሁ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ። ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍን ከሩቅም አገር ምክሬን የሚያደርገውን ሰው እጠራዋለሁ። ተናግሬአለሁ እፈጽምማለሁ አስቤአለሁ አደርግማለሁ" (ኢሳ. 46÷9-11)።

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር በተስፋውም የማይለወጥ ነው። እግዚአብሔር አንዴ ለአንድ ነገር ተስፋ ከገባ ለዚያ ተስፋ በፍጹም ታማኝ ነው።

"ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም÷
ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።
እርሱ ያለውን አያደርገውምን?
የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? (ዘኁ. 23÷19)።

"የእስራኤል ኃይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለምና
አይዋሽም አይጸጸትምም አለው" (1ሳሙ.15÷29)።

በዚህ በሰው ልጆች ዓለም ውስጥ ስንኖር÷ ሰዎች ለእኛ ያላቸውን ግምትና አመለካከት ከሁኔታዎች መለዋወጥ ጋር እያገናዘቡ ይለዋወጡብናል። እግዚአብሔር ከዘላለም አንስቶ ለእኛ ያለው ሐሳብ ግን አይለወጥም። ፈቃዱና የሚገባልን ተስፋም አይቀየርም። ወደ እንዲህ ዓይነት ማንነቱ በጸሎት በምንቀርብበት ጊዜ÷ ዛሬ ተበሳጭቶ ይሆን? ዛሬ ጠባዩ ተቀይሮ ይሆን? ዛሬ እንዲህ ሆኖ ይሆን? እያልን አንሰጋም። ትናንትና ያዩን የፍቅር ዓይኖቹ እንደማይለወጡ ተስፋ በማድረግና ስሙን በመጥራት በፊቱ እንቀርባለን። እርሱ ለጠያቂዎቹ በምድር ላይ እንዳሉ ባለሞያዎች ሰዓትና ቀን አይቀጥርም። ሁልጊዜ አሁን ውስጥ ያለ በመሆኑ÷ ወደ አይለወጤው ማንነቱ የመጡ ሁሉ በዓመት ሦስት መቶ ስድሳ አምስት/ስድስት ቀን÷ በቀን ደግሞ ሃያ አራት ሰዓት ሊያገኙት ይችላሉ። እርሱ አንዴ የሚከፋው÷ አንዴ ደግሞ





ፎልፏሌ የሚሆን÷ ወሰድ መለስ የሚያደርግ ጠባይ ያለው (Moody) አይደለም።[61]

ለኃጢያት ያለው ጥላቻ ከጊዜ በኋላ የጀመረ አይደለም። ድሮም ጅማሬ በሌለው ማንነቱ ሲኖር ኃጢአትን ይጠላ ነበር፤ አሁንም ይጠላል÷ ወደፊትም ይጠላል። ለፈጠረው የእጆቹ ሥራ በተለይም ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ድንገት ያገረሸበት ሳይሆን÷ ገና ዓለም ሳይፈጠር በመለኮት ዕቅዱ ውስጥ የነበረ ነው። ይህንንም÷ ራሱን አሳልፎ በመስጠት በመስቀል ሞት ገልጦታል። *ይህንን አይለወጤ አምላክ መሸንገልም ሆነ የልብን ፈቃድ እንዲሞላ ማሳመን አይቻልም። ጸሎትን ሰምቶ ቢመልስ÷ ሐሳቡን ስለቀየረ ወይም ጸሎት ስላሳመነው ሳይሆን÷ በሰው ልጆች ሕይወት ሉዓላዊ ፈቃዱን ለመፈጸም ሆን ብሎ ያዘጋጀው መንገድ በመሆኑ ነው። ለውጥ ሁሉ ያለው ከሰው አኳያ ነው።*

## 2.ወሰን የሌለውና አካላዊ አምላክ ነው

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እግዚአብሔር በአንድነት ወሰን የሌለውና አካላዊ የሆነ አምላክ ነው። ወሰን የሌለው ነው ስንል÷ ውሱን ለሆነው የሰው ልጅና እንዲሁም ለተፈጥሮ ሁሉ በማንኛውም ዓይነት መልኩና በማንኛውም ዓይነት ማብራሪያ ተገዢ አይደለም፤ እርሱ ግዑዝና ሕያው ከሆኑ ማንኛውም ዓይነት ፍጥረታት ሁሉ÷ እጅግ የበላይና የላቀ ነው ማለታችን ነው። ማንም ቢሆን ወደዚህ ዓይነት ማንነቱ በፍጥነትም ሆነ በአዝጋሚ ሂደት ሊደርስበት አይችልም። ባሕሩ ወሰን የለሽነት የእርሱ ብቻ ነው። ደግሞም በአንጻሩ አካላዊ ነው፤ ስንል÷ ከእኛ ከሰው ልጆች ጋር መስተጋብራዊ ግንኙነት (Interactive relation ) ያደርጋል፤ እኛም አካላዊ ፍጡራን (Personal Beings) ነንና ከእርሱ ጋር እንዲሁ እንገናኛለን። ወደ እርሱ እንጸልያለን÷ እናመልከዋለን÷ እንታዘዘዋለን÷ እንወደዋለን÷ እርሱም እኛን ይናገራል÷ በእኛም ደስ ይለዋል÷ ይወደናልም፤ ይህ ሁሉ አካላዊነቱን ያስገነዝበናል።[62]

በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ላይ ከተመሠረተው ከእውነተኛው የክርስትና እምነት በቀር በአንድ ጊዜ ወሰን

የሌለውና አካላዊ የሆነ አምላክ ያለው ሃይማኖት የለም:: የአንዳንዶቹ አምላክ ወሰን የሌለው ብቻ ስለሆነ ከአምላኪዎቹ ጋር አካላዊ መስተጋብር (Personal Interaction) የማያደርግ ሩቅ ያለ አምላክ ነው፤ የሌሎቹ አምላክ ደግሞ ምጡቅነት የሌለው አካላዊ ብቻ ስለሆነ በሁኔታዎች እየተወሰነ ይለዋወጣል::

ይህ ወሰን የለሽ ምጡቅ አምላክ÷ በገዛ ፈቃዱ ለውስኑ የሰው ልጅ አምላኩን የሚፈልግበትን መንፈስ ሰጥቶታል:: ምጥቀቱ የክብሩና የግርማው መታያ በመሆኑ የሰው ልጅ አክብሮታዊ ፍርሀት ሊሰጠው የተገባ ነው:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ዋጅቶን "አብ አባት" የምንልበትን የልጅነት መንፈስ ቢሰጠንም በመፍራት በመንቀጥቀጥ የሚመለክ አምላክ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንመለከት ይህ አምላክ በክብሩ የተገለጠላቸው ሰዎች ሁሉ በፊቱ የመደፋትና ልብን የማቅለጥ ምላሽ ግድ ሆኖባቸው ነበር:: እንኳን የእግዚአብሔር ሙሉ ክብርና÷ የራእይ ግልጠቱ እንኳ "እኔም ብቻዬን ቀረሁ ይህንንም ታላቅ ራእይ አየሁ፤ ኃይልም አልቀረልኝም÷ ደም ግባቴም ወደ ማሽብሸብ ተለወጠብኝ÷ ኃይልም አጣሁ:: የቃሉንም ድምጽ በሰማሁ ጊዜ ደንግጬ በምድር ላይ በግንባሬ ተደፋሁ::" ይላል ነብዩ ዳንኤል ባየው ራእይ የገጠመውን ሲናገር (ዳን.10÷8-10):: ዛሬ ማናችንም የማናመልጠው ጥያቄ:- ከፍቅሩ የተነሳ በአካላዊነቱ የቀረበንን ይህንን ምጡቅ ጌታ÷ በምን ዓይነት የአክብሮት መንፈስ ነው የምናመልከው? የሚለው ነው:: ሃይማኖታዊ ስብሰባዎቻችን ውስጥ በእርግጥ ነቢዩ ዳንኤልና ነቢዩ ኢሳይያስ የተለማመዱት የልብ መቅለጥ አለ ወይ? ለእግዚአብሔር የምንቀና÷ ልብ የሚመስጡ መዝሙሮች ያሉንና መንፈሳዊያን ለመሆን የምንጥር መሆናችን የሚታወቀውን ያህል÷ እግዚአብሔርን በመፍራታችን እንታወቃለን ወይ? ፈሪሀ እግዚአብሔር እርስ በርስ ባለን የወንድማማች ግንኙነትና ለመሪዎቻችን በምናሳየው ከበሬታ ይታያል ወይ?





ሐ.ዘላለማዊ ነው

"እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው" ስንል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሌለው÷ የማይለወጥ ዘላለም በባሕሪው ጸንቶ የሚኖር÷ ዘመን÷ ዕለት÷ ወር የማይቆጠርለት÷ ሞት የሌለበት የጊዜ መስፈሪያ የሌለው ወይም ለዓለመ ዓለም ያለመሸፈሪያ ወይም ያለልክ የሚኖር ማለታችን ሲሆን፤ በዚህ ዓይነት ጠባዩ ጊዜንና ዘመናትን ሁሉ በአንዴና በእኩል በግልጽ ይመለከታቸዋል:: ሆኖም እግዚአብሔር አንዳንድ ክንዋኔዎችንና ድርጊቶችን በየራሳቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ ይመለከታቸዋል:: እግዚአብሔር በጠባዩ ኢ-አላቂ (Infinite) በመሆኑ የማይወሰን ነው:: ይሄ አስተምህሮ ደግሞ ጊዜ እግዚአብሔርን እንደማይወስነው ያስገነዝበናል::

የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ከእግዚአብሔር አይለወጤነት ጋር በቅጡ የተያያዘ ነው:: እግዚአብሔር አይለወጥም ካልን÷ ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን አይለውጠውም ማለታችን ነው:: ጊዜ በእግዚአብሔር ኀልውና÷ ፍጹምነት÷ ዓላማና ተስፋ ላይ ምንም ዓይነት የለውጥ ተጽዕኖ አያደርግበትም:: ጊዜ በእግዚአ ብሔር ዕውቀትም ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አያመጣም፤ እርሱ አዲስን ነገር አይማርም፤ የሚያውቀውንም ነገር አይረሳም:: ስለዚህ የጊዜ ሂደት መለዋወጥ በእርሱ እውቀት ላይ አይጨምርም ወይም አያጎድልም:: እርሱ ያለፈውን የአሁኑንና የወደፊቱን ነገር በእኩል ደረጃና በግልፅ ሁሉንም ያውቃቸዋል::

1.እግዚአብሔር በኀልውናው ጊዜ የማይገድበውም ነው፡፡[63]

"እግዚአብሔር መጀመሪያም መጨረሻም የለውም" የሚለው እውነታ÷ በመዝሙር 90 ላይ ተጠቅሶአል÷ "ተራራ ዎችን ከመመሥራትህና ዓለምንም ከመፍጠርህ በፊት ለዘላለም አምላክ ነህ ከእንግዲህ ወዲህም የዘላለም አምላክ ሆነህ ትኖራለህ" ደግሞም በኢዮብ መጽሐፍ ላይ ኤሊሁም እንዲህ ብሎ ይናገራል "እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም" (ኢዮ. 36÷26)::

የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት በጊዜ በማይገደብ ኅልውናው መዝለቁን፥ ባለ ራእዩ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ያስቀምጠዋል፡- "ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል" (ራእ.1፥8)። ደግሞም በሰማያዊው የአምልኮ ስፍራ "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ" የሚለው ድምጽ ቀንና ሌሊት ይደመጣል (ራእ. 4፥8)።

"እግዚአብሔር የኅልውና ጅማሬ የለውም" የሚለው እውነታ "እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ፈጥሮአል" የሚለውን ሌላኛ ውን እውነታ እንድናምን ግድ ይለናል። እርሱ ራሱ ቁስ አካላዊ ያልሆነ መንፈስ ነው። እግዚአብሔር አጥናፈ ዓለሙን ከመፍጠሩ በፊት ቁስ አካል (Matter) የሚባል ነገር አልነበረም፤ እርሱ ግን ሁሉን ወደ መኖር አመጣ (ዘፍ.1፥1፤ ዮሐ. 1፥3፤ 1ቆሮ. 8፥6፤ ቆላ. 1፥16፤ ዕብ.1፥2፤ 11፥3)። የፊዚክስ ትምህርት እንኳ እንደሚያመለክተው ከሆነ ቁስ አካል፥ ጊዜና ቦታ በአንድ ላይ ሊከሰቱ የሚገቡ ናቸው፤ የቁስ አካል ክስተት ከሌለ የቦታና የጊዜ ክስተትም የለም ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ አጥናፈ ዓለሙን ከመፍጠሩ በፊት ክረምት፥ በጋ፥ ዓመት፥ መንፈቅ፥ ወር፥ ሳምንት፥ ሰዓት፥ ደቂቃ በሚል ዓይነት መልኩ የተቀመረ ጊዜ አልነበረም፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር አጥናፈ ዓለሙን ሲፈጥር ጊዜንም አብሮ ፈጠረ፤ ጊዜ ራሱ ከቁስ አካል ጋር አብሮ የተፈጠረ ነው ማለት ነው። ልክ እግዚአብሔር አጥናፈ ዓለሙን መፍጠር ሲጀምር ጊዜም ተጀመረ። ሆኖም ግን አጥናፈ ዓለሙም ሆነ ጊዜ ራሱ ከመፈጠራቸው በፊት፥ እርሱ እግዚአብሔር ያለምንም ጅማሬና ያለ ጊዜ ተጽእኖ ኅልው ነበረ። ስለዚህ ጊዜ ራሱም ቢሆን በራሱ ኅልውና የለውም፤ ይልቁንም እንደ ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ለኅልውናው በእግዚአብሔር ዘላለማዊነትና ኃይል ላይ ይደገፋል እንጂ። እንግዲህ የእግዚአብሔር ኅልውና ከጊዜ ወደ ጊዜ ርምደታዊ (Progressive) የሆነ ለውጥ በማምጣት ከአንድ የኅልውና ደረጃ ወደ ሌላ የኅልውና ደረጃ አልተሸጋገረም፤ *ለእርሱ ኅልውናው ሁሉ፥ ሁልጊዜ አሁን ነው።* ምንም እንኳ ይህንን ለመረዳት የሚያስቸግረን ቢሆንም ለእርሱ "ትናንትና" እና "ነገ" ወይም "ቅድም" እና "በኋላ" የሚባሉ ነገሮች የሉም፤ ሁል ጊዜ እርሱ "ዛሬ" እና "አሁን" ውስጥ ነው ያለው። ሆኖም ግን





አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰው በሚገባ መንገድ ራሱን በጊዜ ገድቦ ሲገልጥ እንመለከተዋለን።

2.እግዚአብሔር ጊዜአትን ሁሉ በእኩልና በግልጽ ይመለከታቸዋል

"ለአንተ አንድ ሺህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ነው፥
አልፎ እንደ ሄደው እንደ ትናንት ነው፥
በሌሊትም እንዳለ እንደ አንድ ሰዓት ጥበቃ ነው"
(መዝ. 90፥4 አዲስ ትርጉም)።

እኛ ከሳምንታት በፊት ወይ ከወራት በፊት አለዚያም ከዓመታት በፊት የተፈጸሙ ሁኔታዎችን በቅጡ ለማስታወስ ይቸግረናል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተፈጸሙ ሁኔታዎችን በተቻለ ግልጽነት ብናስታውሳቸውም፥ የትውስታችን መጠን ጊዜ ባለፈ ቁጥር እየደበዘዘ መሄዱ የማይቀር ነው። እግዚአብሔር ግን ሺ ዓመትን የሚመለከተው እንደ ዛሬ ነው። እኛ የዛሬን ነገር በግልጽ እንደምናስታውሰው መጠንና ከዚያም በላይ፥ እርሱ የዛሬ ሺ ዓመቱን ታሪክ እንዲሁ በግልጽና ከዛሬው ሁኔታ እኩል በዝርዝር ያውቀዋል። ስለዚህ በዘመናት ውስጥ ያለፈውን ታሪክ ሁሉ እርሱ በግልጽ በዝርዝርና በእኩል ደረጃ ያውቀዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ጌታና በታሪክም ላይ ልዑል ነው። ስለዚህም በማንኛ ውም ዘመን ተብዬ ውስጥ በሚፈጸመው ማንኛውም የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ጣልቃ መግባት አምላካዊ መብቱ ነው። ለዚህ የፍጥረቱን ፈቃድ አይጠይቅም። በአጠቃላይ እርሱ ጊዜን የሚያ ውቅበት ሁኔታና የእኛ የጊዜ መረዳት ፈጽሞ የተራራቁ ናቸው። እርሱ በማንነቱ ጊዜ የለሽ ነው።

3.እግዚአብሔር ክስተቶችን በጊዜአቸው ያያል በጊዜ ገደብም *ሥራውን ይሠራል*[64]

እስከ አሁን የተገለጸው የእግዚአብሔርና የጊዜ ንጽጽሮሽ እግዚአብሔርን ከጊዜ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው አድርጎ የከረረ ስህተት ውስጥ እንዳይከተን፥ አንጻራዊ ማብራሪ ያዎችን መመልከት ይጠቅመናል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ አምላክ ነው ስንል፥ የሰውን የጊዜ ዕውቀት ጠብቆ ጊዜው የሚጠይቀውን ነገር አያደርግም ማለት አይደለም። ሐዋርያው

ጳውሎስ ይህንን ሁኔታ ሲያስረዳ "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ" (ገላ.4:4÷5):: እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ሁኔታዎች በጊዜአቸው እንዴት እንደሆኑና መቼ እነደሚፈጸሙ በግልጽ አውቆአቸዋል:: እርሱ የጊዜን ሂደት ደረጃ በደረጃ ያያል፣ በፍጥረቱ ውስጥም የተለያዩ ኹነቶች (Events) ይከሰታሉ፤ እናም በትክክለኛው ጊዜ አስፈላጊውን ጣልቃ ገብነት ያደርጋል:: በዚሁ መሠረት "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ" እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ኃጢያተኛ ዓለም ላከ::

ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ እንደሚያስረዱን እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያቶች የተለያዩ ድርጊቶችን ያደርጋል:: ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ለግሪክ አቴና ፍልሱፋን እንዲህ ብሎ ያስረዳል:- "እንግዲህ እግዚአብሔርን ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል ቀን ቀጥሮአልና÷ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለ" (የሐዋ.17:30-31):: ይህ አገላለጽ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ የሠራበትንና ያደረገበትን መንገድ÷ አሁን የሚያደርግበትን መንገድና ወደፊት ደግሞ በጊዜ ውስጥ ሊያደርግ ስለሚችለው ነገር ያብራራል::

በእርግጥ በብሉይ ኪዳን ተደጋጋሚ አጽንኦት የተሰጠበት የእግዚአብሔር የወደፊትን ታሪክ ዕውቀት ስንመለከት÷ እግዚአብሔር ወደፊት ሊያደርግ ያለውን ድርጊት ቀደም ባለ ጊዜ በነቢያት በኩል አስቀድሞ ይናገርና÷ ያንን የተነገረ ድርጊት÷ በኋላ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያከናውነዋል:: እንግዲህ በጠቅላላው ስንመለከት መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉውን ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ÷ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መዳን በተለያዩ ጊዜያቶች ያደረጋቸውን ድርጊቶች የዘገበበት መጽሐፍ እንደ ሆነ እንረዳለን:: ባጭሩ ጊዜአትንና ሰዓታትን የፈጠረ እርሱ ስለሆነ ጊዜንና ሰዓትን ለራሱ ዓላማ ሊሰለጥንባቸው ባለመብት እርሱ ነው፤ ጊዜን ለክብሩ መግለጫ ይጠቀምበታል::





የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት በአባቶች÷ በነቢያትና በሐዋርያት መጻሕፍት እንደሰንሰለት የተተረከለት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው:: *ካልተጀመረ የሃላፊ ጊዜ÷ እስከማያልቅ የወደፊት ጊዜ ድረስ አጽናፍ በማይገታው መለኪያ ነበረ፤ አለ፤ ይኖራልም::* በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ጊዜን አስመልክቶ የሚጠቀሱ ሐሳቦችና ሐረጎች ሁሉ እርሱን የሚመለከቱ ሳይሆኑ ፍጥረቱንና የሰውን ልጆች የሚመለከቱ ናቸው:: *እርሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያሉትን የሰው "ነገዎች" በሙሉ ትናንትና ዛሬ ኖሯቸዋል::*

እኛ ጊዜን የምንለካው ወቅቶች ሲፈራረቁና ሲመሽ ሲነጋ ነው:: በእርሱ ዘንድ ግን ሁልጊዜ የነጋ ነው:: የእኛ የጊዜ ግንዛቤ "በፊት" "በኋላ" የሚሉ ቃላቶች አሉት:: በእርሱ ዘንድ ግን ሁልጊዜ አሁን ነው:: እኛ ፀሐይ ስትወጣና ስትጠልቅ እናያለን፤ በእርሱ ዘንድ ግን ጠልቃ አታውቅም:: እኛ ጨረቃን ለማየት ሌትን÷ ፀሐይን ለማየት ቀንን እንጠብቃለን፤ እርሱ ግን የሌሊትን የሰማይ ሠራዊትና የቀኒቱን ፀሐይ በአንድ ጊዜ በእኩል ደረጃ ያያቸዋል:: *እርሱ ረፍዶበት ዘግይቶ÷ ተጣድፎ ቀድሞ ደርሶ አያውቅም:: እነዚህ ቃላቶች ሁሉ የእኛ የጊዜ እስረኞቹ ቃላቶች ናቸው::*

በዚህ የጊዜ ገደብና የሰዓት ሩጫ ባስደነገጠው የጥድፊያ ዓለም ውስጥ የምንኖር አማኞች ነን:: ምንም እንኳ ጅማሬ ያለን የሰው ልጆች ብንሆንም÷ በውስጣችን ዘላለማዊነት የተፈጠረብን በመሆናችን÷ ለሕይወት የምንሰጠው ፋይዳ ከዘላለም ጋር በጽኑ ለተቆራኙ ጉዳዮች ሊሆን ይገባል:: የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና የሰውን ምውትነት ስናስተያይ÷ በክርስቶስ ማመን ብቸኛ ምርጫ ሆኖ እናገኘዋለን:: ምክንያቱም ክርስቶስ ማለት የዘላለም ሕይወት ማለት ነውና::

በዚህ መጠነኛ የጽሑፍ ገለጻ ሥር÷ የመለኮትን ጠባይ ዘርዝሮ ለማስረዳት ለብቻው የሆነና አንድ መጽሐፍ ጠያቂ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ስለሆነም ምንም እንኳ በ 3:1 ላይ የማይወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት የሚለው በጥልቀትና በዝርዝር ባይገለጥም ለቅኝት (Survey) ጥናት በቂ መሆኑ ስለሚታመን÷ እግዚአብሔር ቢያንስ እስካሁን በተጠቀሱት ጠባያቱ ከሰው ልጆች ፈጽሞ

የተለየ መሆኑን እንደተረዳን በማሰብ በተቃራኒው ደግሞ እግዚአብሔርና የሰው ልጆች ሊመሳሰሉ የሚችሉባቸውን ጠባያት በሚቀጥሉት ማብራሪያዎች ለማየት እንሞክራለን።

3:2 የሚወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት

በዚህ ርዕስ ሥር ልንመልስ የምንሞክረው ጥያቄ "እግዚአብሔር በኀልውናው፥ በኀሊናውና በግብረገባዊ ጠባዩ ከእኛ ጋር ያለው ምስስል እንዴትና ምን ዓይነት ነው?" የሚለውን ነው። በዚህ ጽሑፍ የሚሰጠው መግለጫ ፍጹማዊ ነው፤ ስለዚህ ማንም ሂስ ሊሰጥበት አይገባም ለማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘንድ በሚወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያትና በማይወረሱ የእግዚአብሔር ጠባያት ላይ ትንሽ ክርክር መኖሩ የሚታመን ነውና።

ሀ.የእግዚአብሔርን ነባሪነት (Being) የሚያስረዱ ጠባያት

*መንፈስ/መንፈሳዊነት*[65]

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር "የተሠራበት" ነገር ምን ይሆን? የሚል የዘወትር የልብ ጥያቄ አላቸው። እንደ እኛ ሥጋና ደም ያለው ነውን? ይላሉ። በእርግጥ እንዲህ አይደለም፤ ታዲያ ምን ይሆን የኀልውናው መገኛ? እንዲያው ለነገሩስ እግዚአብሔር ከቁስ አካል የተሠራ ይሆንን? ወይስ ጥርት ያለ ኃይል ብቻ ነው? ወይስ እንዲያው ያለ ሐሳብ ብቻ ነው? እኒህ ጥያቄዎች በአማኝም ሆነ በኢ-አማናውያን ዘንድ በግልፅና በሥውር የሚጠየቁ አይቀሬ ጥያቄዎች ናቸው።

የቅዱሳት መጻሕፍት መልስ ግን ከእነዚህ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር ማንነት የመላምት ጥያቄዎች ከአንዱም ጋር አይስማማም። ይልቁንም ቅዱሳት መጻሕፍት "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" ብለው ይናገራሉ (ዮሐ.4፥24)። ይህንን ቃል የተናገረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የተናገረውም አንዲት ሳምራዊት ሴት እግዚአብሔርን በቦታ ወስና ማምለክ እንደምትችል በተከራከረችው ጊዜ ነው።





እግዚአብሔርን በቁመት መጠን ወይም በወርድና በስፋት ልናስበው አይገባንም አንችልምም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በስፍራዎች ሁሉ ይገኛል ብለን ስናስብም ከማይለካ ትልቅነቱ የተነሳ በአንድ ሥፍራ ክፉይ ማንነቱ በሌላ ሥፍራ ደግሞ ሌላ ክፉይ ማንነቱ ይገኛል ማለታችን ሳይሆን፤ እግዚአብሔር በሁለንተናው በሁሉም ሥፍራ ይገኛል ማለታችን ነው።

"ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?<br>ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?<br>ወደ ሰማይ ብወጣ፥አንተ በዚያ ነህ፤<br>ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ።<br>እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥<br>እስከ ባሕር መጨረሻ ብበርር፥<br>በዚያ እጅህ ትመራኛች፥<br>ቀኝህም ትይዘኛለች" (መዝ. 139: 7-10)።

ደግሞም በሌላ አንጻር እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል፥ ከመንፈስነቱ የተነሳ ፍጹም ሊጨበጥ የማይችል ኢ-ምንት ነው ማለታችንም አይደለም። ምክንያቱም በአጥናፈ ዓለሙ እርሱን መክበብ ወይም መያዝ የሚችል ቦታ የለም። መጽሐፍም ሲናገር "በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዘው ዘንድ አይችልም..." ይላል (1ነገ.8:27)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ኑባሬ (Being) በቀጥታ ከቦታ ጋር ተያይዞ ሊታሰብ አይችልም። እርሱ መንፈስ ነውና ቦታ አይወስነውም። እግዚአብሔር ከእንዲህ ዓይነት ማንነቱና ከሌሎች ልዩ ከሚያደርጉት ጠባዮቹ የተነሳ የሚያመልከው ሕዝብ በፍጹም በምንም ዓይነት ሁኔታና ምክንያት ከሌሎች አማልክት ተብዬዎች ጋር እዳያመሳስሉት ያላሰለሰ ትእዛዝ አስተላልፏል (ዘጸ.20:4-6)።

እንግዲህ የእግዚአብሔር የመንፈስነት ጠባይ ከሚወረሱ ጠባያቱ ውስጥ ከተመደበ በዘመናችን ቤተክርስቲያንን ከሚያስ ጨንቅ "ሰው መንፈስ ነው" ከሚለው ትምህርት ጋር መዛመዱ አይደለም ወይ?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን እስከ አሁን የተሰጠው "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" የሚለው

ትርጓሜ ከፍጥረቱ ውስጥ ማንም ሊጋራው በማይችለው መልኩ መንፈስ ነው የሚል ሐሳብ ነው:: ይህም ከእኛ ቁሳዊ ኀላዌነት እጅግ በመጠቀና በላቀ ሁኔታ ሊታይ የሚገባ ነው:: በአጭሩ እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል እግዚአብሔር እንደሰው ከቁስ አካል ባልተሠራ ኅልውናው፥ ወርድና ስፋት ሳይኖረው በእኛ አካላዊ ስሜቶች ሊደረስበት በማይችል ሁኔታ ከሌሎች ምንም ዓይነት ኅልዋን በልጦና ልቆ ያለ ማለታችን ነው::

እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ጠባይ ለተወሰነ ዓላማ ከእርሱ በተለየ ሁኔታና ባነሰ ደረጃ ለሰው ተሰጥቶአል:: ይህም ማለት እግዚአብሔር ከላይ በተጠቀሰው ትርጉም እና ማብራሪያ መሠረት መንፈስ ሲሆን፥ *ሰው ደግሞ ቁሳዊ የሆነ መንፈሳዊ ፍጡር ነው::* እግዚአብሔር እርሱን የምናመልክበት መንፈስ ሰጥቶናል "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐ.4÷24):: ከዚህም ሌላ ለአምልኮ የተሰጠን መንፈስ እንዳለ በ1ቆሮ.14÷14፤ ፊል.3÷3 ላይ ተጠቅሶአል:: በዚህም መንፈስ ከጌታ ጋር እንተባበራለን "ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው" (1ቆሮ.6÷17):: የእግዚአ ብሔር መንፈስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን የሚመሰክ ርልን በዚያው መንፈስ ነው (ሮሜ 8÷16):: ከሞት ዓለም ባሻገር ወዳለው ወደ ጌታ መገኛም የምንሄደው በዚሁ መንፈስ ነው (ሉቃ.23÷46፤ መክ.12÷7፤ ዕብ. 12÷23፤ ፊል. 1÷23-24):: ነገር ግን ይህ የመንፈሳዊነት ዕድል የሰው ልጅን ወደ መንፈስነት አይቀይረውም::

*የሰውን ማንነት ከሁለንተናው በመነጠል፥ የሰው እውነተኛ ማንነቱ ሥጋው ነው፥ ነፍሱ ነው፥ ወይ መንፈሱ ነው የሚያሰኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ትምህርት የለም:: ሰው፥ ሰው የሚሆነው በመንፈስ፥ በነፍስና በሥጋው ነው:: "ሰው በሥጋ ውስጥ ያለ መንፈስ"[66] ሳይሆን ሰው መንፈስ፥ ነፍስ ሥጋ ያለው ተዳሳሽ ፍጡር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሁለንተናን እንጂ ከፋይ ማንነትን አያስተምርም::* "አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ" ብሎ ቅዱስ ቃሉ ሲናገር፥ አምልኮተ እግዚአብሔር የሰው ሁለንተናዊ ተሳትፎን ጠያቂነቱን ሲገልጽ ነው (ዘዳ.6÷4):: የሰው ሥጋ ለባሽነት ደግሞ ከሞት ወዲህ ብቻ ያለ ጉዳይ ሳይሆን ከሙታን





ትንሣኤ በኋላ እንኳ አማኞች ወደ መንፈስነት አይለወጡም:: ይልቁንም የከበረን ሥጋ ለብሰው ዘላለም ውስጥ ይገባሉ እንጂ (1ቆሮ.15 ÷53):: መጽሐፍ ቅዱስ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው"(ዮሐ.3÷6):: ብሎ ሲያስተምር፥ ሰው በዳግም ልደቱ የሚያገኘውን የባሕሪይ ለውጥ ከመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ ጋር የተስማማ እንደሆነ ሲናገር እንጂ፥ ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑ የምንነት (Essence) ለውጥ ያገኛሉ ለማለት አይደለም፤ ጥቅሱ የአስተምህሮተ ደኅንነት (Doctrine of salvation) እንጂ የአስትምህሮተ-ሰው መመሥረቻ አይደለም::

ለ. የእግዚአብሔርን የኀሊና ጠባያት የሚያስረዱ ሐሳቦች

1. ጥበቡ

የእግዚአብሔር ጥበብ ማለት እርሱ ሁልጊዜ እጅግ ፍጹምና ጥሩ/መልካም የሆነ ግብ ይመርጣል፤ ግቡንም የሚመታበት መንገድ እንዲሁ እጅግ ፍጹምና ጥሩ የሆነ ነው ማለት ነው:: ይህ ትርጉም ከእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ጋር በላቀ መልኩ የሚጣመር ነው::

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ጥበብ በርካታ ማስረጃዎች አሉአቸው:: ሐዋርያው ጳውሎስ "ሊያበረታችሁ ለሚችለው *ብቻውን ጥበብ ላለው* ለእግዚአብሔር" ይላል (ሮሜ 16÷27):: ኢዮብ ደግሞ "*ልቡ ጠቢብ* ኃይሉም ታላቅ ነው" ይለዋል (ኢዮ.9÷4):: ደግሞም "*በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል አለ* ለእርሱ ምክርና ማስተዋል አለው:: "ይላል (ኢዮ.12÷13):: በተለይ የእግዚአብሔር ጥበብ በፍጥረቱ ላይ ረቂቅ ሆኖ ይታያል፤ መዝሙረኛውም "አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው *ሁሉን በጥበብ አደረግህ*' ይለዋል (መዝ.104÷24):: እግዚአብሔር አጥናፈ ዓለሙን ሲፈጥር ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ክብር እንደሚያመጣ አድርጎ በጥበብ ነው የፈጠረው:: የውድቀት ጠንቅ ከመጣ በኋላ እንኳን ፍጥረት የእግዚአብሔርን ክብር ማጉደፍ አልቻለም::

የእግዚአብሔር ጥበብ ታላቅ በሆነው የደኅንነት ዕቅዱ ውስጥም ታይቷል። ለተጠሩት ሁሉ ክርስቶስ "የእግዚአብሔር ኃይልና *የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው*" (1ቆሮ.1÷24-36)። በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀችው በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና" (1ቆሮ.1÷21፤27፤29)። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍና ቁጥሮች የሚናገረው ይሄ ለታናናሾች እንኳ ግልጽ የሆነው የወንጌል መልእክት÷ ጠሊቅ በሆነ ጠቢብነቱ የሰው ልጅ ከሚያስበው በላይ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ዕቅድ የሚያንጸባርቅ ነው በማለት ነው የሚገልጸው። ይህ የእግዚአብሔር ጠሊቅ ጥበብና ዕውቀት ያስደነቀው ጳውሎስ በግርምታ ውስጥ ሆኖ÷ በልቡ የምስጋና ጎርፍ እንዲህ እያለ ይጎርፋል:- "የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ የማይመረመር ነው÷ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም" (ሮሜ 11÷33)።

ሐዋርያው ጳወሎስ ወንጌልን ለአይሁዳውያንም ሆነ ለአሕዛብ በመስበክ በአንድነት የክርስቶስ አካል እንዲሆኑ አደረገ (ኤፌ.3÷6)። "ሁሉን በፈጠረው በእግዚአብሔር" ከዘላለም የተሰወረው ይህ ምሥጢር÷ በክርስቶስ በኩል ስብጥርጥር ያለውን የሰው ዘር አንድ በማድረግ ተገለጠ። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለዘላለም የሰወረውን ይህንን በክርስቶስ አካልነት (በቤተክርስቲያን) በኩል የሚገኘውን የሕዝቦች አንድነት የመስበክ ዕድል በማግኘቱ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

መቼም የማያምን (ከሀዲ) አእምሮ ስለ እግዚአብሔር ጥበብ ምንም ዓይነት ማስረጃ ቢሰጠው አያምንም። የአማኝ ልብ ደግሞ ስለ እግዚአበሔር ጥበብ ምንም ዓይነት ማስረጃ አያስፈልገውም፤ ያምናልና። "እግዚአብሔር ጠቢብ ነው" ብለን የምንሰጠው ማስረጃ ሁሉ በቂ ሆኖ አይደለም፤ ሌላ መግለጫ ስለሌለን ብቻ ነው የምንጠቀምበት። የእኛ መለኪያዎች አንጻራዊ (Rela- tive) ናቸው። የእርሱ ጥበብ ግን ከማንም ጋር ሊነጻጸር የማይችል ፍጹምነት (Absolute) ያለው ነው። የእርሱ የጥበቡ ትንሽ ጭላን ጭል በሚገለጥበት ጊዜ እንደ ኢዮብ እጅ በአፍ ላይ የመጫን ምላሽ ግድ ነው።[67]





የሰው ልጆች ስለእርሱ በሚሰጡት የተወላገደ ሐሳብ ማንነቱ አይዛባም፤ ቢሆንም ሰው ሁሉ ለዚህ ዓለምን ፍጹም በሆነ ጥበብ ላጸና ጌታ የበጎ ምግባር ምላሽ ይሰጥ ዘንድ ይጠበቅበታል። ይህንን አለማድረግ ግን በገዛ ማንነታችን ውስጥ ተቀምጦ ያለውንና ከአራዊቶች የተለየን የሚያደርገንን ማንነት መካድ ነው።

ቀደም ብሎ ስለ ጥበብ የሰጠነውን ትርጓሜ በሌላ አገላለጽ ብንጠቅሰው:- *ጥበብ ማለት የመጨረሻ ፍጹም በሆነ መንገድ በመጠቀም÷ የነገሮችን ፍጹም የሆነ ፍጻሜ ማከናወን መቻል ማለት ነው። ጥበብ÷ ያማረ ፍጻሜን ተምኖ ይጀምራል፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ጥበብ ፍጻሜን የሚያየው ጠብቆ ሳይሆን ገና ሳይጀምር ነው።* ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ማለት ይህ ነውና!

በእግዚአብሔር ዘንድ እያንዳንዱ ክንዋኔ ፍጹም በሆነ ጥበብ የተደረገ ነው። በመጀመሪያ ለራሱ ክብር÷ ከዚያም ለፍጥረት ጥቅም ያደርጋቸዋል። ድርጊቶቹ ሁሉ የጥበቡን ያህል ንጹሐን ናቸው። የትኛውም የእግዚአብሔር ድርጊት ከአምና ዘንድሮ አይሻሻልም፤ የረሳውን ትዝ ብሎት በመሀል አይከትም፤ ባለማድረጉ የቆጨው÷ በማድረጉ የጸጸተው ነገር የለም። ጸጸት ከእግዚአብሔር አኳያ ሲጠቀስ ከመሳሳት ጋር ተዛምዶ አይደለም።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የማዳን ስልትና የሰው ልጆችን ጥበብ ሲያመዛዝን÷ "ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቧ ስላላወቀች÷ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና። ... ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና÷ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና" (1ቆሮ.1÷20-25) በማለት ተናገረ። ይህ ሞገሳም ቃል የሰውና የእግዚአብሔር ልክ የት ድረስ እንደሆነ ምጸትኛ (Sarcastically) ይናገራል። የምድር አዋቂዎች ምርጥ አዕምሮ ሁሉ÷ ተሰብስቦ አንጎላቸው በአንድ የራስ ቅል ሆኖ በአንድ አንገት ቆሞ÷ የመጨረሻ ጥበቡን

ቢጠቀም፥ የእግዚአብሔር የኀሊና ክሂል ደግሞ (አይሆንም እንጂ ቢሆን) የመጨረሻ ሞኝነቱን ቢጠቀም ከዚህ ጭፍልቅ የሰው ጥበብ ይበልጣል ማለቱ ነው።

2. እውነተኛነቱ/ታማኝነቱ

የእግዚአብሐር እውነተኛነት ስንል እርሱ ራሱ እውነተኛ አምላክ ስለሆነ እውቀቱና ቃሉ ሁሉ በጣምራ እውነት ሆነው፥ የማንኛውም እውነት የተባለ ነገር ሁሉ የመጨረሻ የመለኪያ ደረጃ ናቸው ማለት ነው።

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተገለጠው አምላክ እውነተኛና ጭብጥ አምላክ ሲሆን። ሌሎች አማልክት ተብዬዎች ሁሉ ጣኦታት ናቸው፤ ደግሞም አጋንንት ናቸው (መዝ. 96፥5)።

> "እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው... ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ እነዚህ አማልክት ከምድር ላይ ከሰማይም በታች ይጠፋሉ... " (ኤር.10፥10-11)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ እግዚአብሔር አብ ሲናገር እንዲህ አለ፡- "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸው ንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናትና" (ዮሐ.17፥3፤ 1ዮሐ. 5፥20)።

እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ነው ስንል ዕውቀቱ ፍጹም ነው ከሚለው ሐሳብ ነጥለን አናየውም፤ "በዕውቀት ፍጹም የሆነው" ይለዋል (ኢዮ.37፥16)። እርሱ በሐሳቡ ያለ ዕውቀት ሁሉ እውነት ነው። ስለዚህ እኛ የምናስበው እና የምናውቀው ሙሉ በሙሉ ፍጹምና እውነተኛ ነው ለማለት የሚቻለው ከእግዚአ ብሔር ሐሳብና ከእግዚአብሔር ዕውቀት ጋር የተስማማ እንደሆነ ብቻ ነው። እርሱ እውነት የተባለ ነገር ሁሉ መለኪያ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር ሊታመኑበት የተገባ ነው። ከሚገባቸው ተስፋዎች አኳያም ሲታይ ታማኝነቱን ያጎድላል ብለን የማንጠረ ጥረው ሁልጊዜ የተስፋው ፈጻሚ ነው። "እርሱ አምላክ ነው ሥራውም ፍጹም ነው መንገዱም ሁሉ የቀና ነው የታመነ አምላክ





**ክፋትም የሌለበት እርሱ እውነተኛና ቅን ነው"(ዘዳ.32፥4)። ባጭሩ እግዚአብሔር ታማኝ ነው ማለት "አደርጋለሁ" ብሎ ቃል የገባ ውን ነገር ያደርገዋል ማለት ነው። "ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአ ብሔር ሰው አይደለም" ስለሚል (ዘኁ.23፥19፤ 2ሳሙ.7፥28፤ መዝ.141፥6)። እርሱ ሊደገፉበት የሚቻል ነው፤ የገባውን ተስፋ ላመኑ ሰዎች ፈጽሞውኑ ታማኝነቱን አጉድሎ አይገኝም። እግዚአ ብሔር ሲናገር ሁልጊዜ እውነት ይናገራል የውሸት ጠብታ በእርሱ ዘንድ የለም።**

**መቼም እግዚአብሔር የእነዚህ የሚወረሱና የማይወረሱ እያለን የምናጠናቸው ጠባያት ድምር እንዳልሆነ በሁሉ ዘንድ ሊታወቅ ይገባል። እርሱ ሁሉን በሁሉ የሆነ አምላክ ነውና። የጠባያቱ ሙሉ ግንዛቤ ሊኖረን የሚችለው፥ ሁሉን በአንድነት ስንገነዘብ ነው። እግዚአብሔር በራሱ ኀልው ከሆነ፥ በራሱ የበቃ መሆኑ ደግሞ ግድ ነው። በኢ-አላቂነቱ ደግሞ ኃይለኛ ከሆነ፥ ኃይል ሁሉ የእርሱ ነው። እንዲሁ አይለወጤነቱ (Immutability) ሲታሰብ ደግሞ የታማኝነቱን ቅደመ ግንዛቤ ይሰጠናል ማለት ነው። የማይለወጥ ከሆነ የማይታመን መሆን አይችልም። ምክንያቱም የማይታመን ለመሆን የሚለወጥ መሆን ያስፈልጋልና ነው። በግጻዌ መለኮት ዘንድ (With in the Godhead) አንዱ ጠባይ የአንደኛው ማብራሪያ ነው እንጂ አንዱ ጠባይ የአንደኛው ጎዶሎ መሙያ አይደለም። ልንገልጽ እየቃጣን ያለነው እኮ ስለ ፍጹሙ አምላክ ነው! እግዚአብሔር ይህንን ነገር አደረገ ብንል፥ ያደረገው ነገርና እርሱነቱ የተለያዩ አይደሉም። በእርሱ ዘንድ መሆንና ማድረግ አንድ ናቸው።[68]**

በዚህ ረገድ በትምህርታችንና በስብከቶቻችን ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስናስተምር፥ የዚህ ዓይነቱ የፍቅር ትምህርት እግዚአብሔር የፍርድም አምላክ መሆኑን ከገለጠው መጽሐፍ ውስጥ የወጣ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። እግዚአብሔር ሉዓላዊ (በሰማይና በምድር ባለመብት) ነው። ቢሆንም በአንምገነንነት ሁሉን እያነሳ እንደፈለገው የማያደርግ መልካምነትና ፍቅር ያለው አምላክ ነው።

ስለ እግዚአብሔር የአይለወጤነት ባሕርይ በሚታሰብበት ጊዜ አብሮት ያለው ታማኝነት የተባለ ጠባዩ ደግሞ ይታሰባል:: ይህም ማለት፥ በምንነቱ የማይለወጥ ከመሆኑ የተነሳ፥ ቃሎቹና ድርጊቶቹ ሁሉ ይታመናሉ ማለት ነው:: እንግዲህ በዘመን ፍጻሜ የምንጠብቀው "የተባረከ ተስፋ" ያረፈው በእንዲህ ዓይነቱ የታመነ አምላክ ላይ ነው:: ለገባልን የተስፋ ኪዳን እርግጠኞች ሆነን የምንጠብቀው ይህንኑ ታማኝነቱን በመተማመን ነው:: በሕይወት ውጣ ውርድ ተስፋ የቆረጥን፥ መጪውን ዓመት በፍርሃትና በጥርጥር የምንጠብቅ፥ እንዲሁም በልዩ ልዩ ፈተና ውስጥ ገብተን መውጫ ያጣን ሁሉ ለዝንጉ አእምሮአችን የእግዚአብሔርን ታማኝነት እናስታውሰው:: በቀደመው ኪዳን "አሁንም ያዕቆብ ሆይ፥ የፈጠረህ፥ እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ:: በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ነበልባሉም አይፈጅህም" ይላል (ኢሳ.43፥1-3):: ይልቁንም በልጁ ደም ኪዳን ከገባላቸው ጋርማ ታማኝነቱን እንዴት ይገልጥ!!

ይሄ የእግዚአብሔር እውነተኛነትና ታማኝነት ከሚወረሱ ባሕሪያቱ አንዱ ነው:: ባመኑትና መንፈሱን በተቀበሉት ሰዎች ውስጥ የዚህ ባሕሪ ነጸብራቅ ሊታይባቸው የተገባ ነው:: ቅዱስ እግዚአብሔር ባሕሪውን በሙላት የገለጠበትን መጻሕፍት ባጠኑና በመረመሩ ቁጥር ይሄ እውነት ሕይወታቸውን እየቀረጸ የታማኝ ነቱና የእውነተኛነቱ ባሕሪ ተካፋይ ይሆናሉ:: በፍጥረቱ ውስጥም ያለውን የእውነቱን ምስጢር ባወቁም መጠን "አቤቱ አሳቦችህ በእኔ ዘንድ እንደምን የከበሩ ናቸው ቁጥራቸውም እንደምን በዛ" ይላሉ (መዝ.139፥17):: የፍጥረትን ምስጢር በልዩ ልዩ ዓይነት የዕውቀት መስኮች ተሰማርተን ባወቅን መጠን እግዚአብሔር በስፋትና በጥልቀት ከሚያውቀው ዕውቀት መካፈላችን ነው:: በዚህ ባሕሪ እግዚአብሔርን መምሰላችን በእርሱ አምሳል የመፈጠራችን ምልክት ነው::

ከአፍ ለሚወጣው ቃል እውነትነት ግድ በሌለው ኅብረተሰብ ውስጥ ስንኖር፥ የእግዚአብሔር ልጅነታችንንም ሆነ የእርሱንም እውነተኛ ፈጣሪነት ከአፋችን በሚወጣው የእውነት





ቃል ማረጋገጥ አለብን:: በሕይወታችን የተናገርነውና የምንሆነው ነገር ተጋጭተው መገኘት የለባቸውም:: በቆላ.3፥9 ላይ "እርስ በርሳችሁ ውሸትን አትነጋገሩ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል ..."። ሌላም ይህንን የሚያጸኑ ጥቅሶችን (በኤፌ.4፥25፤ ምሳ.4:24፤ መዝ.19:14 ይመለከቷል)::

ሐ. ግብረገባዊ ጠባዩ[69]

1.ቸርነቱ

የእግዚአብሔር ቸርነት፥ ቸርነት ለተባለ ነገር ሁሉ የመጨረሻ መለኪያ ነው፤ ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ራሱም ሆነ እርሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ያለማወላወል ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል::

ቸር (ቸርነት) የሚለው ቃል መልካም (መልካምነት)፥ ደግነት ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው:: እግዚአብሔር ቸር ነው ስንል እግዚአብሔር መልካምና ደግ ነው ማለታችን ነው:: እርሱ የመልካም ነገር ሁሉ ጣራ ነው:: ስለዚህ ሊቀበሉት የተገባ ነው:: ቸርነቱን የሚያረጋግጥ ደግሞ ማንም ሳይሆን ራሱ ነው ምክንያቱም የመጨረሻው የቸርነት መለኪያ ራሱ ነውና ይህንንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያረጋግጥ "ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም" ብሎአል (ማር.10፥18):: ደግሞም መዝሙረኛው ዳዊት ይህንን ደጋግሞ ያጸናዋል "እግዚአ ብሔር ቸር፥ ምሕረቱም ለዘላለም፥ እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና" (መዝ.100፥5)፤ ደግሞም "ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ"(106፥1፤ 107፥1):: እንዲያውም ዳዊት ሌሎች ይህንን ያውቁ ዘንድ ሲያበረታታ እንዲህ ይላል፡- "እግዚአ ብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው" (መዝ. 34፥8)::

እንግዲህ ቸር ወይም መልካም ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ "እግዚአብሔር መልካም ነው" ብሉ ያጸደቀው ሁሉ መልካም ነው:: ከእርሱ የተለየ ከፍተኛ መለኪያ የለም:: ሆኖም የቸርነቱን ነጸብራቅ ለእኛም ስጥቶናልና እግዚአብሔር በሚለካበት

መንገድ ነገሮችን የምንለካ ከሆነ እኛም መልካም የሆነውን ነገር ማጽደቅ እንችላለን::

ከፍ ብሎ በተገለጠው የቸርነት ትርጉም ሙከራችን ላይ "እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ያለማወላወል ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል" ብለናል:: ይህንን የሚያረጋግጥልን መጽሐፍ ቅዱሳዊው የሥነ ፍጥረት ትረካ ነው:: ገና ከመጀመሪያው ፍጥረትን ኀልው አድርጎ ከጨረሰ በኋላ "እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ" ይላል (ዘፍ.1÷31):: መዝሙረኛው ዳዊትም የእግዚአብሔርን ቸርነት ከአድራጎቱ ጋራ በማያያዝ "አቤቱ አንተ ቸር ነህ በቸርነትህም ሥርዓትህን አስተምረኝ" ይላል (መዝ.119÷68):: ስለ እግዚአብሔር ቸርነት በምሥጋና የተሞላ መዝሙር (106 እንዲሁም 107) ናቸው:: በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን በጎና ቸር ፈቃድ እንድናውቅ ይመክረናል (ሮሜ 12÷2)::

ከዚህም ሌላ በዓለም ላይ ያለ መልካም ነገር ሁሉ ምንጩ እግዚአብሔር እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል:: "በጎ (መልካም) ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" ይላል (ያዕ.1÷17፤ መዝ.145÷9፤ የሐዋ.14÷17):: እግዚአብሔር ለልጆቹ ሁልጊዜ በጎ ነገር ብቻ ነው የሚያደርግላቸው "እግዚአብሔር ጠባቂያችንና ጋሻችን ነው ቸርነትንና ክብርን ያበዛልናል ደግ ለሚሠሩ ሰዎች ማናቸ ውንም ነገር አይከለክላቸውም" (መዝ. 84÷11)::

አማኞች ይህንን ጠባዩን ለመውረስ እኛ ራሳችን ቸርነትን መለማመድ አለብን:: ቸር የሆነውን ጌታ የሚያውቁ ሰዎች በልግስናቸው ላይ ጉድለትና መጸጸት የላቸውም፤ የተቀበሉት በቸርነት ነውና በቸርነት ይሰጣሉ ቸርነትንም ያሳያሉ:: "እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተሰዎች መልካም እናድርግ" (ገላ.6÷10፤ ሉቃ.6÷27-33፤35 2ጢሞ.3÷17):: ከዚህም ሌላ የቸርነት መተርጎሚያና ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ባወቅን ጊዜ ልንሻው የሚገባን የቸርነት ሁሉ መገኛ መሆኑን በመገንዘብ አብረን ከዳዊት ጋር "በሰማይ ከአንተ ሌላ ማን አለኝ? በምድርስ አንተን ካገኘሁ ሌላ ምን





እሻለሁ? አእምሮዬና ጉልበቴ ሊደክሙ ይችላሉ፤ እግዚአብሔር እስከ ዘላለም ብርታቴና እለኝታዬ ነው ማለት ብቻ ነው (መዝ. 73÷25፤ 16÷11፤ 42÷1-2)::

2. ፍቅሩ

የእግዚአብሔር ፍቅር ስንል፦ እግዚአብሔር ለዘላለም ራሱን ለሌሎች ይሰጣል ማለታችን ነው:: በዚህ ትርጉም መሠረት ፍቅር ማለት ራስን ለሌሎች ጥቅም ብሎ መስጠት ነው:: ይህ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚያሳየን ለሌሎች በረከትና ቸርነት ለማምጣት ሲል ራሱን መስጠት የእርሱ ጠባይ እንደሆነ ነው::

ዮሐንስ በመልእክቱ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ይለናል (1ዮሐ.4÷8)፤ ደግሞም በወንጌሉ ላይ በሥላሴ አካላት መካከል እንኳ ከፍጥረት በፊት ስላለው ዘላለማዊ ፍቅር ሲናገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ይላል፦ "አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ" (ዮሐ.17÷24):: ስለዚህ ከዘላለም አንስቶ ከአብ ዘንድ ለወልድ ፍቅርና ክብር ተሰጥቶታል፤ ምክንያቱም "አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል" ስለሚል (ዮሐ.3÷35):: ይህ ፍቅር ግን ከአብ ዘንድ ወደ ወልድ ብቻ ሳይሆን ወልድም እንዲሁ ዓይነት ፍቅር ለአብ አለው "ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድድ ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን ሁሉ እፈጽማለሁ" (ዮሐ.14÷31):: በአብና በወልድ መካከል ያለው ይህ የመለኮት ፍቅር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላቸውንም የፍቅር ኅብረት ይጠቀመናል:: እንዲህ ዓይነቱ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው መለኮታዊ የፍቅር ኅብረት መንግሥተ ሰማያትን ልዩ የፍቅርና የደስታ ዓለም አድርጎታል፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ የሥላሴ አካል የሌላኛውን አካል ደስታና ፍስሐ የሚፈልግ ስለሆነ:: ሆኖም ግን የሦስት አማልክት እይታ እንዳይኖረን ልንጠነቀቅ ይገባናል::

ይሄ በሥላሴ ዘንድ ያለ ራስን ለሌላ የመስጠት ባሕሪ እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የሆኑትን የሰው ልጆች የተገናኘበትን ጠባዩን ያሳየናል:: ስለዚህም በ1ዮሐ.4÷10 ላይ "ፍቅር ማለት እንዲህ ነው እኛ እግዚአብሔርን ስለ ወደድነው ሳይሆን እርሱ ስለ ወደደንና ኃጢአታችንን እንዲደመስስ ልጁን ስለ ላከልን ነው"

ሐዋርያው ጳውሎስም "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ5÷8)፡፡ ደግሞም በዮሐንስ 3÷16 ላይ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ይላል፡፡ እንደገናም ሐዋርያው ጳውሎስ በገላ. 2÷20 ላይ፡- "በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው"ይላል፡፡ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ባለ ኅብረትና ፍቅር መወደ ዳችንን ስናስብ ከፍተኛና እውነተኛ ሐሴት ሊሰማን የተገባ ነው፡፡

እኛ ይህንን መለኮታዊ የፍቅር ጠባይ ልናንጸባርቅ የምን ችለው መጀመሪያ ለእግዚአብሔር ፍቅር÷ የፍቅር ምላሽ ስንሰጥ ነው፡፡ ከዚያም ሌሎችን በመውደድ እግዚአብሔር ለእነርሱ እንዴት ያለ ፍቅር እንዳለው በመግለጽ ነው፡፡ ቅዱስ ቃሉ እኛ ከእግዚአብሔር አኳያ ያለብንን ግዴታ ሲነግረን "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፡፡ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት፡፡ ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች÷ እርስዋም÷ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት"ይለናል (ማቴ.22÷37-38)፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የምንወደው ከሆነ ደግሞ ትእዛዙን እንጠብቃለን ፈቃዱንም በማድረግ ደስ እናሰኘዋለን፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ከተጻፉት እውነቶች ሁሉ እጅግ የሚያስደንቀው እግዚአብሔር እኛን ለማስደሰት ራሱን መስጠቱ ብቻ ሳይሆን እኛም እራሳችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ እርሱም እጅግ ደስ የመሰኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ይህንን በትንቢታዊ ቃል ሲያጸና ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲህ ይላል፡- "ጎልማሳም ድንግሊቱን እንደሚያገባ እንዲሁ ልጆችሽ ያገቡሻል ሙሽራም በሙሽራይቱ ደስ እንደሚለው እንዲሁ <u>*አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል*</u>" (ኢሳ.62÷5)፡፡ እንዲሁም በትንቢተ ሰፎንያስ 3÷17-18 ላይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲህ የሚል የመጽናናት ቃል ተጽፎአል፡- "በዚያን ቀን ለኢየሩሳሌም ጽዮን ሆይ አትፍሪ እጆችሽም አይዛሉ አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃይል ነው በደስታ <u>*በአንቺ ደስ ይለዋል*</u> በፍቅሩም ያርፋል በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል" በእግዚአብሔር ደስ መሰኘት እጅግ ታላቅ ዕድል ቢሆንም÷ የሰው ልጅ ይህንን የአጥናፈ





ዓለሙን ጌታ የማስደሰት ዕድል እንዳለው ማወቁ ደግሞ እጅግ የላቀ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሲታወቅ ሰው በምድር ላይ የሚኖረው ኑሮ ታላቅ ለውጥ ያለው ይሆናል፡፡

እንግዲህ እኛ በፍቅር እግዚአብሔርን መምሰላችን ለሌሎች ሰዎች ባለን ፍቅር ይገለጣል፡፡ ዮሐንስ ይህንን ግልጽ አድርጎ ጽፎልናል፤ "ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል" (1ዮሐ. 4÷11)፡፡ እንዲያውም እኛ ለሌሎች ያለን ፍቅር ክርስቶስ በመካከላችን መኖሩንና እኛም የእርሱ መሆናችንን የሚገልጥ ነው፡፡ "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ" (ዮሐ.13÷35፤ 15÷13 ሮሜ 13÷10፤ 1ቆሮ. 13÷4-7፤ዕብ.10÷24)፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሌሎችን እንድንወድ የሚያስችለንን ፍቅር አልነፈገንም (ዮሐ.17÷26)፡፡ ከሁሉም በበለጠ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር መንጸባረቅ ያለበት ለሚጠሉን በምናሳየው ፍቅር ነው፡፡

### 3.ምሕረቱ÷ ጸጋውና ትዕግሥቱ

የእግዚአብሔር ምሕረት÷ ጸጋና ትዕግሥት በተናጠል ያሉ ጠባያቱ ወይም ደግሞ የቸርነቱ መግለጫ ዋና ዋና ነጥቦችም ሆነው ሊታዩ ይቻላል፡፡ አሁንም እኒህን ጠባያት ለመተርጎም ስንሞክር ከቸርነቱና ከበጎነቱ ጋር አዛምደን ነው፡፡

<u>*የእግዚአብሔር ምሕረት ማለት በመከራና በጭንቀት ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚገለጥ ቸርነቱ ማለት ነው፡፡ የእግዚአብ ሔር ጸጋ ማለት ፍርድ ብቻ ለተገባቸው ሰዎች የሚገለጠው ቸርነቱ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ማለት ደግሞ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ኃጢአትን ለሠሩ ሰዎች ፍርዱን ማዘግየቱ ነው፡፡*</u> እነዚህ ሦስት የእግዚአብሔር ጠባያት አብዛኛውን ጊዜ በጣምራ ሲጠቀሱ እንመለከታለን፤ በተለይም ይህ በብሉይ ኪዳን እውነት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ ማንነቱን በገለጠበት ጊዜ "እግዚአብሔር እግዚአብሔር መሐሪ ሞገስ ያለው ታጋሽም ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት" ይለዋል (ዘጸ.34÷6)፡፡ ዳዊትም በመዝሙሩ "እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው ከቁጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ" ይለዋል (መዝ103÷8)፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔር ጠባያት ብዙ

ጊዜ በአንድነት ስለሚጠቀሱ አንዱን ጠባይ ከአንዱ ለመለየት የሚያስቸግር ይመስላል። ሆኖም እያንዳንዱ ጠባይ ከተለያዩ የሰው ልጆች ችግሮች አንጻር ሲገለጹ ይስተዋላል። ለምሳሌ ዳዊት በ2ሳሙ.24÷14 "እጅግ ተጨንቄአለሁ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚ አብሔር እጅ ልውደቅ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው" ሐዋር ያው ጳውሎስ ደግሞ "የምሕረት አባትና የመጽናናት ሁሉ አምላክ ለሆነውና እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ለሆነው አምላክ ምስጋና ይሁን" ይላል (2ቆሮ.1÷3)። ደግሞም በሚያስ ፈልገን ጊዜ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ የዕብራውያን ጸሐፊ ያሳስበናል። "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈል ገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" ዕብ. 4÷16።

ደግሞም የእግዚአብሔር ትዕግሥት በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ተጠቅሶአል፤ ባጭሩ "ለቁጣ የዘገየ ነው" (ዘጸ.34÷6፤ ዘኁ. 14፡18፣ መዝ.86÷15፤ 103÷8፤ 145÷8፤ ዮናስ 4÷2፤ ናሆም 1፡3)። በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ ጳውሎስ "የመቻሉን የትዕግ ሥቱንም ባለ ጠግነት ትንቃለህን?" በማለት ይጠይቃል ሮሜ 2:4። ደግሞም ስለ ራሱ ሲናገር "ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ" ይላል (1ጢሞ. 1÷15-17፤ ሮሜ 9÷22፤ 1ጴጥ.3፥20)።

እኛም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት በውርስ ማንጸባረቅ እንዳለብን ሐዋርያው ያዕቆብ ይመክረናል "ስለዚህ÷ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፡ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን የሰው ቁጣ የእግዚአ ብሔርን ጽድቅ አይሠራምና" (ያቆ.1÷19)። በመከራም ውስጥ ክርስቶስ እንደ ታገሠ እንዲሁ መታገሥ የክርስቲያን ባሕሪ ሊሆን ይገባል (1ጴጥ.2÷20) ኑሮአችንም በትዕግሥት እንዲመራ ያስፈል ጋል። "በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ" (ኤፌ.4÷2)። እንዲሁም ትዕግሥት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎ ች እንደ አንዱ ተጠቅሶአል (ገላ.5÷22) ልንወርሳቸው እንደሚገ ቡን ሌሎች የእግዚአብሔር ጠባያት ሁሉ ቀስ በቀስ በእግዚአ ብሔር በመደገፍ የእግዚአብሔር ተስፋና ዓላማ እርሱ በፈቀደው





ሰዓት በሕይወታችን እንዲፈጸም የምናደርግበት አንዱ መንገድ ትዕግሥታችን ነው (ያዕ.5÷8)።

4. ቅዱስነቱ

የእግዚአብሔር ቅድስና ማለት እርሱ ፍጹም ከኃጢአት ተለይቶ በራሱ ክብር ይኖራል ማለት ነው። በዚህ ትርጉም ውስጥ ሁለት ነገሮች እንመለከታለን፤ አንደኛ ራሱ እግዚአብሔር በራሱ ያለውን ምግባራዊ ልቀት (Moral Quality) ማለትም ከኃጢአትና ከክፋት ተለይቶ ለበጎ መክበሩና ከፍ ማለቱ ሲሆን÷ ሌላው ደግሞ ከሌሎች ጋር ስለሚኖረው የግንኙነት ልቀት ነው።

በመጀመሪያ ቅዱስ ነው ስንል በቅድስናው ፈጽሞውኑ ልዩና ድንቅ ስለሆነ ተወዳዳሪ አይገኝለትም ማለታችን ነው። በዘጸ. 15÷11 "አቤቱ÷ በአማልክት መካከል እንዳተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ ድንቅንም የምታደርግ *በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?*" ይህንኑ የእግዚአብሔርን ከፍታና ልቀት በተመለከተ በ1ሳሙ.2÷2፤ ኢሳ.57÷15 ላይ ተጠቅሶአል። ኢሳይያስም ጌታን ባየ ጊዜ "እግዚአብሔርን አየሁት እርሱም ከፍ ባለና ልዕልና ባለው ዙፋን ላይ ተቀምጦ መጎናጸፊያውም ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበረ አንዱ መልአክ ከሌላው ጋር በመቀባበል "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ክብሩም በዓለም ሁሉ የሞላ ነው ይሉ ነበር" (ኢሳ.6፥1-6)። *ቅዱስ* የሚለው ቃል በዕብራይስጡ *"ቃዳሽ"* ሲሆን በቁሙ የተቀደሰ÷ ክቡር÷ ምስጉን፡ ልዩ፡ ምርጥ፡ ንጹህ ጽሩይ÷ እንደሆነ (በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 764) ላይ ተጠቅሷል። ቅዱስ የሚለው ቃል የተለየ የሚለውን ቃል የሚተካ ነው፤ ይህም "ከተራ" ወይም "ከተለ መደው" ነገር የተለየ ማለት ሲሆን÷ በእስራኤል የሃይማኖት ምግባር ውስጥ "ቃዳሽ" የሚለውን ቃል ለልዩ ልዩ የአምልኮ ተግባራት ለሚውሉ ቁሳቁሶች÷ ለድርጊቶች÷ ለአምልኮ ተሳታፊ ሰዎች እንዲሁም ለራሱ ለመለኮት ይጠቀሙበታል።

የእግዚአብሔር ቅዱስነት በአብዛኛው አምልኮተ እግዚአብ ሔር ከሚካሄድባቸው ወይም የእግዚአብሔር መገለጫዎች ከሆኑ

ብሉይ ኪዳናዊ ቁሳቁሶችና ሥፍራዎች ጋር በመያያዝ ሲጠቀስ እንመለከታለን። ለምሳሌ እግዚአብሔር ለሙሴ በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ሥፍራ ሲገለጥለት "አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው" (ዘጸ. 3፥5)። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በክብር በተገለጠበት ጊዜ፥ ከሙሴ በስተቀር ማንም በተራራው ድንበር እንኳ እንዳይቀርብ ተከልክሎአል (ዘዳ. 19)። እንዲሁም ቅድስተ ቅዱሳኑ ከቅድስት በመጋረጃ የተጋረደ ነበረ (ዘጸ.26፥33፤ 1ነገ. 6፥16) ። እግዚአብሔር የተለየ ስለመሆኑና ስለ ቅድስናው ከሰው የሚሰጠው ተገቢ ምላሽ አድናቆት፥ አክብሮታዊ ፍርሃትና ሥርዓት ያለው ምስጋና ነው። "እጅግ አስፈሪና ክቡር የሆነ ስሙን ሰው ሁሉ ያመሰግነዋል እርሱ ቅዱስ ነው" (መዝ 99፥3)።

ሌላው የእግዚአብሔር ቅድስና እይታችን፥ ፍጹም ከሆነው ንጽሕናውና በጎነቱ አንፃር ነው። ይህም ማለት እርሱ በዓለም ክፋት ያልተነካካና ያልተበከለ ነው ማለታችን ሲሆን በዚህ ጉዳይ በዓለም ስላለው ክፋት በምናስብበት ጊዜ፥ በማንኛውም ዓይነት መልኩ የእርሱ ተሳትፎ የለበትም። ነቢዩ ዕንባቆም ይህን አስመልክቶ ያለውን ልብ እንበል፤ "ዓይኖችህ ክፉ እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው ጠማምነትንም ትመለከት ዘንድ አትችልም" (ዕን.1፥43 ያዕ.1፥13)። ከዚህ አንፃር እግዚአብሔርን ስንመለከት ከሌሎች ሃይማኖት አማልክት ፈጽሞውኑ የተለየ ነው። እነኚህ አማልክት ከአምላኪዎቻቸው ክፉና ኃጢአተኛ ተግባር ጋር ይስማማሉ። እግዚአብሔር አምላክ ግን ከእንዲህ ዓይነት ተግባር የነጻ ነው። "በእውነት እግዚአብሔር ክፉ አይሠራም፥ ሁሉንም የሚችል አምላክ ፍርድን ጠማማ አያደርግም" (ኢዮ.34፥12)። ይህ ማለት ግን ያለ እርሱ ቁጥጥርና እውቀት የሚፈጸም ነገር አለ ማለት አይደለም፤ እርሱ የሁሉ ነገር ገዢ ነውና።

ይኼ የእግዚአብሔር ፍጹማዊነት የእምነታችን፥ ልምምዳች ንና የክርስቲያናዊ ምግባራችን መለኪያ ነው። ማንኛውም ምግ ባራዊ ቀኖናና (ትምህርት) ሥርዓት፥ የእርሱን ቅድስና ተከትሎ ይጓዛል። ለእስራኤል ሕዝብ ተናግሮአቸው የነበረውም ይኼንኑ ነው።

> "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ሰውነታችሁን ቀድሱ ቅዱሳንም ሁኑ እኔ ቅዱስ ነኝና፤ በምድርም ላይ በሚሳብ





> ተንቀሳቃሽ ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ። እኔ አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብጽ ምድር ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር ነኝ እንግዲህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ" (ዘሌ.11፥44-45፤ ዘሌ.19፥2፤ ማቴ.5፥48)።

*እርሱ እንከን የሌለው ከመሆኑ የተነሳ ማንኛውም ከእርሱ ጋር የሚነካኩ ነገሮች ሁሉ እንከን የለሽ ሊሆኑ ይገባል።* ቀሳውስቱ ሆኑ የመሥዋዕት እንስሳት ከእንከን የነጹ እንዲሆኑ ብሉይ ኪዳናዊ ትዕዛዝ አለ። (ዘሌ.1፥3፤10፤ 3፥1፤6፤ 4፥3) እንግዲህ የእግዚአብሔር ቅድስና ከባሕሪያቱ ሁሉ ዋነኛና የሁሉም ባሕርያቱ መገለጫ ነው። ከዚህም የተነሳ ቅዱሳት መጻሕፍት ለእግዚአብሔር ቅድስና ከፍተኛ አጽንኦት ሰጥተዋል። አማኞችም ይህንኑ የእግዚአብሔርን ጠባይ እንዲያንጸባርቁ መጻሕፍት ደጋግመው ተናግረዋል። "እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ጋር አይተባበርም ኃጢአትም በእርሱ ዘንድ የለም" ስንል እርሱ ባለበት ክፋትና ኃጢአት ሊገኝ አይቻልም ማለታችንም ጭምር ነው። እንግዲህ የእርሱ የሆኑት ሁሉ እርሱን ይመስሉ ዘንድ ቅድስናውን መከተል ይገባቸዋል። ኢሳይያስም እግዚአብሔርን ባየ ጊዜ እርሱ ንጽሕና እንደጎደለው ተመለከተ፤ "እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻ ለሁና ወዮልኝ አልሁ" (ኢሳ 6፥5)። ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ ኢየሱስ መሆኑን በተአምራዊ ሥራው በተገለ ጠለት ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ:- ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ አለው" (ሉቃ.5፥8)። እንግዲህ የቅድስና ልክ መመዘኛችን እኛ እርስ በእርስ አለን በምንለው ቅድስና ደረጃ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቅድስና አኳያ መሆን አለበት። ያን ጊዜ ማናችንም ብንሆን ጎዶሎ እንደሆንን እንገነዘባለን (2ቆሮ.6፥14-7፥1፤ 1ተሰ.3፥13፤ 4፥7፤ ኤፌ.5፥27፤ ራእ.15፥4)።

5 ሰላም/ሥርዓታዊነቱ

በ1ቆሮ.14፥33 ላይ "እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው" ይላል። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚገባው ጠባይ የቤተ

ክርስትያን መሥራች የሆነው የእግዚአብሔር ዓይነት ጠባይ ነው በማለት ይመክራል። በዚህ የጥቅስ ዐውድ መሠረት፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ማኅበረ ምዕመናን የእግዚአብሔር ድርጊት በባሕሪው፡- በሰላማ ዊነቱና በሥርዓታዊነቱ የሚታወቅ ስለሆነ፥ እርሱም ራሱ "የሰላም አምላክ" ስለሆነ፥ ማደሪያው የሆነች ቤተክርስቲያን የእርሱን ልዩ ልዩ መገለጦች በሰላማዊ መንገድና በሥርዓት ማስተላለፍ እንዳለባት አጥብቆ ያሳስባል (ሮሜ15፥33፤ 16፥20፤ ፊል.4፥9፤ 1ተሰ.5፥23፤ ዕብ.13፥20፤ ኤፌ.2፥20፤ 2ተሰ.3፥16)። በአመጽ ለሚሄዱ ግን ሰላምና ሥርዓት የላቸውም። "ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር" (ኢሳ.48፥22፤ 57፥21፤ 59፥8)። የእግዚአብሔር ሰላም ማለት እግዚአብሔር በማንነቱም ሆነ በድርጊቱ ከሁከትና ከሥርዓት አልበኛነት በመራቅ ማንነቱን ሕያው በሆነ ሁኔታ ለሰዎች ይገልጣል ማለት ነው። እግዚአብሔር በእንዲህ ዓይነት መልኩ ሰላማዊ ነው ስንል ከልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ራሱን አግልሎ ለብቻው በጸጥታ ይሆናል ማለት አይደለም። ይልቁንም በነቃ ሁኔታ፥ ሆኖና በሥርዓት ሐሳቡንና ፈቃዱን ለሕዝቡ በቃሉ መካከለኛነት በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይገልጣል ማለታችን ነው።





# ክፍል አራት
## ሰው

ሰው ከተፈጥሮው ማንነት የተነሳ የነገሮችን ትርጉምና ምንነት ሳይጠይቅ ያለፈበት ዘመን የለም። ለምን? እንዴት? መቼ? የት? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በማንኛውም የሙያ መስክ ለተሰማሩ ሰዎች ሁሉ የዕለት ተዕለት ቋንቋቸው ነው። ከዚህም የተነሳ "ዓለማት እንዴትና መቼ ተፈጠሩ?" "እንደ ፀሐይና ከዋክብት የመሳሰሉት ሰማያዊ አካላት ያለ ምንም ካስማ ሊንጠለጠሉ የቻሉት ከምን የተነሳ ነው? ደግሞም አንዳንድ እንስሳት በሰማይ ሲበሩ አንዳንዶች በምድር ላይ ይራመዳሉ፤ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?" የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቃሉ። እነዚህ ሁሉ ዕንቆቅልሾች ግማሽ መንገድ እንኳ አልተፈቱም። እንዳውም ጥያቄ ጥያቄን እየወለደ የኑሮን ምንነት ለተፈጥሮአዊው ሰው ውስብስብ አድርጎታል።

ከብዙ የኑሮ እንቆቅልሾች ውስጥ ዘመናትን ያስቆጠረውና የሰውን ከፍተኛ ትኩረት የጠየቀው የራሱ የሰው ልጅ አፈጣጠርና ምንነት ነው። መቼም በየዘመኑ የኖረ ሰው፥ ኋላ ቀር ነኝ ብሎ አያስብም፤ ሁሉም ለየዘመኑ ዘመናዊ ነውና። ታዲያ ይህ "ዘመናዊ ሰው" መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ "እኔ ማን ነኝ?" የሚለውን ጥያቄ ሲጠይቅ ቆይቷል። መልሱ ግን ቀላል አልሆነለትም። ቢሆንም ሰው በፍጥረት ታሪክ ውስጥ ድንገት ብቅ ያለ የራሱ ውጤት እንዳልሆነ ያውቀዋል። እስከ ዛሬ ድረስ ተፈጥሮአዊው ሰው የሰውን ማንነትና ምንነት ገና ጠየቀ እንጂ እቅጭ መልስ አላገኘም። "እኔ ማነኝ?" የሚል አጭር ጥያቄ ቢጠይቅም የሰው ልጅ መልሱን ፍለጋ ያልተንከራተተበት አገር የለም። የ"እኔ ማነኝ?" ጥያቄ ቢያንስ ቢያንስ ግልገል ጥያቄዎች ያስነሳል። ማን ፈጠረኝ? ከምን ተሠራሁ? በእኔ ውስጥ ያለው ነገር ምንድን ነው? እና የመሳሰሉት ናቸው።

"ሰው ምንድን ነው?" የሚለው መሠረታዊ የኑባሬ (Being) ጥያቄ እንዲህ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም። ሰው ውስብስብ ተፈጥሮ አለው። ከፍጥረት አንደኛው ክፍል ነው፤ ይሁን እንጂ ከፍጥረታዊ ማንነቱ በላይ የሆነ ማብራሪያን ጠያቂ

ማንነት አለው:: ፍቅርን የሚፈልግና የሚጠማ ቢሆንም፥ የሰው ልጅ ታሪክ ደግሞ በአብዛኛው ክፋትና ፍቅር የለሽ፥ ኢ-ሰብአዊም የሆነ ድርጊት ነው:: ለሥጋው ምቾት የምድር ኑሮውን በማቅለል እጹብ ድንቅ እርምጃን ቢራመድም፥ የነፍሱ ጥያቄ ከቁሳዊው ዓለም ባሻገር ካለው መንፈሳዊ ክልል የተንጠለጠለ ነው:: ከዚህ ማንነቱ የተነሳ ስለ ሰው በርካታ መላ ምት ብቻ የሆኑና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል:: ነገር ግን የትኞቹም ቢሆኑ በተግባር የታየውንና በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን የሰው ልጅ ማንነት ሙሉ ገጽታ አይሰጡም::

ሰው ስለ ራሱ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ብዙ ሲደክም ይታያል:: አብዛኛው ጥረቱም ራሱን ለማወቅ ነው:: በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ "ሰው ማነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተነሱ ብዙዎች ናቸው:: ከዚህም የተነሳ ሰውን ከተለያየ ነገር ጋር በማነጻጸር የሰውን ማንነት ለመግለጽ ሞክረዋል:: ለምሳሌ ሰው እንደ ማሽን ነው ብለው የሚያስቡ አሉ:: እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች፥ የሰው ምንነት ብያኔ የሚያገኘው፥ "ሰው ምን ሊሠራ ይችላል?" ከሚለው ጥያቄ በመነሳት ነው ብለው ያስባሉ:: እነዚህ ሰዎች የሰውን ማንነት የሚገነዘቡት ሰው ከሚሠራቸው ሥራዎች በመነሳት ነው:: ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ሰው ሥራ ሊሠራ እስከቻለ ድረስ ሰው ነው:: ትርፍ ማስገኘት እስከቻለ ድረስ ሰው ነው:: የሰው ዋጋ (ማንነት) የሚለካው በሥራው ነው:: ሥራ የማይሠራ ከሆነ ግን ሰው አይደለም:: ስለዚህ ቀጣሪ ተቀጣሪውን የሚፈልገው፥ ካለው ኃይልና ጉልበት፥ ከሚሰጠውም የሙያ ብቃት አኳያ ብቻ ነው:: በዚህ ሁኔታ ቀጣሪ የሚቀጥረውን ሰው በቀን የተወሰነ ሰዓት ይከራየዋል:: ስለዚህ በዚህ ረገድ የሰው ዋጋ የሚለካው፥ በሚሠራው ሥራና በሚያስገኘው ምርት/ትርፍ ነው::[70]

ዛሬ ይህን ዓይነት አመለካከት በቤተክርስቲያንም ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ሲንጸባረቅ ይስተዋላል:: ለሰዎች ዋጋ የምንሰጣቸው ለቤተክርስቲያን ምን ጥቅም ይሰጣሉ የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱልን ነው:: አልፎ አልፎም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አመራረጣችንና የአባላት ክትትላችን ላይ፥ ሰዎችን የምንፈልጋቸው ከሚሰጡት ጥቅምና የአገልግሎት አስተዋጽኦ አኳያ እንደሆነም ይስተዋላል:: ሰዎች የሚሰጣቸው ፋይዳ በእውቀት፥ በጉልበትና በንዋያ





ቸው እስከጠቀሙ ድረስ ብቻ ከሆነ፥ ቤተክርስቲያን ሰዎችን አገልጋይ ሳትሆን "ጠቃሚ" ሰዎችን እየመረጠች እንደማሽን የምትጠቀም ልትሆን ነው ማለት ነው:: እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ከዚህ አዝማሚያ ይጠብቅ!

"ሰው ማን ነው?" የሚለው ጥያቄ የሚሰጠው፥ ሌላ አመለካከት ደግሞ፥ "ሰው በግዛተ-እንስሳት (Animal kingdom) ማለትም እንስሳዊ ጠባይና ባሕሪ ባላቸው ፍጡራን መደብ ውስጥ የሚፈረጅ ነው የሚለው ነው:: ሰው በፍጥረት ሚዛን ሲመዘን በምንነት ልቀቱ (Qualitatively) ከሌሎች እንስሳት በምንም አይለይም፤ ብቸኛ ልዩነቱ የደረጃ ልዩነት ነው:: ይህም የሕይወት ልምድ ካዳበረለት የአንጎል-በቀል ክሂሉ (Cranial capacity) የተነሳ ነው:: በተረፈ ሁለቱም በአንድ ጎራ የሚመደቡ ናቸው፤ ሁለቱም አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉትም በአንድ ዓይነት የዕድገት ሂደት ውስጥ ካለፉ በኋላ ነው የሚሉ ናቸው:: በሰውና በእንስሳት መካከል ምንም ዓይነት የይዘት ልዩነት የለም:: ሁለቱም አንድ ዓይነት መጨረሻ አላቸው የሚል ነው::[71]

ስለዚህ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው፥ ለሰው ችግር ከሥነ ሕይወታዊ (Biological) ማብራሪያ ውጪ መፍትሄ እንዳለ አይገምቱም:: በአንዳንድ ቤተክርስቲያንም ውስጥ አልፎ አልፎ ሰውን አስመልክቶ ሊፈጠሩ ለሚችሉ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ክስተቶች፥ (ለበሽታ መለኮታዊ ፈውስ፥ ለሰዎች ከአጋንንት እስራት መፈታት) በአንዳንዶች ዘንድ የሚታየው ሁኔታውን ሳይንሳዊ ትንታኔ ብቻ የመስጠት አዝማሚያ ከዚህ ዓይነቱ አመለካከት የመጣ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ የሰው መንፈሳዊ ተፈጥሮ ለሚጠይቃቸው መንፈሳዊ ጥያቄዎች፥ ሥነ ሕይወታዊ (Biological) መልስ መስጠት መፍትሄ አይሆንም::

ከዚህ ሌላ ሰው የተፈጥሮ ዕድገት ከፍተኛ ውጤት ነው፤ የሚሉም አሉ:: በእንዲህ ዓይነቱ አመለካከት፥ የሰውን ተጨባጭ ማንነት መገንዘብ የሚቻለው፥ የሰው ባሕርይ በተወሰነ ታሪካዊና ማኅበራዊ ሥርዓት መወሰኑን ስንቀበል ነው:: ምክንያቱም ሰው የአዝጋሚ ለውጥ (Evolution) ሂደት ውጤት ነውና::[72] ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የሰውን አካላዊና መንፈሳዊ ትስስር በአንድነት

መመልከት አይችልም:: በዚህ አስተሳሰብ መሠረትም ሰው የሚባለው ግለሰብ ሳይሆን ማኅበራዊ ሰውን ብቻ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ለሰው መንፈሳዊ ማንነት ሥፍራ አይሰጥም:: ይህ የአስተሳሰብ ዝንባሌ ወደ ቤተክርስቲያንም በልዩ ልዩ ዓይነት ገጽታው ሲገባ ቤተክርስቲያን ከመንፈሳዊ ትኩረቷ በማፈግፈግ የእርዳታ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ብቻ እንድትሆን ያደርጋታል::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሐሳቦች ሰው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ከሚሰጡት መልሶች እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው:: እነዚህ መልሶች የሰውን ዋጋ ዝቅ የሚያደርጉና የሰውን ትክክለኛ ማንነት የማይገልጹ የተዛቡና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አመለካከቶች ናቸው:: ምክንያቱም ሰውን እንደ ዕቃ፥ እንደ እንስሳ ወይም እንደ ድንገተኛ የተፈጥሮ ሒደት ግኝት ያደርጋሉና ነው:: ሆኖም እነዚህ የአስተሳሰብ አቅጣጫዎች ሁሉ ሰው ስለ ራሱ በራሱ ሊያውቅ የሚችለው ጥቂቱን ብቻ እንደሆነ ያረጋግጡልናል:: በእነዚህ ሰው ስለ ራሱ በራሱ በሚሰጣቸው ብያኔዎች መሠረት፥ ያሉትን ሐሳቦች ስንመለከት ለምሳሌ:- "ሰው ዕቃ ነው" ካልን፥ ራሱን ሊያውቅ የሚችልበትን እድል ዘግተናል:: ሰው በዚህ አመለካከት ቢበዛ ራሱን ቢረዳ እልኳ ፥ ሌላውን ለማወቅ እንደሚችል ዕድል አይሰጠውም:: እንደገናም "ሰው እንስሳ ነው" ካልን በተወሰነ ሒደት ውስጥ የሚኖር፥ ምኞትና ዕውቀት፥ እምነትና ተስፋ የሚባሉና የመሳሰሉት ጠባያት የሌለው ስለሚያደርገው፥ ማንነቱን ሙሉ በሙሉ አያውቅም ማለት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ "ሰው የዝግመታዊ ለውጥ ውጤት ነው" ካልን፥ ለውጡ ቀጣይ በመሆኑ፥ ዛሬ ስለ ሰው የሚሰጠው የምንነት ትርጓሜ፥ በነገ የለውጥ ሒደት ስለሚለወጥ፥ የሰውን ተፈጥሮና ማንነት አስመልክቶ፥ ቋሚ ብያኔ ለመስጠት የማያስችል ያደርገዋል:: እኛ ግን ከታሪክ ገጽታና ከባሕል ነጸብራቅ መቀያየር በስተቀር፥ የሰው ማንነት የማይለወጥና ከጥንት እስከዛሬ ያው መሆኑን የምናስረዳው፥ ሠሪው/ፈጣሪው ስለ እጁ ሥራ ከሰጠው መግለጫ ተነስተን ነው:: እውነተኛው የሰው ማንነት እግዚአብሔር ራሱ የተናገረው ነውና!

በክርስቲያናዊ አመለካከት፥ የሰውን ተፈጥሮና ማንነት ለማወቅ የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ምዕራፍ ማየት ይበጃል





(ዘፍ.1፥26-27):: ይህ መረጃ ደግሞ የሚጠቁመን የሰው ማንነት የሚታወቀው ከእግዚአብሔር አንጻር ብቻ እንደሆነ ነው:: ስለዚህ በፍጥረቱ የአንድ ነገር አምሳያ ስለሆነ ነገር፥ ሙሉ ግንዛቤ ሊኖር የሚችለው መስለ የተባለው ዋነኛ ነገር ሲታወቅ ነው:: ከዚህም የተነሳ የሰውን ፈጣሪ ሳያውቁ ስለ ሰው ማንነት ለመናገር መሞከር ድምዳሜው ከስህተት አይጠራም:: በዚህችም አጭር መጽሐፍ ላይ አስቀድሞ እግዚአብሔርን ስለማወቅ ለማብራራት የተሞከረው ከዚሁ ግንዛቤ አንጻር ነው::

በክርስትና አስተምህሮአችን ውስጥ የሚነሱ ልዩ ልዩና ዋና ዋና ጥያቄዎች፥ አንደኛው ከአንዱ ሳይበላለጥ ሁሉም እኩል አስፈላጊዎች ናቸው:: ምክንያቱም በአንድ በተወሰነ ሥነ-መለኮታዊ ግንዛቤ የሚገጥመን ስህተት፥ ሌሎች ክርስቲያናዊ ግንዛቤዎቻችንን ሳይነካ ራሱን ችሎ የሚቀር ስለማይሆን ነው:: የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮዎች ተደራርቦ የተደረደረን ውድ ዕቃ ይመስላሉ አንዱ ያለአግባብ ሲነካ ድርድሩ መናዱ አይቀሬ ነው:: ስለዚህ ነው የአስተምህሮ ስህተት የንክኪነት ጠባይ ያለው:: ስለ መስቀል ያለን ግንዛቤ ከተወላገደ ደኅንነትን በቅጡ መገንዘብ አንችልም:: ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን ግንዛቤ ልክ ካልሆነ፥ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸውን መንገዶች በጠራ መልኩ ለመገንዘብ እንቸገራለን:: ስለዚህ ነው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በእኩል ዋጋ ያለው መሆኑ ታውቆ በጥንቃቄ ሊጠና የተገባው:: ይህ ሐሳብ እውነት መሆኑ ከታመነበት ደግሞ፥ የሰውን አፈጣጠር ባሕሪ፥ የተፈጠረበትን ዓላማና የፍጻሜ መድረሻውን ማወቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ ሆኖ እናገኘዋለን:: በዚህም በክፍል አራት ሰውን አስመልክቶ የተዘረዘረውም ሐሳብ ይህንኑ ከግምት ውስጥ በመክተት ነው::

## 1. አስተምህሮተ-ሰው (Doctrine of man) ለምን አስፈለገ?[73]

### 1.1 አስተምህሮተ-ሰው ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮዎች ጋር በመዛመዱ

አስተምህሮተ-ሰው ከዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ጋር በርካታ ተዛማጅነት አለው:: ሰው በምድር ካሉ

የእግዚአብሔር ፍጥረታት ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ነው:: ስለዚህ÷ ስለ ፈጣሪ ያለን ቁንጽል ዕውቀት መጠናዊ ስፋት የሚያገኘው ፍጥረትን በተለይም ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የሰውን ልጅ አፈጣጠር ስናጠናም ጭምር ነው:: ምክንያቱም ከፍጥረት ሁሉ በተለየ መልኩ ሰው "በእግዚአብሔር አምሳል" የተፈጠረ ስለሆነ (ዘፍ 1:26-27) የሰው ማንነት ሲጠና የእግዚአብሔር ጠባይ አብሮ መታየቱ አይቀርም ማለት ነው::

ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ስብእናን የተላበሰ መሆኑን ስለሚናገር÷ ስለ ሰው ለማጥናት በምናደርገው ሂደት ውስጥ ስለ ክርስቶስ ባሕሪ የጠራ ግንዛቤ ይኖረናል ማለት ነው:: በዚህም ሂደት ውስጥ አሁን ያለው የሰው ልጅ ተፈጥሮን÷ ከክርስቶስ ስብእና ጋር በማነጻጸር ሰው አስቀድሞ ታስቦለት የነበረውን የስብእና ደረጃ በክርስቶስ ኅልቶና ከብሮ እናየዋለን:: እግዚአብሔር ሰውን ባይፈጥር ኖሮ የክርስቶስ በሥጋ መገለጥም ሆነ የስርየት ሞቱ ባላስፈለገ ነበር:: ጽድቅና ቤተክርስቲያን የሚባል ነገርም አይኖርም ነበር::

በሥነ መለኮት ጥናት ላይ ያለ አማኝ አስተምህሮተ ሰውን በሚያጠናበት ጊዜ ራሱ ያ ሰው÷ የጥናቱ ማረፊያ (Object) ይሆናል:: ምክንያቱም አስተምህሮተ ሰውን ሲያጠና የሚያጠናው ስለ ራሱ ነውና:: ስለዚህ አስቀድሞ የጠራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮተ ሰው ግንዛቤ ያለው አማኝ የሚደርስባቸው ሌሎች ሥነ-መለኮታዊ መደምደሚያዎች ሁሉ ከተፋልሶ የተጠበቁ ይሆናሉ::

1.2. አስተምህሮተ ሰው የሰው አንገብጋቢ ፍላጎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጠት መገናኛ ነጥብ በመሆኑ

የሥነ-መለኮት ጥናት ንድፈ ሐሳባዊና ፍልስፍናዊ በሆኑ ሐሳቦች ላይ የተመሠረተ ሳይሆን እርግጠኛ እንዲሁም ተግባራዊና ዕለታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው:: ሆኖም ግን በአንዳንድ 'ዘመናውያን' አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ኅልውና÷ የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራና÷ ያደረገውንም ተአምራት ማመን 'ከዘመናዊ' አስተሳሰባቸው ጋር ስለሚጋጭባቸው ሊጠራጠ





ሩትና ላይቀበሉት ይችሉ ይሆናል:: እንዲህም ሆኖ ግን ማንም ሰው ስለሌለው ነገር ይጠራጠር እንጂ ስለ ራሱ ኅልውና እውነትነት አይጠራጠርም:: ሰው በድፍረት እግዚአብሔር የለም የሚለውን ያህል ሰው የሚባል የለም ማለት አይችልም:: ከዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ትኩረት ሁሉ የሰው ልጅ ጉዳይ ላይ ነው::

በየትኛውም ባሕልና አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ÷ ራሳቸውን ከግምት ውስጥ ሳይከቱ ግላዊም ሆነ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ እንደማያደርጉ የታመነ ነው:: እንዲህም ከመሆኑ የተነሳ ነው ስብከቶቻችንም ሆነ ትምህርቶቻችን ተዛምዶአቸው (Applications) የሰዎች የዕለት ተዕለት ጉዳይ ላይ ማተኮር አለባቸው የምንለው:: የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮተ-ሰው ጥናትም የሰውን ማንነት ለሚጠይቀው ለራሱ ለሰው ልጅ ኅሊና መልስ ለመስጠት የሚሞክረው ከዚህ አንጻር ነው:: ማን ነኝ? ምንድን ነኝ? ከየት መጣሁ? ወዴት እሄዳለሁ? የመኖሬስ ዓላማ ምንድን ነው? ለሚለው የሰው ልጅ አንገብጋቢ ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ ግልጠት በመነሳት መልስ ለመስጠት የሚሞክረው ይኸው መጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮተ ሰው ነው::

1.3 የዘመኑ ተምህሮአውያን (Scholars) ከፍተኛ ትኩረት ሰው በመሆኑ

በዚህ ዘመን በርካታ የእምነትና የዕውቀት መስኮች÷ በራሱ በሰው ልጅ የማንነት ትንታኔ ላይ ውስብስብና ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውበታል:: (ጥቂቶቹን በዚህ ክፍል መጀመሪያ ባለው መንደርደሪያ ላይ ተመልክተናቸዋል) እነዚህ የትኩረታቸው ማዕከል የሰው ልጅ የሆነ እምነቶች በኃይለኛ ፍጥነትና ብዛት እያደጉ ነው:: ከዚህ በፊት ተዳስሰው የማያውቁ የባሕርይ ጥናትና ሳይንሶች በታላላቅ የትምህርት ተቋማት በፍጥነት ብቅ ብቅ እያሉ ነው:: የሕክምና ትምህርት ቤቶችም ሕመምንና የሕመም ምልክቶችን ዶክተሮች ሳይሆኑ እራሳቸው ታማሚዎቹ የሰው ልጆች ሊያክሙአቸው ስለሚችሉ ታማሚው ራሱም የፈውስ ማዕከል እንደሚሆን ይገምታሉ:: እንዲህም እያሉ ይጠይቃሉ "የሰው ተፈጥሮ ምንድን ነው?" "ለሰውስ ጥሩው ነገር የትኛው ነው?" ባጠቃላይ የፖለቲካው÷ የሥነ ማኅበረሰቡም ሆነ የኤኮኖ

ሚው የዕውቀት መስክ ትኩረት ሰው የሚባለው ፍጡር ላይ ነው:: ስለዚህ የሰውን የማንነት ትርጉም ፍለጋ ለሚደናበረው ለራሱ ለሰው ልጅ ከይሁንታ መልስ ይልቅ ሥልጣናዊ መልስ የሚሰጥ የሰው ልጅ ባለቤት በሆነ በፈጣሪ ቃል ላይ የተመሠረተ አስተምህ ሮተ-ሰው አስፈላጊም አስቸኳይም ነው:: ምክንያቱም ዋነኛ የሆነው የማንነታችን ግንዛቤም ሆነ የኢ-ክርስቲያናዊው ሥነ- ሰው (Non-Christian Anthropology) ግራ መጋባት መልስ የሚያገ ኘው ከዚሁ ከፈጣሪ ቃል ከሚገኘው አስተሳሰብ ብቻ ነው::

"ስለ ሰው ማጥናት ለምን አስፈለገ?" ለሚለው ጥያቄ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሦስት ምክንያቶች ሌላ በርካታ ተመሳሳይ ሐሳቦች ሊቀርቡ እንደሚችሉ የታመነ ነው:: ምክንያቱም ሰው የራሱን ማንነት ፍለጋ የደረሰበት መከራ ጣጣ ብዙ ነው፣ ይህ ጮርቃ ሕፃናት ገና በሁለት እግራቸው ቆመው መሄድ ሲጀምሩ የሚጠይቁት "የማነኝ?" "ምንድን ነኝ?" ጥያቄ ሰፊ ነው:: ግማሹ ከዝንጀሮ መጣሁ ሲል ከፊሉ ደግሞ የአምላክ ዝርያ ነኝ ይላል:: ታዲያ ቤተክርስቲያንም ውስጥ ያሉ የሰው ልጆች ናቸው:: በአንድም በሌላም "የማነኝ ምንድንነኝ ?" ጥያቄ ሳይነካትለን አያልፍም:: እንግዲህ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ የትምህ ርታችንም ሆነ የስብከታችን መልክ የሚወሰነው ባለን የአስተም ህሮተ-ሰው ግንዛቤአችን ልቀት (Quality) ነው:: የሰው ማንነት ዋነኛው ነገር ተዳሳሽ (ሥጋዊ) ኀልውናው ላይ ነው ካልን፥ የአስተምህሮአችን ትኩረት የሰው የሥጋ ምቾት ላይ ብቻ ያደላል:: ደግሞም ሰው ዋነኛ ኀልውናውን ያስገኘለት ምክኑያዊ ፍጡር (Rational being) መሆኑ ብቻ ነው ብንል፥ የአገልግሎ ታችን ትኩረት የሰውን የኅሊና ጥያቄ ብቻ ለመመለስ የሚሞክር ይሆንብናል:: ደግሞም በአንፃሩ ሰውን በስሜታዊነቱ ብቻ የምንገነዘብ ከሆነ ለሰው ያለን አገልግሎት ስሜቱን ከማነቃቃት አልፎ እውነቱን የማያስጨብጥ ይሆንብናል:: ከዚህ የተነሳ ትክክለኛውን የሰውን ማንነትና ምንነት በመረዳት በትክክለኛው ትምህርተ-መለኮት ላይ የተመሠረተ የአስተምህሮተ- ሰው ግንዛቤ መውሰድ የእውነተኛ ደቀ መዛሙርት መንፈሳዊ ኃላፊነትና ግዴታ ነው:: ይህ ደግሞ ከዘላለም ጉዳይ ጋር አጥብቆ የተያያዘ በመሆኑ "ሰው ለምን ተፈጠረ?" "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ ስንል ምን ማለታችን ነው?" "የሰው ዋነኛና መሠረታዊ





ተፈጥሮ የትኛው ነው?" የሚሉትንና ሌሎች ዝርዝር ሐሳቦችን መመልከት የእምነት ግዴታችን ነው:: ይህንንም በሚቀጥሉት ገጾች በአሰሳ መልክ እንመለከታለን::

2. ሰው ለምን ተፈጠረ?

2.1 እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ሰውን ፈጠረው

በዚሁ ጽሑፍ ክፍል ሦስት ላይ በ3.1.ሀ ተብራርቶ እንደተገለጸው፥ እግዚአብሔር ነፃ እና በራሱ ኅልው ከመሆኑ የተነሳ ለማንምና በምንም ነገር መቼውንም ቢሆን ጥገኛ አለመሆኑን አስተውለናል:: ለእርሱ ኅልውና እኛም ሆንን ሌሎች ፍጥረታት አናስፈልገውም:: ሆኖም ግን እኛም ሆንን ሌሎቹ ፍጥረታት እግዚአብሔርን ልናከብረውና ደስ ልናሰኘው እንች ላለን:: የኅልውናው መሠረት ያረፈው ሌላ አካል ላይ ሳይሆን በራሱ ስለሆነ እርሱ ፍጥረትንም ባይፈጥር ለብቻው አንዳች ነገር ሳይጎድለው መኖር የሚችል ጌታ ነው::

ሆኖም እግዚአብሔር እኛንም ሆነ ሌሎቹን ፍጥረታት ለራሱ ክብር ሲል ፈጥሮአል:: እግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች ልጆቹን ከምድር ዳርቻ ጠራቸው እንዲህም አለ *"በስሜ የተጠራውን ለክብሬም የፈጠርሁትን የሠራሁትንና ያደረግሁትን ሁሉ አምጣ እለዋለሁ"* (ኢሳ.43፥7፤ ኤፌ.1፥11-12):: ስለዚህ *"...ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት"* ለሚለው ቃል ባለዕዳዎች ነን (1ቆሮ 10፥31)::

እዚህ ላይ ስለ ሰው አፈጣጠር በቂ የሆነ ትምህርተ-መለኮታዊ ግንዛቤ መውሰድ አስፈላጊ ነው:: ገና በመጀመሪያው ስለ ሰው ስናወራ "የተፈጠረ" ነው ስንል ለኅልውናው ጥገኛነቱን አሜን ማለታችን ነው:: ሰው ሕያው የሆነ ፍጡር ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር እንዲኖር ስለፈቀደና እንዲኖርም ስላደረገው ብቻ ነው:: ሰው ከመጀመሪያው አንስቶ ሕይወቱን የተቀበለው ከእግዚአብሔር ነው:: በዘመናት ውስጥም ዘልቆ ያለው በአምላክ የማያቋርጥ ዕርዳታና መግቦት (Providence) ነው:: "...በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን" (የሐዋ.17፥28)

የሚለው ቃል የታመነ ነው:: ነገር ግን÷ ሰው "በራሴ ለራሴ" የበቃሁ ነኝ የማንንም እና የምንም ነገር ድጋፍ አልፈልግም÷ "ለእኔ ጎላዊ ሰበቡ እኔው ነኝ" ሊል ይችል ይሆናል፤ ሆኖም ግን ይህ የጥገኝነቱን መሠረታዊ እውነት ሊፍቅ የሚችል ሙግት አይደለም:: ምክንያቱም የሰው ልጅ የኀልውና ታሪክ ሰው ሁልጊዜ ለመሰሉ የሰው ዘርም ሆነ ለፍጥረታት ጥገኛ መሆኑን ይመሰክራልና ነው:: ከባቢው አየር ከአፍንጫው ከመቅስፈት ቢወሰድበት ኀልውናው ወዲያው የሚያከትም ፍጡር ነው:: የሰው ባለቤት የሆነው ፈጣሪም ስለ ሰው በፍጥረትና በፈጣሪ ላይ ጥገኝነት÷ እንዲህ ብሎ ይናገራል:- *"እስትንፋሱ በአፍንጫው ያለበትን ሰው ተውት፤ እርሱ ስለ ምን ይቆጠራል?"* (ኢሳ.2÷22):: ስለዚህ ሰው ለሰከንዳዊ ኀልውናው እንኳ በፍጹም ለራሱ በራሱ የበቃ አይደለም:: እንግዲህ እኛ እንደ ሰው ልጅነታችን የምንኖረው ለእግዚአብሔር ነው እንጂ ለራሳችን አይደለም:: የሰው ልጅ የአጥናፈ ዓለሙ ማዕከል ለመሆን የሚያስችል ማንነት ከቶውንም የለውም:: እኛ የሆንነው ነገርም ሆነ የእኛ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ከእርሱ የመነጩና የተገኙ ናቸው:: ስለዚህ እኛ ለራሳችንም ሆነ በይዞታችን ሥር ላሉ ማንኛውም ነገሮች ባለአደራዎች ነን:: ለአደራ ሰጪው የሰጠንን አደራ ከፍለን ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ነው መልሰን የምንሰጠው:: ጊዜአችን÷ ገንዘባችን÷ እኛነታችን እንዲሁም የሕይታችን ሁለንተና በእኛ ላይ ላለው የማያቋርጥ ባለቤትነቱ ተመልሶ ሊሰጠው የተገባ ነው:: *<u>በዚህም ለእርሱ እንደሰጠታ ሳይሆን መብቱ እንደተከበረ ይቆጠራል:: ምክንያቱም ሁሉ ለራሱ ክብርና በራሱ የተሰራ ነውና፤ ሁሉን ሊገለገልበትና ሊከብርበት መብቱ ነው:: "ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን" (ሮሜ 11÷36)::</u>*

ይሄንን ደግሞ በቅጡ ስንገነዘብ የሰው የመጨረሻው ፋይዳ (Value) ያለው በራሱ በሰው ዘንድ ሳይሆን÷ ይልቁንም ለክብሩ በፈጠረውና የላቀ ፋይዳ ባለው ከፍተኛ አምላክ ዘንድ መሆኑን እናስተውላለን:: *<u>ስለዚህ ሰውንም ጨምሮ የማንኛውም ዓይነት ነገር ልክታ ሲገመገም ለሰው ደስታና ምቾት ከመስጠቱ አኳያ ሳይሆን የእግዚአብሔር ዕቅድ መፈጸሙንና ያ ነገር ለእግዚአ ብሔር ክብር አስተዋጽኦ ማድረጉን ከማሰብ አኳያ ብቻ ነው::</u>*





*<u>እንዲህ ሲሆን ደግሞ የአጥናፈ ዓለሙ ማዕከል ሰው መሆኑ ያከትማል:: ምክንያቱም እርሱም ራሱ ከራሱ ፍጹም በበለጠ ፈጣሪ ኀልውናን ያገኘ ነውና::</u>*

እስከአሁን ያየነው ስለ ሰው የማንነት አስተምህሮ በቂ የመንደርደሪያ ሐሳብ ሊሰጠን እንደቻለ እንገምታለን:: ስለዚህ እኛ ማን ነን? የሚለው ጥያቄ ሊመለስ ሲሞከር እኛ ከየት መጣን? የሚለው ጥያቄ ራሱ መልስ ነው:: ምክንያቱም እውነተኛ የማንነት ጥያቄ "ምንድን ነኝ?" የሚለው ሳይሆን "ማን ፈጠረኝ?" የሚለው ስለሆነ :: ለዚህም መልሱ ሰው በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረትና ለእግዚአብሔር ክብር በራሱ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ፍጡር ነው:: ስለሆነም የሰው የማንነት ጥያቄ የመለኮትን ዕቅድ ማሟላቱና አለማሟላቱ ላይ የሚያርፍ ነው::

ሰው የእግዚአብሔር ፍጡር ነው እንጂ ከእግዚአብሔር የተቆረሰ ወይም የተከፈለ የመለኮት ክፋይ አይደለም:: በውስንነት የተገደበ ነው:: ሁሉን አዋቂና ሁሉን አድራጊም አይደለም:: ምንም እንኳ አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው እርቅ መለኮታዊ ተራክቦ (ኅብረት ማድረግ) ቢችሉም÷ ነገር ግን ሰው እንደ መሆናቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ዲበ-አካላዊ (Methaphysical) ልዩነት የዘላለም ጉዳይ ነው:: ይሄ ዲበ-አካላዊ ልዩነት ደግሞ በሰውና በሌሎች ፍጥረታት መካከል ሳይሆን ሰውን ጨምሮ በፍጥረታትና በእግዚአብሔር መካከል ነው:: ፍጥረት በቀናት ቅደም ተከተል ሲፈጠሩ ሰውም በተመደበለት ቀን የተፈጠረ መሆኑን ስንመለከት÷ ሰው ፈጣሪ ከሆነ ከእግዚአብሔር ወገን የሚመደብ ሳይሆን ከፍጡራን ወገን የሚመደብ ነው:: እንዲያውም በፍጥረት መካከል ያለውን ግብቡ ሥርዓት ያበላሹ ሌሎች ፍጥረታት ሳይሆኑ ሰው ነው:: እርግጥ ነው ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ለሰው ጥቅም እንዲሰጡ ሰውም በዚህ እግዚአብሔርን እንዲያከብር ተፈጥረዋል:: ሆኖም ግን ሰው እንደሌሎች እንስሳት የፍላጎት ተመሳሳይነት ስላለው አሁንም ፍጡር እንጂ ቅንጣት አምላክነት የለውም::

ነገር ግን ሰው ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ልዩ ሥፍራ አለው:: በእርግጥ ቀደም ባሉት አንቀጾች ሰው ፍጡር ስለሆነ ከሌሎች

ፍጥረታት ጋር የሚጋራው መሠረታዊ የጠባይ አንድነት አለው ብለናል። ሆኖም ግን የዛኑ ያህል ሰውን ከሌሎች ፍጥረታት ያላቀውና ልዩ ያደረገው ጠባይም አለ። ሌሎች "እንደ ወገኑ" በሚል ቃል ሲፈጠሩ ሰው ግን ሲፈጠር "በመልካችን እንደ ምሳሌ አችን እንፍጠር" ተባለለት። ስለዚህ በሌሎች ፍጥረታት ላይ በመግዛት ተፈጠረ (ዘፍ.1÷26)። ሆኖም ግን በፍጥረት ላይ ለሚሰለጥነው ሕግ ሁሉ ተገዢነቱ እንደተጠበቀ ነው። ሰው እንደፍጡርነቱ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር በእህል ውሃ ፍላጎቱ ቢመሳሰልም በእግዚአብሔር አምሳል ከመፈጠሩ የተነሳ መንፈሳዊ ጠባይ ስላለው ከሌሎቹ ፍጥረታት ይለያል።

2.2 ሰው የሕይወቱ ዓላማ ምንድን ነው?

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው "እግዚአብሔር ሰውን ለራሱ ክብር ፈጠረው" የሚለው እውነት ነው። የመፈጠራችን ዓላማ ምንድን ነው? አጭሩ መልስ እግዚአብሔር ሲፈጥረን ያሰበውን ዓላማ ለማሟላት መተባበር ነው። ያም እርሱን ማክበር ነው። በሌላ አነጋገር "ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረው እግዚአብሔርን እንዲያከብርና እንዲህም በማድረጉ ለዘላለም በእርሱ ደስ እየተሰኘ እንዲኖር ነው። "(To glorify God and enjoy him for ever)"።[74] ይህ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ እና ሊኖር የሚገባ አስደናቂ ግንኙነት ነው። ክርስቶስም የተገለጠው እንዲህ ዓይነት ሕይወት እንዲሰጠን ነው። ደግሞ ገና በብሉይ ኪዳን÷ የመፈጠሩ ዓላማ የገባው ንጉሥ ዳዊት÷ "የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ÷ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ አለ" በማለት ዘመረ (መዝ.16÷11)። እንዲሁ ሌዋዊው አሳፍ ደግሞ የእግዚአብሔርን ነገር በተጠማች ነፍስ እንዲህ አለ:-

"በሰማይ ከአንተ ሌላ ማን አለኝ?
በምድርስ አንተን ካገኘሁ÷ ሌላ ምን እሻለሁ?
አእምሮዬና ጉልበቴ ሊደክሙ ይችላሉ፤
እግዚአብሔር ግን እስከ ዘላለም ብርታቴና
አለኝታዬ ነው" (መዝ.73÷25-26 አዲስ ትርጉም)።





ፍጹምና ሙሉ ደስታ የሚገኘው እግዚአብሔርን በተፈጠርንበት ዓላማ ስናውቀው ብቻ ነው። ሰው ሊያስበውና ሊደክምለት የሚገባው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ የሚገኘውን ደስታ ለማግኘት ብቻ ነው፤ ይህ የሰው ሁለንተና ነውና።

"የሠራዊት አምላክ ሆይ÷ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው!
ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅ ማለች፤
ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኙ"
(መዝ.84÷1-2)።

"በሌላ ስፍራ አንድ ሺ ቀን ከመቆየት÷ በመቅደስህ
አንድ ቀን መዋል የተሻለ ነው፤
በክፋዎች ቤት ተመችቶኝ ከምኖር ይልቅ÷በእግዚአብሔር ቤት ደጅ እየጠናሁ መኖርን እመርጣለሁ"(መዝ.84:10 አዲስ ትርጉም)።

እንግዲህ በጌታና እርሱም በሚሰጠው ሕይወት ደስ መሰኘት የጤናማ ክርስቲያኖች የልብ ዝንባሌ ሊሆን ይገባል (ሮሜ 5÷2-3፤ ፊል.4÷4፤ 1ተሰ. 5÷16-18፤ ያዕ.1÷2፤ 1ጴጥ.1÷6-8)። እኛ እግዚአብሔርን ባከበርንና በእርሱም ደስ በተሰኘን መጠን እርሱም በእኛ እንዲሁ ደስ እንደሚሰኝ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። "ሙሽራው በሙሽራይቱ ደስ እንደሚለው እንዲሁ አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል" (ኢሳ. 62÷5)። "አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃይል ነው በደስታ በአንቺ ደስ ይለዋል በፍቅሩም ያርፋል በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል ይላል" (ሰፎ.3÷17)። የተፈጠርንበት ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት መሆኑን አውቀን ለዚህ ዓላማ ግብ መምታት ጥረት ማድረግ ስንጀምር አይተነው ከምናውቀው ደስታ የላቀ÷ ደስታ መለማመድ እንጀምራለን።

3. ሰው "በእግዚአብሔር አምሳል"

በከተማ የምንኖር ሰዎች የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ልዩ ልዩ እቃዎችን እንጠቀማለን፤ ከእነዚህም ውስጥ÷ ሜካኒካል የሆኑ

ማሽኖች፥ የኤሌክትሪክ እቃዎችና ልዩ ልዩ መድኃኒቶች ይገኙባቸዋል:: በተለይ እንደ ኤሌክትሪክና መድኃኒት የመሳሰሉትን እቃዎች ስንገዛ እቃዎቹ በሚቀመጡበት ካርቶን ውስጥ ምንነታቸውንና አጠቃቀማቸውን የሚያስረዳ መምሪያ (Manual) እናገኛለን:: ይሄ መምሪያ ደግሞ እቃዎቹን በሚሸጡ ወይም በሚያከፋፍሉ ሰዎች የተጻፈ ሳይሆን፥ እቃዎቹን ባበጁአቸውና በሠሩአቸው ሰዎች ነው:: ነገር ግን ብዙ ሰዎች የኤሌክትሪክ እቃዎችንም ሆነ መድኃኒቶችን፥ ፋብሪካው የሠራውን መምሪያ ሳያነቡ ይጠቀማሉ:: ይህንን የሚያደርጉትም እቃዎቹን ከሠሯቸው ሰዎች ይልቅ "እኔ አቃቸዋለሁ" የሚል ስሜት ሲያድርባቸው ነው:: ነገር ግን የአንድን ፋብሪካ ወይም ኢንዱስትሪ ውጤት ከአምራቹ ይልቅ አከፋፋዩ፥ ቸርቻሪው ወይም ተጠቃሚው ሊያወቅ አይችልም:: ስለ እቃው ሙሉ እውቀት የሚኖረው፥ እቃውን የሠራው ብቻ ነው:: ፋብሪካዎች ደግሞ ስለ ምርቶቻቸው ምንነትና አጠቃቀም ሙሉ ሐሳባቸውን ወይም ተጠቃሚው ሊያውቀው የሚገባውን ያህል በመምሪያው ላይ በዝርዝር ጽፈዋል:: መምሪያውን በትክክል ማንበብ ማለት እቃውን አስመልክቶ የአምራቹን አዕምሮ ማንበብ ማለት ነው:: ሰውም ቢሆን ስለ ራሱ ለማወቅ "እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም" (መዝ.100፥3) ለሚለው ቃል በመገዛት፥ እኔን የሰራኝና ያበጀኝ ስለ እኔ አሠራር ምን ያለውና የተናገረው ነገር አለ? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ይገባዋል:: እንግዲህ ከሥነ-መለኮታዊው ትንታኔ ውጪ ሊጠየቁ የሚሞከሩ የ"ማን ነኝ?" "ምንድን ነኝ?" ጥያቄዎች ሁሉ ትክክለኛ መልስ ሊያገኙ የሚችሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር ሲስማሙ ብቻ ነው ማለት ነው::[75]

ይህም መጽሐፍ ስለ ሰው አፈጣጠር እንደዚህ ብሎ ይናገራል:: "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን _ከምድር አፈር_ አበጀው" በአፍንጫውም የሕይወት _እስትንፋስን እፍ አለበት_" (ዘፍ.2፥7):: እንግዲህ ሰው፥ ከምድር አፈር በመበጀቱ እንደሌሎች ፍጥረታት ቢቆጠርም፥ በአፍንጫው የተደረገለት የመለኮት እስትንፋስ ደግሞ ከፍጥረት የመጠቀ ያደርገዋል:: በምንነቱ ከሌሎች ፍጥረታት የሚጋራ ቢሆንም፥ ከአምላክ ጋር ኅብረት ማድረግ መቻሉ ደግሞ ከቀረው ፍጥረት የተለየ ያደርገዋል:: ከዚህ የተነሳ የሰው ሥነ-ኑባሬአዊ አካል (Ontological Structure) የሁለታዊነት፥





ማለትም "መንፈሳዊ"ና "ቁሳዊ" የሚል የማንነት ግንዛቤ ሊሰጠው የተገባ ነው:: ቢሆንም ሁለቱም ሰውን በሙሉነት ለመረዳት ይበጃሉ እንጂ ለየብቻቸው የሰውን የማንነት ትርጉም አይሰጡም::[76]

ሰው በተፈጣሪነቱ ከፍጥረታት መደብ የሚመደብ መሆኑ አነጋጋሪ አይደለም:: ነገር ግን በኀሊና ክሂሉና በምግባር ልቀቱ ደግሞ ከሌሎች ፍጡራን የተለየ መሆኑ የፍጥረትና የሰው ልጅ ታሪክ የሚመሰክሩት ጉዳይ ነው:: በርካታ በሌሎች ፍጥረታት ላይ የሚታዩ ሥነ-ሕይወታዊ ገጽታዎች (Biological Features) በሰውም ላይ ስለሚታዩ፥ ሰው "እንስሳዊ አፈጣጠር" የለኝም እንዳይል አድርገውታል:: በልብ ዋና ቢሮነት የሚካሄደው የደም ሥርዓተ ኡደት (Circulatory system) ፥ ከአፉ ጀምሮ እስከ ታሕታዊ መውጫው ድረስ የሚካሄደው የምግብ ሥርዓተ እንሸርሽረት (Digestive system) ፥ አምስቱን የስሜት ህዋሳቱን የሚያስተዳድርበት ነርቫዊ ቅንባሮ (Nervous system) ፥ ከቡድ ገላው ወዘፍዛፋ እንዳይሆን ደግፎ ያቆመው የአጽም ቅንባሮ (Skeletal system) ፥ እንዲሁም ሌሎች ሌሎች ገጽታዎቹ ሰውን በተፈጥሮአዊ ማብራሪያ ለመገንዘብ የሚያስችል ማንነት ሰጥተውታል:: ይሁን እንጂ ሰው ተዳሳሽ ገላው ለጠየቀው ጥያቄ ሁሉ መልስ አግኝቶ የሚረካ ፍጡር አይደለም:: በተለይ ነፍሱ ከሞት ባሻገር ካለው ዓለም ጋር የማያቋርጥ ሙጥኝታ ያላት ናት:: ከሚታየው ይልቅ የማይታየው ዓለም ናፍቆት ልቡን የያዘው ፍጡር ነው::ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት ደግሞ ሰው በእግዚአብሔር "መልክና አምሳያ" በመፈጠሩ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ "መልክና አምሳያ" ፈጠረው ይበል እንጂ፥ ዝርዝር ሐሳቡ ለሁሉም ቀላል ሆኖ ባለመገኘቱ በርካታ አስተያየቶች የተሰነዘሩበት ጉዳይ ነው:: እግዚአብሔር የፍጥረት ሥራው መጨረሻ በሆነው በስድስተኛው ቀን "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" አለ (ዘፍ.1፥26):: ይህ ምን ማለት ነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ አስቀድመን "የእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው ግንዛቤ በአዲስ ኪዳን ትምህርትና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሰጠውን ግንዛቤ ከተመለከትን በኋላ ለስያሜው ፍቺ አጠቃላይ ትርጓሜ ለመስጠት እንሞክራለን::

ETHIOPIAN EVANGELICAL BAPTIST CHURCH
9120 FERGUSON ROAD
DALLAS, TEXAS 75228



### 3:1. "የእግዚአብሔር አምሳል "በአዲስ ኪዳንና በቤተክርስትያን ታሪክ[77]

ሰው እግዚአብሔርን የሚመስለው በምን በምን መልኩ እንደሆነ ቀደም ባሉት የመንደርደሪያ ሐሳቦች ለማተት ተሞክሮአል:: ከዚህም ሌላ በሚወረሱና በማይወረሱ የእግዚአብሔር ባሕሪያት መካከል ያለውን ልዩነት ስንመለከት ይህንኑ ምስስል አይተናል:: አሁን ደግሞ በታሪክ ውስጥ ያለፈችው ቤተክርስቲያን የነበራትን ግንዛቤና አዲስ ኪዳናዊውን ትምህርት እንመለከታለን:: በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ "የእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው በተለያዩ አመለካከቶች የታየ ቢሆንም ሁለቱን ዋና ዋና አመለካከቶች ካየን በኋላ አዲስ ኪዳናዊውን ትምህርት እናያለን::

"<u>ውቅራዊ አመለካከት:-</u>" ይህ አመለካከት "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል" ለሚለው ቃል በቤተክርስቲያን አባቶች (Church Fathers) ለረጅም ጊዜ ተይዞ የቆየ የትርጉም አቋም ነው:: ይህ አመለካከት በተሐድሶ አራማጆች ተግዳሮት ገጥሞት የነበረ:: ቢሆንም እስከ አሁን በብዙ የክርስትና ክፍሎች ፕሮቴስታንቶችም ጨምሮ ደጋፊ ያለው ሐሳብ ነው:: በዚህ የትርጉም ሐሳብ መሠረት ሰው በተፈጥሮው የተሠራበት አወቃቀር፥ በውስጡም ሰው ያደረገው ነገር "የእግዚአብሔር አምሳል" እንዲሆን አድርጎታል ይላል:: ስለዚህ ሰው ሁሉ በሁሉም ቦታ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ይመስላል:: ከሁሉም በላይ ሰው ምክኑአዊ (Rational) መሆኑና ግብረገባዊ ተፈጥሮው እንዲሁም የቅድስና ዝንባሌው ሰውን የእግዚአብሔር አምሳል እንዲኖረው አድርጎታል ይላል ይህ አመለካከት:: ሆኖም ግን ይህ አመለካከት ሰው በኃጢአቱ ከወደቀ በኋላ በተፈጥሮ ያገኘውን "የእግዚአብሔር አምሳልን" እስከ ምንድረስ ነው ያጣው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያዳግተዋል:: ከዚህም የተነሳ "በመልካችን እንደምሳሌአችን" የሚለውን ለሁለት በመክፈል ሰው በኃጢአቱ የተነሳ "በመልካችን" የሚለውን ሲያጣ "እንደምሳሌአችን" የሚለውን ግን በኃጢአት የተነሳ አላጣውም ይላሉ:: ይኼ ግን ከይሁንታ ትርጉም ያለፈ አይመስልም::





<u>ግንኙነታዊ አመለካከት:-</u> ውቅራዊ አመለካከት መልክንና ምሳሌን ለሁለት ከፍሎ ማየቱን ተገቢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቲት (Exegesis) ላይ ያልተመሠረተ ሥነ-መለኮታዊ ግድፈት ያለው ነው በማለት የተሐድሶ አራማጅ "ፋና-ወጊ" የሆነው ማርቲን ሉተር፥ ሰው የእግዚአብሔር አምሳል አለው ማለት የመጀመሪያው ሰው ያልተበረዘ ያልተከለሰ ጭንጩ (Original) ጽድቅ አለው ማለት ነው ይላል:: ሉተርም ሆነ በጊዜው የነበረው ካልቪን፥ በዚህ ሐሳብ በመስማማት ሰው በውድቀቱ የተነሳ የመለኮትን ምስል ሙሉ በሙሉ አላጣም፤ ሆኖም ኃጢአት በሰው ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል አጨለመው ይላሉ:: ስለዚህ የነሉተር አስተሳሰብ፥ የሰው አሠራር ላይ ሳይሆን ሰው በእግዚአብሔር ፊት መቆም የመቻሉ ጉዳይ ላይ ዋና ትኩረት ያደርጋል:: ይህም በአምላክ ፊት የመቅረብ ችሎታ፥ አዳም በኃጢአት ሲያጣው አማኝ በክርስቶስ መልሶ አግኝቶታል ይላሉ:: ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን አምሳል የያዘው ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት በመቻሉ ነው ይላሉ:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ "የእግዚአብሔር አምሳል" በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ምን እንደሚመስልና ከምን ጋር እንደተዛመደ እንመለከታለን::

<u>"የእግዚአብሔር አምሳል" በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች:-</u> በአሪት ዘፍጥረት ላይ የተጠቀሰውን የሰውን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር በሚያውጠነጥን ኀሊና ሆኖ ሐዋርያው ያዕቆብ ለአማኞች ምግባራዊ ምክር ይለግሣል "በእርሱ (በአንደበት) ጌታንና አብን እንባርካለን በእርሱም *እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች* እንረግማለን፤ ወንድሞቼ ሆይ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም" (ያዕ.3፥9):: ለያዕቆብ በዓለም ያለ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን አምሳል የተሸከመ በመሆኑ የመርገም ቃል ይናገሩበት ዘንድ አይገባም::

ለሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ሰው የሆነው ክርስቶስ የእግዚአብሔር አምሳል በክብርና በሙላት የተገለጠበት ነው:: ለእርሱ የወንጌል ዋነኛ መልእክቱ ይህንኑ ክርስቶስ መግለጥ ነው:: "ለእነርሱም *የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው የክርስቶስ* የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" (2ቆሮ.4፥4፤ ቆላ.1፥15):: እንደ

ጳውሎስ ገለጻ የእግዚአብሔር ምሳሌ ፍጹም በሆነ መልኩ የተገለጸበት ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: ይኼ የጳወሎስ ሥነ-ክርስቶሳዊ ግንዛቤ አማኞች ከዚህ የእግዚአብሔር ክብር ሙሉ መንጸባረቂያ ከሆነው ክርስቶስ ጋር ካላቸው ቁርኝት የተነሳ የክርስቶስ ክብር መታያ ናቸው የሚል እውነትን የያዘ ነው:: ምክንያቱም "እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ አንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ስለሚል (2ቆሮ.3÷18):: እንደ ሮሜ 8÷29 መሠረት ደግሞ የመጠራታችን ዓላማ "የልጁን መልክ" እንድንመስል ነው:: ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ ደግሞ "በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" ይላል (ኤፌ.4÷12):: ይህ ማለት ደግሞ አማኞች አሁን ባላቸው እምነት በሚኖሩት ኑሮ በኃጢአት የደበዘዘው የእግዚአብሔር ምስል ርምደታዊ በሆነ መልኩ የሚታደስበትን ሕይወት ይኖራሉ ማለት ነው::

ይኼ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካኝነት በአማኞች ሕይወት በከበረ መልኩ ወደ ቀደመው ሥፍራ የሚመለሰው "የእግዚአብሔር አምሳል" ፍጹምነቱ የሚረጋገጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም መገለጥ ብቻ ነው:: ምክንያቱም ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ "ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን" ስለሚል (1ዮሐ.3÷2):: ይህም በሙታን ትንሣኤ አማኞች "ከመሬታዊው መልክ" "የሰማያዊውን መልክ" እንደሚለብሱ "ከሚበሰብሰው" "የማይበሰብሰውን" "ከሚሞተው" "የማይሞተውን" ሲለብሱ በዚህም ሞት ድል በመነሳት እንደሚረጋገጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረውን ያሳስባል (1ቆሮ.15÷49-56):: ስለዚህ እግዚአብሔር በሥነ-ፍጻሜ (Eschatology) የሰውን ልጅ በክርስቶስ በኩል አስቀድሞ ሲፈጥረው ወዳቀደለት ዓላማ ይመልሰዋል::

"የእግዚአብሔር አምሳል" በአዲስ ኪዳንና በቤተ ክርስቲያን ያለውን ገጽታ በመጠኑ ለማስተዋወቅ ያህል እስካሁን የዘረዘርነው ሐሳብ በቂ እንደሆነ በመቁጠር÷ ይህንን መሠረታዊ ሐሳብ በዝር





ዝር ትርጉም መልክ በሚከተለው ዋና ነጥብና ንኡሳን ነጥቦች እንመለከታለን::

### 3:2 "በእግዚአብሔር አምሳል" ማለት ምን ማለት ነው?

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ (ተበጀ) የተባለለት ሰው ብቻ ነው:: ይህም ማለት ሰው እግዚአብሔርን የመሰለና እግዚአብሔርን የወከለ ነው ማለት ነው:: የፍጥረትን ቅደም ተከተል ስንመለከት ደግሞ ሌሎች ፍጥረታት በእግዚአብሔር የቃል ትእዛዝ "ይሁን" በሚል ቃል ሲፈጠሩ የሰው አፈጣጠር ግን ለየት ያለ ነው:: ሌሎች ፍጥረታት "እንደወገኑ" በሚል ሲፈጠሩ ሰው ግን "በመልካችን እንደ ምሳሌአችን" ተባለለት፤ ደግሞም ሌሎች ፍጥረታት የጾታ ልዩነት ቢኖራቸውም÷ በጾታ ልዩነታቸው ትኩረት ሳይደረግባቸው ተፈጠሩ፤ ሰውን ግን "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" ተብሎለታል:: ደግሞም በፍጥረታት ላይ እንደሰው የስለጠነ አለመኖሩን ሲገልጽ "ሁሉን ግዙአቸው" ተብሎለታል:: በእነዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች ሰው ከሌሎች ፍጥረታት ፈጽሞ የተለየ ነው:: በተለይም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ የልዩነቱ ዋና ምክንያት ነው:: ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ የአመለካከት ልዩነቶች በመነሳታቸው ቃሉ ከሚለው በላይ የተለጠጠ ትርጉም በመስጠት ሰው የፍጥረት የበላይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር አኩያም ነው ወደ ማለት ተደርሷል:: ስለዚህ "ሰው በእግዚአ ብሔር አምሳል" ተፈጠረ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተገቢ ትንታኔ መስጠት አስፈላጊ ነው::

ሰውን አስመልክቶ በእግዚአብሔር "አምሳልና መልክ" የሚለው ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድም በሌላም መንገድ ከስድስት ጊዜ በማያንስ ተጠቅሷል (ዘፍ.1÷27፤ 5÷1፤ 9÷6፤ 1ቆሮ.11÷7፤ ያዕ.3÷9፤ ቆላ.3÷10):: በተመሳሳይም ሁኔታ ኤፌ.4÷24 ላይ ሲጠቀስ÷ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ በእግዚአ ብሔርና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያስተምር በሐዋ.17 ÷28-29 ቀጥተኛ ባልሆነ አገላለጽ ሐሳቡን አንስቶታል:: ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳያ ተፈጥሯል የሚለውን ሐሳብ ለማብራራት "መልክ" እና "አምሳያን" ለየብቻ በማየት ብዙዎች ሰፊ ትንተና ለመስጠት ሞክረዋል:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ጥቂቶቹን

ለማየት እንሞክራለን። ይሁን እንጂ ዋና ትኩረታችን "የመልክና የአምሳያን" ፍቺ ለመስጠት ሳይሆን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ማለት ምን ማለት ነው? ጥቅሙና ኃላፊነቱስ ምንድን ነው? የሚለው ሐሳብ ይሆናል።[78]

"በእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው ቃል "በመልካችን እንደ ምሳሌአችን" ከሚለው በመውሰድ የሰውን ማንነት ለማብ ራራት የተጠቀምንበት መግለጫ ነው። እንግዲህ ሰው እግዚአብ ሔርን በምን ይመስላል? የሚለው ጥያቄ በብዙ ሰዎች ብዙ መልስ ሊሰጥበት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አካላዊ ምስስል አለው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ግብረገባዊና መንፈሳዊ ማንነቱ ከእግዚአብሔር አመሳስሎታል ይላሉ። ከእነዚ ህም ሌላ ደግሞ ሰው ከእግዚአብሔር የሚመሳሰለው በፍጥረት ላይ ባለው የመግዛት ስልጣን ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሰው እራሱን የማወቅ ችሎታ ስላለው ነው እግዚአብሔርን የሚመስለው ይላሉ። እነዚህ ሁሉ ለየብቻቸው ከታዩ አጥርተው "የመምሰልን" መልስ አይመልሱልንም። ስለዚህ አንዳንዶቹ በውስጣቸው የራሳቸው የሆኑ እውነቶች ያሉአቸው በመሆናቸው፥ ለበቂ ክርስ ቲያናዊ ግንዛቤ ዘርዘር ያለ ምልከታ እናደርግባቸዋለን።

ይሄ "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው ቃል ፍቺ የመጽሐፍ ቅዱሳዊውን አስተምህሮተ-ሰው (Biblical Doctrine of man) ጥናት በሚያካሂዱ ተምህሮአውያን ዘንድ አነጋጋሪ የሆነ ርዕስ ነው። እኛም ብንሆን እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን በምንድን ነው አምላካችን እና ንጉሣችንን የምንመስለው? ከዚህስ አኳያ ያለብን ግዴታ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ በሚገባ መጠየቅም መመለስም መቻል አለብን። ምክንያቱም የአሁኑ ማንነታችን ከተፈጠርንበት ዓላማ ጋር መስማማት አለመስማማቱን በየጊዜው ማረጋጥ ስለሚገባን ነው። ሰው በሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች የእግዚአብሔር አምሳል ይታይበታል።





1.ኅብረት ማድረጋችን

በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል አውቀነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የምናመልከው አምላክ በፍቅር፥ በፈጠራ ችሎታውና በመለኮታዊ ኅብረቱ በሥላሴነት ኀልው የሆነ አምላክ ነው። ሰዎች የሚያሳዩት ፍቅርና በመካከላቸው ያላቸው ኅብረት በሥላሴ ዘንድ ያለው ኅብረትና በእነርሱም ዘንድ ያለው የእግዚአብሔር አምሳል ነጸብራቅ ነው። በሌላ አነጋገር፥ ጌታ በእግዚአብሔርነቱ ያለውን ኅብረትና አንድነት በሰዎች የእርስ በእርስ ኑሮ ውስጥም እናያለን። ሰብአውያን ግንኙነታቸው በተለያየ አቅጣጫ ሊገለጥ ይችላል። በዋነኛነት ደረጃ ከአምላክ ጋር ባላቸው ግንኙነት ሲሆን ይህም ለእርሱ ያላቸውን ጥገኝነት በማያቋርጥ ኅብረት ሲገልጡት ይታወቃል። ሰው አፈጣጠሩ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቋረጠ ግንኙ ነት መሆኑ፥ አሣ ከውኃ ጋር ያላቋረጠ ግንኙነት ሊኖረው የሚገባውን ዓይነት ግንኙነት ነው። በኃጢአት የተነሳ ከእውነተ ኛው አምላክ ጋር ያላቸው ኅብረት የተቋረጠባቸው ሰዎች፥ ከመፈ ጠራቸው ዓላማ በመውጣት በባሕር ዳር ባለ አሸዋ እንደተተፋ አሣ ይመስላሉ።

ከዚህ ሌላ የሰው ግንኙነታዊ ባሕሪ መገለጫ ደግሞ ከሌሎች ጋር በሚያደርገው ኅብረት ነው። በመለኮትነቱ አንድ በአካል ሦስት በሆነው አምላክ ዘንድ ያለው ሥላሴያዊ ኅብረት በሰው ልጆች የእርስ በርስ ግንኙነት ይንጸባረቃል። *በሰብአውያን ዘንድ የሚታይ መተሳሰብና ፍቅር የምድር አፈር ጠባይ ሳይሆን የመለኮት እስትንፋስነት ውጤት ነው። የኃጢአት ውድቀት ቢያደበዝዛቸውም ፍቅር፥ መውደድና መተሳሰብ ድምጥማጣቸው አልጠፋም። ከዚህም የተነሳ በሰው ዘንድ የማኅበራዊነት ጠባይ ይታያል። ብቸኝነት የሰው ልጅ ጤነኛ ጠባይ እንዳልሆነ ሰው በእድሜው ዘመን ሁሉ አይቶታል።*

እግዚአብሔርም ፍጥረትን ሁሉ ሲፈጥር "መልካም እንደሆነ አየ" ሲል፥ ነገር ግን ወደ ሰው ዘወር ባለ ጊዜ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" አለ። ሰው በእግዚአ ብሔር አምሳል በመፈጠሩ የተነሳ እርስ በርሱ ኅብረት የሚያደርግ ፍጡር መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ተለይቶ

ከፈጣሪው ጋራ የጠበቀ ተራክቦ (Communion) ማድረግ የሚችልም ነው:: ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ከሰው ጋር መነጋገርና ኪዳን መግባት ይችላል:: ስለዚህ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን መሆናችን እውንነቱ የሚረጋገጠው፥ ከሰውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በፍቅር ካለን ኅብረት አንጻር ጭምር ነው::[79]

2. የመግዛት ችሎታችን

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የመፈጠሩ ትርጉም የሚታየው፥ በምድር ላይ አምላክን *ወክሉ* (አምላክ ሆኖ ማለት አይደለም) ፍጥረትን በማስተዳደር የመግዛት ችሎታው ነው:: ሰው በፍጡርነቱ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ጥገኛ ይሁን እንጂ በሌላ አንጻር ደግሞ ነፃ የሆነ ሥልጣንና መብትም አለው:: ይህ ታላቅ ምስጢርን የያዘ እውነት ነው:: እግዚአብሔር ሌሎቹን ፍጥረታት ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በርሱ ፋንታና ስለ ራሱ ተወክሎ ሰው በወንድና በሴትነቱ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት *ግዙአትም* የባሕርን ዓሳዎችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱት ንም ሁሉ ግዙአቸው" የሚል ሥልጣን ተሰጠው (ዘፍ.1÷28):: ስለዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰውን ሲፈጥር ከሌሎች ፍጥረ ቶቹ የሚገናኝበት አድርጎ ነው የፈጠረው:: ይህ በፍጥረት ላይ ያለው የመግዛት መብት አሁንም ቢሆን በኃጢአት ምክንያት ደበዘዘ እንጂ አልተነጠቀም:: ስለዚህ ሰው ለእግዚአብሔር የምድር ላይ ወኪልና የክብሩ መታያ ነው:: ይህ ደግሞ እንኳን ለሌሎች እንስሳት ለመላእክትም ቢሆን አልተሰጠም::[80]

3.ባሕርያችን

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ ሲባል ቁሳዊ ወይም አካላዊ ምስስል ሳይሆን የጠባይ ምስስል ላይ ያተኩራል:: ሰው በባሕርዩ የእግዚአብሔር ክብር መንጸባረቂያ ነው:: ሰው ከውድቀት በፊት ያለኃጢአት መሆኑ፥ አፈጣጠሩም ዘላለማዊ መሆኑ፥ (ቢሆንም ጅማሬ አለው) ከእግዚአብሔር ጋር ያመሳስለዋል:: በሰው ሕይወት የሚታይ ፍቅር፥ ይቅርታ ማድረግ፥ ደግነት ታማኝነትና የመሳሰሉት ጠባያት እግዚአብሔርን





ከመምሰሉ የተነሳ የሚታዩ ጠባያት ናቸው:: ስለዚህ የሰውን አፈጣጠርና የባሕሪ ሥርዓት መተቸት ማለት በተዘዋዋሪ እግዚአ ብሔርን መተቸት ማለት ነው::

4. "እኔ" የሚል ማንነት ያለው ፍጡር (አካላዊ) መሆናችን[81]

"በእግዚአብሔር አምሳል" የተፈጠረው የሰው ተፈጥሮ እውነተኛው ማንነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን "እኔ" የማለትን የአካልነት ጠባይ በመውረሱም ነው:: በዚህ በአካልነቱ (Personlity) የሚታዩበት ልዩ ልዩ ጠባያት አሉት፤ አንደኛው ከአንዱ ተወራራሽ በመሆኑም ለየብቻ አይታዩም:: ስለዚህ ሰው በእግዚአብሔር አምሳልነቱ የተነሳ አካላዊ ፍጡር ነው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በሚከተሉት ነጥቦች እንገልጻለን:: በዚህ ማብራሪያ ውስጥም አካላዊ ብለን የምንጠራው ኢ-ተጻሳሽ የሆነውን የሰው ጠባይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

- *ግለ-ኅሊና ምክኑያዊነት (Self-conscious Rationality):-* ሰው በአካላዊነቱ ልክ "እንደ እግዚአብሔር" የነገሮችን ትክክለኛ ብያኔ መስጠት የሚያስችል ምክኑያዊነት አለው:: ይህ ደግሞ ራስን የማወቅና የመገንዘብ ጠባይ ከሌላቸው የቀሩት እንስሳት ፈጽሞ ይለየዋል:: ሰዎች አእምሮአውያንና ባለ ኅሊና ናቸው እንጂ እንደሌሎች እንስሳት ደመነፍሳውያን አይደሉም (ይሁዳ 10):: ይህ ግለ-ኅሊናዊነትም ሰዎች ከሰዎች ጋር ሕብረትና ግብቡነት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል::

- *ሰዎች ለራሳቸው የመወሰን ነጻ ፈቃድ አላቸው:-* ሰዎች የስብእናቸው ማዕከል ከእግዚአብሔር ማንነት ጋር የሚያ መሳስላቸው፥ የራሳቸው ፈቃድ ያላቸውና ለራሳቸው መወሰን የሚችሉ መሆናቸው ነው:: ሰው ውጪያዊ በሆኑ ቀስቃሽ ነገሮች ተጽእኖ ሳይደረግበት በራሱ የማሰብ ችሎታ ውሳኔ የመወሰን ችሎታ ስላለው፥ የእግዚአብሔር አምሳልነቱ ይረጋገጣል:: ይሁን እንጂ ሰው ፍጹም ባለመሆኑ ይህ የውሳኔ አቅሙ ገደብ ያለው ነው:: ሰው የራሱን ፈቃድ በሚገልጥበት ጊዜ ግን ተገላጭ ፈቃዱ የጽድቅ፥ የቡኅነትና የቅድስና እንዳይሆን ውድቀት አጉድሮበታል::

ስለዚህ ሰው ሙሉ በሙሉ ፈቃድ ያለው ፍጡር ቢሆንም ፈቃዱ ፍጹምነትን አጥቷል (ሮሜ 3÷9-20)።

• *ግብረ ገባዊ ፍጡር ነው፦* ሰው ምንም እንኳ ባለ ኅሊናና ባለ ነፃ ፈቃድ ፍጡር ቢሆንም፥ ምግባራዊ ማንነትም ስላለው የፈቀደውን ሁሉ በተግባር አያውልም። ልክ ነው? ልክ አይደለም? ከሚለው ኅሊናው ጋር ይማከራል። ይሁን እንጂ የኃጢያት ወደ ዓለም መግባት ሰው ክፉና ደጉን ለይቶ የሚያደርግበትን የኅሊና አቅም አስሮበታል። ቢሆንም ክፉና ደጉን መለየት ጨርሶ አልተ ሳነውም። ይህ ግንዛቤ በሰዎች ልብ የተጻፈ ሕግ መሆኑን ከሐዋ ርያት ትምህርት መረዳት ይቻላል (ሮሜ.2÷14-15)።

• *የቀድሞ ኃጢአት የለሽ አፈጣጠሩ፦* ሰው በተፈጥሮው የእግዚአብሔር አምሳል አለው ከምንልበት ምክንያት አንደኛው አስቀድሞውንም ሲፈጠር ከእግዚአብሔር ጋራ ቀጥተኛና የጽድቅ ግንኙነት ስላለው ነው። ይህም ማለት በእግዚአብሔር ፊት ያለነቀፋ ሊቀርብ የሚችል መሆኑ ነው።

5. የሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የሰው ዘር በሙሉ የሚዳስስ ነው።[82]

ይህ ሐሳብ በዘፍ. 9÷6 "የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል፤ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና" ተብሎ በተጠቀሰውና በያዕ. 3÷9-10 "... እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች..." በሚለው ጥቅስ መሠረት ይረጋገጣል። ከዚህም የተነሳ ማንኛውም የሰው ልጅ ከሌሎች የሰው ልጆች በበለጠ ሁኔታ የእግዚአብሔር አምሳል የተገለጠበት ነው ማለት አይቻልም። ሰው ሁሉ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠረው ከአዳም ዘር የወጣ ከመሆኑ የተነሳ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው። የትኛውም ትውልድ ከየትኛውም ትውልድ ሳይበልጥ እኩል የእግዚአብሔር አምሳል መታያ ነው።





3.3 "በእግዚአብሔር አምሳል" መፈጠር ያለው ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ[83]

ብሉይ ኪዳናዊ፥ አዲስ ኪዳናዊ እንዲሁም ታሪካዊ የሆነው ይህ የአስተምህሮተ ሰው ትንታኔ ምን ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ አለው? ሰው የእግዚአብርን አምሳል ተሸካሚ መሆኑ ለእኛ ምን ጥቅምና ኃላፊነት ይተውልናል? እነዚህን ጥያቄዎች በከፊልም ቢሆን ከዚህ በታች በተዘተዘሩት ሐሳቦች ለመመለስ እንሞክራለን።

1.በፈጣሪአችን ፊት ልዩ ቦታ ያሰጠናል

በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን መሆናችን በቀጥታ የርሱ ፍቅር ተቀባዮች እንድንሆን አድርጎናል። ይህም ማለት እያንዳንዱ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፊት ከፍጥረት ሁሉ በተለየ መልኩ ልዩ ቦታ አለው። ይህ ብቻ ሳይሆን ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ከመፈጠሩ የተነሳ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቀባይም ነው። ስለሆነም ኃፊነትን የተቀበለ ፍጡር ነው። ሰው በእግዚአብሔር የቃል ትእዛዝ በተፈጠሩት ሌሎች ፍጥረታት ላይ ሙሉ በሙሉ የመግዛት መብት ተሰጥቶታል። ስለዚህ ለፍጥረት በውክልና የመለኮትን ባሕሪ ማንጸባረቅ መቻል ይጠበቅብናል። በሰማይና በምድር መካከል አንድ አምላክ ብቻ አለ። ይህ አምላክ ደግሞ ምን እንደሚመስል ፍጥረት ሁሉ ያውቅ ዘንድ እርሱን የምንመስለውን እኛን አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞናል። ስለዚህ የሥራ ፈጠራ ችሎታንን ማዳበርና ፍጥረትን በኃላፊነት ማስተዳደር እንዲሁም በከፍተኛ የሥራ ስሜት አምላካዊ አደራችንን መወጣት በተለይም የእኛ የክርስቲያኖች ኃላፊነት ነው፡

2. ከፈጣሪአችን ጋር ልዩ የሆነ ኅብረት እንዲኖረን አድርጓል

በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችን በፊቱ ልዩ ቦታ እንዲሰጠን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖ ረንም አድርጓል። እግዚአብሔር ሲፈጥረን ዓላማው ለመለኮታዊው ፍቅሩ ምላሽ የሚሰጥ ፍቅር እየሰጠነው ትእዛዛቱንም እንዲሁ እንድንፈጽም ነው። ሰው የሆነ ሰው ይህንን ሲያደርግ ብቻ ነው የተፈጠረበትን ዓላማ ግብ መታ የሚባለው ።

### 3. በሥነ ፍጻሜ እውነታ ላይ እንድንደገፍ ያደርገናል

ምንም እንኳ የሰው ልጅ በሙሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል ብንልም የእግዚአብሔር አምሳል በሙላትና ያለመጓደል የተገለጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እንዴት ሊሆን እንደሚገባ አስቦት እንደነበረ በክርስቶስ ትሥጉት (Incarnation) ተገልጦአል፡፡ ሰውን ወደ ተፈጠረበት ወደዚያ ዓላማ የሚመራው ይሄው ክርስቶስ ነው፡፡ አማኞች ደግሞ የእግዚአብሔርን አምሳል በክብር ለማንጸባረቅ ከዳግም ውልደታችን አንስቶ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጻት ድረስ ርምደታዊ በሆነ ሁኔታ ባሕሪያችን ባሕሪውን እንዲመስል ጥረት እናደርጋለን፡፡

የሥነ-ፍጻሜ ተስፋችንን እያሰብን በአዳም አጥተነው በክርስቶስ ወደ ተዘጋጀልን የክብር ግብ ስናመራ÷ በግል ሳይሆን በኅብረት ነው፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር አምሳል ሙሉ መገለጥ የሚከናወነው በአንድ አማኝ ሳይሆን በአጠቃላይ በአካሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞም ቢሆን ሰውን በምሳሌውና እንደ መልኩ ሲፈጥር "ብዙ ተባዙ" የሚለው ትእዛዙ የእግዚአብሔር መልክ በአዳም ብቻ ሳይሆን በአንድ በሚመሠረት ሕዝብ ለፍጥረት ሁሉ ይገለጥ ዘንድ ነው፡፡

### 4. የእግዚአብሔር ገንዘቦች መሆናችንን ያስገነዝበናል

"በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረናል" የሚለው እውነት አንዳንድ ባሕሪያቶቹን በተወሰነ መልኩ መውረሳችንን ያሳየናል፡፡ በዚህም ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ ሁኔታ የእርሱነታችንን ያስገነዝበናል፡፡ በማር.12÷13-17 በተጠቀሰው ላይ በቀጥታ "የእግዚአብሔር አምሳል" የሚል ባይኖርም ሰው የእግዚአብሔር ንብረት መሆኑን የሚያስረዳ ብርሃን አለበት፡፡ ጌታን በጥያቄ ሊያጠምዱት ከፈሪሳውያን ከሄሮድስ ወገን የሆኑት "ለሮም ቄሳር ግብር መክፈል ተፈቅውዶአልን? ወይስ አልተፈቀም? እንገብር? ወይስ አንገብር? ብለው በጠየቁት ጊዜ÷ በጊዜው በነበረው ገንዘብ ላይ ያለውን እንደ ማስተማሪያ ምሳሌ አድርጎ በመጠቀም፡- "በዚህ ገንዘብ ላይ ያለው መልክና የተጻፈው ስም የማን ነው?"





ሲል ጠየቃቸው እነርሱም "የቄሳር ነው" አሉት እርሱም "እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ" ሲል መለሰላቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ ሲል በንብረት ደረጃ የቄሳር ምስል ያለበት ለቄሳር ከተገባው÷ የእግዚአብሔር ምስል/መልክ ያለበት የሰው ልጅ ደግሞ እንዲሁ ለእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ የተገባ ነው የሚል የተዛምዶ-ፍቺ መርህ (Principle Application) ማውጣት እንችላለን፡፡ ስለዚህ መስጠት÷ ፍቅር÷ ታማኝነትና አገልግሎት እግዚአብሔር በምስሉ ከፈጠረው ሰው የሚጠብቀው መብቱ ነው፡፡

### 5. የክርስቶስን ምሳሌ እንድከተል ያደርገናል

የእግዚአብሔር አምሳል በሙላት የተገለጠበት ክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌአችን ሊሆን ይገባል፤ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስብእና ኃጢአት ሳያበላሸው በእርሱ ዘንድ ይታያልና (ዕብ.4÷15)፡፡ የመታዘዝንና ፈቃድን የማስገዛት ምሳሌ ከእርሱ እንማራለን (ማቴ.26÷39፤ ዮሐ.9÷4)፡፡ እርሱ ሕይወትና ሞቱ ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው ሊከተለው የተገባ ነው" ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" (ዮሐ.15÷12)፡፡ ስለዚህ ጻድቃን ሁሉ የልጁን መልክ ይይዙ ዘንድ ተጠርተዋል (ሮሜ 8÷29)፡፡ አንድ ሰው ሙሉ የሆነ ሰውነት መኖር የሚችለው በጨዋነት÷ በቅንነት ወይም ሰብዓዊ ርኅራኄ ብቻ በማሳየት ሳይሆን÷ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በሚገኝ የደቀመዝሙርነት ሕይወት ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም "ያን መልክ" መስሎ "ከክብር ወደ ክብር" የመለወጥ ተስፋ ከእግዚአብሔር ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ስለሚገኝ ነው(2ቆሮ.3÷18)፡፡ *ብዙ ጊዜ እኛ እንደሚመስለን መጽሐፍ ቅዱስ "ከክብር ወደ ክብር መለወጥን" ሲያስተምረን÷ በምድራዊ ኑሯችን መሳካት ከአንድ ደረጃ ወደ አንድ ደረጃ ከመሸጋገር ጋር የተያያዘ ሳይሆን ክርስቶስን በየእለቱ ከመምሰል ጋር የተያያዘ ነው፡፡*

## 6. የሰው ልጅ ክቡርነትን እንድናስተውል ያሳስበናል

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ውድና ክቡር እንዲሆን አድርጎታል፤ እግዚአብሔር በመልኩ የፈጠረውን የሰውን ነፍስ የሚያጠፉትን እንኳን ከሰው ልጅ÷ ከአራዊት ሁሉ እጅ እሻዋለሁ ብሎ ለሰው ነፍስ ከፍተኛ ስፍራ ሰጥቶአል (ዘፍ9÷5-6)። ስለዚህ ኃጢአተኛ የሆነው የሰው ልጅም ሁሉ እንኳ÷ ከፍተኛ አክብሮትና ጥንቃቄ ሊሰጠው ይገባል። ምንም እንኳን ያለንበት ዘመን በሕዝብ ብዛት መጨመር÷ በሰዎች ጎዳና ላይ መፍሰስ÷ እንዲሁም በጦርነትና በራብ ብዛት÷ የሰዎችን ዋጋ ያረከሰ መስሎ ቢታይም እኛ ግን እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን ለሰዎች ያለንን ከፍተኛ አክብሮት መቀነስ የለብንም። ይህ የእግዚአብሔር አምሳል ደግሞ በቦታ ሳይገደብ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰው ሁሉ ላይ እኩል የሚንጸባረቅ ነው። ስለዚህ የዘር የቀለም ልዩነት በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ኃጢአት ነው።

ሰው በእናቱ ማሕጸንም ሆነ ወይንም ተወልዶ÷ ደግሞም በሕጻንነቱም ሆነ በእርጅናው ሰው ያው ሰው ነው። ሀብት ቢኖረው ወይ ባይኖረው÷ ቢማር ወይ ባይማር÷ "ኋላ ቀር" የጫካ ነዋሪ ሆነ ወይ "ዘመነኛ" ከተሜ ሰብአዊነት የሚለካው በእግዚአ ብሔር አምሳል በመፈጠር ብቻ እንጂ ሰው በሚገኝበት ማኀበ ራዊ÷ ፖለቲካዊ÷ ሥነ-ልቦናዊና ኤኮኖሚያዊ አቋም አይደለም። በእውነትና በቅንነት ካሰብነው ደግሞ "እገሌ ሰው አይደለም" "ከብት ነው" "ውሻ ነው" ወዘተ. የምንላቸው ልማዳዊ ቋንቋዎቻችን÷ በሥነ-ፍጻሜ በአምላክ ፊት እንደሚያስጠይቁን ከቶ የማይቀር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሙን (እንደርሱ ያለን ሰው) "ጨርቃም" የሚል ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ሲል ያሳስበናል (ማቴ.5÷21-22)። ድግሞም ወንድምን ገንዘብ ሳያደርጉ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደማይቻል ያስረዳል (ማቴ.5÷23-26)።

*አሜን!*





## ማጣቀሻዎች


[1] ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1946 ዓ.ም.) ገጽ 1155
[2] መሠረት ስብሐት ለአብ÷ ሥላሴ በተዋህዶ (አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1988) ገጽ 26
[3] Milard J. Erickson, Christian Theology (Michigan: Baker Book House, 1983), p. 153
[4] Wayne Grudem, Systematic Theology (Michigan: Zondervan Publishing House 1994) , p. 123
[5] Steve Bryan, Theology proper (Bth.lecture note,E.T.C., Addis Ababa 1995), unpublished matetial
[6] David S. Dockery, Christian Scripture (Nashvill, Tennessee: Broadman & Holman Publishers 1995), pp. 16-17
[7] ኃይሉ መኮንን (ቄስ /ተርጓሚ) እምነታችን (The West Minister Cofession of Faith)
[8] Erickson , p,167
[9] Dockery, p,18
[10] Erickson, p, 155
[11] John stott,
[12] Dockery, p, 18
[13] Bruce Milne, Know the Truth (Leicester, England: Intervarsity press, 1982), p.24
[14] Bryan, Steve
[15] ምኒልክ አስፋው የቅዱሳት መጽሐፍት አፈታት ጥበብ፤ ያልታተመ የማስተማሪያ ኖት።
[16] Bryan, steve
[17] ኃይሉ መኮንን (ቄስ፤ ተርጓሚ) የትምህርተ መለኮት ጥናት (በፕሮፌሰር ሉውስ በርክኾፍ ተጻፈ፤ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት 1987 ዓ.ም.) ገጽ 35
[18] J.D. Douglas, (ed) “Miracle” New Bible Dictionary second edition, (Leicester,England: Inter- Varsity press, 1962)
[19] Josh Mcdowell, Evidence That Demands a Verdict (San Bernardino, C.A.: Here`s Life Publishers, Inc. 1979), p.89
[20] Ibid
[21] R.C. Sproul, Following Christ (Wheaton, Illinois : Tyndal House publishers, Inc., 1991), p. 43
[22] ምኒልክ አስፋው "ሎጎስም እግዚአብሔር ነበረ" ነጸብራቅ መጽሔት ቁ.2 1984 ገጽ 13
[23] ምኒልክ አስፋው

[24] Sproul, p. 46
[25] Sproul, p. 47
[26] ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፤ <u>የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u> (አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1946 ዓ.ም አዲስ አበባ) ገጽ 194
[27] Erickson, p .722
[28] Ibid
[29] Henrietta C. Mears, <u>What The Bible is All About</u> (California: Regal Books 1966), p. 8
[30] Blomburg, <u>Introduction to bibilical interpretation</u> p.88
[31] Grudem,wayne p.74
[32] ብርሃን መጽሔት የቆየ
[33] Norman L. Geisler, <u>Christian Ethics</u> (Leicester, England : Apollos (an imprint of Inter- Varsity Press 1989), pp. 17-22
[34] Ibid
[35] ከሣቴ ገጽ 703
[36] የኢትዮጲያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተመው በራሪ ጽሑፍ "መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?"
[37] J.I. Packer, <u>Knowing God</u> (Illinois : Inter - Varsity Press 1973), p29
[38] Randy Alcorn, <u>Money Possessions and Eternity</u> (Illinois : Tyndal House 1989), p.187
[39] Packer, p.31
[40] Ibid
[41] በፍሬው ታምራት ምሥራቅ አጥቢያ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን "እግዚአብሔርን ማወቅ" በሚል የተሰጠ ትምህርት 1988 ዓ.ም. አዲስ አበባ
[42] Bryan, Steve
[43] ፍሬው
[44] Bryan,
[45] Davis, John J. <u>Moses and the Gods of Egypt</u> (Grand Rapids, Michigan: Baker Book House 1971), pp. 3o4
[46] ፍሬው
[47] Bryan,
[48] Peter C. Craigie, <u>Word Biblical Commentary</u> Psalm 1-50 (Texas : Word Books Publishers 1983), p. 326
[49] A.W. Tozer, <u>The Knowldge of The Holy</u> (San Francisco: Harper and Row, Publishers 1961), p.1
[50] Bryan,
[51] Packer, p.23
[52] Bryan,





[53] ከሣቴ ገጽ 888
[54] Stein, Robert H. <u>Playing By The The Rule</u> (Rapids: Baker Books 1994), p. 193
[55] Bryan,
[56] Packer, p.32
[57] ፍሬው
[58] Grudem,
[59] Grudem, p156
[60] Grudem, p 161
[61] Tozer, p.49
[62] Grudem, p167
[63] Grudem, p 169
[64] Grudem, p. 172
[65] Grudem, p. 186
[66] Kenneth E. Hagin
[67] Tozer, p.59
[68] Tozer, p. 78
[69] Grudem, p. 197
[70] Erickson, p. 462
[71] Erickson, p. 464
[72] ምኒልክ አስፋው "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" <u>ተስፋ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁ.2 1ኛ ዓመት
[73] Erickson, pp.156-162
[74] The West Minester Confession of Faith
[75] Myles Munroe, Dr. " The Power and Potential of Purpose" Vidio Cassettee
[76] J.P. Moreland and David M. Ciocchi (Editors) <u>Christian Perspective on Being Human</u> (Grand Rapids, Michigan: Baker Books 1993,) p.21
[77] Grenz, p. 218
[78] Morland and Ciocchi, p. 22
[79] Stanly Grenz, <u>Theology For The Community Of God</u> (Nashvill: Broadman and Holman Publishers 1994), p.218
[80] David Atkinson, <u>The Message Of Genesis</u> 1-11 (Leicester, Englad: Inter- Varsity Press 1990), p.41
[81] Moreland and Ciocchi, pp. 27-28
[82] Erickson, p. 516
[83] Erickson, p. 515